የቅዱሳን
መነጠቅ
ተሰ 4፥17

የአውሬው
መምጣት
ራዕ 13

የመከራው
ዘመን
ራዕ 6-19

የበጉ ሠርግ
ራዕ. 19

የጌታ ዳግም
ምፅዐት
ራዕ. 19




የመጨረሻ
ዘመን
ምልክቶች
ማቴ. 24

የአርማጌዶ
ጦርነት
ራዕ. 19

የቤተ
ክርስቲያን
መመሥረት
ሐሥ 2

የሠይጣን
መታሰር
ራዕ. 20

የሺህ ዓ
መንግሥ
ራዕ. 20

የሰይጣን
መፈታት
ራዕ. 20

የዘላለም
መንግሥት
ራዕ. 21-22

⊘

የነቢያት
ትንበያ
ዕብ
1፥1-2

የክርስቶስ
መወለድ
ኢሳ 9:6

# የቅዱሳን በአየር መነጠቅ

(...ጌታን በአየር ለመቀበል ...በደመና እንነጠቃለን።)

መጋቢ ተኩ ከበደ

የመጀመሪያ እትም 1999 ዓ.ም.

የመጀመሪያው ዕትም ለናዝሬት ምሥራቅ
መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ

ይህንን መፅሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ
ማባዛት ወይም ማሣተም
በሕግ የተከለከለ ነው።

Pastor Teku Kebede
All Rights Resereved
Printed In Ethiopia
© 2007

# ምስጋና

ካለመኖር ወደ መኖር ካለማወቅ ወደ ማወቅ፣ ከማወቅ ወደ ማሳወቅ፣ በንግግር፣ በአኗኗር ዕውነትን ከመግለጥ ወደ መግፋ፡ ያደረሰኝን እውነተኛውን አባቴን፣ አምላኬም፣ ጌታዬም የብርታቴም ምንጭ የሆነውን ሁሉን አዋቂውን እግዚአብሔርን እጅግ አድርጌ አመሰግነዋለሁ::

በተጨማሪም ለዚህ መጽሐፍ መገኘት ከ1980ዎቹ ጀምሮ ጽሑፉን በመተየብና በኮምፒውተር አዘጋጅቶ የስቀማ ሥራን በመስራት፣ ከ20 ዓመታት በላይ በፀሎትና በሐሳብ የረዳችኝን ከማይሳሳተው የጋብቻና የህይወት መሃንዲስ የተቀበልኳትን ውድ ባለቤቴን እህት ምሥራቅ አበበን አመሰግናለሁ:: እንዲሁም:

1. በጽህፈት ሥራ የረዱኝን የደቡብ አጥቢያ መሠረተ ክርስቶስ ቤ/ክ ፀሐፊዎች እህት መሠረት አያሌውን እና እህት ገዳምነሽ ወርቁን
2. በ1983, 1984 ዓ.ም በሾኔ አምቡርሴ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያንና በ1980ዎቹ አጋማሽ በቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያናት በተካሄደው ኮንፍራንስ ስለምፅዐት መጽሐፍ እንድዕፍና ስአገልግሎቴም አጥብቃችሁ በጉባኤ የፀለያችሁልኝን
3. በነገረ ፍጻሜ ትምህርት ተጋብዤ ባገለገልኩባቸው አጥቢያዎች በፀሎት፣ በምክር፣ ማቴሪያል በመስጠትና በማደፋፈር የፀለያችሁልኝን
4. «ቶሎ ቶሎ ባታገለግልበት ይህ ፀጋ ይወስድብሃል በርታ » በማለት በምክር ያነቃችኝን ወንጌላዊት ጥሩነሽ ይመር/ቺካጎ-አሜሪካ/.
5. ይህንን ጽሑፍ በማየት በአርትኦት ስራ የረዱኝን ስማቸው በዚህ መጽሐፍ ላይ የተጠቀሰውን ውድ ወገኖች
6. መጽሐፉን ስሕትመት ያበቁትን የናዝሬት ምስራቅ መሰረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አገልጋዮችና ምዕመናንን

7. ለእኔ መገኘትና መበረታታት፣ ዕድገትና መንፈሳዊ መነቃቃት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለመሩኝ፣ ለፀለዩልኝና ላበረታቱኝ የመ/ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አመራር፣ አገልጋዮችና አጥቢያዎች በሙሉ
8. ይህንን የጌታ ምዕዐት ትምህርት እንዳስተላልፍ የመጽሔት፣ ጋዜጣ፣ የሬድዮ/ህያው ተስፋ/ የጉባኤ መድረክ ላመቻቻችሁልኝ ቤተዕምነቶች፣ /አጥቢያዎች/፣ ኅብረቶች፣ ለጋስ ድርጅቶችና በሩቅና በቅርብ ላላችሁ ጓደኞቼ በሙሉ
9. ለሰዓሊ ካሌብ በለጠ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

የሥራው ባለቤት እግዚአብሔር ይባርካችሁ

መጋቢ ተኩ ከበደ



# መግቢያ

ተኩላዎች በሚኖሩበት ጫካ ረፍራፊ ረሃብ ይገባል:: የጓደኞቻቸውን ዕልቂት የተረዱ ሁለት ጓደኛሞች ተኩላዎች ተቀምጠው በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ምክር ያካሂዳሉ:: ከብዙ ውይይት በኋላ ባገኙት መላ ተስማምተው ያንን አካባቢ ጥለው ምግብ ያለበት ፍለጋ ወደ ሌላ ጫካ ይጓዛሉ:: ጫካው ውስጥ እንደገቡ ሁለቱም ሳይራራቁ ምግብ ፍለጋውን ይያያዙታል:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሁለቱም የሚፈልጉትን አግኝተው በተራብ ጉልበት ሆዳቸው እስኪወጠር በልተው ይጠግባሉ:: በመቀጠልም ሁለቱም ጋደም ጋደም ይላሉ:: ሁለቱ እኩል ቢጠግቡም አተኛኘታቸው ግን ለየት ያለ ነበር:: አንደኛው ተኩላ እግሮቹን ወደ ላይ ገልብጦ ሲተኛ ሌላኛው ግን ነገር አዋቂ ስለነበር ጋደም ባለበት ቦታ አካባቢውን እየቃኘ ተኝቶ ነበር::

እነዚህ ሁለት ተኩላዎች በልተው፣ ጠጥተውና ጠግበው በተኙበት አካባቢ ግን ሌላ ትዕይንት ይካሄድ ነበር:: ይኼውም አንድ በጣም የተራበ ነብር ምግብ እየፈለገ ወደ ተኩላዎች መቅረቡ ነበር:: ይህ ነብር ወደ ተኩላዎቹ በቀረበ ጊዜ አስቀድሞ የተመለከተው ጋደም ቢልም እንቅልፍ ያልወሰደውን ተኩላ ነበር:: ልክ ነብሩ ተኩላውን ሲያየው ተኩላውም ነብሩን ተመለከተው: ነብሩ አቅም ተኩላው ደግሞ ልብ በማጣታቸው ሁለቱም በፍርሃት ተፋጠጡ፣ በዚህ ፍርሀት ውስጥ እያሉ ሁለቱም በቋንቋቸው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ፤ ነብሩ አምላኬ ሆይ! እኔ በረሃብ ልሞት ነውና ይህንን ተኩላ አብላኝ! አብላኝ! አብላኝ! በማለት ሲጸልይ ተኩላው ደግሞ እግዚአብሔር ሆይ! እኔ ፈርቻለሁና ከዚህ ከነብር አውጣኝ! አውጣኝ! አውጣኝ! በማለት ጸለየ:: ሁለቱም በዚህ ሁኔታ ተፋጥጠው ባሉበት እግዚአብሔር ይፀልይ ለነበረው ነብር ዞር ብሎ እንዲያይ ይነግረዋል:: ነብሩም ዞር ብሎ ሲያይ ሁለተኛው ተኩላ ሙሉ በሙሉ ተኝቶ ያገኘዋል:: ነብሩም በተኛው ተኩላ ላይ በመዝለል ይበላዋል::

ይህ ታሪክ ምሳሌያዊ አነጋገር አለው ይኸውም _አውጣኝ ያለ ወጣ፣ ኣብላኝ ያለ በላ፣ ዝም ያለ ተበላ_ የሚል ነው::

ከላይ ለተጠቀሰው ታሪካዊ ሃተታ የተለያዩ አመለካከቶች ቢሰነዘሩም አንድን ትልቅ ቁም ነገር እንደሚይዝ ማመልከት እፈልጋለሁ:: ይህ ዘመን የምቾት ዘመን ነው:: ሰው ሁሉ ምቾት ውስጥ(Comfort Zone) ለመግባት ዋጋ በመክፈል ላይ ይገኛል:: ይህም ከችግር ለመሸሽ ሊሆን ይችላል:: ሰው ከችግር ሲሸሽ ዓላማው ይብዛም ይነስ ምቾት ውስጥ ለመግባት ነው:: ምቾት ደግሞ የራሱ አሉታዊ /ጥሩ ያልሆነ/ ተፅዕኖ አለው:: ለምሳሌ ሰው ሲመቸው እንደ ጠቢቡ ሰለሞን ያመቻቸለትን ፈጣሪ ማየት ሊያቅተው ይችላል፣ ሰው ሲመቸው የበለጠ ምቾትን ይከተላል:: ሲመቸውም መልከ ብዙ ተከታዮች፣ ይከብቡትና አጀንዳዎችን ያበዙበታል፤ ያበዙለታል:: በዚህም ምክንያት ልቡ ይከብድና ከፈጣሪው በመለየት ፈተና ውስጥ ይወድቃል::

አሁን ያለንበት ጊዜ አብዛኛው ሰው ከቴክኖሎጂው ጋር ለመራመድ ደፋ ቀና የሚልበት ወቅት ነው:: በኤኮኖሚ በፖሊተካ በማሕበራዊው አኗኗር ከፍተኛ ውድድር እየተካሄደ ያለበት ጊዜ ነው:: በመጠን የመኖር ምርጫ እንደ ድህነትና ውርደት የሚቆጠር ስለሆነ እንደ ሌላው ወይም ከሌላው ሰው በላይ አልፎ ወይም ተመሳስሎ ለመገኘት ሁሉም ነገር ጥረት ጠያቂ የሆነበት ዘመን ነው:: ከዚህም የተነሳ በሉቃ 21:34 እንደተጠቀሰው በተወሰኑት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የልብ መከበድ ይታያል::ልብ ደግሞ ሲከብድ አቅጣጫው /ዝንባሌው/ ወደ ምድራዊ ነገር ይሆናል::

ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ ሁለት ሰዎች በአንድ እርሻና ወፍጮ እንደሚሆኑ ሆኖም ከሁለቱ አንደኛው ብቻ እንደሚወሰድ ተናግሮአል:: ማቴ24:40-41:: የአንደኛው/ዋ/ አለመወሰድ ከእምነት ብልሽት ወይም ማነስና መጥፋት ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳያል::



መቼም ክርስቶስ ሲመጣ ሲል እርሱን እየጠበቁ ከእርሱ ጋር በመስማማት መሄድ አለመቻል እጅግ አሳፋሪ ነው:: በአሁኑ ጊዜ ከእግዚአብሔር በረከትን የሚካፈሉ ብዙ ሰዎች አሉ:: በአንጻሩ ደግሞ ከበረከቱ የራቁም አሉ:: ሰዎችን ከጊዜአዊውና ዘላለማዊው የጌታ በረከቶች እንዲርቁ ከሚያደርጋቸው ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ ስለ ተገለጠው የእግዚአብሔር ዕውነት ማወቅ አለመፈለግ ወይም ካወቁ በኋላ በእምነቱ ተሳታፊ መሆንን አለመፈለግ ናቸው::

አንዳንድ ክርስቲያኖች በዕምነታቸው ጥብቅ መሆንን አይፈልጉም:: የማይፈልጉበትም ምክንያቶች ነፃነታቸውን የሚያጡ፣ በጓደኞች የሚናቁ/የሚገፉ/፣ ተቀባይነትን የሚያጡ፣ ችግር የሚገጥማቸው ወዘተ መስሎ ስለሚታያቸው ነው:: ሆኖም ግን የሚያዋጣው ቢከብድም በአፍ ጣፍጦ በሆድ/በኑሮ/ መራራ ቢሆንም /ራዕይ10:9/ ዕውነትን መፈለግና ማግኘት ከዚያም ከዕውነት ጋር መጣበቅ ነው:: ምክንያቱም ዕውነት ባለበት መሄጃው መንገድ ይታወቃል፣ ያም መንገድ ጌታ ኢየሱስና የላከው መንፈስ ቅዱስ ናቸው:: ዕውነትና መንገድ ባለበት ህይወት፣ ህይወትም ባለበት ብርሃን፣ ብርሃንም ባለበት ቅድስና ቅድስናም ባለበት ነፃ መውጣት አለ:: ዩሐ14:3 ፣ 1:3 17:17:: ኑሮን በዚህ ዓይነት መንገድ ካላስተካከሉት በስተቀር የአካባቢውን ሁኔታ መቃኘት ተስኖት በእንቅልፍ ተውጦ የነበረው ተኩላ የደረሰበት አደጋ እኛም ላይ ሊደርስ ይችላል:: ከዚህ አውጣኝ ማለት ትልቅ ጸሎት ነው:: ጥንቃቄ ያልተደረገበት ምኞትና ምቾት ፍለጋ ሩጫ በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ መንፈሳዊ እንቅልፍን ያመጣል::

ስለሆነም ይህ መጽሐፍ ክርስቶስ ኢየሱስ በራሱና በታማኝ አገልጋዮቹ የገለጠልንን የቅዱሳን ከመጨረሻ ዋና ዋና ተስፋዎች ውስጥ አንዱ ስለሆነው ስለ ቅዱሳን መነጠቅ /ስለ አሁኗ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ/ እርግጠኛነት ለማሳወቅ የተፃፈ ነው:: መጽሐፉ አስራ ሁለት ዋና ዋናና ተጨማሪ ንዑሳን ክፍሎች አሉት::

ክፍል አንድ ስለ መነጠቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን እንደተፃፈ ይገልጽልናል::

ክፍል ሁለት ስለ መነጠቅ ትርጉምና ምንነት ያትታል:: ክፍል ሦስት ለብዙ አማኞች ልዩነቱን ለማየት አስቸጋሪ ስለሆነባቸው በመነጠቅና በጌታ ዳግም ምፅዓት መሃከል ያለውን ልዩነት ያሳያል:: ክፍል አራት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጠቀሱት የተለያዩ የመነጠቅ ዓይነቶችና በምን ጊዜ እንደሚሆኑ ይገልፃል:: ክፍል አምስት ይህ መነጠቅ ከመከራው በፊትና በኋላ ወይስ በመሃል ላይ በየትኛው ጊዜ እንደሚፈፀም ያብራራል::

ክፍል ስድስትና ሰባት - መነጠቅ ከመከራው በፊት ስለመሆኑ የቀረቡ ማስረጃዎችና በመነጠቅ ጊዜ በዚህ ምድር ስለሚከናወኑት ሁነቶች ያብራራል:: ክፍል ስምንት - እግዚአብሔር መነጠቅን ስላዘጋጀበት ምክንያቶችና ዓላማዎች ይዘረዝራል:: ክፍል ዘጠኝ ከመነጠቅ በኋላ በሰማይና በምድር ስለሚፈፀሙ ትዕይንቶች እንዲሁም በክፍል አስርና አስራ አንድ በወቅቱ ያለነው ለመነጠቅ የምንፈልግ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያናት ለመነጠቅ ምን ማሟላት እንዳለብንና ይህንኑ መነጠቅ ለምን መናፈቅና ማስቸኮል እንዳለብን ያትታል:: በመጨረሻም በክፍል አስራ ሁለት በክርስቶስ አማኝ ነኝ/ነን/ የሚሉ ስለ መነጠቅ በተሳሳተ መንገድ ከመረዳት ወይም ካለማወቅ የተነሳ አሳዛኝ ነገር እንዳይደርስባቸው ምን ዓይነት ልምምዶች ላይ ማትኮር እንዳለባቸው ይገልፃል::

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በቅድሚያ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ውስጥ ስለ መነጠቅ ምን እንደተጻፈ ለማሳወቅና የመነጠቁን ቀን በማስቸኮል እንዲጠብቁ ማበረታታትና ማነሳሳት ነው፤ ሆኖም በማጠቃለያው እንደተጠቀለው የመነጠቅን ትክክለኛ ቀን በሚመለከት ከሚፈጠረውም ቀውስ አማኙ ራሱን እንዲጠብቅ ለማዘጋጀት ነው:: በተጨማሪም ይህ የመነጠቅ ዕድል ሊያመልጣቸው ላሉት ከቤተ ክርስቲያን ለራቁ ከሃዲዎችና ጌታን ላልተቀበሉ ሁሉ እውነቱን ለማመልከት እንዲቻል ለቅዱሳን ሁሉ መገልገያንና ማገልገያ መሣሪያን ለማስጨበጥ ነው::



... በረኛው እንዲተጋ አዘዘ ማር 14፥34

መጋቢ. ተኩ ከበደ

# የቅዱሳን በአየር መነጠቅ

ማውጫ


- ምስጋና ........................................ I
- መግቢያ ........................................ III

ክፍል አንድ: መነጠቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ........................................ 1
ክፍል ሁለት: የመነጠቅ ፍቺ ........................................ 4
ክፍል ሦስት: የቤተ ክርስቲያን መነጠቅና የዳግም ምፅዓት ልዩነት.... 6
ክፍል አራት: የመነጠቅ ዓይነቶች ........................................ 9
ክፍል አምስት: የመነጠቅ ጊዜ አመለካከቶች (ቅድመ መከራ፤ መንፈቀ-መከራና ድህረ-መከራ) ........................................ 17
ክፍል ስድስት: የቅድመ መከራ መነጠቅ ማስረጃዎች (መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይኖራል?) ........................................ 23
ክፍል ሰባት: ትዕይንተ-መነጠቅ ........................................ 70
ክፍል ስምንት: የመነጠቅ ዓላማዎች (እግዚአብሔር የመነጠቅን ሥርዐት ለምን አዘጋጀ?) ........................................ 84
ክፍል ዘጠኝ: ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች (ከመነጠቅ በኋላ በሰማይና፣ በምድር ምን ይከናወናል?) ........................................ 92
ክፍል አስር: ለመነጠቅ መሟላት ያለባቸው ልምምዶች(ዝግጅቶች) .100
ክፍል አስራ-አንድ: መነጠቅን ለምን መናፈቅ ይኖርብናል? ........................................ 113
ክፍል አስራ-ሁለት: ማስጠንቀቂያ ........................................ 121
ማጠቃለያ ........................................ 152
ልዩ ማስታወሻ ........................................ 153
ሙዳየ-ቃላት ........................................ 154
ምህጻረ-ቃላት ........................................ 167
መዘክረ-መጻህፍት ........................................ 167




# ክፍል አንድ

## ስለመነጠቅ የሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

| ተ.ቁ. | የሚገኙበት ቦታ | የተጠቀሰው ዓረፍተ ነገር |
|---|---|---|
| 1. | ሉቃ. 21:36 | እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትፀልዩ ሁልጊዜ ትጉ። |
| 2. | ዮሐ. 14:3 | ሔጄም ሥፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ። |
| 3. | ኤፌ. 5:27 | እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንደህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ |
| 4. | 1ኛቆሮ.15:51-53 | እነሆ አንድ ሚስጢር እነግራችኋለሁ ... የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሳሉ እኛም እንለወጣለን። |
| 5. | ፊልጵ. 3:21 | ... የተዋረደው ሥጋችንን ...ይለውጣል.. 2ኛቆሮ. 5:1-9 ... በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሰራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሰራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና። ...በሥጋ ስናድር... ከሥጋ ተለይተን... |

| | | |
|---|---|---|
| 6. | 1ኛተሰ. 4:13-17... | በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ ከዚያም በኋላ እኛ ህያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለቋቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና <u>እንነጠቃለን::</u> |
| 7. | 2ኛተሰ. 2:1-7 | ... ወደ እርሱ <u>ስለመሰብሰባችን</u> ... ብቻ ከመንገድ <u>እስኪወገድ</u> ድረስ አሁን የሚከለክል አለ፤ |
| 8. | ቆላ. 3:4 | ... በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር <u>በክብር ትገለጣላችሁ</u>:: |
| 9 | 1ኛዮሐ. 3:2 | ... ዳሩ ግን ቢገለጥ (እኛነታችን) እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን:: |

ከላይ የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጐች የተሰያዩ ቢሆኑም ስርወ-ግንዳቸው ሲመረመር በቀጥታ መነጠቅን ያመለክታሉ::

በሉቃስ 21:36 ያለው *"<u>ለማምለጥ</u>"* የተሰኘው ቃል የሚያመለክተው በመጨረሻው ዘመን ያሉ ቅዱሳን በምዕራፉ ከተጠቀሱት ቁጣዎች ማምለጥ የሚችሉት በመነጠቅ መሆኑን ነው:: *"<u>ማምለጥ</u>"* የሚለው ቃል ራሱ የሚያመለክተው ከአንድ ሁኔታ መሰወር፣ ለሁኔታው አለመጋለጥን፣ መሸፈንን ነው:: በሉቃስ 21 የተጠቀሱት ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን እንደሚሆኑ የገለጻቸው ሰውን የሚያስጨንቁ ሁኔታዎችን ላለማየት የሚቻለው በመነጠቅ ነው::

በዮሐንስ 14፣1-3 ደግሞ ጌታ ኢየሱስ *"<u>እወስዳችኋለሁ</u>"* ሲል ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ወደ ተዘጋጀላቸው ሰማያዊ ስፍራ የሚሸጋገሩበትን መንገድ ያመለክታል:: ይህም መንገድ መነጠቅ ነው:: ጳውሎስ ለኤፌሶን ቅዱሳን ሲጽፍ ጌታ ኢየሱስ ያለ ነውር የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ የሚያቀርበው



በመነጠቅ እንደሆነ ያመለክታል:: *"<u>እንዲያቀርብ</u>"* የሚለው ቃል በምድር ያሉትን ቅዱሳን ወደ ሰማይ ማጓጓዝን (ማንቀሳቀስን) ያመለክታል:: ይህም መነጠቅን ይጠቁማል::

በ1ኛቆሮ. 15:51-53 ባለው ክፍል *"እንለወጣለን"* *"ይነሳሉ"* የሚሉት ቃላት የኋለኛው መለከት በሚነፋበት ጊዜ ቅዱሳን የሚያልፉበትን ሁኔታ ያመለክታል:: ትንሳኤ በሚሆንበት ጊዜ ቅዱሳን በሙሉ በቅጽበተ ዓይን ተለውጠው ጉዞ ይጀምራሉ:: ትንሳኤ ሆነ ማለት መለወጥ ሆነ ማለት ነው:: አላሶ ወይም አላሶሜታ የሚለው የግሪኩ *የእንለወጣለን* አቻ ቃል የሚያመለክተው ከአንድ ሁኔታና ማንነት ወደ ሌላ ማንነት መቀየርን ወይም መግባትን ነው::

በ2ኛቆሮ. 5:1-9 የተጠቀሱትም ሐረጐች ማለትም <u>"ከእግዚአብሔር" የተሰራ ህንጻ፣ "መኖሪያችንን እንድለብስ"</u> የተሰኙት ቃላት ሰው ከዚህ ከሟችና በስባሽ አካል ከተለየ በኋላ የሚጐናጸፈውን ዘላለማዊ ሰውነት ያመለክታል:: ይህም ሰውነት በመነጠቅ ጊዜ የሚገኝ ነው::

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቅዱሳን *"ስለመሰብሰባችን"* በማለት የተጠቀመው ቃል የሚገልጸው ቅዱሳን ወደ ጌታ የሚሰበሰቡት በመነጠቅ እንደሆነ ለማመልከት ነው:: የእውነተኛው የክርስትና ሕይወት የእድገት መጨረሻ ጌታ ኢየሱስ ነው:: እድገታችንም ወደ ክርስቶስ ሙላት ነው:: ጌታ ኢየሱስ ሁለንተናው ፍጹምና ያለ ኃጢአት ነው:: የእኛም የእድገት አቅጣጫ ክርስቶስን ወደ መምሰል ያተኩራል:: አዲሱን አካላችንን ስንለብስ ማንነታችን ይገለጣል:: ይህም ሰውነታችን የክርስቶስን አካል የሚለብሰው በመነጠቅ ወደ እርሱ ስንደርስ ነው::

# ክፍል ሁለት

## የመነጠቅ ፍቺ

የነገር ብልሽት ወይም ፈር ይዞ መሔድ መሠረቱ ለነገሩ የተሰጠው ፍቺ ወይም ትርጉም ነው:: ትክክለኛ የሆነ ፍቺ (ትርጉም) የተሰጠው ነገር አገልግሎቱም ያንኑ ያህል ጥራትና አስተማማኝነት ያለው ይሆናል:: እውነተኝነት በሌላው መንገድ የተብራራ ጉዳይ ደግሞ ያንኑ ያህል አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ረብ የለሽ ይሆናል:: ስለዚህ ትክክለኛ የሆነ አመለካከትን ለመያዝ የመነጠቅን ፍቺ ማየቱ መልከም ነው:: ..*መነጠቅ*.. የሚለውን ቃል ትክክለኛ ፍቺ/ትርጉም በሚከተለው መንገድ በዝርዝር እንመለከታለን::

### 2.1. የጥሬ ቃሉ ትርጉም

..መነጠቅ.. የሚለው የግሪኩ ቃል ..ሃርፓጂስምታ.. ሲሆን የላቲኑ ደግሞ ..ራፔመር.. ነው ፍቺውም ..ወደላይ መወሰድ..፣ ..መወገድ..፤ ..መነሳት.. ማለት ነው:: ወይም ደግሞ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ዞር ማለት ሳይሆን ከታችኛው ወደ ላይኛው ክፍል/አቅጣጫ መንቀሳቀስን የሚያመለክት ነው::

### 2.2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መነጠቅ ማለት የኋለኛው መለከት በሚነፋበት ጊዜ፤

***<u>በመጀመሪያ ደረጃ</u>*** በጌታ ያንቀላፉ (ጌታን እንደግል አዳኛቸው ተቀብለው የሞቱ) ቅዱሳን የማይሞተውን፣ ዘላለማዊውን፣ ያልተዋረደውን ነገር ግን የተከበረውን፣ የማይበሰብሰውን፣ ምድራዊ ያልሆነውን ነገር ግን ሰማያዊውን፣ መንፈሳዊ የሆነውን፣ የክርስቶስን አካል የመሰለውን፣ የማይጠፋውን አዲስ ለውነት (አካል) ለብሰው በመነሳት፤<u>በሁለተኛ ደረጃ</u> በዚህ ዓለም በሥጋ ያሉት (ያልሞቱት) ቅዱሳንም የሚነሱት የለበሱትን ዓይነት ዘላለማዊ አካል ለብሰው በቅጽበተ ዓይን በመለወጥ፤ጌታን ክርስቶስ



ኢየሱስን ከሰማይ ሲመጣ በአየር ለመቀበል ወደተወሰነ የሰማይ ክልል የሚያደርጉት ጉዞ መነጠቅ ይባላል:: 1ኛተሰ. 4:13-17፤ 1ኛቆሮ. 15:20-57::

በዚች ምድር እግዚአብሔር የራሱ ርስት አለው:: ይህም ርስቱ ቤተ ክርስቲያን ናት:: እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልጁም በኢየሱስ ክርስቶስ የፀጋ ሥራ ከነገድ፣ ከወገን፣ ከቋንቋና ከሕዝብ ሰዎችን አድኗል፤ ከዲያብሎስ እጅ፣ ከክፉ ቀንበር ነጻ አውጥቷል:: በራሱ ጊዜና ፈቃድ በመላው ዓለም የክርስቶስን የድነት ጥሪ አምነውና ገዝነምን (የዘላለሙን ቅጣት) ፈርተው ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ ወደ ሰማያዊቱ ከተማ ይሰበስባል:: እግዚአብሔር በልጁ በጌታ ኢየሱስ በኩል ዋጅቶ በመንፈስ ቅዱስ ያተማቸውን እውነተኛ አማኞች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደ ሰማያዊ ስፍራቸው ይወስዳቸዋል::

# ክፍል ሦስት

## የመነጠቅና የጌታ ዳግም ምጽዐት ልዩነቶች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመፍታት ከሚያስቸግሩ ጉዳዮች ውስጥ አንደኛው የጊዜና የቅደም ተከተል ነገሮች ናቸው:: አንዱ ትዕይንት ከሆነ በኋላ የሚቀጥለው የትኛው እንደሆነ ለመለየት አስቸጋሪ ቢሆንም ጊዜንና ልብን አገናኝቶ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ለታገለ የእግዚአብሔር ሰው ግን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እውነት እንደሚገለጥለት አሌ የማይባል ሐቅ ነው:: ምክንያቱም ወደ እውነት ሁሉ የሚመራው መንፈስ ቅዱስ ስላለ ነው:: ዮሐ.16:13::

አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠኑ የእግዚአብሔር ሰዎች በመነጠቅና በጌታ ዳግም ምጽዐት መካከል ልዩነት እንዳለ ሳይገነዘቡ ቀርተዋል:: ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመምጣቱ ሁኔታ በግልጽ ይሁን በስውር (ሁኔታውን) የሚመጣበት ጊዜ (ወቅት) ለምሳሌ ከመከራው በኋላ ወይስ በፊት የሚለውን የሚመጣባቸውን ምክንያቶች፣ ከማን ጋር እንደሚመጣ፣ ማለትም ቅዱሳኑን ሲወስድ፣ ከቅዱሳኑ ጋርም ሲመጣ፣ ሌሎችንም አጠቃላይ ሁኔታዎች ከሚከተለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል::

| <u>በመነጠቅ ጊዜ</u> | <u>በዳግም ምጽዐት ጊዜ</u> |
|---|---|
| 1. ጌታ ኢየሱስ ለቅዱሳን ብቻ ይታያል 1ኛተሰ. 4:17 | 1. ለዓለም ሁሉ ይገለጻል (ይታያል) ራዕይ 1:7፣ ማቴ. 24:30 |
| 2. በአየር ውስጥ ይገለጣል 1ኛተሰ. 4:17 | 2. ወደ ምድር ይመጣል:: ራዕይ 19:11-19:: ማቴ. 24:30፤ ሐሥ.. 1፣11 |



| | |
|---|---|
| 3. ቅዱሳኑን ለመውሰድ ይመጣል ዮሐ. 14:3 | 3. ከቅዱሳኑ ጋር ይመጣል ይሁዳ. 14-15፤ ዘካ.14:5፤ ራዕ. 19:14 |
| 4. በቅዱሳኑ ሊከበርና ሊገረም ይመጣል 2ኛ ተሰ. 1:9-10:: | 4. በምድር ነዋሪዎችና በቅዱሳኑ ዘንድ ሊከብር 2ተሰ.1:10፣ ኢሳ.11:9:: |
| 5. ለመዋጋት ሳይሆን ቅዱሳንን ለመውሰድ ይመጣል:: ራዕይ 19:11፣14-20:: | 5. ለመዋጋትና በጽድቅ ለመፍረድ ይመጣል:: 1ኛተሰ. 4:17-18:: |
| 6. በ70ኛው ሱባኤ መጀመሪያ ይመጣል 2ኛተሰ. 2:6-7:: | 6. በ70ኛው ሱባኤ ማብቂያ ይመጣል ዳን.9:27ና 2ኛተሰ.2:3-8 ይነጻጸር |
| 7. ሐሰተኛው ክርስቶስ ሳይገለጥ 2ኛተሰ. 2:3-8:: | 7. ሐሰተኛው ክርስቶስ ተገልጾ ከሰራ በኋላ:: 2ኛተሰ. 2:3-8:: |

ከላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር ተነጻጽረው በቂ መረጃ ሊሆኑ ይችላሉ::

የመነጠቅ ዓይነቶችን በዝርዝር አልተመለከትንም:: ከመነጠቅ ዓይነቶች ውስጥ ..የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ.. በዚህ ክፍል ከተጠቀሰው የጌታ ዳግም ምጽዐት ጋር ሊወዳደር የሚገባው ነው:: ሌሎቹ የመነጠቅ ዓይነቶች ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጋር ሲነጻጸሩ አፈጻጸማቸው አንድ ዓይነት ይሁን አይሁን በግልጽ የተጻፈ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም::

በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን መነጠቅና የጌታ ዳግም ምጽዐት መካከል የአንድ ሱባኤ ወይም የሰባት ዓመታት(ሙ.ቃ.ይ.) ልዩነት አለ:: በራዕይ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ውስጥ ስለቤተ ክርስቲያን መኖር በዝርዝር ይናገራል:: በምዕ. 19:14 ላይ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱሳን ጋር

ተዳምራ ወደ ምድር ስትወርድ ይታያል:: ይህ የክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት በሺሁ ዓመት መጀመሪያ በ70ኛው ሱባኤ መጨረሻ ከሆነ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በራዕይ 4:1 ላይ ወይም በቤተ ክርስቲያን ዘመን ማብቂያ ላይ ሆኗል ማለት ነው:: ይህም ከ7ቱ የመከራ ዓመታት በፊት ነው:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ ጊዜ ከክርስቶስ ዳግም ምጽዐት ጋር አንድ እንደሆነ ልናስብ አይገባም:: ሁለቱ ልዩነት አላቸው:: መነጠቅ የክርስቶስ መፅአት አይደለም:: መነጠቅ የሚሆነው ጌታ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሲመጣ ሲሆን ዳግም ምጽአት ግን በግልጽ ለአለም ህዝብ ሁሉ እየታየ ነው:: ራዕይ. 19:11-19::



# ክፍል አራት

## <u>የመነጠቅ ዓይነቶች</u>

በዚህ ክፍል ስለ መነጠቅ ዓይነቶች ሲገለጽ ልናተኩርበት የሚገባው ነገር መነጠቅን ከጊዜና ከቅደም ተከተል ከኳያ መመልከቱ ላይ ነው:: በመጀመሪያው ትንሳኤ የሚፈጸሙ አምስት የመነጠቅ ዓይነቶች አሉ:: እነዚህም የመነጠቅ ዓይነቶች አፈጻጸማቸው በቅደም ተከተል ነው:: ስለ መነጠቅ ጊዜ (በቅድመ-መከራና፣ በመከራው መካከል ስለመሆን) የተለያዩ አመለካከቶች ሊፈጠሩ ከቻሉባቸውም ዐበይት ምክንያቶች ውስጥ አንደኛው የመነጠቅን ዓይነቶች በዝርዝር አለማወቅ ነው:: በተጨማሪም የቅድመ መከራ ቅዱሳንና የመከራውን ዘመን ቅዱሳንን አብሮ ከማያያዝ የተነሳ ነው:: ምልክቶችንና መንፈስ ቅዱስን መሰረት በማድረግ የመነጠቅን የጊዜ አካባቢ፣ ለመረዳት ዋነኛው መሠረት መነጠቅ ማንን እንደሚመለከትና በምን ዓይነት ሁኔታዎችና ጊዜአት እንደሚፈጸም ከእግዚአብሔር ቃል በትጋት መመርመር ነው::

### አምስቱ የመነጠቅ ዓይነቶች

እስካሁን በተደረገው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አምስት የመነጠቅ ዓይነቶች ተገኝተዋል:: ሆኖም ግን አንዳንዶች በሰባኛው ሱባኤ መጨረሻም ላይ በቅድመ ሺህ ዓመት ጅማሬ ላይ ስድስተኛውን የመነጠቅ ዓይነት ማመልከት የሚፈልጉም መኖራቸው ሊዘነጋ አይገባም:: አምስቱ ዋና ዋና የመነጠቅ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው::

### 4.1. የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን መነጠቅ

ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ስንመለከት ጌታ ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጐ የሞትና የሲኦልንም መክፈቻ ወስዶ ከተነሳ በኋላ በብሉይ ኪዳን ዘመን በህይወታቸው ዘመን ሁሉ በሰይጣን አስፈራሪነት በስጋት ይሰቃዩ የነበሩትን የአማኞች (ዕብር. 2:14) ነፍሳት ከማረከ በኋላ አሁን ባዶ ከሆነው ከታችኛው ገነት (ሙ.ቃ.ይ.) ወደ ላይኛው ገነት ጠራርጐ ወስዷቸዋል:: አሁን እነዚህ ነፍሳት በዕብ. 12፣23 እንደተጠቀሰው ..በጻድቃን መንፈሶች ጉባኤ ይገኛሉ:: ማቴ. 27፣52-52፤ ኤፌ.4፣8-10፤ 1ኛጴጥ. 3፣18-19::

እነዚህ ነፍሳት ያለ እኛ ፍጹማን ስለማይሆኑ ከታችኛው ገነት ወደ ላይኛው ገነት በመነጠቅ ተወሰዱ እንጂ አዲሱን አካል አልለበሱም:: ጌታ ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጐ እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ ሰይጣን እያስፈራራቸው ይፎክርባቸው ነበር:: በኋላ ግን ..ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሳትህ የት አለ? እንደተባለ ጌታ ሞትን ድል ሲያደርግ በሞት ፍርሃት በህይወታቸው ከሚሰቃዩበት ከታችኛው ገነት (የአብርሃም ዕቅፍ) ነጻ በማውጣት ወደ ላይ ማለትም ወደ አራተኛው ገነት(አሁን ቅዱሳን ሲሞቱ የሚሄዱበት ስፍራ) ወስዷቸዋል:: ለዚህም ነው «ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ሥጦታን ሰጠ» በመባል የተጻፈው ነው ኤፌ.4:8:: ይህንን ጉዞ የመጀመሪያው መነጠቅ እንለዋለን:: እነዚህም ቅዱሳን (ያልተገለጠውን ነገር እንዳለ ትተን) ከአቤል ጀምሮ እስከ ጌታ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ያንቀላፉትን ቅዱሳን በሙሉ የሚጨምር ነው::

በዚህ ክፍል መነጠቅ ስንል ከታችኛው ገነት ወደ ላይኛው ገነት የተካሔደውን የነፍሳትን መዛወር እንጂ አዲሱን አካል ለብሰዋል ለማለት አይደለም:: ይህ አዲሱን አካል የመልበሱ ጉዳይ ፍጹም የሚሆነው ወደፊት የመጨረሻው መለከት ከተነፋ በኋላ ነው::



### 4.2. የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ

ይህ የመነጠቅ ዓይነት: ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደግል አዳኛቸው በማድረግ የተቀበሉትንና የዳግም ልደትን ህይወት በማግኘት የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑትን ቅዱሳን አማኞች በሙሉ የሚያጠቃልል ነው:: እነዚህም ሁለት ክፍሎች አላቸው:: ይኸውም በጌታ ያንቀላፉ ማለት ጌታን አምነው የሞቱና በህይወት ሳይሞቱ ያሉ ናቸው:: እነዚህ ክፍሎች የመከራውን ዘመን ቅዱሳን አማኞች ወይም የመከራውን ዘመን ቤተ ክርስቲያን አይጨምርም:: እነዚህ ቅዱሳን ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 16፣18 ቤተ ክርስቲያኔን እሰራለሁ እንዳለ ቤተ ክርስቲያንን ከመሰረተበት ጊዜ አንስቶ እስከ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ያሉት ቅዱሳን ናቸው::

በዚህ ክፍል እውነተኛ አማኞች የሆኑ ሁሉ ፈጽሞ አይቀሩም ሁሉም ይነጠቃሉ:: ወደ ተዘጋጀላቸውም የእረፍት ስፍራ ይወሰዳሉ:: ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች መመልከት የበለጠ ይጠቅማል:: 1ኛቆሮ.15፣23፤ 51-54፤ ዮሐ. 14፣1-3፤ ሉቃስ 21፣34-36፤ 2ኛቆሮ.5፣1-8፤ ኤፌ.5፣27፤ ፊልጵ. 3፣20-21፤ 1ኛተሰ. 2፣19፤ 2ኛተሰ. 2፣1፣7፤ 1ኛዮሐ. 2፣28፤ 3፣2፤ 1ኛጴጥ. 5፣4::

የኋለኛው መለከት ሲነፋ በዘመኑ ፍጻሜ በክርስቶስ ያመኑና የሞቱ በህይወትም ያሉ ሁሉ የትንሳኤን ህይወት ወይም በቅጽበተ-ዓይን የመለወጥን ህይወት አግኝተው ይነጠቃሉ:: አንዳንድ አማኞች እንደሚሉት ደካማ ህይወት ያላቸው ያልነቁ ቅዱሳን አይነጠቁም የሚሉት ፈጽሞ ስህተት ነው:: ሆኖም ግን ጌታን ከተቀበሉ በኋላ በዕብ.10፣26 እንደተጠቀሰው ወደው በድፍረት ኃጢአት የሚሰሩና መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑ ከሆነ ከወይኑ ግንድ የመቆረጫው ወይም ከጌታ አፍ የመተፊያው አንዱ መንገድ ..መነጠቅ.. እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል::

## 4.3. የ144000 አይሁዶች መነጠቅ

እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ዓላማ አለው:: ይህንንም ዓላማውን ከፍጻሜ ለማድረስ የሚጠቀምባቸው የራሱ የሆኑ አሰራሮች አሉት:: መላዕክት፣ ሰዎችና ልዩ ልዩ ፍጥረታት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከሚፈጽሙት ኃይላት ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው:: እግዚአብሔር የሰይጣንን ፈቃድና ሐሳብ ለማፍረስ በመከራው ዘመን ካቆማቸው (ከተከላቸው) አገልጋዮቹ ውስጥ 144000 አሁዶች ዋነኞቹ ናቸው::

እነዚህ 144000 አይሁዶች በራዕይ 12፣4-5 ..ህጻን.. ወይም ..ወንድ ልጅ.. ተብለዋል:: በዚህ ክፍል (ራዕይ 12) ሴት የተባለችው የእስራኤል አገር፣ ዘንዶው የተባለው ሰይጣን፣ በተጨማሪም ወንዱ ልጅ የተባለው 144000 አሁዶች እንደሆኑ መገንዘቡ እጅግ ጠቃሚ ይሆናል:: ..ወንድ ልጅ.. የሚለው ሐረግ ትርጉም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስን ሰዎች ያጨቃጨቀ ቢሆንም ትክክለኛ ፍቺውን በመልቀቅ ሴቲቱን እንደ ማርያም ወይም ቤተ ክርስቲያን: ወንዱን ልጅ እንደ ጌታ ኢየሱስ በመተርጐም መውሰድ ከታሪክና ከትንቢት አንጻር ሲተረጐም የማይጣጣም ሁኔታን ይፈጥራል:: ምክንያቱም የራዕይ መጽሐፍ የተጻፈው በአብዛኛው በመጨረሻው ዘመን ሲሆኑ ላሉ ነገሮች ስለሆነና የ[illegible]ም ነገሮች ፍጻሜ ቀደም ተከተላዊ በመሆኑ ነው::

አንዳንድ የ[illegible] ቅዱስ ሰዎች «ወንዱን ልጅ» ጌታ ኢየሱስ: <u>ሴቷን</u> ደግሞ እንደ ቤተ ክርስቲያን እንደሆኑ ለማስረዳት ይሞክራሉ:: ይህ ግን ከመፃዕያን: ከታሪካውያንና ከሐላፍያን የአቡቀለምሲሳዊ የትርጉም ሕግ አንጻር ሲታይ የሚጣረስ ይሆናል:: ምክንያቱም፤

4.3.1. <u>የራዕይ መጽሐፍ ከ1-3 ስለቤተ ክርስቲያን ዘመን ከተናገረ በኋላ ቀጥሎ ከ4-22 ያለው በሙሉ የሚናገረው ስለ ወደፊቱ ማለትም የቤተ **ክርስቲያን መነጠቅ**</u> ከሆነ በኋላ ያለውን በመሆኑ፤ ራዕይ 12 ስለ ማርያምና ጌታ ኢየሱስ የሚናገር ከሆነ፤ ማርያም በህይወት አለች:: ኢየሱስም ገና



ይወለዳል ወደሚል ትርጉም ሊወስደን ነው:: የራዕይን መጽሐፍ ቁልፍ ሐሳብ የያዘው ራዕይ 1፣19 ..ከዚህ በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን.. ሲል የሚያመለክተው ከራዕይ 4፣1 በኋላ ያለውን ነው:: ስለሆነም ራዕይ 12 ፈጽሞ ገና አልተፈጸመም ስለ ጌታ ኢየሱስና ስለ ማርያምም አይገልጽም::

4.3.2. <u>*በራዕይ 12፣6 እና 12፣14 የተጠቀሰው 1260 ቀናትና ዘመን፣ ዘመናትና የዘመንም እኩሌታ*</u> *የሚያመለክተው በዳን. 9፣24-27 እንደተጠቀሰው የ70ውን ሱባኤ ሁኔታ ስለሆነ ይህም*

*ሱባኤ ገና ወደፊት የሚፈጸምና ሱባኤውም የተነገረው ስለ እስራኤል መሆኑ፤*

4.3.3. <u>በኢሳ. 66፣7-8 የተነገረው ትንቢት እስከ አሁን በዓለም ታሪክ አለመፈጸሙ፤ ነገር ግን ወደፊት በ70ኛው ሱባኤ አጋማሽ የሚፈጸም መሆኑ</u> በዚህ ክፍል ኢሳይያስ .....ወንድ ልጅ ወለደች.. .....በአንድ ጊዜ ህዝብ ይወለዳልን?.. .....አገር በአንድ ቀን ታምጣለችን.. በማለት ይናገራል:: በማያያዝ ወላጇ ሴት እንደሆነች እርሷም ..አገር.. እንደሆነች የተወለደው ወንድ ልጅ ደግሞ ..ሕዝብ.. እንደሆነ ይገልጻል:: ይሔ ትንቢት እስካሁን አልተፈጸመም:: አገር ያላት ጽዮንን እንደሆነ በማሳየት ጽዮን አገር (እስራኤል) ከሆነች ሕዝቧ ደግሞ እስራኤላውያን ማለትም 144000 አይሁዶች መሆናቸውን ኢሳ.66 እና ራዕይ 12ትን በማገናዘብ መረዳት ይቻላል::

4.3.4. <u>ሴቷ የምትወክለው ..ብሔራዊ እስራኤልን.. ማለትም ህዝብን ከሆነ ሴቷ የምትወልደውም ..ወንድ ልጅ.. ባህሪዋን የሚመስል ልጅ ህዝብ መሆን ስላለበት ነው::</u> እነዚህ 144000 አይሁዶች ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ስለመነጠቃቸውና በምድር ስለሚገጥማቸው ሁኔታ ለመጻፍ በራዕይ 12፣4 ላይ ..ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ህጻንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ.. የሚለው ዓረፍተ ነገር ትርጉም ማየት ያስፈልጋል :: በእስራኤል እግዚአብሔር እነዚህን 144000 አይሁዶች በራዕይ 7፣3 እንደተጠቀሰው በ70ኛው ሱባኤ ለአገልግሎቱ ይለያቸዋል:: እነርሱም

በታተሙበት ዓላማ መሠረት የመጀመሪያውን ሦስት ተኩል ዓመታት ካገለገሉ በኋላ ማንነታቸው በአውሬው ይታወቃል:: በዚህ ጊዜ ሐሰተኛው ክርስቶስ ሊያጠፋቸው ይነሳባቸዋል:: በዚህ ወቅት ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ መነጠቃቸውም የሚረጋገጠው በራዕይ 14፣1-3 ባለው ክፍል ነው:: ራዕይ 7፣1-8 መታተማቸው (መለየታቸው) ይታያል:: ባሪያዎች ናቸውና አገልግሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ በራዕይ 12፣5 እንደተጠቀሰው በመከራው ዘመን እህዛብን በብረት በትር ገዝተው አገልግሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ወደ ሰማይ ወደ ተዘጋጀላቸው ስፍራ (ይወሰዳሉ) ይነጠቃሉ:: ይህም የ144000 (መቶ አርባ አራት ሺ) አይሁዶች መነጠቅ.. ይባላል::

## 4.4. <u>የታላቁ የመከራው ዘመን ቅዱሳን መነጠቅ</u>

ይህ አራተኛው የመነጠቅ ዓይነት ነው:: እነዚህ ቅዱሳን በ7ቱ ዓመታት መከራ ውስጥ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው በመቀበል ደህንነትን ያገኙ ቅዱሳን ናቸው:: በራዕይ 6፣1-19፤21 በተገለጸው የመከራ ጊዜ ከነገድ፣ ከወገንና ከቋንቋ የተቤዡ ናቸው (ራዕይ 7፣9):: እነዚህ ቅዱሳን በዳን. 9፣27 ከተጠቀሰው 70ኛው ሱባኤ ወይም ሰባት ዓመታት የመከራ ዘመን ውስጥ ስመዳናቸው ማስረጃ የሚሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ራዕይ 7፣14 እና 20፣4 ናቸው::

በራዕይ 7፣14 ላይ ..እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው.. የሚለው ዓረፍተ ነገር፣ ሐሳቡ የሚያመለክተው ከመከራው ጅማሬ እስከ ፍጻሜ ኖረው ከመከራው ውስጥ የወጡና በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የቀረቡ ቅዱሳን መሆናቸውን ነው:: ቁጥራቸው ሊታወቅ አልተቻለም:: እነዚህ አይሁዶች ብቻ ናቸው ለማለት አይቻልም፤ ምክንያቱም ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ውጪ ይሆናል:: ከዚህ ጋር ማያያዝ የምፈልገው ነገር አለ:: ይኸውም እነዚህ ቅዱሳን ከመከራው ውስጥ ከምድር ወጥተው በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ለመቅረብ ያበቃቸው ልብሳቸውን በበጉ ደም ማጠባቸው መሆኑን ነው:: ይህም ከሆነ የመዳን በር በመከራው ዘመን ለአይሁዶችም ሆነ ለአህዛብ ዝግ



አለመሆኑንና የመከራው ዘመን ጽኑ የእግዚአብሔር ቁጣ ቢገለጽበትም ለንስሀ ዕድል የማይሰጥበት የፍዳና የቁጣ ዘመን ብቻ አለመሆኑን መረዳት ያሻል::

የራዕይ 20፣4 ሐሳብ ደግሞ ..በሺሁ ዓመት.. መንግስት ከክርስቶስ ጋር የመንገስ ስልጣን የተሰጣቸው ለአውሬውና ለምስሉ ያልተንበረከኩ ቅዱሳን እንደሆኑ ይገልጻል:: አውሬው (ሐሰተኛው ክርስቶስ) የምድር ነዋሪዎች እንዲሰግዱለት ማስገደድ የጀመረው ስልጣን ከጨበጠበት ጊዜ አንስቶ ነው:: በኖረበት ሰባት ዓመታት በግዛቱ ያሉትን አስገብሯል (ያስገብራል):: ያልሰገዱለትን ሁሉ ከተነጠቁት በቀር በሰባቱም ዓመታት ውስጥ በራዕይ 17፣6፤ 18፣24 እንደተጠቀሰው በጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን በኩል አስጨፍጭፏል (ያስጨፈጭፋል):: እነዚህ ቅዱሳን፤ ማለትም ከጌታ ጋር ለሺህ ዓመት ኖረው የሚነግሱት በአውሬው ዘመን በአገልግሎታቸው ምክንያት (ራዕይ 20፣4) ራሶቻቸው የተቆረጡባቸው ከሆኑ ለዚህ ዕድል የበቁት በመጀመሪያው የቅዱሳን ትንሳኤ (ራዕይ 20፣6) ዕድል ፈንታ የነበራቸው ናቸው ማለት ነው:: የትንሳኤው ጊዜ የተከናወነበትን ትክክለኛ ጊዜ ለማወቅ የሚያስቸግር ቢሆንም 70ኛው ሱባኤ ማለቂያ፣ የሺሁ ዓመት መንፍስት መጀመሪያና የገሃነም ደጆች አለቃ መታሠሪያ ጊዜ ላይ መሆኑን መገመት ይቻላል::

## 4.5. <u>የሁለቱ ነቢያት መነጠቅ</u>

የሁለቱ ነቢያት መነጠቅ ከቀሩት ሁሉ የመነጠቅ ዓይነቶች የመጨረሻው ነው ተብሎ ይገመታል:: እነዚህ ነቢያት የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሃሣብ በአውሬውና በተከታዮቹ በቀሩትም የምድሪቱ ሐጢአተኞች ላይ የሚገለጹ የእግዚአብሔር የቁጣው በትሮች ናቸው:: የአውሬውን (የሐሰተኛውን ክርስቶስ) ፈቃድ ሙሉ በሙሉ የሚቃወሙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው:: ከሁለቱ የመከራ ክፍሎች በኋላኛው የሶስት ተኩል ዓመታት ታላቅ መከራ መጀመሪያ ላይ ተነስተው ለ3፡ ዓመታት ያህል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽማሉ:: በመጨረሻም (ራዕይ 11፣7-11)

አገልግሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ አውሬው ከጥልቁ ይወጣል ይዋጋቸዋል፤ ያሸንፋቸውማል፤ ይገሉላቸውማል:: ስጋቸውም ለ3½ ቀናት ይሰቀላል:: ሰዎችም ሁለቱ ነቢያት በመሞታቸው ይደሰታሉ:: ከዚያም የህይወት መንፈስ ይገባባቸዋል ወደ ሰማይም ይነጠቃሉ:: ይህ 5ኛው መነጠቅ ነው::



# ክፍል አምስት

## <u>የቤተ ክርስቲያን የመነጠቅ ጊዜ</u>

በዚህ ክፍል የምንመለከተው መነጠቅ ምን ጊዜ እንደሚሆንና ለተሰጡትም የመነጠቅ ጊዜ ሃሣቦች የቀረቡትን መረጃዎች ይሆናል:: ..የመነጠቅ ጊዜ.. ሲባል ከመጨረሻ ነገሮች ውስጥ ማለትም የምልክቶች መታየት፣ የሺህ ዓመት ሥርዓት፣ የመከራው ዘመንና የጌታ ዳግም ምጽዐት የመሳሰሉትን ስናስብ *<u>አሁን ያለችው ቤተ ክርስቲያን የመነጠቅ ጊዜዋ በቅደም ተከተል ሲቀመጥ የት ስፍራ እንደሚሰለፍ ለማመልከት ነው::</u>*

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በዚህ ሃሣብ ላይ የተለያዩ ማስረጃዎችን በማቅረብ መጻሕፍት ጽፈዋል:: መነጠቅ የሚፈጸምበትን ትክክለኛ ቀን፣ ሰዓትና ወር ለማወቅ ባይቻልም ከፍጻሜ ነገሮች አሰላለፍ አኳያ ግን መነጠቅ ከምን በፊትና በኋላ እንደሚሆን ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ማወቅ ይቻላል:: የመነጠቅ ጊዜ ከትንቢቶች ፍጻሜ ቅደም ተከተል አንጻር መቼ እንደሚሆን ሃሣብ የሚያቀርቡ ሦስት ክፍሎች አሉ:: እነርሱን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን::

### ስለ መነጠቅ ጊዜ የቀረቡ አመለካከቶች

ስለ መጨረሻ ዘመን ስናስብ ከስድስቱ መሰረታዊ ቅደም ተከተላዊ ትዕይንቶች ውስጥ ማለትም 1ኛ. ምልክቶች 2ኛ. መነጠቅ 3ኛ. ታላቁ መከራ 4ኛ. የጌታ ዳግም ምጽዐት 5ኛ. የሺህ ዓመት መንግስትና 6ኛ. የዘላለም መንግስት ውስጥ ***መነጠቅ*** ሁለተኛውን ደረጃ ይይዛል:: ከመከራው ጋር በተያያዘ ደግሞ የመነጠቅ ጊዜ መቼ እንደሚሆን ሶስት ዋና ዋና ሃሣቦችና አመለካከቶች ጎልተው ይታያሉ:: እነርሱም የሚከተሉት ናቸው::

5.1. ቅድመ-መከራ መነጠቅ አመለካከት

5.2. መንፈቀ-መከራ መነጠቅ አመለካከት

5.3. ድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት ይገኛሉ:: የእነዚህንም አመለካከቶች ዋና ዋና ሃሣቦችና ፍቺ በጥቂቱ እንደሚከተለው ይሆናል::

## 5.1. ቅድመ-መከራ-መነጠቅ አመለካከት

በቅድመ-መከራ መነጠቅ የሚያምኑ ክፍሎች 70ኛው በዳንኤል የተባለው ሱባኤ (የሰባቱ ዓመታት መከራ) ከመጀመሩ ወይም አውሬው ከእስራኤልና ከዓለም ሕዝብ ጋር የአንድ ሱባኤ ቃል ኪዳን አድርጐ በግልጽ ከመውጣቱ በፊት የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል የሚሉ ናቸው:: በዚህ ጊዜ የሚነጠቁት ጌታን ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉ አማኞች ሁሉ እንደሚሆኑ ያምናሉ:: የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች አሉ:: እኔም በቅድመ መከራ መነጠቅ ከሚያምኑት ክፍል ስለሆንኩ ዝርዝር እውነቶችንና ማስረጃዎችንም ጭምር በሚቀጥሉት ክፍሎች እንመለከታለን::

## 5.2. መንፈቀ-መከራ መነጠቅ አመለካከት

የዚህ አመለካከት ተከታዮች የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በመከራው አጋማሽ እንደሚሆን የሚያምኑና የሚያስተምሩ ክፍሎች አቋማቸው እንደሚከተለው ነው:: መከራው የመጀመሪያው ሦስት ተኩል ዓመታት ..አነስተኛ መከራ.. እና የኋለኛው 3½ ዓመታት ..ታላቁ መከራ.. የሚል ሁለት ክፍሎች እንዳለው ያምናሉ:: በመጀመሪያው 3½ ..አነስተኛ የመከራ.. ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንዳለችና በመከራው ውስጥ እንደምታልፍ ከዚያም የኋለኛው ..ታላቁ መከራ.. ማለትም ታላቁ የእግዚአብሔር ቁጣ ሳይጀምር የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል ይላሉ::

በዚህ በመከራው አጋማሽ መነጠቅ እንደሚሆን ከሚያስተምሩት መሪዎች ውስጥ እ.ኤ.አ. በ1895-1976 የኖረው ጄምስ ኦ በዝዌል እና በ1874-1960 የኖረው ኖርማን ቢ. ሃሪዘን ዋነኞቹ ናቸው:: ሆኖም ግን ኖርማን ቢ ሃሪዘን ከጄምስ ኦ በዝዌል በላቀ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በመከራው አጋማሽ መሆኑን ያጠነክራል፣ ያስተምርማል:: እንደ ሪቻርድ ኤሪክሰን አገላለጽ በ«መንፈቀ-መከራ» መነጠቅ አምነው ከሚያስተምሩት ሰዎች አንዱ



ሃሪዘን ሃሣቡን ለማጽናት ከሚያቀርባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

5.2.1. እስከ ራዕይ 11 የተጠቀሰው መከራ ..ታላቁ መከራ.. ሳይሆን ..የምጥ ጣር መጀመሪያ.. ከሰባቱ ዓመታት የመጀመሪያው 3½ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ታልፍና ልክ ግማሽ ላይ ትነጠቃለች::

በማቴ. 24:8፤ቁ.21ና በራዕይ 6-9 የተጠቀሱት የሰባቱ መለከቶችና የሰባቱ ማህተሞች ቁጣ ሲፈጸም ቤተ ክርስቲያን ትኖራለች ይላል:: ሃሪዘን የተባለው የዚሁ የመነጠቅ ክፍል አማኝ ..የእግዚአብሔር ቁጣ.. የሚፈጸመው ..በታላቁ መከራ.. ጊዜ እንደሆነ ይህም ታላቁ መከራ የእግዚአብሔር የሰባቱ የቁጣ ጽዋዎች የሚፈሱበት ጊዜ መሆኑን ገልጿል:: በመለከቶቹና በማህተሞቹ ጊዜ ..ቁጣ.. እና ..መቅሰፍት.. የሚለው ቃል ስላልተጠቀሰ ይህ የምጥ ጣር መጀመሪያ ነው:: ራዕይ 14:10፤ 19፤ 15:7፤ 16:1:: በራዕይ 11:18 ላይ ..ቁጣ.. የሚለው ቃል ገና መጠቀሱ ስለሆነ ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ጽኑ ቁጣ ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በኋላ መጀመሩን ነው ይላል::

5.2.2 . የ1ኛው ቆሮንቶስ 15:52 ..የኋለኛው መለከት.. መነፋት

በመከራው አጋማሽ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል የሚሉ ክፍሎች በመረጃነት የሚያቀርቡት ጥቅስ በቆሮንቶስ የተጠቀሰው ነው:: በ1ኛ ቆሮ. 15:52 የተጠቀሰው የኋለኛው መለከት በራዕይ 11 ውስጥ ከተጠቀሰው 7ኛው መለከት ጋር አንድ ዓይነት ነው:: በራዕይ 11:15 ሰባተኛው መልአክ የነፋው መለከት የመጨረሻው ነው:: ከዚያ በኋላ ሌላ መለከት አልተነፋም፤ ይህ የኋለኛው መለከት በመሆኑ ከቆሮንቶስ ጋር ይሄዳል፤ በመቀጠል የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል የሚል ማስረጃ ያቀርባሉ::

ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በሚመለከት ትክክለኛ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሌሎችንም ማስረጃዎች ..በቅድመ-መከራ-መነጠቅ.. በምዕራፍ ስድስት ውስጥ አቀርባለሁ::

## 5.3. <u>ድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት</u>

ይህንን ትምህርት የሚከተሉ አማኞችና ቤተ ክርስቲያናት ያላቸው አቋም የሚከተለው ነው:: ቤተ ክርስቲያን በታላቁ መከራ (በሰባኛው ሱባኤ) ውስጥ ታልፋለች:: መከራው ካለቀ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መነጠቀ ይሆናል የሚሉ ሲሆኑ ይህንንም አቋም አንዳንድ የሮም ካቶሊክ፣ የግሪክ ካቶሊክ፣ ወግ አጥባቂ የሆኑ የፕሮቴስታንትና የሌሎችም ቤተ ክርስቲያናት በጥብቅ ይከተላሉ::

የድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት ቀላል ዓይነት ፍቺ ያለው ቢመስልም፣ በውስጡ ሦስት ያህል የተለያዩ ክፍሎችን ይዟል:: እነርሱም፣

5.3.1. አምናዊ ድህረ-መከራ መነጠቅ

5.3.2. ከፊል-አምናዊ ድህረ-መከራ መነጠቅ

5.3.3. ነጋዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ ናቸው::

### 5.3.1. <u>አምናዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ</u>

በዚህ የመነጠቅ ጊዜ የሚያምኑ ክፍሎች መከራው ገና ዱሮ በቤተ ክርስቲያን ላይ ስለሆነ ታላቁ መከራ ተፈጽሟል (አልፏል) የሚሉና ምናልባት ከሩብ ያነሰው መከራ እንደሚቀር የሚያምኑ ናቸው::

የዚሁ የአምናዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ መሪ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ጂ-ባርተን ፓይን ስለ መከራው የተነገሩት ትንቢቶች መፈጸማቸውን ያጠነክራል:: ከዚሁም ጋር የተያያዘውን ማስረጃ በሚከተሉት አራት ነጥቦች ማጠቃለል ይቻላል፤ ባርተን ፓይን፤

5.3.1.1. የክርስቶስ ዳግመኛ ምጽፀት ቅጽበታዊ ሆኖ የቤተ ክርስቲያንንም መነጠቅ ይጨምራል::

5.3.1.2. ይህም ዳግም ምጽፀት ከመከራው በኋላ ይሆናል::



5.3.1.3. በቅድመ-ዳግም-ምጽፀት የሚሆነው መከራ ግልጽ ወይም ቃል በቃል የሚፈጸም (ሊትራል) ሳይሆን ምሳሌያዊነትን ወይም ረቂቅ ትርጉምን (ፊገራቲቭ) የያዘ ነው::

5.3.1.4.1. ከክርስቶስ ዳግም ምጽፀት በኋላ ግልጽ የሆነ-የሚታይ (ሊትራል) የሺህ ዓመት ሥርዓት ይቀጥላል ይላል::

ፓይን ይህንን ሃሣቡን በይበልጥ ያገኘው ከቀደሙት አባቶች ትምህርት መሆኑን ገልጿል:: ከእነዚህም ውስጥ "የመጀመሪያው የቀሌምንጦስ መልዕክት"፣ "የበርናባስ መልዕክት"፣ "የኢግናቲየስ መልዕክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች" እና "የኢግናቲየስ መልዕክት ወደ ፖሊካርፕ" ጥቂቶቹ ናቸው:: በተጨማሪም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚጠቅሳቸው ክፍሎች አሉት::

### 5.3.2. <u>ከፊል አምናዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ</u>

የዚህ መነጠቅ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ተከታዮች ደግሞ የመከራው ዘመን ቀድሞ ጀምሮአል፤ በከፊል ተፈጽሟል፤ ሆኖም ግን ሙሉ በሙሉ አላለቀም የሚል ሃሣብ አላቸው:: ይህንንም ሃሣባቸውን በማጠናከር የመከራው ዘመን ቀደም ብሎ የጀመረና አሁን ቤተ ክርስቲያን ካለች መነጠቅ ወደፊት ይሆናል የሚለውን የቅድመ-መከራ መነጠቅ አማኞችን አመለካከት እንደ ሞኝነት ይቆጥራሉ:: እነዚህም ቢሆኑ እርስ በርሳቸው የተለያየ አመለካከት አላቸው::

የከፊል-አምናዊ ድህረ-መከራ መነጠቅና ባጠቃላይ የድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት ተከታዮች ስለ መነጠቅ ወይም ስለ ፍጻሜ ነገሮች ሲያስቡ የትንቢቶችን አፈጻጸም ቃል በቃል ሳይሆን በረቂቅ ሁኔታ እንደሚያልፉ ያምናሉ::

### 5.3.3. ነጋዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ

የነጋዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ አመለካከት ያላቸው ክፍሎች መከራው (ታላቁ መከራ) ፈጽሞ ገና እንዳልጀመረና ወደፊት እንደሚቀጥል ያምናሉ:: መከራው ተጀምሮ ካለቀ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል:: በቤተ ክርስቲያን መነጠቅና በክርስቶስ ዳግም ምጽዐት መካከል የለባት ዓመታት የጊዜ ርዝመት እንዳለ ያምናሉ:: እስከ ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይህ አመለካከት በሰዎች ዘንድ ጐልቶ አልታወቀም ነበር::

በድህረ-መከራ መነጠቅ የሚያምኑ ክርስቲያኖች ቀደም ብሎ ካየናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች በተጨማሪ የሚያቀርቧቸው አሉ:: ለምሳሌ በሐሥ 8:1-3 ..በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ::.. ይላል:: ይህንንም እውነት በመጥቀስ ..ታላቅ ስደት.. የሚያመለክተው ..ታላቅ መከራን.. ነው:: የእስጢፋኖስም መወገር ታላቁ መከራ መጀመሩን ከሚያመለክቱት መረጃዎች አንዱ ነው:: ጌታ ኢየሱስም በማቴ. 24:21 ..ታላቁን መከራ.. ለመግለጽ የተጠቀመበት ..ስሊፕሲስ.. የተሰኘ ው የግሪክ ቃልና በሐሥ. 8:1 ላይ የተጠቀሰው ..ታላቅ ስደት.. የሚለው ቃል አንድ ዓይነት ስለሆኑ የመከራው ዘመን ቀድሞውኑ ጀምሯል ይላሉ:: በምዕራፍ አምስት ..የመነጠቅ ጊዜ.. ንዑስ ርዕሶች ስር ስለ አመለካከታቸው እንጂ ሊሆን ስለሚገባው ትክክለኛ ሃሣብ ምንም ማስረጃ አልቀረበም::



# ክፍል ስድስት

## ቅድመ-መከራ መነጠቅ

በዚህ ክፍል ስለ ቅድመ-መከራ መነጠቅ ምንነት፣ አመለካከት፣ የቀረቡትንም ልዩ ማስረጃዎችና የታወቁትን የዚህ እምነት ተከታይ መሪዎች በዝርዝር እንመለከታለን::

### 6.1 የቅድመ-መከራ መነጠቅ አመለካከት

የዚህ መነጠቅ ክፍል ተከታዮች ቀደም ብሎ በምዕራፍ አምስት እንደጠቀሰው በዳንኤል የተባለው ሰባኛው ሱባኤ (የሰባቱ ዓመታት መከራ) ሳይጀምር የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል:: የከራዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንጂ አሁን ያለችው ቤተ ክርስቲያን በ ታላቁ መከራ ውስጥ ፈጽሞ አታልፍም:: በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጊዜ ክርስቶስ ኢየሱስ ለዘህ ዓለም ለመታየት በግልጽ አይመጣም፤ ሆኖም ግን ወደ ተወሰነ የአየር ክልል መጥቶ ቅዱሳኑን በመውሰድ በሰማይ ወደ ተዘጋጀው ስፍራ ይመለሳል:: ከዚያም የመከራው ዘመን ካለፈ በኋላ ለሺህ ዓመት ለመንገስ ወደ ምድር ይመለሳል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ አቋሞቻቸው ናቸው::

### 6.2. የቅድመ-መከራ መነጠቅ ማስረጃዎች

ከነባራዊ እውነታ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር ሲነገር ወይም ሲደረግ፣ ለዚያ ለተከናወነው ነገር እውነተኝነት ማስረጃ ይቀርባል:: ያም ማስረጃ የአንድን ድርጊት ወይም አባባል ርቱእነተ ለማስረገጥና በሌሎችም ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በወኪልነት ለመቆም ብቃት ያለው ይሆናል:: ሆኖም ግን የማስረጃ ሁሉ ብቁነት (ትክክለኛነት) የሚጸናውና የሚጸድቀው ማስረጃውንና አቅራቢውን የሚዳኝ ሌላ የበላይ የሌለው እውነተኛ እስኪገለጥ ይሆናል::

ቀደም ባለው ምዕራፍ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ የሚሆንበትን ጊዜ ለማመልከት ሦስት ያህል ዋና ዋና ሃሣቦች እንዳሉ ጠቅሻለሁ:: በዚህኛው

ምዕራፍ ግን ባለፈው ምዕራፍ በቂ ማብራሪያና ገለጻ ያልሰጠሁበትን የ..ቅድመ-መከራ መነጠቅ.. ሁኔታ ማስረጃዎችን አቀርባለሁ:: እኔም ብሆን የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት ይሆናል፤ ቤተ ክርስቲያን በ70ኛው ሱባኤ መከራ አታልፍም ከሚሉት ስለሆንኩ በተለያዩ ጊዜያት ከመጽሀፍትና ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክም ያገኘኋቸውን ማስረጃዎች ለማቅረብ እሞክራለሁ::

***<u>የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት::</u>***

### 6.2.1. <u>የ..ዮሐንስ ራዕይ.. መጽሐፍ ቅደም ተከተላዊ አቀማመጥ</u>

ከ66ቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ውስጥ ሐዋርያው ዮሐንስ የጻፋቸው መጻሕፍት የክንዋኔዎችን ቅደም ተከተል ከጊዜ አንጻር ከሚገልጹት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: ከእነዚህም ውስጥ የሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌልና የዮሐንስ ራዕይ ናቸው:: በሁለቱ የዮሐንስ መጻሀፍት ውስጥ አንድ ድርጊት ከተፈጸመ በኋላ ሌላው እንደሚቀጥል የሚያመለክቱ ሐረጎች ብዙ ጊዜ ተጠቅሰዋል::

ለምሳሌ:- ..<u>ከዚህም በኋላ</u>..፣ ..<u>ከዚያም በኋላ</u>..፣ ..<u>ከእነዚህም ነገሮች በኋላ</u>.. ... <u>**የተሰኙት ይገኛሉ::**</u> እነዚህንም ሐረጎች በዮሐ. 3:22፤ 5:1፤ 6:1፤ 7:1፤ 21:1፤ 5:14፤ 13:7፤ በራዕይ 1:19፤ 4:1፤ 7:1፤ 9:12፤ 18:1፤ 19:1፤ 15:5፤ 20:3፤ እናገኛቸዋለን::

እነዚህ ሐረጎች የተጠቀሱበት ምክንያት የነገሮችን ክንዋኔ ከጊዜ አንጻር ለማመልከት ነው:: የእነዚህ ሐረጎች (በተለይም ..ከዚህ በኋላ.. የሚለው) በዮሐንስ ተደጋግመው መነገራቸው የዮሐንስ መልዕክት በይበልጥ ነገሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ላይ ያተኮረ እንደሆነ ያመለክተናል (ያረጋግጥልናል):: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን እነዚህን ሐረጎችና



ጠቅታዊውን የታሪክ ምስክርነት መሠረት በማድረግ የዮሐንስ ራዕይን መጽሐፍ በአምስት ተከታታይ ክንዋኔዎች መክፈል ይቻላል::

***<u>የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ አከፋፈል</u>***

| <u>ተ. ቁ.</u> | <u>ምዕራፍ</u> | <u>ትዕይንቶች</u> |
|---|---|---|
| 1 | 1 | አጠቃላይ መልዕክት (መግቢያ) |
| 2 | 2-3 | የቤተ ክርስቲያን ዘመን ክንዋኔ |
| 3 | 4-5 | ቅዱሳን በሰማይ (ድህረ-መነጠቅ) |
| 4 | 6-19 | የታላቁ መከራ (70ኛው ሱባኤ) ጊዜ |
| 5 | 20 | የሺህ ዓመት መንግሥት ክንዋኔ |
| 6 | 21-22 | የዘላለም መንግሥት (የአዲስ ሰማይና ምድር ሥርዓት) |

በተራ ቁጥር 4 ላይ ጥቂት ምዕራፎች የመከራውን ዘመን ትዕይንት የሚያመለክቱ አሉ::

ማንኛውም የራዕይን መጽሐፍ የሚያጠና የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ጥራት ባለው መረዳት በሠንጠረዡ ውስጥ እንደተቀመጠው ቅደም ተከተል መጽሀፉን ለማጥናት ካልሞከረ ችግር ይገጥመዋል:: በመንፈቀ-መከራ መነጠቅና በድህረ መከራ መነጠቅ ለሚያምኑ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን እንዳይቀበሉ ካረጋቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ የራዕይን መጽሐፍ በቅደም ተከተል መቀመጥ አለመገንዘብ ነው::

***<u>የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ቁልፍ ጥቅስ የሆነውን ምዕ.1:19 ስንመለከት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሏል:: ይኸውም:-ያየኸውን፣ አሁንም ያለውን የሚለውና ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን የሚሉት ናቸው::</u>***

..ያየኸውን.. ሲል በራዕይ 1:11-17 ያለው፤ ..አሁንም ያለውን.. ሲል በራዕይ 2 እና 3 በወቅቱ ያለውንና የወደፊቱ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ፤

..ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን.. ሲል ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ሁኔ ካበቃ በኋላ (በራዕይ 4:1 እንደተመለከተው) ማለትም የቤተ ክርስቲያ መነጠቅ ከሆነ በኋላ የሚፈጸመውን ለማመልከት የቆመ ሃሣብ (እውነት ነው:: የራዕይ መጽሐፍ የተጻፈበት ዋነኛ ሃሣብ ከራዕይ 1:1 ስንመለከ ..ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ለማሳወቅ (ለማሳየት) ነው:: ምዕራ 1:19ኝንም ስናይ መጽሐፉን በሦስት ክፍሎ አጠቃላይ መልዕክቱን በቅደ ተከተል ያስቀምጥልናል:: የራዕይ መጽሐፍ በሙሉ በቅደም ተከተ በመጨረሻው ዘመን ለሚፈጸሙ ነገሮች (ትዕይንቶች) የተጻፈ ለመሆኑ በ መረጃ ልናገኝ የምንችለው የቅድመ-መከራ መነጠቅን ማስረጃዎች በሙ ከተመለከትን በኋላ ስለሚሆን ወደሚቀጥለው ማስረጃ ማለፉ ይመረጣል::

ከዚያ በፊት ግን በራዕይ መጽሐፍ በቅደም ተከተል ላይ ጥያቄ ቢኖር የዘላለም መንግስትና የሺሁ ዓመት መንግሥስት አለመጀመሩ በጥብቅ መረዳት፤ በተጨማሪም 70ኛው ሱባኤ (የሰባቱ ዓመታት መከራ) ላለመጀመሩ ዋነኛ ማስረጃ የሐሰተኛው ክርስቶስ ከእስራኤል ጋር የአንድ ሱባኤ ቃል ኪዳን አለማድረጉን መረዳት አንዱ ማስረጃ መሆኑን ማወቅ መልካም ነው:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከራዕይ መጽሐፍ አሰላለፍ አንጻር ከመከራው በፊት ይሆናል ማለት ነው::

### 6.2.2. የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በራዕይ 4:1 እንደሚሆን መረጃዎች መኖራቸው:

በራዕይ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ውስጥ ስለ ቤተ ክርስቲያን መኖር ይናገራል:: እንደ ኀላፍያንና ታሪካውያን አተረጓጎም ሁለቱ ምዕራፎች ስለ ሰባቱ የወቅቱ ቤተ ክርስቲያናት ሲናገር፤ እንደ መጻዕያንና በድጋሚ እንደ ታሪካውያን አተረጓጎም ደግሞ ሁለቱ ምዕራፎች እስከ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ድረስ በመላው ዓለም የምትገኘውን የዐለምአቀፋዊቱን ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ታሪካዊ ይዘት የሚያሳይ ነው:: ራዕይ 2ና3 ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚተርከው በ 4:1 ላይ ሰማይ ከመከፈቱ በፊት ነው:: ራዕይ 4:1



ላይ ግን ሰማይ ስከፈት ያሳያል:: ለምን? ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የበጉ ሚስት ክፍል ሆና በ19:14 ላይ ለሺህ ዓመት ስርዓት ከሰማይ ወደ ምድር ስትወርድ ያሳያል (ራዕይ 17:14):: ከራዕይ 19ኛው ምዕራፍ በኋላ ሰማይ ተከፍቶ አልታየም:: በዚህ ክፍል ግን ከሰማይ በአምባላይ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ፊት ፊት እየሄደ የሚመራቸው ከሰማይ የሚመጡትን ቅዱሳን ነው:: እነዚህ ቅዱሳን በራዕይ 17:14 እንደተጠቀሰው ከጌታ ኢየሱስ ጋር ሆነው አውሬውን በመዋጋት የሚያሸንፉ (ድል የሚያደርጉ) ናቸው (ራዕይ 19:19)::

በራዕይ 19:14፣17:14 የተጠቀሱት ቅዱሳን በራዕይ 19:11 ከተጠቀሰው በጽድቅ ፈርዶ ከሚዋጋው ከጌታ ኢየሱስ ጋር የሚተባበሩ ናቸው:: አውሬውንም ለመዋጋት የሚመጡትም ከሰማይ ከሆነ ደግሞም ..የበጉ ሚስት.. ቅዱሳን ከሆኑ ..የበጉ ሚስት.. የተባሉት ደግሞ የዘመናት ቅዱሳን ከሆኑ ..የበጉ ሰርግ.. የተካሄደው በሰማይ ከሆነ እነዚህ ቅዱሳን እንዴት ሆነው ወደ ሰማይ ወጡ ወደሚል ጥያቄ እንደሚመራን አሌ የማይባል ሐቅ (እውነት) ነው::

መልሱ በበጉ ሰርግ ተካፋይ የሚሆኑት የታመኑት የተጠሩትና የተመረጡት ቅዱሳን ከምድር ወደ ሰማይ የተሸጋገሩት በመነጠቅ ነው:: ይህም መነጠቅ (በራዕይ 4:1፣ 7:13-14፣ 7:1-8ትን ከ14:1-3 እና 12:5እን በማወዳደር) የተፈጸመና የተከናወነ ነው ማለት ነው:: ስለእነዚህ ቅዱሳን ዝርዝር ነገሮችን ለማየት በምዕራፍ አራት ..የመነጠቅ ዓይነቶችን.. ይመልከቱ:: የራዕይ 4:1 መነጠቅ ግን በተለይ የበጉ ሚስት ክፍል ከሆኑት ቅዱሳን ..በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ.. ላይ ያተኩራል:: የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በራዕይ 4:1 ላይ ይሆናል:: አሁን ላለችው ቤተ ክርስቲያን ከራዕይ 4:1 የተለየ የመነጠቂያ ቦታ የለም:: ራዕይ 7:13-14 የመከራውን ዘመን ቅዱሳን መነጠቅ፣ ራዕይ 7:1-8 እና 14:1-3፣ 12:5 የ144000 አይሁዶችን መነጠቅ፣ ራዕይ 11:12 የሁለቱን ነቢያት መነጠቅ የሚያመለክት ከሆነ ራዕይ 4:1 የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ የሚያመለክት ስመሆኑ ምንም አያጠራጥርም::

የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በራዕይ 4:1 ላይ ስመሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከታሪክ ማስረጃ ማግኘቱ ትክክል ሊታምን ይገባል:: ስለሆነም የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት::

### 6.2.2.1. ..ከዚያ በኋላም.. የተሰኘው ሐረግ

..ከዚያ በኋላም.. የሚለው በራዕይ 4:1 ላይ የተጠቀሰው ሐረግ የሚያመለክተው በዮሐንስ ራዕይ ከምዕራፍ 1-3 የሚታዩ፡ የሚደረጉና የሚነገሩ ነገሮች ወይም ትዕይንቶች ከተፈጸሙ በኋላ ያለውን ድርጊት የሚጠቁም ነው:: ..ከዚያ በኋላም.. የሚለው ሐረግ ከቤተ ክርስቲያን በኋላ ወይም ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገረው ሁሉ ከሆነና ከተፈጸመ በኋላ ወይም የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከሆነ በኋላ የሚለውን ሃሣብ ሁሉ ያካትታል::

ከራዕይ 2-3 የተነገረው ትንቢት ሁሉ በዮሐንስ ዘመን በነበሩት ሰባቱ ቤተ ክርስቲያናት ላይ ብቻ ያተከረ አይደለም:: ሰባቱ ቤተ ክርስቲያናት ታሪካዊ ዕውነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በትንቢታዊ መልኩ ደግሞ በመላው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዘመንና ህልውና ሊገጥሙ ስለሚችሉት ሁኔቶችም በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው:: የቤተ ክርስቲያን ዘመን እስካበቃ ድረስ በዓለም የሚመሰረቱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ ሊገጥማቸው ያለ ባህሪና አሰራር በዋና ደረጃ በእነዚህ በትንሹ እስያ ባሉት ቤተ ክርስቲያናት ተካተቶ ቀርቧል:: የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈ ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏል ስለሚል ለእነርሱ የተጻፈውን በማንበብ እኛም ልንጠነቀቅ ይገባል::

እግዚአብሔር ለሰባቱም ቤተ ክርስቲያናት መልዕክቱ እንዲተላለፍ ሲያደርግ ቢያንስ ሰባት ያህል ደረጃዎችን የያዘ እውነት በውስጡ አስቀምጦ ነው:: ለምሳሌ 1. ስለ ክርስቶስ ማንነት የሚገልጡ ስሞችን 2. የቤተ ክርስቲያናቱን ብርቱ ጎንና 3. ደካማ ጎን 4. ማስጠንቀቂያ 5. የመንፈስ ቅዱስን መልዕክት ስለመቀበል 6. የንስሐ ጥሪ 7. ማበረታቻና ሽልማት ይገኛሉ:: በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያሉትን ቤተ ክርስቲያናት ስንመለከት



በአብዛኛው ከላይ ከተጠቀሱት ሰባት ደረጃዎች የራቁ አይደሉም:: አንዳንዶች ምናልባት አይመስከተንም ማለት ይችሉ እንደሆን ራሳቸውን በትክክል መመዘን ከቻሉ አይከለከሉም:: ሆኖም ግን የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ልብና ኩላሊት መርማሪ ክርስቶስ ነው:: ራዕይ 2:23:: ከላይ የተጠቀሱት ሁነቶች በሙሉ ወይም በከፊል ከተፈጸሙ በኋላ የመነጠቅ ጊዜ ሲሆን አሁን ያሰችው የቤተ ክርስቲያን አኗኗር ያበቃል ማለት ነው:: ስለሆነም በዘመኑ ያለን ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ ማንነታችንን በጥንቃቄ መመርመር አለብን::

..ከዚያ በኋላም.. ሲል ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በኋላ መሆኑን ያመለክታል:: ይህ ከሆነ እስከ ዛሬ ድረስ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ አልሆነም:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን አሁን ካለ ..መነጠቁ.. ወደፊት ይሆናል:: መከራውም አሁን ካልጀመረ እርሱም ወደፊት ይሆናል ማለት ነው:: የቤተ ክርስቲያን ዘመን (ራዕይ 2-3) ከተፈጸመ በኋላ በራዕይ 4:1 መነጠቅ ይሆናል:: መነጠቅ ከሆነ በኋላ ደግሞ ከራዕይ 4 ና 5 እንደምናየው ስተነጠቁት ቅዱሳን በሰማይ ፕሮግራም ይያዛል ማለት ነው::

### 6.2.2.2. ..በሰማይ የተከፈተ ደጅ.. (በር) የሚለው ሐረግ

ይህ ..በሰማይ የተከፈተ ደጅ.. የሚለው ሐረግ በቀጥታ የሚያመለክተው ደጁ በሚከፈትበት ወቅት በምድር ላይ በቀጣይነት ከሚፈጸሙ ነገሮች ጋር የተያያዘ ታሪክን ለመግለጽ መሆኑን ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስድስት ያህል ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ሰማይ ተከፍቶ አይተዋል:: ከእነዚህም ውስጥ፣

6.2.2.2.1. ሕዝቅኤል (1:1) ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት ራዕይን ከእግዚአብሔር ለመቀበል

6.2.2.2.2. ጌታ ኢየሱስ (ማቴ.3:16፣ ማር.1:10) ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት ከእግዚአብሔር አብ ስለ ጌታ ማንነት፡ ስለ ስው ልጆችና ስለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል መውረድ ምስክርነት ለመስጠት፤

6.2.2.2.3. ናትናኤል (ዮሐ.1:51) ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት የእግዚአብሔር መላዕክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ለማሳየት፡

6.2.2.2.4. እስጢፋኖስ (የሐዋ.7:56) ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት የአብና የወልድ ለእስጢፋኖስ መጽናኛ መታየት

6.2.2.2.5. ጴጥሮስ (የሐዋ.10:11) ከእግዚአብሔር ለጴጥሮስ መልዕክት ለማስተላለፍ (ምልክት ለማሳየት)

6.2.2.2.6. ሐዋርያው ዮሐንስ (ራዕይ 4:1፣ 11:19፣ 19:11)

በራዕይ 4:1 ላይ ግን የሰማይ ደጅ ለምን ተከፈተ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ ለዮሐንስ መልዕክት ለማስተላለፍ እንደሆነ ነው:: የተላለፈለት መልዕክት፣ወደዚህ ውጣና ሲል ከምድር ወደ ሰማይ እንዲወጣና ቀጣዩን መልዕክት እንዲቀበል ነው:: ይህ ቀጣይ መልዕክት ምንድን ነው? ዮሐንስ ወደ ሰማይ የወጣው በዚህ አካሉ አይደለም፤ በመንፈስ ነው:: በመንፈስ ከሆነ ይህ ለምን ተፈጸመ ስንል የቤተ ክርስቲያንን የቅዱሳንን ወደ ሰማይ መሸጋገር የሚተነብይን (የሚገልጽን) እውነት በውስጡ እንደያዘ እናገኛለን:: በራዕይ 2 እና 3 ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ሁሉ ነገር ከተፈጸመ በኋላ የሰማይ ደጅ የተከፈተው ያለ ምክንያት አይደለም:: በራዕይ ከ1-3 ባለው ትንታኔ ከሰማይ መልዕክት ሲመጣ ሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክቱን የተቀበለው ወደ ላይ ሳይወጣ ከሆነ ልዩ ትዕይንት ከሌለ ለምን ወደ ላይ መውጣት አስፈለገ?

ራዕይ 19:11ን ስንመለከት ሰማይ የተከፈተበት ምክንያት ከመጀመሪያው መነጠቅ እስከ መጨረሻው መነጠቅ በበጉ ሰርግ ተካፋይ የሆኑት ቅዱሳን በሰማይ የሰርጉን ስርዓት እንደጨረሱና ወደ ምድር መመለሳቸውን ለማመልከት ነው:: ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው ሰማይ ሲከፈት በሰማይና በምድር መካከል የድምጽ፣ የራዕይ ወይም የእንቅስቃሴ ግንኙነት እንደሚሆን ነው:: ስለሆነም በራዕይ 4:1 ላይ ሰማይ ተከፍቶ ከታየ



ከራዕይ 2 እና 3 በኋላ ለቤተ ክርስቲያን መነጠቅ መንገድ እንደሚዘጋጅ ግንኙነትም እንደሚሆን ያመለክታል::

የሥነ ከዋክብት ጥናት ማስረጃ

የመጽሐፍ ቅዱሳችን ደራሲ ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስመሆኑ ከሚያስረግጡልን እውነቶች ውስጥ በቅርብ የተገኘው የሥነ-ከዋክብት ተመራማሪዎች መረጃ ነው:: ብዙ የዓለም አዳዲስ የሚመስሉ ግኝቶች አስቀድመው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተተንብየዋል:: ዳን. 12:3-4:: ምርምርንና ዕውቀትን መሰረት በማድረግ በአሁኑ ጊዜ ሳይንቲስቶች ብዙ ግኝቶችን ለማቅረብ ሞክረዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ከአራቱ የምድር ሰማያዊ ማዕዘናት ሦስቱ በከዋክብት ክምችት የተሞሉ ሲሆኑ አንደኛው ማለትም ሰሜናዊው ክፍል ክፍት የመሆኑ ጉዳይ ነው:: ይህ የከዋክብት አጥኚዎች በሰሜን በኩል ያገኙት ክፍተት ዲያሜትሩ 16 ትሪሊየን ማይልስ መሆኑን አረጋግጠዋል:: ይህ በሰማይ የሚገኘው ክፍተት በአሁኑ ዘመን አስትሮኖመሮቹ (የከዋክብት አጥኚዎቹ) ከማግኘታቸው በፊት እግዚአብሔር በመንፈሱ ለባሪያዎቹ (ለቅዱሳን አገልጋዮቹ) ገልጾ ነበር:: ከእነዚህም ውስጥ፣

በኢዮብ 26:7 ላይ ..እግዚአብሔር ሰሜንን በባዶ ስፍራ ላይ ይዘረጋል.. ይላል:: በመቀጠልም በዚሁ በሰሜን በኩል የሚያስፈራ ግርማ ያለው ወርቅ የሚመስል ብርሃን እንደሚወጣ ይገልጻል:: ይህም ጌጠኛ ወርቅ መሳይ ብርሃን ጌታ ኢየሱስ ነው::

በኢሳ. 14:13-14 ደግሞ የእግዚአብሔር ዙፋን በሰሜን በኩል መሆኑንና ሰይጣንም በሰሜንም ዳርቻ እቀመጣለሁ ሲል ከምድር ወደ እግዚአብሔር ዙፋን አቅጣጫ ትኩረት ማድረግንና መንገስን እንደፈለገ ያመለክታል::

በኢሳ.41:25 ደግሞ ..እግዚአብሔር አንዱን ከሰሜን አነሳሁ፣ መጥቷልም.. ይላል:: ይህ ከሰሜን የሚመጣው ማንነት ከምድራዊ ፖለቲካ ጋር ካልታያያዘ በስተቀር ጌታ ኢየሱስን የሚያመለክት ነው::

ይህንን ጥቅስ በማስረገጥ ሕዝቅኤል ደግሞ በምዕራፍ 1:4 ላይ ..እነሆ ከሰሜን በኩል አውሎ ነፋስና ታላቅ ደመና የሚበርቅም እሳት ወጣ ... የወርቅ ምስያ ነበር.. በማለት ጽፏል:: በዚህም ምዕራፍ ውስጥ ሕዝቅኤል ኢሳይያስ ባየው ክብር ዓይነት የእግዚአብሔርን ክብር አይቷል:: በዚህ የሰሜናዊ ክፍል ክፍተት ውስጥ ከአስትሮኖመሮች አንዱ ፕሮፌሰር ሴአርኪን እንደገለጹት አስደናቂ ነገር እየታየ መሆኑን ነው:: ይህም አስደናቂ ነገር ግሩም የሆነ ውበትና ቀለሙ በምድር ተወዳዳሪ የሌለው፣ እንደ መስታዎት አንጸባራቂ ወንዝ፣ በከበረ ድንጋይ የተሰሩ የሚያበሩ ምሰሶች፣ በዕንቁና በብዙ ሚሊየን አልማዝ ከተሰራ ግድግዳ በስተጀርባ አንጸባራቂ ብርሃን መሰል ከተማ ከበስተሰሜኑ ኦርዮን ባሻገር መኖሩን አረጋግጠዋል:: ይሄ የሰሜን ጉዳይ ምን ይሆን? እስቲ ምርምራችንን እንቀጥል! ሌላ ነገርስ ይኖር ይሆን?

ከዚህ መረጃ የምንረዳው ነገር ይኖራል:: ሁሉን ቻይ: ሁሉን አዋቂ፣ በሁሉ ቦታ ተገኚና ዘላለማዊ ባህሪ ያለው እግዚአብሔር ለኢዮብ፣ ለሕዝቅኤልና ለኢሳይያስ ሰሜናዊው የሰማይ ክፍል ክፍት መሆኑን፣ የእግዚአብሔርም የዙፋን ክብር በስተ ሰሜን በኩል መሆኑንም ገልጾላቸዋል:: ለሐዋርያው ዮሐንስ ግን በየትኛው አቅጣጫ መሆኑን ባይገልጽለትም (አልተጻፈም) ሰማይ ክፍት ሆኖ በራዕይ 4:1 እና 19:11 ላይ አሳይቶታል:: ከእነዚህ ጥቅሶች ሰሜናዊው ክፍል ከከዋክብት በከፍተኛ ደረጃ ነጻ የሆነው የእግዚአብሔር ብርሃን ያለበት፣ ዙፋኑም በዚያ ያለ፣ ወደፊትም ከሰማይ ወደ ምድር የሚመጣው ከዚሁ አቅጣጫ መሆኑን ነው:: ይህም ደግሞ በእግዚአብሔር ሰዎች ብቻ ሳይሆን የዓለም ሳይንቲስቶችም በደረሱበት ደረጃ ማረጋገጥ ችለዋል:: በራዕይ 4:1 ላይ የተጠቀሰው ..የተከፈተ ደጅ.. የሚለው ሐረግ የያዘው ሃሣብ በእግዚአብሔር ዙፋንና በምድር መካከል ግንኙነት



መደረጉን ነው:: ግንኙነቱም ከቤተ ክርስቲያን ዘመን (ከራዕይ 2 እና 3) በኋላ መሆኑንና ቤተ ክርስቲያንም በዮሐንስ 14:1-3 እንደተጠቀሰው ልትወሰድ መንገድ መዘጋጀቱን የሚያመለክት ነው::

### 6.2.2.3. ..ወደዚህ ውጣና.. የሚለው ሐረግ

ጌታ ኢየሱስ ከራዕይ 1:3 ያለውን ክንዋኔ ዮሐንስ በምድር በነበረበት ጊዜ አስተላልፎታል:: ሆኖም ግን በራዕይ 4:1 ላይ ለምን ..ወደዚህ ውጣና... ከዚህ በኋላ የሚሆነውን አሳይሃለሁ አለው? ቀድሞ እንዳስተላለፈለት ባለበት ሁኔታ ወደላይ ሳይወጣ ለምን አላስተላለፈለትም? ይህ የሚያመለክተን የዮሐንስ ቦታ መቀየር (ወደ ላይ መውጣት-ለመውጣቱም የበር መከፈቱ ጉዳይ) ወደፊት መከራ የሚጀምርና አስጨናቂ ዘመን የሚቀጥል በመሆኑ ከመሆኑም በፊት ሎጥና ኖህ ከጥፋት እንደተወሰዱ ለቤተ ክርስቲያን መነጠቅ/መወሰድ ምሳሌያዊ ነገርን ለመተው እግዚአብሔር ያዘጋጀው እንደሆነ ቢተረጎም ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ይስማማል እንጂ አይቃረንም::

### 6.2.2.4. ..ቤተ ክርስቲያን.. የሚለው ቃል አለመኖር

በራዕይ 4:1 ላይ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ለመሆኑ ለማስረጃነት ከሚቀርቡት ሐሳቦች ውስጥ አንዱ ..ቤተ ክርስቲያን.. የሚለው ስም በመከራው ዘመን ማለትም ከራዕይ ምዕራፍ 6-19 ውስጥ አንዴም አለመጠቀሱ ነው:: ..ቤተ ክርስቲያን.. የሚለው ስም (ቃል) ከራዕይ ምዕ. 1-3 ውስጥ 19 ጊዜ ተጠቅሷል:: ከራዕይ 6-19 አለመጠቀሱ ግን የሚያመለክተን የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ የመከራው ዘመን ከመጀመሩ በፊት በራዕይ 4:1 ላይ መፈጸሙን ነው:: ቤተ ክርስቲያን ለምን ከራዕ. 6-19 ትዕይንት ውስጥ አልተጠቀሰችም? ይህንን ቀጥሎ ካለው ታሪካዊ ማስረጃ እስቲ እንመልከት::

በ..ሴሎ.. ቤተ ክርስቲያን ኮንፍራንስ ቢዘጋጅና ለሰባኪነት የተጋበዘው ሳኦል ቢሆን አገልጋዩም ሳይመቸው ቢቀር የፕሮግራሙም ዝግጅት በሙሉ በቪዲዮ ቢቀረጽና የቪዲዮውን ቅንጅት ሌሎች ቢመለከቱ ሳኦል በቪዲዮው

ውስጥ ይታያል አይታይም? መልሱ ለሁላችንም ግልጽ ነው:: ለባኪው ፈጽሞ ሲታይ አይችልም:: ለባኪው ሳኦል ያልታየበት ምክንያት በፕሮግራሙ ላይ ባለመገኘቱ ነው:: ስለሆነም የመከራው ዘመን በቅድመ መከራ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ስለማይመለከት ነገር ግን በእስራኤልና በአህዛብ እንዲሁም በመከራው ዘመን ቅዱሳን (በመከራው ዘመን ቤተ ክርስቲያን) ላይ ያተከረ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በትንቢት መልኩ በራዕይ 4:1 ላይ ተከናውኗል ማለት ነው:: በተግባር ወደ ፊት ይቀጥላል::

### 6.2.3. የ24ቱ ሽማግሌዎች በሰማይ ዙፋን መገኘት

እነዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ በ24ቱ ዙፋኖች የተቀመጡት ሽማግሌዎች የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን (የቤተ ክርስቲያን) ቅዱሳን ተወካዮች ናቸው:: በእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት ስልጣን በዘመናት መካከል ለእግዚአብሔር ክብር የቆሙ ታማኝ አገልጋዮች ስለሆኑ ተመርጠው በእግዚአብሔር ፊት ለመቀመጥ ችለዋል::

ቁጥራቸው 24 የሆነበትን ምክንያት በእርግጠኝነት ለመጥቀስ ቢያስቸግርም ከ1ኛዜና.24:1-9 የብሉይ ኪዳን የቤተ ክህነት አገልጋዮች ቁጥር 24 መሆኑን ማየት ይቻላል:: በተጨማሪም በራዕይ 21:10-14 በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ደጆች ላይ የ12ቱ የጌታ ደቀ መዛሙርትና የ12ቱ የእስራኤል ነገዶች ስም መጻፉና በአንድነት ቁጥራቸው 24 መሆኑ ሌላኛው ማስረጃ ነው:: ሌሎችም አመለካከቶች አሉ::

በሰማይ የታዩት እነዚህ 24 ሽማግሌዎች ቅዱሳን መላዕክት እንጂ ቅዱሳን ሰዎች አይደሉም የሚል አከራካሪ ሃሣብም አለ:: እነዚህ ሽማግሌዎች መላዕክት አይደሉም:: ላለመሆናቸውም የሚከተሉትን እውነቶች መመልከቱ ይጠቅማል::



#### 6.2.3.1. ሰው ስሆነ ሽማግሌና ስመላዕክት የተሰጡት መጠሪያ ስሞች መለያየት

«ኢልደር» በአማርኛው ..ሽማግሌ.. የሚለው ቃል በራዕይ መጽሐፍ በግሪኩ ሲታይ ..ፕሪስቡቴሮስ.. በቀጥታ የሚያመለክተው ሰው ለሆነ ፍጡር የተሰጠ ስምን እንጂ መላዕክትን አይደለም:: ለመላዕክት የቆመው የግሪኩ ቃል ..አጌሎስ.. የሚለውና ..ማላክ.. የሚለው የእብራይስጡ ቃል ተመሳሳይነት ሲኖራቸው መንፈሳዊ ኃይላትን ያመለክታሉ:: በራዕይ 4:4 ላይ ስተጠቀሱት ሽማግሌዎች የቆመው ቃል ..ፕሪስቡቴሮስ.. እንጂ ..አጌሎስ.. ወይም ..ማላክ.. ስላልሆነ ፈጽሞ ቅዱሳን መላዕክትን አያመለክትም:: ስለዚህ የራዕይ 4:4ቱ ሽማግሌዎች ከመነጠቅ በኋላ በሰማይ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ የሚቀመጡ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን ተወካዮች ናቸው:: ይህም ከከፈሉት ዋጋ አንጻር የተሰጣቸው ቦታና ክብር ሊሆን ይችላል::

#### 6.2.3.2. ነጭ ልብስ መልበሳቸው

የራዕይ መጽሐፍ ብዙው ክፍል ነጭ ልብስ መልበስ የተሰጠው በክርስቶስ ኢየሱስ ለተዋጁ ቅዱሳን እንደሆነ አጠንክሮ ይገልጽልናል::ለምሳሌ፤በራዕይ 3:5 ላይ ድል ለነሱ አማኞች የነጭ ልብስ ሽልማት፣ ቁ. 18 ላይ ነጭ ልብስ የቅዱሳን የንጽህና ህይወት አቋም፤በራዕይ 6:11 ደግሞ ስለክርስቶስ ለሚገደሉ፤በራዕይ 7:9 ደግሞ ከመከራው ለተዋጁ ቅዱሳን፤በራዕይ 19:8 እና ቁ. 14 ..ለበጉ ሚስት.. ማለት በዘመናት ተነጥቀው ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለገቡ ሁሉ የተሰጠ መሆኑን እናያለን:: ነጭ ልብስ የቅዱሳንን የጽድቅ ሥራ ያመለክታል:: እነዚህ ነጩን ልበስ የለበሱት ቅዱሳን ናቸው:: የተገኙትም በላይ በሰማይ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ነው:: የቀሩት ቅዱሳን ነጭ ልብስ የመልበስ ስልጣን እንደተሰጣቸው ሁሉ እነዚህ ሽማግሌዎች ከሰዎች የተዋጁ ስለሆነ ድል ስላደረጉ ነጩን ልብስ ለብሰዋል::

### 6.2.3.3. ከመላዕክት ተለይተው መሰለፋቸው

የራዕይን መጽሐፍ በጽሞና ስንመለከት በዙፋኑ ዙሪያና ፊት ያሉትን ክፍሎች ዘርዝሮ ይነግረናል:: በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያና ፊት 24ቱ ሽማግሌዎች፣ አራቱ እንስሳት፣ ከታላቁ መከራ የመጡ ቅዱሳን፣ ቅዱሳን መላዕክትና 144000 አይሁዶች (በገና ደርዳሪዎች) ይገኛሉ:: ይህንንም ከራዕይ 5:11፤ 7:13 እና 14:1-3 መረዳት እንችላለን:: ራዕይ 5:11ን ስንመለከት ቅዱሳን መላዕክት የሚገኙት በዙፋኑ፣ በእንስሶቹና በሽማግሌዎቹ ዙሪያ ነው:: ስለሆነም በራዕይ 4:4 የተጠቀሱት ሽማግሌዎች ከመከራው በፊት የተነጠቁት ቅዱሳን አማኞች ተወካዮች እንጂ መላዕክት እንዳይደሉ የእግዚአብሔር ቃል ያስገነዝበናል::

### 6.2.3.4. ያላቸው አክሊልና በዙፋን መቀመጣቸው

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ አክሊል (ዘውድ) እና ዙፋን ሲጠቀስ ብዙው እጅ ድል ካደረጉ በኋላ ከሚሸለሙ ቅዱሳን ጋር በተያያዘ ነው:: በተለይ በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ መላዕክት በዙፋን ተቀምጠውና አክሊል ተጭኖላቸው ፈጽሞ አልተጠቀሰም:: ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በማቴ. 19:28፤ ራዕይ 3:21 እና 20:4 እንደምናነበው በዙፋን መቀመጥ የተሰጠው ድል ላደረጉ ቅዱሳን ሰዎች ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኢሳ. 14:12-14 እና ቆላ. 1:16 ውስጥ መላዕክት ከዙፋን ጋር በተያያዘ መልኩ ተጠቅሰዋል:: ይህም ቀድሞ ከነበረው የእግዚአብሔር አሠራር ጋር በተያያዘ እንጂ ከተጋድሎ በኋላ በሽልማት መልክ ስለሚሰጠው ሥልጣን አይደለም:: በተጨማሪም ከ1ኛቆሮ.9:25-27፤ ከራዕይ 2:10 እና ከ2ኛጢሞ. 4:8 የምንረዳው ለቅዱሳን አክሊል የሚሰጠው ታግሎ ከማሸነፍ በኋላ እንደሆነ በግልጽ መረዳት ይቻላል:: ህይወታቸውም ተሰውቶ ከሞት የተነሱም ናቸው:: ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በራዕይ 4:4 የተጠቀሱት ሽማግሌዎች ከመከራው በፊት የተነጠቁ ቅዱሳን ተወካዮች መሆናቸውን ማየት ይቻላል::



እነዚህ 24ቱ ሽማግሌዎች የመከራው ዘመንና 144000 እስራኤላውያን ሳይነጠቁ በፊት የተነጠቁት ቅዱሳን አማኞች ጉባኤ ተወካዮች ሊሆኑ ይችላሉ:: ሆኖም ግን መቼና የት እንደነበሩ እነማን እንደሆኑም ለማወቅ ይቸግራል::

### 6.2.4. የኖህና የሎጥ ዘመን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ታሪካዊ ምስክርነት

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም መጨረሻና ስለራሱ ወደዚህ ዓለም መመለስ ትንቢት ከተናገረባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ሉቃስ 17 ነው:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በ26ኛውና በ30ኛው ቁጥር ላይ ጌታ በኖህና በሎጥ ዘመን የሆነው ሁሉ እርሱም ሲመጣ እንደዚያው እንደሚሆን ገልጧል:: የዚህን ዝርዝር ለማወቅ ስለ ምልክቶች በዝርዝር መመልቱ የሚጠቅምና መልካም ነው::

ከኖህና ከሎጥ ዘመን ጋር ከተያያዙት ዐበይት ነጥቦች ውስጥ በይበልጥ መጥቀስ የምፈልገው የቅዱሳንን ሁኔታ ብቻ ነው:: የማያምኑት ክፍሎች ሲበሉ ሲጠጡ ሲዘፍኑ፣ ሲያገቡ ሲጋቡ፣ ሲሸጡ ሲገዙ፣ ቤት ሲሰሩና ሲተክሉ ነበር:: ኖህ ሎጥና ቤተሰቦቻቸው ግን በአመጸኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሳቸውን ያስጨንቁ ነበር::2ኛጴጥ. 2፤7-8:: የለምቹ የሴሰኝነት ኑሮና የአመጻ ህይወት እነዚህን ጻድቃን ለመናቅና ለመወገዝ አሳልፎ ለጥቷቸው ነበር:: ይገፉም ነበር:: በህብረተሰቡም ዘንድ የተናቁ ነበሩ:: በኃጢያተኞች መካከል ሲኖሩ በማያዩትና በማሰሙት፣ በእነዚህ ሁለት ታላላቅ ነገሮች ነፍሳቸው ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገብታ ነበር:: በጴጥሮስ መልዕክት ውስጥ ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር ሳለ እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በአመጸኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና እንደተባለ ስቃያቸውም የሚቋረጥ አልነበረም:: ዕለት ዕለት ይሰቃዩ፣ ይጨነቁ ነበር:: ውጤቱስ? እነዚህን ጻድቃን እግዚአብሔር አዳናቸው ያዳነበትን መንገድ ስንመረምር እንደሚከተለው ነበር::

### 6.2.4.1. <u>ኖህና ቤተሰቡ</u>

ኖህ ሊመጣ ስለነበረው የእግዚአብሔር ፍርድ ከእግዚአብሔር መልዕክት በደረሰው ጊዜ ተቀበለ:: በታዘዘው መሠረት በወቅቱ የነበረውን የኃጢአተኞች ነቀፌታ ወደ ጐን በመተው መርከብ መስራት ጀመረ:: ቀኑም ሲደርስ ከቤተሰቦቹ ጋር ወደ መርከቡ ገባ:: ከእግዚአብሔር መመሪያ ተቀብሎ በሰራው መርከብ ከአሰቃቂው የውኃ ጥፋት ዳነ::

እግዚአብሔር ለኖህ በሰራው መርከብ ላይ እንኳን በሩን ለመዝጋት ሥልጣን አልሰጠውም ነበር:: ዘፍ. 7:16:: የእግዚአብሔር ቁጣ ከተፈጸመ በኋላ ግን ኖህ የመርከቡን በር ለመክፈት ችሏል:: እግዚአብሔር ለምን በሩን ዘጋ? ኖህን እንዲዘጋ ለምን አልፈቀደለትም? በህዝቡ በደልና ሐጢአት እግዚአብሔር እንደተቆጣ፣ ሁሉንም ሊያጠፋቸው እንደወሰነና ቃሉን ሊፈጽም እንዳሰበ ያመለክታል:: ምናልባትም የኖህ ርህራሄ በሩን ሊያስከፍተውም እንደሚችል አስቦ ሊሆን ይችላል:: ጻድቅ ሰው ብዙ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ልብ ላይራራና ላይጨክን ይችላልና::

ዝናቡ መዝነብ፣ ቀላዩም መነደል ሲጀምር ሰዎችም ሲሰቃዩ እንዲያይ ለኖህ አልተፈቀደለትም:: ለምን? ኖህ አስቀድሞ ኃጢአተኛው ዓለም ሲበላ ሲጠጣ በየዓይነቱ ሲደለት ተጨንቆ ነበር:: አሁን ግን ወደ እረፍት ገብቷል:: አሁን ሊያዝንም ፈጽሞ አይገባውም:: አስቀድሞ ሥራቸውን በማየትና ንግግራቸውን በመስማት እጅግ ብዙ ተሰቃይቷል:: በእግዚአብሔር ኃይል ስለተጠበቀና ወደ እረፍት ስለገባ ወደ ኋላ ሊመለስ አልተፈቀደለትም:: የጭንቀት ዘመን አልፏል:: የሥነ ልቡና ስቃይ ሊቀበል ፈጽሞ አላስፈለገም:: መዳን መዳን ነውና::

### 6.2.4.2. <u>ሎጥና ቤተሰቡ</u>

እግዚአብሔር የሰዶምና የገሞራን ከተሞች ለማጥፋት ወሰነ:: የእነዚህ ከተሞች ህዝብ ከኖህ ዘመን የበለጠ በርኩሰት የበዙበት ዘመን ነበር::



እግዚአብሔር ከቀድሞ ጀምሮ ብዙ ታግሷቸዋል:: የሎጥን የቅድስና ህይወት አይተው ለመመለስ ፈጽሞ ፈቃደኞች አልነበሩም:: ዘፍ. 19:1-11:: ሰማያዊና መንፈሳዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን በጐ ነገር የሚፈልግ ልብ አልነበራቸውም:: በአመጸኛ ሥራቸው ጌታን ያስቆጡ ስለነበር በኖህ ዘመን ኃጢአተኛውን ዓለም እንደ ቀጣ የሎጥንም ዘመን ሰዎች ሊቀጣ ተነሳ::

እግዚአብሔር ሎጥንና ቤተሰቡን የሚያድንበት መንገድ አዘጋጀ:: ሎጥ የእግዚአብሔርን የማዳን ዓላማ ቢረዳም እንደተገሰጠለት ባስቸኳይ እርምጃ አልወሰደም ነበር:: ሎጥ ለአካባቢው ዘመዶቹ ሁኔታውን አሳወቀ፣ የእነርሱ የቸልተኝነት አቋም ልቡን አዛለበት:: ቶሎ ሊወጣ አልቻለም:: በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በድጋሚ በመላዕክቱ በኩል እጁን ይዞ ከጥፋት ከተማ ሊያወጣው ቻለ:: ሎጥ ከሰዶም ከመውጣቱ በፊት እግዚአብሔር ከሰጠው ትዕዛዛት አንደኛው በጣም ለየት ያለ ነበር:: ይኸውም፤

...ወደ ኋላህ አትይ... የሚለው ነበር ::ዘፍ. 19:17:: ለምን ይህንን ትዕዛዝ ሰጠው? እግዚአብሔር ይህችን ከተማ በእሳት ማጋየት ከጀመረ፣ ሁሉ ነገር እየነደደ ከሆነ በዚህ ወቅት ሎጥ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ቢመለከት ምን ይገጥመው ነበር? የከተማይቱ መቃጠል ጭንቀት ሃዘንና ሁከት ያመጣበታል:: ወይም ደግሞ እሳቱ ካልነደደ ለካስ ውሸት ነው፤ ቃዥቼ ሊሆን ይችላል:: ወደ ከተማዬ ልመለስ ሊልም ይችል ነበር::

የሎጥ ሚስት ከህያውነት ወደ ግዑዝነት በመለወጥ ጨው አምድ ሆነች:: ለምን? ይህ የደረሰባት በእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ላይ በመጠራጠርና በማመጿ ሊሆን ይችላል:: በተጨማሪም በከተማይቱ ላይ እየወረደ ያለው መቅሰፍት ያመጣባትን ድንጋጤ መቋቋም አቅቷት ሊሆን ይችላል:: ሎጥና የቀሩት ቤተሰቡ ግን ትዕዛዙን በመቀበላቸው ሊድኑ ቻሉ:: ዳኑ ማለት ፊት ለፊታቸው ለአመጸኞች ተዘጋጅቶ የነበረው የእግዚአብሔት በትር ሳያገኛቸው ቀሩ፤ ተከለሉ፤ ተጠበቁ ማለት ነው::

በኖህና በሎጥ ዘመን የነበሩት ቅዱሳን ከዚህ አሰቃቂ ቁጣ ከዳኑ፣ በሰው ልጅ ዘመን ደግሞ ልክ እንደዚሁ ከሆነ፣ እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን በተመሣሣይ ሁኔታ ያድናቸዋል 2ኛ ጴጥ.2:8:: እግዚአብሔር የሰው ፊት አይቶ አያደላምና:: ስለሆነም በዚህ ዘመን መጨረሻም ከራዕይ 6-1 ከተጠቀሰው ቁጣ ቤት ክርስቲያንን ያድናል:: የሚያድንበትም መንገ ..መነጠቅ.. ነው:: የሚከተሰውን ሠንጠረዥ እንመልከት::

| የጠፉበት ዘመን | የዳኑት ሰዎች | የዳኑበት መንገድ |
|---|---|---|
| 1. በኖህ ዘመን | እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ኖህና ቤተሰቡ | በኖህ መርከብ |
| 2. በሎጥ ዘመን | ሎጥና ሁለት ልጆቹ | በመላዕክት እጅ |
| 3. በሰው ልጅ ዘመን | ቅዱሳን (ቤተ ክ.) | በመነጠቅ (በጌታ መምጫ ጊዜ) |

እነዚህን ዘመናት ስንመለከት በሶስቱም ከፍተኛና ዓለም ዓቀፍ የጥፋት ጊዜአት ጌታ የተለያዩ የማዳኛ መንገዶች ነበሩት:: ደረጃቸውም ለየት ያለ ነበር:: የሰው ሐጢአቱ እየከፋ በመጣ መጠን የማዳኛ መንገዱም ከበድ እያለ መጥቶአል:: በሶስቱም ጊዜአት የማዳኛ መንገዶቹን የቀየሰው እግዚአብሔር ሲሆን የፈጸሙት ግን የተለያዩ ናቸው:: መርከብ የሰው እጅ ሥራ፡ መላዕክት ከመርከብ እጅግ የላቀ ጉልበት ያላቸው፤ መነጠቅን ደግሞ ተግባራዊ የሚያደረገው ክርስቶስ ከሁሉም እጅግ የላቀ ጉልበትና አቅም ያለው ናቸው::

## 6.2.4.3. <u>3ኛው በትንቢታዊ መልኩ ይታይ ሉቃስ 17: 26-30:</u>

በ6.2.4.2 ውስጥ ከተጠቀሱት የጥፋት ዘመናት ውስጥ ሶስተኛው የሰው ልጅ ዘመን ገና አልተፈጸመም:: ይህ ዘመን ለ2000 ዓመታት ያህል ቆይቷል:: በሰው ልጅ ዘመን (በጌታ መምጫ ጊዜ) በዳንኤል እንደተተነበየው (ዳን. 11:31፤ 12:11) የጥፋት እርኩሰት (የአውሬው አሰራር) በተቀደሰው ሥፍራበእስራኤል እኔ እግዚአብሔር ነኝ! በማለት ሲቆም የክርስቶስ መምጫ



እጅግ የተቃረበበትና በምድርም የሚቆምበትም ጊዜ እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: ይህ ጊዜ በ2ኛጢ.ሞ. 3:13 እንደምናነበው የሰዎች ክፋት እየባሰ የሚሔድበት ጊዜ ይሆናል:: የጻድቃንንና የእግዚአብሔርን ልብ የሚያሳዝን የአመጽ፣ የኃጢአት ሥራ እጅግ የሚበዛበት ጊዜ ነው:: ይህንን ሁኔታ እግዚአብሔር ዝም ቢለው በጉ ነገር በክፉ ሊዋጥ ይችላል:: ይህ ደግሞ ከእውነት ውጭ ስለሆነ እግዚአብሔር አመጻን ሁሉ (አሰመታዘዝን) እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ደረጃ በደረጃ በፕሮግራም ክፋዎችን ይበቀላል:: በዚህ ጊዜ ግን እግዚአብሔር በእርሱ ያመኑትን ..የአምልኮ መልክ ብቻ ያልሆኑትን ያድናል..::

ታዲያ እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን እንዴት ነው የሚያድናቸው? ሠንጠረዡ እንደሚያሳየን በመነጠቅ ወዳዘጋጀላቸው ስማያዊ ስፍራ በመውሰድ ነው:: የመከራው ዘመን እስኪያልፍ በራዕይ 4:1 የተከፈተው በር በራዕይ 19:11 እስኪከፈት ዘግቶ በማስቀመጥም ነው:: ስለዚህ ኖህንና ሎጥን ቤተሰቦቻቸውንም ከአሰቃቂ ፍርዱ እንዳዳናቸው ከታላቁ መከራም እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ከመከራው በፊት ይወስዳል:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት ይሆናል::

## 6.2.5. <u>ግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች</u>

እስከአሁን የተመለከትናቸው የቅድመ-መከራ መነጠቅ ማስረጃዎች ጥቂቶቹ በተዘዋዋሪ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ በቀጥታ የተቀመጡ ናቸው:: የሚከተሉት እውነቶች ግን ከመከራውና ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጋር በተያያዘ ምንም የማያሻማ ግልጽ የሆነ መረጃን ማቅረብ የሚችሉ ናቸው::

### 6.2.5.1. <u>ሉቃስ 21:36</u>

በዚህ ክፍል ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመንካቱ በፊት የተያያዙ ሐረጐችን ይዘት መግለጽ እፈልጋለሁ:: የተጠቀሰው ዓረፍተ ነገር (እውነት):

..እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፣ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁልጊዜ ትጉ::.. የሚል ነው::

ጌታ ኢየሱስ ..ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ሲል በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር 5-35 የተዘረዘሩትን ለሰው ልጆች የማይበጁ አስከፊ ሁኔታዎች ለማመልከት ነው:: ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ሁሉ ሲነግራቸው ለራሳቸውም ሆነ ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡት ወገኖቻቸው በማሰብ ልባቸው ብዙ ሳይታወክ የቀረ አይደለም:: የሚሆኑትን ነገሮች በተለይ ከቁጥር 23-24 የተጠቀሱትን ሲያስቡ ልባቸው ታውኳል:: በዚህ ምክንያት ጌታ የማምለጫውን ዘዴ ነገራቸው:: ከሚመጣው አለቃቂ ሁኔታ መዳን ይቻላል በማለት ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች እንደተናገረው በማረጋጋት፣ አጽናናቸው::

በታላቁ መከራ ዘመን የመንፈስን ዓይን የሚያሳውሩና ልብ የሚሰርቁ ሐሰተኞች ነቢያትና ክርስቶሶች፤ ጫፍ የደረሰ ጦርነትና የጦርነት ወሬ (ቀዝቃዛና የጋለ ጦርነት)፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መነሳት (የእርስ በርስ ጦርነት) ረሃብና ቸነፈር፣ የመንግሥት በመንግስት ላይ መነሳት (የተለያዩ ብሔሮች ጦርነት)፣ የሐይማኖቶች መብዛትና መከፋፈል፣ እርስ በርስ አንዱ በሌላው ላይ ከጥላቻ ሙላት የተነሳ መነሳትና አሳልፎ መስጣጠት፣ ፍቅር ጭልጥ ብሎ ከብዙዎች መራቅ፣ ከፍተኛ የሆነ የሰውን ነፍስ የሚያስጨንቅ የተፈጥሮ አደጋ (የምድር ነውጥ፣ የውቅያኖሶች ማዕበል፣ እስከ 40 ኪሎ የሚመዝን የበረዶ ዝናብ በሰዎች ላይ ወዘተ እንደሚደርስ ጌታ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተናግሯል:: የእነዚህ ነገሮች ሁሉ መታያ ጊዜ ..እስከዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ እንደሚመጣ ተገልጿል::ማቴ. 24:21:: ጌታ ኢየሱስ ከእነዚህ ሁሉ ማምለጥ እንደሚቻል አስታውቋል::

ሌላኛው ሐሣብ ጌታ ኢየሱስ በዚህ ክፍል የተናገረው ***በፊቱ ስለመቆም*** ሁኔታ ነው:: ..በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ.. ሲል ይህ በፊቱ መቆም ምንድነው? ይህስ የሚፈጸመው የት ነው? ጌታ ከሞት ተነስቶ



ካረገበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን የሚገኘው በሰማይ በአብ ዘንድ ነው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰማይ እስኪለቀቀው ድረስ ለቅዱሳኑ በመንፈሳዊ አካሉ አልታየም ::ሐሥ. 3:21::ከአሁን በኋላ ጌታ ለቅዱሳኑ የሚታየው በ1ኛተሰ. 4:17 መሰረት ከኋለኛው መለከት መነፋት በኋላ በአየር ስንነጠቅ ነው:: ለመጀመሪያ ጊዜም በፊቱ የምንቆመው በመነጠቅ ሰዓት ነው:: ከዚያ በኋላ በተለያዩ ሁኔታዎች በፊቱ ልንቆም እንችላለን:: በአንጻሩ ደግሞ በራዕይ 6:16-17 በጌታ ኢየሱስ ፊት መቆም የማይችሉም አሉ::

ለእኛ ለቅዱሳን በጌታ ፊት መቆም እጅግ የተከበረና ዘወትር ልንናፍቀው የሚገባ የልባችን ናፍቆት ነው:: ***የዓለም ስውርና ግልጽ የክፋት ኅጺስ አሰራር ከውስጣችን ፍቆ ሊያወጣው የማይችል ሀያው ተስፋችን ሊሆን ይገባል***:: ይህንን ማጨናገፍ ከቻለም ማስቀረት የዲያብሎስ መርህና ምኞት ነው:: ይህንን መገለጥና መታየታችንን እንኳን እኛ በእግዚአብሔር መስመር ያሉ ፍጥረታት ሁሉ የሚናፍቁት ጉዳይ ነው:: የእኛን በጌታ ፊት መቆም መላዕክት እንኳን ለማየት ይናፍቃሉ:: የሰማይ መላዕክት ስለምድር ሰዎች መዳን ይነገራቸውና ሐሴት ያደርጋሉ እንጂ እስከ አሁን አላዩንም:: ሉቃስ 15:7:10:: የእኛ በከበረው የጌታ ደም ከምድር መቤዠት (መዋጀት)፣ የጌታም እኛን ከአብ መቀበል በኤፌ. 5:27 እንደተጠቀሰው እኛን ለአብ ወስዶ በማቅረብ ፍጻሜ ይደመደማል:: ይህ ስጋችን ማንም ሊቀርብ በማይችል በድንቅ ብርሃን በሚኖረው በአብ ፊት መቆም ስለማይችል የጌታን ክቡር ስጋ እንዲመስል ይለወጣል (ፊልጵ. 3:21):: ከዚያም በአብ ፊት ይቀርባል በዚያም የጌታ ኢየሱስ የዘመናት ሥራ በእግዚአብሔር ቅዱሳን መላዕክት ፊት ይገለጣል:: ታላቅ መደነቅም ይሆናል:: ይህ ሁሉ የሚሆነው በሰማይ ነው::1ኛጴጥ. 1:12::

እንግዲህ ከላይ በተዘረዘሩት መሠረት ወደፊት በዓለም ኃጢአተኞች ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ ማምለጥ (መሰወር) ይቻላል:: ይህም የሚቻለው በሰማይ ባለው ባልተገለጠው ሊመጣም ባለው በጌታ ኢየሱስ

በማመንና ፀንቶ በመቆም ነው:: ከዚህ ከመከራው በማምለጥ በሰማይ ባለው በጌታ ፊት መቆም የሚቻለው ..በመነጠቅ.. ሰርዓት ውስጥ በማለፍ ብቻ ነው:: እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ይህ ሃሣብ በተለይ ከመከራው በፊት ለሚገኙት ቅዱሳን የቆመ (የተጠቀሰ) መሆኑን ነው:: በመከራው ዘመን የሚገኙ ቅዱሳን (የመከራው ዘመን ቤተ ክርስቲያን) ከእግዚአብሔር ቁጣ ይጠበቃሉ፤ አንዳንዶቹም በአውሬው ድል ይደረጋሉ፤ ድል በመሆንም ድል ያደርጋሉ:: በእግዚአብሔር ተቆጣጣሪነት በሰይጣን ቁጣ በጋለሞታይቱ አንገት እስከ መቆረጥ፡ መሰደድና ግድያ ይደርስባቸዋል:: ራዕይ 13:10፤20:4-6:: ግማሾቹም በቅጽበተ ዓይን ተለውጠውና ከሞት ተነስተው ከመከራው ይነጠቃሉ:: ሆኖም ግን በመከራው ዘመን የሚኖሩ አማኞች የዚህ መነጠቅ ባለመብት የሚያደርጋቸው ትልቁ ነገር አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ይጸልይና ይማልድ እንደነበር በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ በትጋት መጸለይ ነው::

### 6.2.5.2. 1ኛተሰ.5:9.

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ..እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ ይላል:: ..ቁጣ.. የሚለው ቃል በቀጥታ የሚያመለክተው በአመጸኞችና በማይታዘዙ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ታላቅ መከራ፣ የእግዚአብሔር መቅሰፍትና በትር ነው:: ይህም ቁጣ በ1ኛተሰ. 5:2-3፤ በራዕይ 6:1-19፣ 21፤ እና በማቴ. 24:15-21 በዝርዝር ተገልጿል:: ይህ ቁጣ ከእግዚአብሔር በሰዎች ላይ የሚደርሰው ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ከእውነት ይልቅ ውሸትን ስለመረጡ ነው:: በዚህ ባህሪያቸው ሰዎች ራሳቸውን ለዚህ ቁጣ መርጠዋል:: ወይም ለይተዋል:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን እንዲድኑ ነበር::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በልዩ ልዩ ቦታ የእግዚአብሔር ቁጣ ሲወርድ ታይቷል:: ለምሳሌ፣



በ2ኛዜና 36:16 የአይሁድ ሕዝብ የእግዚአብሔርን እውነት ስላልተቀበሉ ቁጣው በህዝቡ ላይ ወጣ ውጤቱን ከቁጥር 17-23 ማየት ይቻላል:: በዚህ ጊዜ ግን ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል ስለሰማ ከጥቂቶች ጋር ተርፏል:: ቁጣው አላገኘውም ዘፀ. 22:24::

ዘሁልቁ 11:33-34 የእግዚአብሔር ቁጣ በህዝቡ ላይ ነደደ ... እግዚአብሔርም ህዝቡን በታላቅ መቅሰፍት እጅግ መታ ...::

2ኛዜና 12:12 ... የእግዚአብሔር ቁጣ ፈጽሞ እንዳይጠፋው ከእርሱ ዘንድ ተመለሰ::

ራዕይ 6:16 ... ከበጉ ቁጣ ሰውሩን

ራዕይ 6:17 ... ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቷልና ...

ራዕይ 11:18 ... አህዛብም ተቆጡ ቁጣህም መጣ::

ይህ ጥቅስ በተለይ (ራዕይ 11:18 እና 6:17) የእግዚአብሔር የቁጣ ቀንና ቁጣው (በትሩ ራዕይ 19:15) አስቀድሞ እንደተዘጋጀ ስለሰዎች መዳን ብቻ እግዚአብሔር ቁጣው እንዳይገለጽ እንደያዘው ያመለክታል::

ራዕይ 14:10 ... እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል ...

ራዕይ 14:19 ... ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር ቁጣ መጥመቂያ ጣሉ ...

ራዕይ 16:19 ... የብርቱ ቁጣው ወይን ጠጅ የሞላበትን ጽዋ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች::

ከላይ ከተዘረዘሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ የእግዚአብሔር ቁጣ በአመጸኞች ላይ ሊገለጽ በዝግጅት ላይ እንዳለ ግልጽ ነው:: ከዚህ ቁጣ ጋር በተያያዘ የእግዚአብሔር እቅድ ወይም ፈቃድ በማቴ. 3:7፣ በሉቃስ 3:7 እና በራዕይ 18:3-5 እንደምናነበበው ሕዝቡ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሁሉ ከኃጢአት እንዲለዩና እንዲድኑ ነው::

እንግዲህ ..እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንም.. ሲባል ከቁጣው ለመዳን ተጠርተናል፣ ተመርጠናል ማለት ነው ሮሜ. 5:9:: ስለሆነም ወደፊት የሚመጣውና በሐጢአተኛ ዓለም ላይ የሚፈስሰው የእግዚአብሔር ቁጣ ቤተ ክርስቲያንን አያገኝም:: አስቀድሞ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ይሆናል::

**6.2.5.3. <u>2ኛ ተሰ. 2:6-7</u>**

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ በሚስጢር ስለሚሰራው ሐሰተኛው ክርስቶስና በግልጽ እንዳይሰራ ስለሚከለክለው (ስለሚቋቋመው) ኃይል ጽፏል:: *የጻፈውም ቃል ..በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ:: <u>የአመጽ ሚስጢር</u> አሁን ይሰራልና ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ::..* የሚል ነው::

..የሚከለክለው.. እና .. ከመንገድ እስኪወገድ.. የተሰኙት ቃላት ማንን እንደሚያመለክቱ በሦስት ሐሳቦች ከፍለን (አንዳንዶች በ5 ይከፍሉታል) እንመለከታለን:: የሚከለክለውና ከመንገድ የሚወገደው ማንነት: 1. የዓለም መንግሥታትን 2. ቤተ ክርስቲያንን 3. መንፈስ-ቅዱስን የሚጠቁሙ ናቸው የሚል ሀሳብ ይሰነዘራል:: ይህም ብቻ አይደለም፤ አንዳንዶቹ የአውሬው ከልካይ 4. ሰይጣን 5. ሁኔታዎች ናቸው የሚሉም አሉ:: ወደ ትክክለኛው ወይም ቀራቢ. ትርጉም ለመድረስ በቅድሚያ የቃላቱን ፍቺ በደንብ መረዳቱ ጠቃሚ ነው::

..<u>መወገድ</u>.. የሚለው ቃል ወደ ሌላ ቦታ መወሰድን ወደ ላይ መሔድን፣ ከቀድሞ የእንቅስቃሴ ሁኔታና ቦታ ዞር ማለትን ሲያመለክት፤ሲሆን ..<u>መከልከል</u>.. ደግሞ አንድ ማንነት ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ወደፊት እንዳይራመድ መቋቋምን ያሳያል:: ሐሰተኛው ክርስቶስ በግልጽ እንዳይሰራ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቅዱሳን ከጻፈበት ጊዜ አንስቶ እስከዛሬና ወደፊትም የከለከለው (የሚከለክለው) ማነው? መንግሥታትና መንፈስ ቅዱስ ሊቋቋሙት ይችላሉ:: ሆኖም ..መወገድ.. ወደሚለው ቃል



ስንመጣ አይሰራም:: ምክንያቱም አውሬው በግልጽ መሥራት ሳይጀምርም ሆነ ሲጀምር ጀምሮም ሁለቱም ክፍሎች በምድር ይኖራሉ:: ቤተ ክርስቲያን ግን አይኖርም:: ምክንያቱም የመነጠቅ ስርዓት ስለሚሆን ነው::

አንዳንድ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን በቤተ ክርስቲያን መኖር የሚረዱበት መንገድ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚስማማ አይደለም:: ለምሳሌ፣..መንፈስ ቅዱስ የሚኖረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በሚሆንበት ጊዜ የት ይኖራል? ስፍራ ስለማይኖረው እርሱም አብሮ ይነጠቃል፤የሚል ነው:: ይህ ሃሣብ መንፈስ ቅዱስ የሚኖረው በቤተ ክርስቲያን ማንነት ውስጥ ብቻ እንደሆነና፣ በዚያም እንደተወሰነ የሚያመለክት አዝማሚያ አለው:: በቅድመ ቤተ ክርስቲያን ምስረታ የነበረበትንና መለኮታዊነቱን መንፈሳዊ አካል እንዳለውና የማይወሰን መሆኑንም የመዘንጋት መልክ አለበት:: መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም በቤተ ክርስቲያን (በቅዱሳን አካል) እንዲኖር ተሰጠ ማለት ከዚህ ስፍራ ሌላ መኖሪያ የለውም በሚል ሃሣብ ብቻ ከተተረጐመ ትልቅ ስህተት ነው:: ይህ የመንፈስ ቅዱስን ማንነት እንደ ሰው መንፈስ መወሰን ስለሚሆን ከእውነት ይርቃል::

የተለያዩ መረጃዎችንና ሌሎችንም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ስናነጻጽር መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠና የቅዱሳንም ተግባርና ሕይወት መሪ ነው:: ከመከራው በፊት እንደለ ሁሉ በመከራውም ዘመን ይኖራል፤አይነጠቅም:: እስከዛሬ አውሬውን የከለከለውና የተቋቋመው የቤተ ክርስቲያን ህልውና ነው እንጂ መንፈስ ቅዱስ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሥልጣን የተቀበለችው ከመንፈስ ቅዱስ ነው:: ከላይ የተጠቀሰው ከልካይ ከመወገድ አንጻር በቀጥታ የሚያመለክተው ቤተ ክርስቲያንን ነው:: ምክንያቱም ክርስቶስ ሲመጣ ሲል በዚህ ምድር ላይ መንግስታት:ሰይጣን:መንፈስ ቅዱስ: ሁኔታዎችም ስለሚኖሩ ነው:: እነዚህ ፈጽሞ ከምድር አይወገዱም:: የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ሲሆን ሐሰተኛው

ክርስቶስ አሁንም የእግዚአብሔር መንፈስ በፈቀደለት መጠን ብቻ ይሰራል:: የቤተ ክርስቲያን አለመኖር ሥራውን በከፍተኛ ደረጃ አፋጥኖ እንዲያካሂድ ይረዳዋል:: ስለሆነም አውሬው በ70ኛው ሱባኤ መጀመሪያ ላይ ለ7 ዓመታት ቃል ኪዳን አድርጐ የሚነሳ ከሆነ (ዳን. 9:27) ይህም ጊዜ የመከራው ዘመን (ታላቁ የያዕቆብ የመከራ ጊዜ) ከሆነ በዚህ ጊዜ ደግሞ ከልካዩ ከተወገደ ይህም ከልካይ ቤተ ክርስቲያን ከሆነ የቅዱሳን መነጠቅ ከመከራው በፊት ይሆናል ማለት ነው:

### 6.2.5.3.1. መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይኖራል ወይስ ይነጠቃል?

ቀደም ባለው ክፍል ከልካዩ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነና በመከራውም ዘመን እንደማይኖር/ እንደማትኖር ተገልጦአል:: ከዚህ ሐሳብ ጋር በማዘያያዝ ዘርዘር ባለ መልኩ ስለ መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን መኖርና አለመኖር፣ ስለ አጠቃላይ ሁኔታዎችም እንመለከታለን::

ከላይ በተጠቀሰው ርዕስ-ጥያቄ ላይ ሁለት ዓይነት ሃሣቦች /አመለካከቶች/ አሉ:: እነርሱም፤

6.2.5.3.1.1. መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይሄዳል / ይነጠቃል/ የሚሉና

6.2.5.3.1.2. መንፈስ ቅዱስ አይሄድም: ይኖራል የሚሉት ናቸው::

#### 6.2.5.3.1.1. መንፈስ ቅዱስ ይሄዳል/ይነጠቃል/ የሚሉት የሚያቀርቡአቸው ማስረጃዎች

(1). በ2ኛ ተሰ. 2:6-7 ያለውን (የሚከለክለው) እና (ከመንገድ እስኪወገድ) የሚለው ሃሣብ በዚህ ክፍል የሚከለክለው እና ከመንገድ እስኪወገድ የሚሉት የስም ምትኮች የሚያመለክቱት መንፈስ ቅዱስን ነው:: መጠሪያ ስሙ በወንድ ጾታ ስለሆነ በድንግልና ንጽህት ሴት የተመሰለችውን ቤተ ክርስቲያንን አያመለክትም:: ስለሆነም የሚወገደው መንፈስ ቅዱስ ነው::



(2). በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ እንዳልኖረ ሁሉ በመከራውም ዘመን መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማይኖርበት ዘመን ይሆናል:: የመከራውና የብሉይ ኪዳን ዘመናት አንድ ዓይነት ይሆናሉ::

(3). መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ቦታ በመገኘት ኃይሉ ይሰራል፤ ሆኖም ግን የማጥመቁ፣ በውስጥ የመኖሩ፣ የማተሙና የመሙላቱ ሥራ ይቋረጣል ወይም ያቆማል:: 1ኛ ቆሮ. 12:12-13፤ ኤፌ.1:13፤ 4:30 እና 5:18:: ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ይህንን የሚሰራው በአማኙ ውስጥ እየኖረ ከሆነ ከወጣና ከሄደ ሊሰራው አይችልም::

(4). መንፈስ ቅዱስ ከተወሰደ በመከራው ዘመን የመዳኑ ሁኔታና አሰራር እንዴት ይሆናል? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጡት ማስረጃ፤

<u>በመጀመሪያ</u> መዳን በእምነት መርህ ይሆናል የሚል ሲሆን የሚጠቀሰው ክፍል /ዕብ.11:1-40፤ ሮሜ 4:2/ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ መዳን በክርስቶስ ኢየሱስ ደም /በበጉ/ ነው:: ማስረጃ /ራዕ. 7:14፤ 12:7/ ይጠቅሳሉ:: በመጨረሻም መዳን በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይሆናል ሲሉ ማስረጃቸው መንፈስ ቅዱስ በዮሐ. 3:5-6 እንደተጠቀሰው ሆኖ ባይሰራም በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሰዎችን የማዳኑን ሥራ ስለሰራ ዛሬም በቅዱሳን ውስጥ ሳይኖር እንደቀድሞው የማዳን ሥራውን ይፈጽማል:: የዳግም ልደቱንም ሥራ ሊሰራ ይችላል ይላሉ::

#### 6.2.5.3.1.2. <u>መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን አይሄድም (አይነጠቅም)</u>

ማስረጃዎቹም የሚከተሉት ናቸው::

<u>*(1). የ2ኛ ተሰ. 2:6-7 ከልካይ መንፈስ ቅዱስ ስለመሆኑ*</u>

ብዙዎቹ የመንፈስ ቅዱስን ከመከራው በፊት ከዚህ ዓለም መሄድ የሚደግፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የሚጠቅሱት 2ኛ ተሰ. 2:6-7 ን ነው:: ለዚህም *የሚከለክለው* የተባለው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነና ለመሆኑም ማረጋገጫው በወንድ ጾታ መጠቀሱ ነው የሚል ነው:: ከዚህም ጋር

በማያያዝ *የሚከለክለው* የሚለውና *ከመንገድ የሚወገደው* ቤት ክርስቲያን ብትሆን ኖሮ በንጽህት ድንግል /በሴት/ ትጠራ ነበር ይላሉ:: ሆኖም ግን የአተረጓጎም ልዩነት ካልሆነ በቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን "እርሱ" በሚል የወንድ ጾታና ያለ ጾታም መጠራቷን መረዳት ይቻላል:: አንዳንዶች ግን ቤተ ክርስቲያንን እንደ ንጽህት ሴት ድንግል ብቻ የሚመለከቱም አሉ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን /በኤፌ. 2:15፣ 4:13/ እንደ ወንድ ጾታ *አዲስን ሰው፣ ሙሉ ሰው* /በ1ኛ ቆሮ. 12:12-13፣ ኤፌ. 1:22-23፣ ቆላ.1:18/ ደግሞ *የክርስቶስ አካል* በመባል ተጠርቷል:: እነዚህ ጥቅሶች የሚያመለክቱት ቤተ ክርስቲያንን ነው:: ሆኖም ግን ቤተ ክርስቲያንን በንጽህት ድንግል መመሰል ስህተት አይደለም:: ስለዚህ በ2ኛ ተሰ. 2:6-7 የተጠቀሰው አውሬውን የሚከለክለው የክርስቶስ አካል ተብሎ የተጠራው ቤተ ክርስቲያን እንጂ መንፈስ ቅዱስ አይደለም:: ይህም ከመንገድ እስኪወገድ በሚለው መንፈስ አኳያ ብቻ ማለት ነው::

## (2). የሰማይ ርስት መያዣ መንፈስ ቅዱስ መሆኑ

በኤፌ. 1:13-14 *...እርሱም የርስታችን መያዣ ነው* ሲል አንድ ሰው ወደ ጽዮን ተራራ፣ አዲሲቱና ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም፣ ወደ ጻድቃን መንፈሶች ጉባኤ መግባት የሚችለው በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ሲታተም ነው:: በአዲስ ኪዳን ሰሚገኝ ለማንኛውም እውነተኛ ንስሃ ለገባና ጌታን ለተቀበለ ይህ የልጅነት መንፈስ ተሰጥቶታል:: በዚህም ዮሐ. 1:12-13 የልጅነት ስልጣን መሠረት በሮሜ 8:17 እንደተጠቀሰው በዮሐ. 14:1-3 በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የተዘጋጀውን ሰማያዊ ርስት ይወርሳል:: ይህ የተስፋ መንፈስ ቅዱስ ቀድሞውኑ ከተሰጠና ይህም ደግሞ የፈሰሰው በአዲስ ኪዳን ከሆነ በመከራውም ዘመን ለሚገኙ ሁሉ ስጦታው መስጠት እስከሚያቆምበት ጊዜ መስጠቱ ይቀጥላል::



## (3). የመንፈስ ቅዱስ በሰው ለዘላለም መኖርና ቅዱሳንን በማጽናናት የሚሰራቸው ነገሮች፤

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ዓለም ለቅቆ ከመሄዱ በፊት ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገራቸውን የተስፋ ቃሎች እስቲ እንመርምር:: በዮሐ. 14:17፣ 26 ምዕ. 16:7 ላይ መንፈስ ቅዱስ "አጽናኝ" ተብሏል "አጽናኝ" ማለት ደካማውን / በቂ ኃይል የሌለውን ሐይል በመስጠት/አይዞህ ወይም በርታ በማለት ለመርዳትና ለማማከር ከጉን የማይጠፋ መካሪና አበረታች ማለት ነው:: የመከራው ዘመን በጣም አስፈሪ ነው:: እንኳን በሰባቱ ዓመታት የመከራ ዘመን ይቅርና ጌታም እንኳን ምድርን በለቀቀበት ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ የነበረው የጊዜው አስፈሪነት ቀላል አልነበረም::

የሰባቱ ዓመታት ባለስልጣኖች አውሬውና አበሮቹ በምድር በሚገለጡበት ጊዜ በርኩሳን መናፍስት ኃይል ተሞልተው ስለሚሰሩና ኃይላቸውን በከፍተኛ ደረጃ ስለሚለቁ በዚያን ዘመን፣ ያለ መንፈስ ቅዱስ አጽናኝነትና ረዳትነት የመከራውን ሁኔታ መቋቋም /መታገስ/ እጅግ ከባድ ነው:: ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን መኖር ምንም አሌ የማይባል እውነት ነው::

## (4). የመንፈስ ቅዱስ ወቃሽነት

ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 16:8 ላይ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ዓለምን ስለ ኃጢአት፣ ፍርድና ስለጽድቅ እንደሚወቅስ አስተምሯል:: በዚህ ክፍል የተጠቀሰው "ወቀሳ" የሚለው ቃል አንድ ሰው እየተጓዘበት ያለው መንገድ ልክ አለመሆኑን በማሳየት ገስጾ፣ መክረ ትክክለኛውንም ጉዳና አሳየ ማለት ነው:: ዓለም ማለት ማንኛውም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሃሣብ ያልሆነ በስውርም ሆነ በግልጽ የጽድቅ ጠላት የሆነ ስርዓት የሚካሄድበት ማንነትና ስርዓቱ ሁሉ ነው:: በ70ኛው ሱባኤ የዓለም ስርዓት እጅግ በተጠናከረና በከፋ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ በከፍተኛ ፍጥነት የሚራቅበትና የሚረከስበት ጊዜ ነው:: ታዲያ መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን የሚሄደው

የወቀሳ ሥራውን ጨርሶ ነው? አይደለም:: እንዲያውም የመንፈስ ቅዱስ ወቃሽነት የሚያይለው ሰዎችንም ወደ ንስሃ የሚመራው በዚህ ወቅት ነው። ስለዚህ የዓለም ስርዓት በመከራው ዘመን ካለ የመንፈስ ቅዱስም ወቀሳ እጅግ በጠነከረ ሁኔታ ይኖራል ማለት ነው:: ለዚህም ነው ቁጥሩ የበዛ ሰው በመከራው ዘመን የሚድነው ::ራዕ. 7:8-13::

## (5). የጌታ ኢየሱስ አለመመለስ

ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ወደ አባቱ እንደሚሄድ በነገራቸው ጊዜ ልባቸው ታውኮና አዝኖ ነበር ዮሐ. 14:1-3:: ከዚህም ሁኔታቸው በመነሳት ሦስት ታላላቅ አበረታችና አጽናኝ የሆኑ ተስፋዎችን ሰጥቶአቸዋል:: እነዚህም ተስፋዎች፤ስፍራ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ፤ተመልሼ እመጣና እወስዳችኋለሁ፤አጽናኙን መንፈስ ቅዱስ እልክላችኋለሁ የተሰኙት ነበሩ::

የዮሐንስን ወንጌል በተለይ ከምዕ. 14-16 ብንመለከት፤ ጌታ የደቀ መዛሙርቱን ልብ ለማጽናትና ለማበረታታት የማጽናኛና የተስፋ ቃሎችን የተናገረበት ምዕራፎች ናቸው:: ጌታ በማስተማር ብቻ ሳይሆን በ17ኛው ምዕራፍ ላይ የደቀመዛሙርቱን አጠቃላይ ሁኔታ በጸሎት ለአባቱ አቅርቧል:: እነዚህን ነገሮች ከፈጸመ በኋላ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት በዮሐ. 16:7 ላይ አንድ ልዩ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን እውነት ተናግሯል:: ይኸውም፤ "እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፣ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል:: እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፣ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ::" የሚል ነበር:: በዚህ ጥቅስ መሠረት ጌታ ኢየሱስን በመተካት ልክ ደቀ መዛሙርቱ በጌታ እንደሚደገፉና እንደሚጽናኑ ሊሆንላቸው የሚችለው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እንረዳለን:: የተጻፈ ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏል እንደተባለ ያ ለደቀ መዛሙርቱ እጅግ አስፈልጓቸው የነበረ የተስፋ መንፈስ 1/ ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ እስከዛሬ ላሉ ቅዱሳን 2/ ወደፊትም በመከራው ዘመን ለሚድኑ ቅዱሳን ያለ ጥያቄ አስፈላጊ ነው::



ጌታ ኢየሱስን የተካ መንፈስ ቅዱስ ነው:: ጌታ ካረገበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ምድር ለመኖር በሚታይ ክብሩ አልተመለሰም:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የመጣበትን ዓላማ ከፍጻሜ ሳያደርስ አይተውም:: በመከራውም ዘመን በጌታ ቦታ ሆኖ ይሰራል፤እውነትነም በመግለጽ ሰዎችን እየወቀሰ ወደ ጌታ መንግሥትም ያፈልሳል::

## (6). የምህረት በር አለመዘጋት

ምንም እንኳ የመከራው ዘመን የእግዚአብሔር ቁጣ በአስቃቂ ሁኔታ በምድር ላይ የሚፈስበት ጊዜ ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠሩ ሁሉ አመድ ይሆናሉ፣ ሰው ከምድር ገጽ ይጠፋል ማለት አይደለም:: የመንፈስ ቅዱስን ከምድር መሄድ ሃሣብ ከሚያጠብቁ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የምህረቱ በር ይዘጋል የሚል ሃሣብ ያላቸው ናቸው:: ለዚህም ደግሞ መነሻው የመንፈስ ቅዱስ መሄድ ነው የሚሉ ናቸው:: ሆኖም ግን ራዕ. 7:9ኝን ስንመለከት ማንም ሊቆጥራቸው ያልቻለ ታላቅ ህዝብ ከታላቁ መከራ እንደወጡና ልብሳቸውን በበጉ ደም በማጠብ እንደዳኑም ያሳያል:: በመከራውም ውስጥ አልፈው ለሺሁ ዓመታት ስርዓትም ለመብቃት የደህንነት ወንጌል የሚሰበክላቸው አሉ:: የሰዎች መዳን የእግዚአብሔርን ምህረት ማለትም የመንፈስ ቅዱስን አለመወሰድ ያሳያል::

## (7). የቤተ ክርስቲያን መነጠቅና የመንፈስ ቅዱስ አለመነጠቅ ከዓላማ አንጻር.

በክፍል 8 ውስጥ "የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ዓላማዎች /ምክንያቶች/" በሚለው ዐቢይ ርዕስ ሥር ቤተ ክርስቲያን የምትነጠቅባቸውን ዋና ዋና ምክንያቶች ተገልጠዋል:: መንፈስ ቅዱስ በቅድመ መነጠቅ የሠራቸውን ሥራዎች ሁሉ በድህረ መነጠቅና በሺህ ዓመት መንግሥትም ይሰራል::

(8). <u>የመንፈስ ቅዱስ በወንዶችና በሴቶች የእግዚአብሔር ባሪያዎች ላይ መፍሰስ</u>

ኢዩ. 2:18-29 ስንመለከት እግዚአብሔር *በመጨረሻው ዘመን በስጋ ለባሽ* ሁሉ ላይ በተለይም *በወንዶችና ሴቶች ባሪያዎቹ* ላይ ከመንፈሱ እንደሚያፈስ በነቢያቱ ተናግሯል:: በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ዘመን የተባለው፤

- ጌታ ኢየሱስ ከተወለደበት ዘመን አንስቶ ሐዋርያት እያገለገሉ ቤተ ክርስቲያን ተመስርታ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ እየሰራ ያለበት ዘመን /1ኛ ዮሐ. 2:18/
- የ70ኛው ሱባኤ: የሰባቱን ዓመት መከራ ወይም የያዕቆብ የመከራ ዘመን /ዘዳ. 4:30፤ ኤር. 23:20፤ 30:24፤ ዳን. 9:24-27::
- ጌታ ኢየሱስ ለመንገሥ ወደዚህ ዓለም በመምጣት የአርማጌዶንን ጦርነት የሚዋጋበት ጊዜ /ህዝ. 38:8፤ 16፤ 1ኛ ጴጥ. 1:5/
- የሺሁን ዓመት ስርዓትና ጊዜ /ኢዮ. 19:25/
- የመነጠቅ ጊዜ /ዮሐ. 6:39፤ 40፤ 44፤ 11:24/ ናቸው::

የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ባሪያዎች ደግሞ እግዚአብሔር በአይሁዶችና በአህዛብ መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ አፍርሶ ከሁለቱ ያወጣው "አንድ ሰው" "የክርስቶስ አካል" ቤተ ክርስቲያን ነው:: ወንጌልን ለማሰራጨት የእግዚአብሔርን ልጅነት ስልጣን የተቀበሉት አይሁዶችና /ከጌታ መወለድ ጌዜ እስከ አሁን የዳኑ አይሁዶችና ወደፊትም የሚታተሙት 144000 እና ሌሎችም አይሁዶች/ በተጨማሪም አህዛብ የጌታ ባሪያዎች ናቸው:: ስለሆነም በዚህ ዘመን መጨረሻ በመከራው ዘመን ጌታ መንፈሱን በነዚህ ባሪያዎቹ ላይ ያፈስሳል ማለት ነው:: *ሥጋ ለባሽ* የተባሉት የምድር ነዋሪዎች ናቸው::



(9). <u>የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ዓላማ.</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ96 ጊዜ ያላነሰ መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውናቸው *ሥራዎች* ተገልጸዋል:: ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ:: መንፈስ ቅዱስ ወደዚህ ምድር ከመጣባቸው ዋና ዋና ዓላማዎቹ ውስጥ፤

- ያመኑ ሰዎችን ከዓለማዊነት /ከሰይጣን ልጅነት/ ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ሊሰውጥ ሮሜ 8:15፤ 9:4፤ ገላ. 4:5 እና ኤፌ. 1:5::
- በሰዎች አድሮ ለሌሎች ሊናገር፤ 2ኛ ሳሙ. 23:2፤1ኛ ጢሞ. 4:1::
- በስውር ጠላት የሚሰራውን ነገር /የተደበቀውን/ ሊገልጽ 1ኛ ዜና 28:12፤ ሐሥ. 11:28፤ 21:4::
- ስለ እውነት ወይም ስለ ክርስቶስ ሊመሰክር ነህ. 9:20፤ 30፤ ዮሐ. 15:26፤ 1ኛ ዮሐ. 5:7::
- ውበትን ሊሰጥ /ኢዮ. 26:13/ በመከራው ዘመን ሰዎች በውስጣዊም ሆነ በውጪአዊው ማንነታቸው በከፍተኛ ደረጃ የሚወላልቁበትና የሚበላሽበት ጊዜ ስለሆነ የመንፈስ ቅዱስ መኖር በመከራው ዘመን እጅግ አስፈላጊ ነው:: እንኳን በመከራው ዘመን ይቅርና በቅድመ-መከራ ያለችውም ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ችግር ውስጥ ገብታለች::
- በሰዎች ላይ በማረፉ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ሊያድል ኢሳ. 11:2 ማቴ. 3:16፤ ዮሐ. 1:3::
- በልዩ ኃይልና ስልጣን ሰዎችን ለአገልግሎት ሊለይ ኢሳ. 61:1፤ ሉቃ. 4:18::
- ለሰዎች/አማኞች/ ፀጋንና የምልጃን ህይወት መስጠት፤ዘካ. 12:10-13፤ ኤፌ. 6:18፤ ዕብ. 10:29::
- ቀድሞ በጌታ የተነገረውን ማስታወስ /ዮሐ. 14:26/ ነገሮች በተምታቱበትና ግራ በሚያጋባ የጨለማ ዘመን የለው የማስተዋሉ ደረጃ በሚጠፋበት በመከራው ዘመን በተሰጠው የተስፋ ቃል፤ኢዩ. 2:28-29 መሠረት በሙላት ይሰራል::

- ሰዎች ካመኑ በኋላ በቀጥታ መዳናቸውንና በሰማያዊ ስፍራ በሕይወት መጽሐፍ መመዝገባቸውን ያረጋግጣል፣ ያጸናል:: ሮሜ 8:16::
- በእውነተኛ አማኞች ተአምራትንና ድንቅን መሥራት ሮሜ 15:19፤ 1ኛ ቆሮ. 12:7-11፤በራዕ. 13 ውስጥ ሐሰተኛው ነቢይ እንኳን እሳት በሰዎች ፊት እያወረደ ህዝቡን ሲያስደንቅ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በተከታዮቹ የማይሰራበትና በሙሴ በኩል የፈርኦንን ቃላተኞችና አስማት አዋቂዎች እንዳሳፈረ በመከራውም ዘመን የማይሰራበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም::
- ሰዎችን በክርስቶስ አካል ማጥመቅ /1ኛ ቆሮ. 12:13/ ለሰዎች ማለትም ጌታን አምነው ለሚከተሉ የዳግመኛ መወለድን ስልጣን ሰጥቶ ወደ ክርስቶስ አካል ቤተ ክርስቲያን የማስገባት ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ነው::
- የእግዚአብሔር ባህሪይ በአማኝ ውስጥ ለማስቀመጥ፤ ገላ. 5:22::
- ከሞትና ከሐጢአት ህግ ነጻ ለማውጣት፤ ሮሜ 8:1-2::
- በሰዎች ሕይወት ውስጥ ፍቅርን ለማፍሰስ፤ ሮሜ 5:5፤ 15:30::
- የውስጥ ሰውነትን ለማጠንከር ኤፌ. 3:16::
- ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለዘላለም ሕይወት ሊጋብዝ ራዕ. 22:17
- ባጠቃላይ ትክክለኛ መስዋዕትን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ የሚረዳ፣ የአማኞች የጽድቅ ምንጭ፣ በሥጋ ኃይል ላይ ድልን የሚሰጥ፣ መንፈሳዊ መልካችንን ወደ ክርስቶስ መልክ የሚለውጥ፣ 2ኛ ቆሮ. 3:18፣ የትንሳኤን ሕይወት ሰጪ፣ ወደ ፍጹምነት ለመድረስ ረዳትና ከመርገምም ሁሉ የሚያነጻው መንፈስ ቅዱስ ነው::

ከላይ የተዘረዘሩት የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በጣም ጥቂቶቹ በብሉይ ኪዳን የታዩ ሲሆኑ የተወሰኑት ግን በአዲስ ኪዳን በብዛት ታይተዋል:: መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ሥራዎች ያከናወነው በመጨረሻው ዘመን ከሰዎች



ጋር በተያያዘ እንጂ ከመላዕክት ጋር አይደለም:: የአሁኑና የወደፊቱ የመከራ ዘመን በሰው ሕይወት ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ ክፋት የሚበዛበት፣ ልዩ ልዩ ወደ ሐጢአት መንጓዣ መስመሮች የሚበዙበት ጊዜ ስለሆነ ከላይ በተዘረዘሩት ተግባሮች አንጻር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሰርቶ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ አካል /ቤተ ክርስቲያን/ የሚያመጣበትም ጊዜ ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ዓላማ በክርስቶስ ቦታ ሆኖ በመሥራት ሰዎችን ወደ ደህንነት /ወደ ክርስቶስ/ ማምጣት እስከሆነ ድረስ መዳን በሚያስፈልግበት የመከራው ዘመን መንፈስ ቅዱስ ምድርን ለቅቆ ይሄዳል የምህረቱም በር ይዘጋል ማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ውጪ ነው::

### (10). መንፈስ ቅዱስ የሚወርድባቸው ሦስት ዘመናት

ወደዚህ ርዕስ ዝርዝር ሃሣብ ከመግባቴ በፊት አንባቢን የምጠይቀው ጥያቄ አለ:: ይኸውም በሺሁ ዓመት ስርዓት መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳኑ ሁኔታና ይዘት በምድር ይኖራል ወይስ አይኖርም? የሚል ነው::

መንፈስ ቅዱስ በሺሁ ዓመት እንደሚኖር የሚነግሩን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ኢዩ. 2:28-32፤ ኢሣ. 32:15፣ 44:3፤ ሕዝ. 36:26-27፣ 39:29 እና ዘካ. 12:10 እና ሌሎችም ናቸው:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች በኢዩ. 2:28-32 በመጨረሻው ዘመን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ እግዚአብሔር ከመንፈሱ ሊያፈስ የሰጠው ተስፋ ሦስት የተለያዩ ቅደም ተከተላዊ ጊዜአት አሉት ይላሉ:: ይኸውም

- የበዐለ ሃምሣውና ከዚያም በኋላ ያሉት ጊዜአት ሐሥ. 2:28::
- የመከራው ዘመን /ሰባቱ ዓመታት/ እና ኢዩ. 2:28-32ይህ
- የሺሁ ዓመት ስርዓት /ኢዩ.2:28-32፤ ሐሥ. 2:16-17፤ ኢሣ. 32:15፣ 44:3፤ ሕዝ. 36:26-27፣ 39:26 እና ዘካ. 12:10 ናቸው:: ይህ ሃሣብ ከዚህ ጽሑፍ የመጨረሻ ዘመን ትርጉም ሰጪ ሃሣቦች ጋር አይቃረንም::

ከላይ የተጠቀሱት ሦስት ጊዜያት የተከሰቱትና ሊከሰቱ ያሉት በዚህ ዘመን መጨረሻ ላይ ለመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ብቻ ሳይሆኑ ታሪክም ይመሰክራል:: ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው ሃሣብ ለአይሁዶች ብቻ የተጠቀሰ ቢመስልም በሺሁ ዓመታት ውስጥ ግን መንፈስ ቅዱስ የማዳኑን ሥራ በአይሁዶችና በቅዱሳን አማኞችም ሕይወት ይሰራል::

እዚህ ቦታ ልብ ልንለው የሚገባ እውነት አለ:: ከላይ በተዘረዘሩት ሦስት ሃሣቦች ላይ በመቆም የመንፈስ ቅዱስን ሁኔታ ከመከራው ዘመን ጋር በተያያዘ እንድንመረምር ነው:: ቀደም ካሉት የእግዚአብሔር ነቢያት አንዱ ኢዩኤል በመጨረሻ ዘመናት መንፈስ ቅዱስ በምድር እንደሚወርድ ተናግሯል:: ይህ በእግዚአብሔር ቅዱሳን የተነገረው ትንቢት ፍጻሜው ሲቀርብ ጴጥሮስ በሐሥ. 2:38-39 እንደተነገረው የተስፋው መንፈስ በሐሥ. 2:1-4 ፈስሶ ሰዎችም ተቀብለውታል:: እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ ከበዐለ ሐምሳ ጀምሮ እስካሁን ካለና ከሰራ፡ እንዲሁም በሺሁም ዓመት የሚሰራ ከሆነ በመሐል በመከራው ዘመን የማያቆምበት ምንም ምክንያት አይኖርም:: የመንፈስ ቅዱስ ከበዐለ ሃምሳ ጀምሮ እስካሁን ካለ በሰባቱ ዓመታት መከራ መጨረሻም /ዘካ. 12/ በሺሁ ዓመታት ከእስራኤልና አህዛብ ጋር በተያያዘ ካለ በሰባቱ ዓመታት ውስጥ ወደ ላይ የሚሄድበት ምክንያት ስለማይኖር መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይኖራል::

## (11). የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አስፈላጊነት

ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው በመከራው ዘመን በአለማችን የሚከሰተው የአመጽ ሁኔታ ዲያብሎስና አጋንንቱ ለሺህ ዓመትና ለዘላለም ሊፈረድባቸው ጥቂት ዘመን እንደቀራቸው አውቀው /ራዕ. 12:11-12/ በታላቅ ቁጣ የሚወርዱበት ጊዜ ስለሆነ አስጨናቂነቱ እጅግ በጣም ከፍተኛና ከባድ ነው:: 2ኛ ጢሞ. 3:1-9፤ ሮሜ 1:18-32፤ ማቴ. 8:28-29:: በማቴዎስ ውስጥ "ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን ወደዚህ መጣህን" የሚለው የአጋንንቱ ጥያቄ የሚሰቃዩበት ቀን እንዳለና ያም ቀን ወደ እነርሱ እየገሰገሰ እንደሆነ መረዳታቸውን ያሳያል:: ያ ቀን ግን ከመድረሱ በፊት ለመሥራት አጋንንቱ



በአሰቃቸው በዲያብሎስ አማካይነት ቁጣ ውስጥ መግባታቸውንም ከራዕይ 12:11-12 እንረዳለን:: በመከራው ዘመን ለሚኖሩ ቅዱሳን ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚያስፈልጋቸው በዚህ ዘመን ነው:: ራዕይ 13:10::

የኤልያስ ተከታይ የነበረው ኤልሳዕ ኤልያስን ከአንተ ሳልወሰድ /ሳልለይ/ የምትፈልገውን ለምን ባለው ጊዜ፣ መንፈስ በእርሱ ላይ እጥፍ ሆኖ እንዲወርድ የጠየቀው የመብለጥ መንፈስ ናፍቆት ይዞት ወይም ከኤልያስ የበለጠ ዝነኛና ክቡር ሆኖ ለመታየት ስለፈለገ አልነበረም:: ይህ ቢሆን እግዚአብሔር ባልመለሰለትም ነበር:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ትዕቢትን ስለሚቃወም ነው:: ነገር ግን ከኤልያስ ጊዜ ይልቅ በኋላ ያለው የከፋና የማይመች ስለሚሆን ያንንም ሁኔታ በህይወቱ በሚሰራው የመንፈስ ኃይል ለመግጠም ስለፈለገ ነው::

ጌታ ኢየሱስም በሉቃ. 24:49 እና በሐሥ. 1:8 ኃይልን እስክትለብሱ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ያለው፤ በዚያን ወቅት የእግዚአብሔር ኃይል ለሥራው እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ስላወቀና አስቀድሞም ስለተመሰከተ ነው:: ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል አስፈጊነት አንጻር ጌታ ኢየሱስ በዚያን ጊዜ የነበረው አቋም ዛሬም አልተለወጠም:: በኤልሳዕ ጊዜ ያስፈለገው የኃይል መጠን ሁለት እጥፍ ነበር በሐዋሪያት ዘመን ያስፈለገው የኃይል መጠን በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ሆኖ በመከራው ዘመንስ የሚያስፈልገው የኃይል መጠን ከጊዜው አስፈሪነትና አስከፊነት አንጻር ምን ያህል እጥፍ እንደሚሆን በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩና የሚያስተውሉ ይመልከቱት /ይገምቱትም/::

<u>በመከራው ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለሚከተሉት ዋና ዋና ነገሮች ያስፈልጋል</u>::

- *የእግዚአብሔርን ቃል ሀያውነት ለመግለጽ፣*

ላዘኑ መጽናኛ፣ ለተሰበሩ መጠገኛና መፈወሻ መድኃኒት፣ ግራ ለተጋቡ መንገድ አመልካች ለመሆን፤ ለሰዎችም በትክክል ገልጦ

ለማስረዳትና ወደ እውነትም ሁሉ ለመምራት፤ የጌታ ኢየሱስን ለስ[illegible] ኃጢአት መሞትና መነሳት፣ ማረግና ተመልሶ መምጣት ለመመስከር::

- ***ለጸሎት፤***

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሐዋርያትና ነቢያት ጉልበታቸው መ[illegible] እስኪያወጣ በመጸለይና በእምባ የጌታን ፍለጋ የተከተሉት (ዕብ. 5:7) ጌ[illegible] ኢየሱስም ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን ያቀረበ[illegible] ካረፈበት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተነሳ ነው:: በሮሜ 8:28 መንፈስ ቅዱ[illegible] የቅዱሳንን ድካም የሚያግዝ፣ የአጸላለይን ዘዴ የሚያስተምርና በማይነገ[illegible] መቃተት የሚማልድ ሆኖ ተገልጧል:: ከመከራው በፊትም ሆነ በመከራው[illegible] ጊዜ ለሚገኙ የወንጌል ምርኮኞች ማጥቂያና ድል ማድረጊያ መሣሪያ ጸሎ[illegible] ነው:: ለዚህም መንፈስ ቅዱስ እጅግ ያስፈልጋል::

- ***ከገሃነም ደጆች ጋር ለመጋደል***

ጌታችን ኢየሱስ (ቤተ ክርስቲያኔን በዚች ዓለት ላይ እሰራለሁ[illegible] የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም (ማቴ. 16:18) ሲል ወደ ክብሩ ወንጌል[illegible] የተጠሩ ቅዱሳን ምን ያህል ጦርነት /ተጋድሎ/ እንደሚጠብቃቸው[illegible] ማመልከቱ እሙን ነው:: የገሃነም ደጆች ማለትም ሰይጣን፣ ርኩሳ[illegible] መላዕክት፣ አጋንንትና እነዚህ የሚገለገሉባቸው መሣሪያዎች /ሰው፣ እንስሳ[illegible] ግዑዝ ነገር፣ .../ ቀላል ሰራዊት አይደሉም:: /ኤፌ. 6:12-18/ ስላልሆኑም[illegible] ከእነዚህ ጋር ትግል ገጥሞ ለመቋቋምና የድል ባለቤት ለመሆን ኃይል[illegible] ያስፈልጋል:: ሁለተኛው ሺህ አልቆ በሦስተኛው ሺህ ውስጥ የአዲሱ ዘመ[illegible] እንቅስቃሴ ተከታዮች ሰው ሁሉ ወደ አምላክነት ደረጃ ይደርሳል በማለት[illegible] ያስተምራሉ:: ለዚህ የሚጠቀሙበት ዘዴ ርኩሳን መናፍስትን ወ[illegible] ውስጣቸው በማስገባት ነው:: በመከራው ዘመን ሰው እግዚአብሔር ነው[illegible] በሚባልበትና በርኩሳን መናፍስት ሰዎች በተሞሉበት ዘመን ያለ መንፈስ[illegible] ቅዱስ ኃይልና እርዳታ እንዴት መቋቋም ይችላሉ? ስለሆነም ለዚህ ሥራ[illegible] መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን አስፈላጊ ነው ማለት ነው::

- ***የወንጌልን ሥራ ለማንቀሳቀስ /ለማስፋፋት/***



ወንጌል ከተሰበከበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬና ወደፊትም ይሰበካል፤ ይሰራጫል:: በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሐሥ. 11:12፣ 19፤ 8:4-10፤ 29፣ 39-40፤ 16:7፤ ራዕ. 2:7፣ 11፣ 17፣ 29፤ 3:6፣ 13 እና 22 ስንመለከት መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን /አገልጋዮችን ሲመራ እናያለን:: በመከራው ዘመን ለሚኖሩ ቅዱሳን የዚህ ዓይነት ምሪት እንደሚሰጥ አያጠራጥርም:: ይህም ግን በበአለ ሃምሣ ዕለት በወረደው ዓይነትና ዛሬም በተለያዩ አገሮች በሚሰራው ዓይነት እንጂ በብሉይ ኪዳኑ ሁኔታ ብቻ አይደለም::

እንግዲህ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለማናቸውም ዓይነት የእግዚአብሔር ሥራ ያስፈልጋል:: እንዲያውም ከመነጠቅ በፊት በአሁኑ ዘመን ያለን አማኞች በልዩ ኃይል ተሞልተን በስልጣንና በእውነተኛነት ወንጌሉን ልንሰብክ የተዘጋጀን ነን:: ስለሆነም የምንጠብቀው ከዛሬ 30 ዓመት በፊት በኢንዶኔዢያ በኮሪያና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ወይም የዛሬ 2000 ዓመታት በኢየሩሳሌም የፈሰሰው መንፈስ ቅዱስ በኢትዮጵያም እንደሚያልፍ ነው:: ይህም ሲባል መንፈስ ቅዱስ በኀይል ባይወርድም ልንሰራው ያለውን በትጋት እየሰራን መጠበቅ ይኖርብናል:: ሐይል እስኪመጣ ብለን ቁጭ እንዳንል ልንጠነቀቅ ያሻናል::

## (12). <u>የእግዚአብሔርና የሰይጣን እቅድ /ዓላማ/ አፈጻጸም</u>

መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና በዚች ዓለም ላይ ዓላማ ያለው እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ሰይጣንም እንደሆነ ነው:: ኤፌ. 1:4፤ 2ኛ ጴጥ. 3:9፤ በራዕ. 20:3፣ 12:9:: በራዕይ 12:12 ዲያብሎስ ዕቅዱን ተፈጻሚ ለማድረግ በታላቅ ቁጣ ወደዚህ ምድር ነዋሪዎች ሲመጣ የእግዚአብሔርስ ሁኔታ ምን ይሆናል ብለን እንገምታለን ወይም እናምናለን? እግዚአብሔር አስቀድሞ በልጁ በኢየሱስ የጀመረውን ሥራ ሙሉ በሙሉ አልፈጸመም:: የጌታ ኢየሱስን ጠላቶች ገና ከእግሩ ሥር ሙሉ በሙሉ አላስገዛለትም:: ገና ልዩ ልዩ ጥበቡን በስብከት ሞኝነት በሚያምኑ የክርስቶስ አካልና /ቤተ

ክርስቲያን/ በመከራው ዘመንም ቅዱሳን/ አማካኝነት ይገልጻል:: ኤፌ. 3:10፤ 1ኛ ቆሮ. 12:7-11::

እግዚአብሔር ክብሩን የገለጸውና የሚገልጸውም በህዝቡ ነው:: በ1ኛ ቆሮ. 12:8-11 የተጠቀሱት የፀጋ ስጦታዎች ሥራቸው እግዚአብሔርን መግለጽ (በግሪክ ፋኔሮሲስ) ነው:: ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ነው:: ስለሆነም በመከራው ዘመን ሰዎች በጨለማና ግራ በመጋባት ውስጥ እያሉ የአፍቃሪውንና የቸሩን አምላክ እጅና ፊት በሚናፍቁበት ወቅት መንፈስ ቅዱስ አላማውን ሳይፈጽም ይነጠቃል ማለት አያስደፍርም::

### (13). ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል ታላቅ ህዝብ ሁኔታ

በሐሥ. 4:12 ውስጥ መዳን በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ተገልጿል:: አንድ ሰው ዳነ የሚባለው መንፈሱን ገድሎት የነበረው ኃጢአት ሲነሳለት ነው:: ኃጢአት ደግሞ ከሰው ላይ የሚሠረየው ከጥቂቶች በቀር በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው:: 1ኛ ዮሐ. 1:7:: በራዕ. 7:9-17 ውስጥ የተጠቀሱት ታላቅ ህዝብ በተለይ በቁጥር 14 ላይ ያሉት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በፈሰሰው ደሙ ከሐጢአት መንጻታቸውን ያመለክታል:: እነዚህን ቅዱሳን ***የመከራው ዘመን ቤተ ክርስቲያን*** እንላቸዋለን:: አስቀድሞ በምድር የነበሩና በኋላ ግን በሰማይ ርስታቸውን ጨብጠው ከተገኙ ለዚህ የበቁት በመንፈስ ቅዱስ ታትመው ነው ማለት ነው:: ሮሜ 8:16::

### (14). የመጽሐፍ ቅዱስ በመከራው ዘመን መኖር

በመከራው ዘመን ለሚኖሩ ሰዎች ወንጌል ይሰበካል ወይስ አይሰበክም? ወንጌል እስከ ዓለም ፍጻሜ ለዓለም ሁሉ ይሰበካል:: የሚሰበክ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ በመከራው አይኖርም የሚሉ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለመንፈስ ቅዱስ የተነገረውን እውነት ምን ያደርጉታል?

የሰባቱ ዓመታት መከራ ከፖለቲካ ከኢኮኖሚና ከህብረተሰባዊ አኗኗር አንጻር በተጨማሪም የአገሮችንና የመልክአ ምድርን አቀማመጥና ይዘት



ስንመለከት በውጪአዊ መልኩ አሁን ካለንበት እምብዛም የማይለይ ሲሆን በይዘቱ ግን ከፍተኛ አሉታዊ ለውጥ ይኖረዋል:: 2ኛ ጢሞ. 3:1-9:: መከራው በጣም ያይላል:: የሰው ስቃይ ይጨምራል:: ለሰው ጠቃሚ የሆኑ /ሮችም በአብዛኛው በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠፋሉ:: ሆኖም ግን ሰው በሚሻውና በሚያቀደው መንገድ በቴክኖሎጂ የፈጠራ ሂደት ይራቀቃል፤ ይመራመራል:: በዚህ ሁኔታ ሳለ የመከራው ዘመን ይጀምራል:: በዚያን ዘመን ፀሎት ቤቶች ይዘታቸው በተወሰነ ደረጃ ቢለወጥም ቅርጻቸው ይኖራል:: በእውነተኛ አማኞች ዘንድ ከመጋረጃ በስተኋላና በአደባባይ ወንጌል ይሰበካል:: ወንጌል በቅንነት ይሁን በማመካኘት መሰበኩ አይቀርም:: በቅርብ ጊዜ በብዙ ሚሊዩን የሚቆጠሩ አማኞች ቅዱሳን ከዚህ ዓለም በመነጠቅ ሲጠፉ፣ ብዙ ሰዎች በከፍተኛ ናፍቆትና ፍርሃት በዳን. 12:4 እንደተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት ይመረምራሉ፤ ያጠናሉ:: መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሰዎችን በመውቀስ ወደ እውነት ይመራል:: ከዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎች ወደ እውነት ይመጣሉ::

ከመከራው በፊት የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ሲሆን ዛሬ በየፀሎት ቤቱ የሚሰብኩ፣ የሚያስተምሩ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዲግሪ፣ ዲፕሎማ፣ ዶክትሬት እና ፒ.ኤች.ዲ. ያላቸው ነገር ግን ያልተለወጠ /ያልዳነ/ ሕይወት ያላቸው ሲቀሩ፣ ሁለት ባልና ሚስት /አማኝና የማያምን / በአልጋ ተኝተው ወይም በመንገድ እየተጫወቱም ሆነ እየተጨቃጨቁ አሊያም በመደባደብ ላይ ሳሉ አንዱ በቅጽበት ዓይን ቢሰወር /ቢነጠቅ/፣ አንድ ቅዱስ የዩኒቨርሲቲ ምሁር /ሌክቸረር/ በብዙ ተማሪዎች ፊት እያስተማረ ቢነጠቅና በየትምህርት ቤቱ፣ መሥሪያ ቤቱ፣ በየቤቱ፣ በየመንገዱ፣ ስፖርት ሜዳው፣ ወዘተ ያሉ ቅዱሳን ሁሉ ቢነጠቁ /ከዚህ ዓለም ቢጠፉ/ በአካባቢው ያለው ተመልካች ምን ይላል? በዚህ ወቅት በየአቅጣጫው የዘመድ ፍለጋ፣ የልጅ ፍለጋ፣ የስልክ መደወል፣ የደብዳቤ መጻፍ፣ የሬዲዮ ግንኙነትና በየመስመሩ መሯሯጡ የማይቀር የተለመደ ነገር ነው:: ማንም ሚስቱ ጠፍታ አርፎ የሚቀመጥ፣ ልጆቹ ...

ተሰውረው ዝም ብሎ የሚቀመጥ አምብዛም ነው:: ይህ ሁኔታ ሰዎችን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ይመራቸዋል::

በዚህ ወቅት ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ይመረምራሉ፤ ያጠናሉ፤ ይጠያይቃሉ:: መንፈሳዊነት አይኑራቸው እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያላቸው ብዙ ከሃዲዎች በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ወደ ንስሃ ይመጣሉ:: በዚህም ጊዜ ነው እግዚአብሔር ለክብሩ ያዘጋጃቸውን ሰዎች የሚያስነሳው:: 144000 አይሁዶችም በዚህ ወቅት ወንጌልን ይሰብካሉ:: ሰዎችም በንስሃ ወደ ክርስቶስ ይመለሳሉ:: ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ለመግለጽ በመከራው ዘመን ይኖራል:: ምክንያቱም የቃሉ ዋነኛ ደራሲ መንፈስ ቅድስ ስለሆነ ነው::

## (15). የስላሴዎች የአሰራር ግንኙነት

በዮሐ. 15:26 መንፈስ ቅዱስ ወደዚህ እንደሚመጣ ጌታ ኢየሱስ ተናግሯል:: በዮሐ. 16:14 ላይ ደግሞ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል ይላል:: የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በዚህ ክፍል ምንድነው? የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጌታ ኢየሱስን ለሰዎች መግለጽ ሲሆን የጌታ ኢየሱስ ደግሞ አብን መግለጽ ወይም መተረክ ነው:: /ዮሐ. 15:26፤ 1:18/::

በእነዚህ ምዕራፎች የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ክርስቶስ በስጋ ወደ ምድር በመምጣት፤ ለሰው ልጆች በመስቀየት በሞትና በትንሣኤም በማለፍ በአብ ቀኝ ከሆነ በኋላ ወደፊት ወደ ምድር በመመለስ የሚፈርድ መሆኑን መመስከር ከሆነ በመከራው ዘመን ደግሞ መዳን ካስ መዳንም በኢየሱስ ከሆነ ያስ መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ይሄንን የጌታ ሥራ እንዴት ይረዱታል? በመከራው ዘመን ጌታ ኢየሱስ በምድር የለም:: ግን ስለ እርሱ ወንጌል ይሰበካል በዮሐ. 16:13-14 እግዚአብሔር አብ መንፈሱን ለወልድ ሰጥቷል:: ወልድም መንፈሱን አፍስሷል:: ክርስቶስ መጥቶ እስኪነግሥ መንፈስ ቅዱስ የማተም ሥራውን ይቀጥላል:: ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከጌታ ኢየሱስ ወስዶ ሰዎችን ወደ እውነት /ኢየሱስ/ መምራት ከሆነ በመከራው



ዘመን ለሚድኑ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ይነጠቃል ማለት ከቃሉ ጋር ተጣራሽ ነገር መፍጠር ነው::

## (16). የብሉይና የአዲስ ኪዳን አገልግሎት

እግዚአብሔር ለህዝቡ ከመዳናቸው ጋር በተያያዘ የሚበጃቸውን ኪዳን በተለያዩ ዘመናት ሰጥቷቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስንመረምር በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ቢያንስ ከ80 የሚበልጡ የአገልግሎት ልዩነቶችን እናገኛለን:: ከእነዚህም ውስጥ፤

| ብሉይ | አዲስ |
|---|---|
| የሥጋ ህግ ሮሜ 7:5-6 | የመንፈስ ህግ ሮሜ 8:2 |
| የእስራት ቀምበር /ገላ. 5:11 | የነጻነት ቀምበር /ህግ/ ያዕ. 1:25 |
| ጥላ የሆነ ሥራ ቆላ. 2:14-17 | እውነት የሆነ/የማያልፍ/ ሥራ ዕብ.10:1-18 |
| ጽድቅ በእንስሳት ደም ዕብ.9:16-22 | ጽድቅ በክርስቶስ ደም ማቴ. 26:28 |
| እግዚአብሔር የማይረካበት ኢሣ. 1:13-14 | እግዚአብሔር የሚደሰትበት/ የሚረካበት ዕብ. 10:5-18 |
| ለለውጥ የተዘጋጀ ዕብ.9፤ገላ.3 | የማይለወጥ/ዘላለማዊ ኪዳን/ዕብ.13:20 |
| ተፈጥሮአዊ ፕሮግራም ዕብ. 9:10-13 | መንፈሳዊ ፕሮግራም 2ኛ ቆሮ. 3:6፣ 18 |
| ወደ ፍጹምነት የማያደርስ ዕብ. 7:19 | ወደ ፍጹምነት የሚያደርስ ዕብ. 10:14 |
| በውድቀትና ድካም የተሞላ ዕብ. 10:11 | በብርታትና በክብር የተሞላ ዕብ. 10:10-18 |
| ምህረት የሌለበት ዕብ. 10:28 | ምህረት ያለበት /ፍጹም/ ዕብ. 8:12 |

| | |
|---|---|
| መርገምን የሚያመጣ ገላ. 3:10 | ከመርገም የሚያነጻ ገላ. 3:13 |
| ለእስራኤል ብቻ የተሰጠ ዘዳ. 4:7-8፣ 5:8 | ለሰው ሁሉ የተሰጠ ማቴ. 26:28 |

ከላይ የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ከ2ኛ ቆሮ. 3:6 ጋር ማስትም እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ህይወትን ይሰጣል ከሚለው ጋር በማነጻጸር ስንመለከተው የአዲስ ኪዳን አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሰራ ይጠቁመናል:: ታዲያ ይህ ከሆነ በመከራው ዘመን ለእስራኤልና ለአህዛብ የተገባው የአዲስ ኪዳን አገልግሎት ይቆማል ማለት ነው? አይደለም:: የመከራው ዘመን በዓይነቱ ከሁሉም ጊዜ ይልቅ የከፋ ይሁን እንጂ የአዲስ ኪዳንን ሁኔታ ለውጦ ወደ ፍዳነት የሚለውጥ አይሆንም:: ስለዚህ በመከራው ዘመን መንፈስ ቅዱስ አለ::

## (17). የራዕይ መጽሐፍ ምስክርነት

ራዕ. 12:17፣ 19:10 መንፈስ ቅዱስ በምድር እንዳለ ያመለክትታል:: በዚህ ክፍል ***የኢየሱስ ምስክር*** የሚለው ሐረግ በዮሐ. 15:26 እና ራዕ. 19:10 እንደተጠቀሰው የጌታ ኢየሱስን ማንነት ለአይሁዶችም ሆነ ለአህዛብ የሚመሰክር መንፈስ ቅዱስ ነው:: ዘካ. 12:10-13:: ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በራዕይ ውስጥ ከመከራው በፊት ባለው ሁኔታ አንዴም አልተጠቀሰም ይህም አለመኖሩን ያመለክታል:: መንፈስ ቅዱስ ግን በዚህ በድቅድቅ የህይወት ጨለማ ዘመን ጌታ ኢየሱስን ሲገልጽ እናያለን:: መንፈስ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስን ይተርካል፤ ወልድ ደግሞ አብን ይተርካል:: ይህም መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ታላቅ ሥራ እንዳለው ያሳስበናል::



## (18). የመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎች መኖር

ስለ መንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎች በጥቂቱ ቀደም ባሉት ቁጥሮች ውስጥ አለፍ አለፍ ብዬ ጠቅሻለሁ:: በተጨማሪ ግን በመከራው ዘመን ከእግዚአብሔር ዓላማ አንጻር የፀጋ ስጦታዎች ሥራ ምን እንደሚመስል ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ:: የመከራው ዘመን የሰይጣን የሥራ ጊዜ ሊያበቃ ጥቂት ዘመን እንደቀረው የሚያመለክት የሽግግር ወቅት ነው:: በተጨማሪም ደግሞ የእግዚአብሔርም ቁጣ የሚሰለጥንበት ጊዜ እንደመሆኑ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ታላቅ ተጋድሎ የሚደረግበት ምዕራፍ ነው:: ሰይጣን ዙፋኑን ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ አድርጐ የልዑልነት ቦታውን ለመቀማት መጋደል የጀመረው ከብዙ ዓመታት በፊት እንደሆነ ኢ.ሣ. (14:12-14) ይነግረናል:: ይህ እቅዱ እስከ ዛሬ ተግባራዊ አልሆነለትም:: ሆኖም ግን ትግሉን ፈጽሞ አልተወም:: ትግሉንም በስውር በማካሄድ ላይ ይገኛል:: የዲያብሎስን ማንነትና ባህርይ በአስቆሮቱ ይሁዳና በአቤሴሎም በግልጽ ማየት ይቻላል:: 2ኛ ሳሙ. 14 እስከ 15:: አቤሴሎም በውስጡ ንጉሥ የመሆን አንድ ትልቅ ምኞት አደረበት:: ከዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎችን አስከትሎ መስዋዕትም በማቅረብ እንደነገሠ መለከት ያስነፋል ያሳውጃል:: ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰለሞን እንዲነግሥ ስለነበር:: አቤሴሎም ጊዜና ሁኔታን ፈልጐ መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ ብዙ እንደጣረ በኋላ ግን ለሞት አልፎ እንደተሰጠ እናያለን:: የአስቆሮቱ ይሁዳም ጌታን በመሳም አሳልፎ ለመስጠት እርምጃ ቢወስድም የመጨረሻ ዕድሉ ሞት ነበር:: በጣም በተመኙና በናፈቁ መጠን ራሳቸውን ለአደጋ አጋለጡ:: መጽሐፍ ቅዱስ ምኞት እንደሲኦል ጨካኝ እንደሆነች ይነግረናል::

ዲያብሎስን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከተቀደሰው ተራራው /መንግሥቱ/ ጣለው፤ ቀጥሎ ደግሞ በመከራው ዘመን ወደ ምድር ይጥለዋል:: በድጋሚ ደግሞ ለሺህ ዓመታት እስር ወደ ጥልቅ ይጥለዋል:: በመጨረሻም ወደ ገሃነም ይጥለዋል:: ለዚህም ሁሉ ያበቃው ምኞቱ ነው:: በዚህ ሁሉ ግን ሰይጣን ከትግሉ ወደ ኋላ አላለም:: መጨረሻው እንደ ልጁ

እንደ ሐሰተኛው ክርስቶስ ይሆናል:: የዲያብሎስ በፈጣሪው ሥልጣን ላይ አምጾ ባለሥልጣን የመሆን ምኞቱ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ በዚህ ዘመን መጨረሻም ሰዎችን ወደ ራሱ ማርከ በእግዚአብሔር ላይ በይበልጥ እንዲያምጹ ለማድረግ ልዩ ልዩ ሐሰተኞች ምልክቶችን፣ ድንቆችንና ተዓምራትን ያደርጋል:: ከዚህም የተነሳ ሰውን ወደ ገሃነም የመጣል እቅዱ በተወሰነ ደረጃ /መጠን/ ይከናወንለታል:: 2ኛተሰ.2:9-12፤ ራዕ.13:13-14:: ሰይጣን ያለ ኃይሉን በየአቅጣጫው አጠናክሮ የሰውን ልጆች በከፋት ሊበቀል ሲሰራ እግዚአብሔርም ዝም ብሎ አያየውም:: ለመንገሥ ካለው ምኞቱም የተነሣ ብዙ ሰዎችን ያስታል ዳን. 8:23::

የእግዚአብሐር እቅድ ሰውን ማዳን ወደ እውነት ሁሉ መምራት እንደሆነ ሁሉ በሐሥ. 2:22 እንደተጠቀሰው ልጁ በምድር በነበረበት ጊዜ በተዓምራት፣ በድንቆችና በምልክቶች ሰዎች ወደ ድነት እንዲመጣ ነገም በመከራው ዘመን በ144000 አይሁዶች፣ በአህዛብ፡ በሚድኑ ቅዱሳንና በሁለቱ ነቢያት አማካይነት የዲያብሎስን ሐሰተኞች ድንቅና ተዓምራት በሚውጥ ሁኔታ ክንዱን ይገልጣል::

በ1ኛ ቆሮ. 12:7-11 ያለው የመንፈስ ቅዱስ አሰራር አይለወጥም:: በመከራው ዘመን በሚኖሩም አማኞች ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ እንደተባለ መንፈስ ቅዱስ በፀጋ ስጦታዎቹ አማካይነት ራሱን፣ ወልድንና አብን ይገልጣል:: 1ኛ ቆሮ. 12:7፤ ዮሐ. 15:26:: በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ጌታ ተዓምራት ያደረገው ሰዎች እንዲያምኑ ነው፤ተዓምር ማለት ከተፈጥሮአዊው ነገር ለየት ያለ የመለኮታዊነት ሥራ ባህርይ ያለውና ሰው የማይሰራው ማለት ሲሆን ሰዎች ይህንን ሲያዩና ሲያምኑ ወደ እግዚአብሔር ከሚቀርቡበት መንገድ አንደኛው ነው:: ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ ሰይጣን በከፍተኛ ደረጃ እየሰራ ባለበትም ዘመን /በመከራው/ ጌታ ኢየሱስን ለማስተዋወቅ ክንዱን በደካማ ሸክላዎቹ እንደሚገልጽ ነው:: ይህም



የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በተሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት እንጂ በብሉይ ኪዳኑ አሠራር ብቻ አይደለም:: ሐሥ. 2:16-17::

ከላይ የተብራሩት 18 ማስረጃዎች በድጋሚ ከሌሎች ጥቅሶች ጋር በማገናዘብ ብንመለከታቸው የመንፈስ ቅዱስን በመከራው ዘመን መኖር የሚጠቁሙ ናቸው:: መንፈስ ቅዱስ በመከራው ይሄዳል ቢባል ግን ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስን ሌሎች እውነቶች እርስ በርስ ማጋጨትና ብዙ ችግር መፍጠር ይሆናል:: ከዚህም በመነሳት መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን ይኖራል እንላለን::

የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን የተለያዩ ዋና ዋና ማስረጃዎችን በዐቢይና በንዑስ ርዕሶች ከፋፍለን ተመልክተናል:: ከጊዜና ከሁኔታ አንጻር መከልከል ስላለ እንጂ ሌሎችንም ማቅረብ ይቻላል:: ለምሳሌ፣..የዳንኤል 70ኛው ሱባኤ..፣ ..የእስራኤልና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ግንኙነት..፣ ..የመነጠቅ ዓይነቶች መነጻጸር.. የመሳሰሉት ጥቂቶቹ ማስረጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: እስካሁን ባደረኩት ጥናት ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጊዜ ለአመለካከቶች መብዛትና መለያየት መንስኤው የመነጠቅ ዓይነቶችን መኖርና ቅደም ተከተል በደንብ አለማወቅ ነው:: በቅድመ መከራ መነጠቅ እንዳለ ሁሉ በድህረ መከራና በመንፈቀ መከራም መነጠቅ እንዳለ ጠንቅቆ ማወቁ እጅግ መልካም ነው:: ይህ የመካከል ለፋሪነትንና የተጠራጣሪነትን አቋም ለመያዝ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኝነት ለመግለጽ ነው::

# ክፍል ሰባት
# ትዕይንተ መነጠቅ

**ልዩ ትኩረት:**

***ስለ ትእይንተ መነጠቅ ሲነሳ በሌሊት ይሁን በቀን ሰዎች በተለያዩ መስኮች ላይ መሆናቸው የማይቀር ነው:: ያኔ በየቦታው ያሉ ቅዱሳን ሲነጠቁ ሊፈጸም ያለውን ትእይንት በራሳችን ማስተዋልና በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ማሰብ እንችላለን:: በአንጻሩ ደግሞ አንዳንድ ክርስቲያን አርቲስቶች ሳይንቲስቶች ሊሆን ያለውን ነገር በክርስቲያን ፊክሽን መልክ ገልጠው ማስቀመጥ እንደሚፈልጉትም አይነት ማየቱ ክፋት ላይኖረው ይችላል:: ስለሆነም በዚህ ክፍል የተገለጡትን ትዕይንቶች በሆነ መልኩ ብትተረጉሙት ውጤቱን ለታሪክና ለታሪክ ባለቤት ለጌታ እንድንተወው እናሳስባለን::***

በዘመናት መካከል ያልጠፋው መጽሐፍ ቅዱስ በያዛቸው ታላላቅ የእውነተኛ አማኞች ተስፋ ውስጥ አንዱ በሆነው በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ነው:: መነጠቅ አፈ-ታሪክ ወይም ልብ ወለድ ሳይሆን በእግዚአብሔር የታቀደ ሊፈጸም ያለ ትንቢታዊ እውነት ነው:: የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ በዓለም የሚገኙ ቅዱሳን ከዚህ ምድር ይሰወራሉ:: ወደ ተዘጋጀላቸውም ስፍራ ይወሰዳሉ ::ዮሐ. 14:1-3:: እነዚህ ቅዱሳን የሚኖሩት በኅብረተሰቡ መካከል ነው:: ስለሆነም በህይወታቸው የሚያልፈውን ነገር ሁሉ ከሃዲዎችና ስማዊ ክርስቲያኖች እንዲሁም በሌላ እምነት ያሉ ሁሉ ይመለከታሉ:: ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን ያገኙ እውነተኛ ክርስቲያኖች ከዚህ ዓለም ከከሃዲዎች መካከል ተለይተው ሲነጠቁ ወይም ሲወሰዱ ብዙ ነገር ይፈጸማል:: ታይቶ የማይታወቅ ለአንዳንዶችም ተሰምቶ የማይታወቅ ፈጽሞም ያልታሰበ ያልተጠረጠረ ነገር ይሆንባቸዋል:: በመነጠቅ ጊዜ በዚህ ምድር ሊፈጸሙ ይችላሉ ተብለው የታሰቡትን አንዳንዶችም በጽሁፎቻቸው ያሰፈሩአቸውን አብዘኞቹም በእርግጥ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን::



1. **በመነጠቅ ጊዜ ሊፈጸሙ የሚችሉ ትዕይንቶች**

.1.1. **የቤተ ሰብ ሁኔታ**

ጌታ ኢየሱስ በማቴ.19:13-14 እና በ18:1-10 እንዲህ ሲል ናግሯል:: .....ሕጻናትን ተዉአቸው፣ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ ትከልክሏቸው፤ መንግሥተ ስማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና...:: ከዚህ ቃል መነሳት የእግዚአብሔር እስትንፋስ የተሰጣቸው ሕጻናት ሁሉ ይነጠቃሉ ለት ነው:: የእድሜው ጣሪያ ሙሉ በሙሉ አይታወቅም፤ ይህ ሚስጢር እኛ አልተገለጠም:: አንዳንዶች ከ7-9 ዓመት እድሜ ያላቸው በሕጻናት ልል ይጠቃለላሉ የሚል አቋም አላቸው:: የቀሩት ደግሞ ከ5 ዓመት በታች ሉ፤ ከፊሎቹ ደግሞ ልጆች ክፉና መልካሙን የሚለይ ህሊና እስካሌላቸው ረስ ይነጠቃሉ የሚሉም አሉ:: የልጃቸው እድሜ 7 ዓመት ከአንድ ቀንና 9 መት ከ5 ወር የሆኑ ወላጆች ይህንን በተመነው ሰው ላይ ፈራጅ እንዳይሆኑ ድሜውን ገደብ ለጌታ እግዚአብሔር ትተን ወደ ትእይንቱ መመለሱ የተሻለ ው::

.1.1.1. **ሙዋዕለ ሕጻናት**

ታዳጊ ሕጻናት በወላጆቻቸው አማካይነት ወደ መዋዕለ ሕጻናት ልከዋል እንበል፤ አስተማሪዎቻቸው በሙሉ ወይ በክፍል እያስተማሯቸው ሊያም ደግሞ ለእረፍት ወጥተው ሕጻናቱ ሲሯሯጡ፤ ሲጣሉ ሲታገሉ፣ ሳቁ እየተመለከቱ ሊሆን ይችላል:: ምናልባት ይህ የታዳጊ ሕጻናት መዋያ ተማ መካከል ሊሆን ይችላል:: ብዙ የከተማው ህዝብ በአጥር ላይ ንጠልጥሎ ወይም አሾልኮ የሚሆነውን እየተመለከተ ቢሆን፣ በዚህ ወቅት ለከት ቢነፋ፣ እነዚህ ሕጻናት ምን ይሆናሉ? የተገባቸው ሁሉም ባሉበት ቅጽበተ ዓይን ተለውጠው ይነጠቃሉ ማለት ነው:: ወደ ቤታቸው ሚመለሱበት ሰዓት ደርሶ ወላጆቻቸው መኪኖቻቸውን አዘጋጅተው ጠብቋቸው የሕጻናቱ መሰወር ሪፖርት ሲደርሳቸው ምን ይላሉ? በዚህ

ሁኔታ ከሕጻናት ታሪክ ጋር ብቻ በተያያዘ በመላው ዓለም የሚወራውንና በወላጅ ህይወት የሚያልፈውን ስቃይ አእምሮ ያትኩርና ይረዳው:: ልጅን መልሶ ለመሳምም ሆነ ለማየት መንገዱ አንድ ብቻ ነው:: ይኸውም ቶሎ ንስሀ ገብቶ ጌታን በመቀበል ዳግመኛ መወለድ ነው::በእናት እቅፍ ያሉ ሕጻናት ዘጠኝ ወር ተሸክማ፣ መቼ ወልጄ አቅፌ ስሜ በማለት ለረጅም ጊዜ ትናፍቅ የነበረች እናት ወልዳ ከባሏ ጋር ቁጭ ብለው ልጃቸውን ወደ ላይ ሽው ሽው እያደረጉ ሲያጫውቱ መለከት ተነፍቶ በቅጽበተ ዓይን ልጃቸው ስትሰወር (ሲሰወር) ክርስቶስን የማያምኑ ወላጆችና የቅርብ ተመልካችስ ምን ይሉ ይሆን?

### 7.1.1.2. <u>የልጆች የልደት ቀን</u>

ወላጆች በየዓመቱ የልጃቸውን ልደት ያከብራሉ:: ዘመድ ጓደኛ ፎቶ አንሺ (ካሜራ ማን) የልጃቸው ጓደኞች ሁሉ ለታላቅ ደስታ ይጠራሉ፤ የሚበላው የሚጠጣው ስጦታውም ሁሉ ይጐርፋል:: ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶ ፌሽታው ሊጀምር ደቂቃ ሲቀር ኃጢአት የማያውቃቸው ሕጻናት በሙሉ ቅዱሳን የሆኑ ጌታን በትክክል ያመኑ ወላጆች ከሕጻናቶቻቸው ጋር ከዚህ ዓለም ሲነጠቁ በስመ ክርስትና እየኖሩ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን በደል የሚፈጽሙ ሰዎች ልጅ አልባ ሆነው በድንጋጤ ሲፋጠጡ ማየት እጅግ ያሳዝናል:: ተጠያቂው ማነው? ተከሳሽስ ይኖር ይሆን? ከዚህ ለመዳን ብቸኛ ው መፍትሄ ቶሎ ዳግመኛ መወለድና እንደ ሕጻናቱ መሆን ነው:: መቴ.18:3::

### 7.1.1.3. <u>የሞት አፋፍ ሕጻን</u>

ወላጆች ልጃቸው በከፍተኛ ሕመም እየተሰቃየ ተቸግረው ወደ ሆስፒታል ይዘው ይሄዳሉ እንበል፤ እንደደረሱ የሕጻናቱ ዶክተር ተቀብሎ እያገላበጠ ካየ በኋላ መርፌና መድኃኒት እየለጠ እያለ ሕጻኑ በመነጠቅ ቢጠፋስ? ወላጆች ምን ይላሉ? ዶክተሩስ? የዘመኑ ዶክተሮች ከአስማት ጋር ጥብቅ ወዳጅነት ጀምረዋል:: በአስማት ልጃችንን ሰወረብን ብለው ዶክተሩን ይከሰስ ይጀምሩ ይሆን ወይስ ባልየው መሣሪያ ይዞ ከሆነ ልጃችንን ውሰድ ሎ ዶክተሩን አፋጥጦ ይይዝ ይሆን? የወላጆቹስ ልብ? በእንቅርት ላይ ጆሮ ግፍ አይደል? ጌታ እግዚአብሔር ከዚህ ውርደት ና ሐዘን ይጠብቀን:: የቤተ ርስቲያን መነጠቅ እንደሆነ ወዲያው የመከራው ዘመን ይጀምራል:: ናልባት እግዚአብሔር ሐጢአተኞችን ከሚቀጣባቸውና ለመከራ ሚገልጥባቸው መንገዶችና አሰራሮች ውስጥ አንዱ ልጃቸውን በመከራው መጀመሪያ ላይ ከእጃቸው ነጥቆ በመውሰድ ይሆን? አንዳንድ የሥነ መለኮት ሁራን እግዚአብሔር ሕጻናትን ለመከራው ዘመን አሳልፎ ቢሰጥ በእውነት ይህ ለእርሱ የጽድቅ ሥራ ስለማይሆን በመነጠቅ ሥርዐት ወደ መንግሥቱ ማሳለፍ ይታደጋቸዋል ይላሉ:: በዚህ ቅጣትና መከራ ጌታ የክፉ ወላጆችን ልብ የሚያገኝና የሚመልስ የሚያድናቸውም ቢሆን ድንቅ አሰራር አይደል?

ይህንንና ሌላውንም የመሰለ ነገር ማሰብ ይቻላል:: አእምሮን ሰፋ አድርጐ በጽሞና ተቀምጦ በቅንነት ለመረመረ ሰው በእግዚአብሔር እርዳታ ነገር ሊሰወርበት አይችልም:: እናንተ ወላጆች ዛሬ የጋለሞታይቱን ቤተ ክርስቲያን ድምጽ (ስብከት) ሳይሆን የእውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን ድምጽ ብትሰሙ እጅግ ይመረጣል:: በእውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል እንጂ በብዙሃን ድምጽ፣ በሆያሆዬ ድምጽ አትሂዱ:: የማንም ንግግር አይጐትታችሁ የማንም ወሬ አይግፋችሁ:: ነገር ግን በቃሉ አማካይነት እውነትን በመመርመር መኖር ይበጃል::

### 7.1.1.4. <u>ባልና ሚስት</u>

በአሁኑ ጊዜ በዚች ምድር ላይ ከሚኖሩት ውስጥ ጥቂቶቹ ባልና ሚስት ናቸው:: ሁለቱም ጌታን ክርስቶስን በትክክል አምነው መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ሊሆን ይችላል:: አሊያም ከሁለት አንዱ ሲያምን ይችላል:: ሚስት ብታምንና ባልየው ባያምን ይህም ባል ተሳዳቢ፣ ተጨቃጫቂ፣ ነገረኛ ስኒ ሰባሪ፡ ቴሌቭዥን ረጋጭ ...ቢሆንና አንድ ቀን በሆነ ነገር ይጣላሉ እንበል:: ባልም እንደልማዱ በትሩን አንስቶ ሚስቱ በተኛችበት ያለ ርህራሄ በያዘው

በትር ወይም መሳሪያ ሊመታ ሲል መለከት ቢነፋና ያቺ ክርስቲያን በቅጽበተ ዓይን ብትሰወር ያም በትር አልጋው ላይ ቢያርፍ ባል ምን ይላል? ዱላው ተመልሶ የሚመታው መስሎት በድንጋጤ ይወድቅ ይሆን? የሚያምኑ ባሎቻቸውንም የሚያሰቃዩ ሚስቶችም እንዲሁ አሉ:: እነርሱስ ምን ይገጥማቸው ይሆን?

### 7.1.1.5 <u>ልጆችና ወላጆች</u>

በአሁኑ ጊዜ የቤተሰብን አቋም ስንመለከት፣ በሙሉ አማኝ የሆኑ፣ እናትና አባት ዳግም ያልተወለዱ ልጆች ግን በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉና የዳኑ፣ ጥቂት ልጆች ጌታን የተቀበሉ ጥቂት ያልተቀበሉ፣ አባትና ልጆች ወይም እናትና ልጆች ጌታ ኢየሱስን አምነው የቀሩት ያላመኑ ቤተሰብ ያሉአቸው ይኖራሉ እንበል:: ከዚህ ሁኔታ ውስጥ እናትና አባት ጌታን ያልተቀበሉና በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቁ ሆኖም 10 ልጆች ያሉት ቢሆኑ ልጆቻቸውም በሙሉ ዳግም የተወለዱና ጌታቸውን በተለወጠ ሕይወት የሚያመልኩና የሰርጋቸው ቀን በተከታታይ የቀረበ የሃብታም ልጆች ናቸው እንበል:: አንድ ቀን ቤተዘመዱ ጐረቤቱም ሁሉ ያሰበት ልዩ ግብዣ ቢደረግና እየበሉ እየጠጡ እየተደሰቱ ሳለ መለከት ቢነፋ ልጆቹ ሁሉ ሲነጠቁ ወላጆች ግን ይቀራሉ:: ይህንን ነገር ወላጆችና ሌሎች እድምተኞች ምን ይሉት ይሆን?

### 7.1.1.6. <u>ሰካራም አባት</u>

እስከ ሌሊቱ 6 ሰዓት ሲጠጣ ቆይቶ በጣም ሰክሮ ወደ ቤቱ ሲሄድ ሳለ ልክ በሩ ላይ ሲደርስ ጭንቅላት የሚፈነክት የበረዶ ናዳ ያለው ዝናብ ቢጥል፣ በሩ የተቆለፈና አማኝ ቤተሰቡ ከ15 ደቂቃ በፊት ተነጥቀው ቢሆን ይህ ሰው ምን ይደርስበታል? በማለዳስ ምን ይል ይሆን?



### .1.1.7. <u>ከእንቅልፍ በኋላስ</u>

ቤተሰብ በሙሉ ማታ በሰላም ተኝቶ ጠዋት ወደ ስራ ለመሄድ ሲነሱ ማሹ የሚያምነው ሲጠፋ ግማሹ ሲቀር ይህ በተመልካቹና በአስተዋዮች ይወት ምን ይፈጥርና ያሳድር ይሆን? ምንስ ይከተላል?

## .1.2. <u>የተሽከርካሪዎች ሁኔታ</u>

### .1.2.1. <u>መኪኖች</u>

በዓለም ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ያለበት በቀን እስከ ሦስት ሚሊዮን መኪኖች የሚመላለሱበት መንገድ (አደባባይ) በሜክሲኮ ይገኛል:: ማለዳ ሰው ሁሉ ወደየ ሥራው ሲሮጥ ከእነዚህ ሁሉ መኪኖች ውስጥ 28 መቶው የቅዱሳን ናቸው እንበል:: በዚህ የከፍተኛ ፍጥነት ጉዞ ላይ እያሉ ኋለኛው መለከት ቢነፋ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ ሲነጠቁ መኪኖቹ ያለ ሾፌር በከፍተኛ ፍጥነት የመብራት ህግ ጥሰው ሌላውን ሲገጩ የሚፈጠረውን እልቂት፣ የንብረት መውደም ማሰብ ይቻላል:: መኪኖች ከመንገድ በመውጣት ትልልቅ ህንጻዎችን ሲያፈርሱ፣ እግረኛውን ተጓዡና እንስሳውን፣መናፈሻ የቆሙትን ሌሎች ልዩ ልዩ ተንቀሳቃሾችን ሁሉ ሲያነጉዱ ምን ይባል ይሆን?

ሁኔታው ሁሉ እጅግ አሳዛኝ ይሆናል:: ከተገዛች ሁለት ቀን ያልሞላት ዘመናዊ መርሰዲስ፣እየተነዳች ሳለ መልስ የሚሰጥ ባለቤት የሌለው መኪና ከኋላ መጥቶ ሲገጫትና እንዳልነበረች ሲያደርጋት ሌሎችም መኪኖች ርስ በርስ ተነባብረው ሲጋጩና ብዙ ሰው ሲያልቅ እንዴት ይከብድ ይሆን? ከአዲስ አበባ ወደ ጂማ ወይም ድሬዳዋ ሲኬድ በግራና በቀኝ መኪና ሳይ ሆኖ በሚታየው ገደል ሲደረስ መለከት ቢነፋና ሾፌሩ ዳግም የተወለደ ከሆነ ይነጠቃል:: ሌሎች ግን ጌታን ያልተቀበሉ ሁሉ ባለው ገደል ውስጥ ከነመኪናቸው ይሰምጣሉ::

## 7.1.2.2. <u>አውሮፕላን</u>

በቀደሙትም ሆነ በአሁኑ ጊዜ ቅዱሳን የሆኑ ፓይለቶች (አይሮፕላን አብራሪዎች)በየ አገሩ ይገኛሉ:: አንድ ፓይለት ከአንድ አገር ተነስቶ ወደ ሌላው አገር በበረራ ላይ ቢሆን፤ ምናልባት አውሮፕላኗ በሕንድ ወይም ሰላማዊ ውቅያኖስ ላይ ስታንዣብብ መለከት ቢነፋ ፓይለቱ አማኝ ከሆነ በቅጽበተ ዓይን ተሰውሮ ይነጠቃል:: አውሮፕላኗ እየተምዘገዘገች እየተገላበጠች በውስጧም ያሉ በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቁ አማኝ (ክርስቲያን) ነን ባዮች ወደ ውቅያኖሱ ውስጥ መስጠማቸው የማይካድ ሐቅ ነው:: በተመሣሣይ ሁኔታና መልኩ በዓለም ልዩ ልዩ ቦታዎች ይቀጥላል::

## 7.1.2.3. <u>ብስኪሌት (ሞተር ብስኪሌት) የሚነዳው</u>

በከተማም ሆነ በገጠር መንገዶች ላይ ተራ ተጫዋቾችና ኮርሰኞች ሲወዳደሩ እናያለን:: ውድድር ሲካሄድ በመኪና እየተከታተሏቸው ቆይተው ማብቂያው ላይ ሲደርሱ ከእነዚሁ ኮርሰኞች (ተወዳዳሪዎች) ሁለቱ ህያው አማኞች ቢሆኑ ህዝቡ እያጨበጨበ ሲቀበላቸው ሲወጣ መነጠቅ ቢሆን እነርሱ ሲነጠቁ ሰው የሌበት ቢስክሌት (ሞተር ሳይክል) እየሮጠች መጥታ ስትገጫቸው ምን ይባላል? አንድ ሌላ ተራ የሆነ ብስኪሌተኛ እየነዳ ቢነጠቅ ሰው የሌለባት ብስኪሌት ከኋላ መጥታ በሰላም የሚሄደውን መንገደኛ ስትለትመውስ? በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሌሎች ብዙ ነገሮችን ማሰብ ይቻላል::

## 7.1.3. <u>የቅዱሳን (ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች) ሰርግ</u>

በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሙሽራውና ሙሽሪት ከአጃቢዎች ጋር ገብተው የምሳ ግብዣ ስነ ሥርዓት ሲፈጽሙ ሁሉም በዝግጅት ላይ ነው እንበል:: ከዚህ ሰርግ እድምተኞች ውስጥ የሙሽሪትና የሙሽራው ከፊል ዘመዶችና ጓደኞች በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ያልተወለዱና በፈጣሪ መኖር የማያምኑ ቢሆኑ ለሙሽሮቹና ለእድምተኞቹ የምሳ ግብዣው ሲቀርብ ሲል ሁሉም በዝግጅት ላይ እንዳሉ መለከት ቢነፋ በሠርጉ ያሉ ሙሽሮችና የዳኑ



ዝብ በሙሉ በመነጠቅ ይሰወራሉ:: በዚህ ሁኔታ ላይ ያሉና ይህንን ሚመለከቱ ወላጆችና ሌሎች ታዳሚዎች ምን ይሉ ይሆን? ወይኔ ልጄ ከርግሽ እለት እንዲህ ተዋረድሽ! ወይኔ ልጄ! ቀኝ እጄ ተቆረጠ! ከአሻሮ ይነት ወጣሁ ስል እንዲህ ሆኖ ቀረ! አዬ! አዬ! ጉድ ይባል ይሆን?:: ወይስ ሉም ግራ ተጋብቶ ዝም ይባል ይሆን? ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ግን ነጥቀዋል:: በዚህ ትዕይንት ህዝብ ምን ይሰማው ይሆን?

እውነተኛ ክርስቲያኖች ያልሆኑ እናት አባቱን ወይም የሌላ ዕምነት ከታይ የሆኑ ወላጆቹን በመኪና ይዞ ከአዲስ አበባ ወደ ሐረር የሚጓዝ ዛዥ ልጅ አማኝ ነው እንበል:: መተሃራ ሐሩር ሲደርሱ መለከት ቢነፋ ቅጽበተ ዓይን እንደሚሰወርና ወደ ተዘጋጀለት ሰማያዊ ስፍራ እንደሚሔድ ሙን ነው:: መኪናው ውስጥ ያሉ እነዚያ ሰዎች ምን እንደሚደርስባቸው ገመት አያስቸግርም? በጣም ጨለማና አስቃቂ ለአዕምሮም የሚከብድ ሉታዊ ትዕይንት ሲሆን ይችላል::

እነዚህንና ሌሎችንም የመሳሰሉ ነገሮች መልካቸውና አቀራረባቸው ንሽ ለወጥ ቢልም በቅርብ ጊዜ በዚህ ምድር ኀጢአተኞች ነዋሪዎች ላይ ደርሳሉ:: ሊመጣ ያለው ይህ ክፉ ነገር እንዳይደርስብን ከሚመስልና ተሳሳተ ሃይማኖት (እምነት) ወጥቶ እውነተኛውን የሚያድን ዕምነት ሬውኑ መያዝ ነው:: ልበ ጠንካራና ግትር ከመሆን ግራና ቀኙን ማየቱና ስተዋሉ ትክክለኛ አቋም ነው:: ቶሎ ወደ አዳኙ ጌታ ኢየሱስ ተመለስ::

## .1.4. <u>በየሥራ መስኩ ያሉ ቅዱሳን</u>

በአሁኑ ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች (መንፈሳዊ ሰዎች) በትምህርት ቶች በዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች በፍርድ ቤቶች በሆስፒታሎችና ወዘተ ታዎች በብዛት ይገኛሉ:: ባሉበት ሁኔታ ሳሉ መለከት ቢነፋ በቅጽበተ ዓይን ሰውጠው ወደ ሰማይ ይወሰዳሉ:: ለምሳሌ አንድ ክርስቲያን መምህር ዩኒቨርሲቲ ወይም በኮሌጅና በከፍተኛ መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

በብዙ ተማሪዎች ፊት እያስተማረ ሳለ መለከት ቢነፋ ይነጠቃል። ይህ መምህር በጥቁር ሰሌዳው ላይ እየጻፈ፣ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ንግግር እያደረገ ሲሆን ይችላል መለከት ቢነፋ ወይም ወደዚህ ውጣ የሚል ድምጽ ቢሰማ ሁሉም እያዩት ወዴት እንደሔደ ሳይታወቅ በቅጽበተ ዓይን መሰወሩ አሌ የማይባል ሐቅ ነው። በዚህ መምህር መሰወር ብቻ እንኳን የሚወራው ወሬ ዓለምን ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ሊያጥለቀልቅ ይችላል። እንኳን በሺህና በሚሊዮን የሚቆጠሩ መምህራን ከምድር ገጽ ጠፍተው (ተሰውረው) ይቅርና። በየአገሩ በዚህ ዓይነት መልኩ ብዙ ክርስቲያን ሰራተኞች ቢጠፉ ለአንዲት አገር ቀላል ውድቀት ይሆን? በዚሁም የሰባቱ ዓመታት መከራ ይጀምራል። ታላቅ ቀውስም ይሆናል። በዚህም መንገድ እግዚአብሔር ወንጌል ለሰዎች እንዲነገር ያደርጋል። በኢዮብ 33:14 ላይ እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላውም ይናገራል፤ ሰው ግን አያስተውለውም ይላል። ይህ መነጠቅ ሲሆን ስታዩ ወንዶችም ሆናችሁ ሴቶች ይህ የጻፍኩላችሁ ምልክት ይሁናችሁ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማኝ ክርስቲያኖች ከምድሪቱ ላይ ሲጠፉ ስትገነዘቡ ያ መነጠቅ እንደሆን ልብ በሉ፤ አስተውሉ፤ ይህ እንደሆነ ወዲያው የሰባቱ ዓመት ወይም የ3 ተኩል ዓመታት መከራ ይጀምራል፡ አውሬውም በሐይል ስለሚሰራ መከራው ይደርስባችኋል። ንስሀ ከገባችሁ ግን ቆይታችሁ በመነጠቅ ወይም በመሞት ወደ ዘላለም ህይወት ትደርሳላችሁ። ጌታን በትክክል ያልተቀበላችሁና ያላገኛችሁ ከሆናችሁ ከወዲሁ አዳኙን ክርስቶስ ኢየሱስ ክርስቶስን ብትቀበሉ አብረን እንነጠቃልን፤ሆኖም ግን ይህ የመነጠቅ ዕድል ቢያመልጣችሁ ፊታችሁ የታላቁ መከራ ዘመን ይጠብቃችሁአል፤ ንስሐ ከገባችሁ የአውሬውን መከራ ተቀብላችሁ ትድናላችሁ።

ብዙ ክርስቲያን (ቅዱሳን) ዶክተሮች በአሁኑ ጊዜ በየሆስፒታሉ ይገኛሉ። ሁለት ወይም ሦስት ዶክተሮች አንድን በሽተኛ ቀዶ ጥገና በማድረግ እያስተናገዱ ነው እንበል። ሌሎች ጌታን ያልተቀበሉ ዶክተሮችም ቢኖሩ የህመምተኛውም ቤተሰቦች በውጭ በሃዘን ላይ ቢሆኑ ወደ ሰማይ ጥሪ



ቢደረግ ቅዱሳን ዶክተሮች በሙሉ ከሆስፒታሉ ይሰወራሉ። አካባቢው (ተመልካቹ) ይህንን ምን ይላል? የበሽተኛው ቤተ ዘመዶች ያንን ሁኔታ ቢሰሙ ዶክተሮች ሲጫወቱ ሲቀልዱ ዘመዳችንን ገደሉት ብለው ክስ ይመሰርቱ ይሆን? ሌላም ማሰብ ይቻላል።

እናንተ ክርስቶስን እናምናለን፣ ክርስቲያኖች ነን ወይም ደግሞ መንግስተ ሰማይ እንገባለን የምትሉ ሆኖም ግን ጌታ ኢየሱስ በማቴ.8:22 እንደተናገረው <u>በቁም መንፈሳችሁ የሞተ</u>፣ ሬጋ ብሎ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ራስን በመመርመርና የታማኝ አገልጋዮችንም ምክርና ምሪት በማግኘት ህይወታችሁን አስተካክሉ። (***<u>ዝርዝር ነገሮችን ከክፍል 10 እና 12 ውስጥ ይመልከቱ</u>***) የመንፈስ በኩራት የሌላችሁ የወደዱት ሁሉ በምኞት አይገኝምና ቶሎ ብላችሁ ዳግመኛ ተወለዱ። ለዚህም ትክክለኛውን የደህንነት መንገድ ምሪት የሚያሳዩአችሁ ቅዱሳን አማኞች በየቦታው ይኖራሉ። ከእነዚህም ውስጥ ብዙዎች <u>ጴንጤ</u> ብለው የሚጠሩአቸው ቅዱሳን ናቸው። እነዚህ ጴንጤ የሚባሉ ቅዱሳን በአሁኑ ጊዜ ቦወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናቱም፡ በግልም፡ በካቶሊኩም፡ በኦርቶዶክሱም፡ በፕሮቴስታንቱም፡ ወዘተ ይገኛሉ። ከፍሬአቸው ስለሚታወቁ ጠጋ ብላችሁ ካሁኔው ሳይነጠቁና ሳይጠፉ አነጋግሩአቸው። አሁን ያለው ጭላንጭል ተስፋ ወደ ድቅድቅ ጨለማ (ጭንቅ) ሳይለወጥ መጽሐፍ ቅዱስን አንብበ፡ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ጠይቁ፡ እነርሱንም አማክሯቸው። ከሁሉም በላይ ከተማጸናችሁት መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል ።ዮሐ. 8:11-13። እርሱ የመጣው ለስራ ነው።

### 7.1.5. <u>ልዩ ልዩ አካባቢዎችና ስፍራዎች</u>

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የታወቁ መንፈሳዊ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች በውስጣቸው እውነተኛ አማኝ ሳይሆኑ ነን ብለው የገቡትን፣ በውጭ ቆንጆ መስለው ውስጥ ለውስጥ ጌታን የካዱትን፣ በግልጽ ተቃዋሚ የሆኑትን፣ እውነተኛ የሆኑትንና ለውጥ ያላቸውን ቅዱሳን ይዘዋል። ከመምህራኑም፣

ከተማሪዎቹም፣ ከቢሮ ሠራተኞቹም የእነዚህ ዓይነት ሰዎች ይኖራሉ:: መስከት ሲነፋ የቆሙ የሚመስላቸው መውደቃቸውን የሚያውቁት አብሯቸው ይፈጭ(ተመሳሳይ ሥራ የሚሰራው) የነበረው ከአጠገባቸው ሲነጠቅ ነው:: ሰዎች ይህንን ሁሉ ሲያዩ ንስሀ ይገባሉ ወይም ልባቸውን ያደነድናሉ:: ከተመለሱ ደግሞ ይድናሉ::

በዓለም እጅግ ታላቅ የሆነ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ቅዱሳንን የያዘ ፀሎት ቤት አለ እንበል:: በዚህ ፀሎት ቤት ዓመታዊ ኮንፍራንስ ቢዘጋጅና ብዙዎች ቢጋበዙ በዚህ ግብዣ የሰው እባቦችና እፉኝቶች፣ ችግር ያባረራቸው መንታፊ ሌቦች፣ እውነተኞች፣ ሞራሊስቶች፣ ሰማኞች፣ ሆድ የባሳቸው: ለመዝናናት የመጡ መኖራቸውን ልብ እንበል:: ከወደ ሰማይ የጥሪ መለከት ቢነፋ ዳግም የተወለዱ ሁሉ ሲነጠቁ ሌላው እንዳለ ይቀራል:: ሰዎቹ ሲነጠቁ ወርቃቸው: በሰውነታቸው ላይ ያሉት ጌጣ ጌጦች አብረው አይነጠቁም፤ መኪኖቻቸውን: በመኪኖቻቸው ውስጥ ያሉትን ንብረቶች በሙሉ ትተው ነው የሚነጠቁት፤ ታዲያ ሌቦቹም ሆኑ ሌሎች ያንን ሁሉ ሐብት መሬተ ወድቆ ሲመለከቱ ዝም ብለው ትተው ይሄዱ ይሆን? ወይስ ከሌቦቹ ጋር ይተባበሩ ይሆን? ስንቱንስ ትተው ስንቱን ይወስዱ ይሆን? ወስደውስ ምን ያህል ይባረኩበት ይሆን? ዳሩ ምን ያደርጋል ወዲያው የመከራው ዘመን ይቀጥል የለ? መንግስት ደግሞ በቤቶቻቸውና በማምለኪያ ቦታዎቻቸው ላይ ምን አዋጅ ያወጣ ይሆን? እውነተኛ ሰውጥ ያላቸው ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ሁሉ ያላቸውን ጥሪት በሙሉ ጥለው ይሄዳሉ:: መጨረሻው ይሔው ነው:: አንተም እውነተኛ ቅዱስ ሆይ መመሪያህ ቆላ. 3:1-3 ይሁን:: ልብህ አይክበድ ተጠንቀቅ(ቂ)ም: ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደዚህ ወዳለው የክበረ ሕይወት ሲያመጣን ነውና የክበረ የህይወት የሆነውን ወርቃችንን በእርያ አፍንጫ ላይ አናውለው :: ትጋ(ጊ)ና የመነጠቁ ባለቤት ለመሆን ተፋለም(ሚ):: እንፋለም::

ሌላው አስደናቂ ትዕይንት ከሚካሔድባቸው ስፍራዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የመቃብር ሥፍራዎች ናቸው:: አንዳንዱ ዘመዱን ከቀበረ አንድና ሁለት ቀን ሲሆን ይችላል:: ሰው ሁሉ ወደ መቃብር ስፍራዎች ሩጫ



ይቀጥላል:: ታይቶና ተሰምቶም የማይታወቅ አዲስ ነገር ለብዙዎች ሰዎች ይሆናል:: መቃብሮች ባዶ ናቸው:: በድኖች ተነስተዋል:: ለቅሶ ይሆን ደስታ? ወይም ትካዜ ወይስ መቀወስ? አንዳንድ ለውኮ በድን ተነስቶ ጠፋብኝ ብሎ ያለቅስ ይሆናል? ግራ ሲገባ እኮ እንዲህ ያደርግ ይሆናል:: ሰው ከእውነተኛ ፈጣሪው ሲርቅ እኮ ይዘበራርቀውና ይዘበራረቅበታል:: አያድርስ ሲባል የሚገባው ይሄ ነበር:: ምን ይሆን ይህንን ህዝብ የሚገጥመው?

አንዳንድ ቀልጣፋ የሆኑ የመሰላቸው ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በመንፈሳዊ ተቋሞች አስገብተዋል:: ለካስ ልጆቹ እዚያ ገብተው ጌታን አግኝተው ኖሮአል:: መለከቱ በተነፋ ገዜ ተነጥቀዋል:: የመነጠቅን ወሬ ሰምተው ወደ ኮሌጆች እየሮጡና መኪና እያበረሩ ሲደርሱ አብዛኞቹ ተነጥቀው የራሳቸውም ልጅ ተነጥቆ ያገኙታል:: በአንድ በኩል ደስታ በሌላ በኩል ደግሞ ኃዘን ይሆናል::

እናንተ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠራችሁ ሁሉ ምርምራችሁ ጥሩ ቢሆንም (ዳን. 12:4) መስመር የሳተ ምርምርና እውቀት ለትንሽና ዘለቄታ ለሌለው ህይወት ብቻ ይጠቅማል:: ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን በትክክል እንዳታውቁና በህይወታችሁም ክርስቶስ ገዢና ጌታ ሆኖ እንዳይኖር እንዳይጠቅማችሁም የሚከለክልን ምርምር ሁሉ ልትቃወሙት ይገባል::

ዛሬ በዓለማችን ይጐዳል የተባለው ሲጠቅም ይጠቅማል የተባለው ደግሞ ሲጐዳ፤ ክፉ የተባለው ደግ፣ ደግ የተባለው ክፉ ሲሆን ይታያል:: ሰው ወድዶ አይስክር፣ ወድዶ አይወድቅ፣ ወድዶ አይሰበር:: አንተም ሰው ሆይ ህይወትህ ለአንተ እንቁ ነው:: ገና ስትፈጠር ልትገዛበት የሚገባ የህይወት ህግ በአንተ ውስጥ ተቀምጧል:: ያስቀመጠውም እንደዲያብሎስ ሐሰት የሌለበት እውነተኛው ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው:: ያንን ፈልገህ በማግኘትና የሙጥኝ በማለት ፈጽሞ ልትመራበት ይገባል:: ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለስ:: መጽሐፍ ቅዱስን ከዓለም መጻሕፍት ሁሉ ልዩ የሚያደርገው

የእግዚአብሔር መንፈስ ስላለበት ነው:: ስለዚህ ማንበብ ማንበልበል ብቻ ሳይሆን አጥናው (ብላው) ለሁሉም ጾታ እውነቱ አንድ ነው:: ሕዝ. 3:1-3 ኤር. 16:16፣ ቆላ. 3:16::

## 7.2. <u>የመነጠቅ ውጤቶች</u>

ይህ የመነጠቅ ሥርዓት እንደተፈጸመ በተከታታይ የሚፈጸሙ እጅግ ብዙ ነገሮች ይኖራሉ:: ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

7.2.1. በሎጥና በኖህ ዘመን እግዚአብሔር በእርሱ ያመኑትን ቅዱሳን በመርከብና በመላዕክት ኃይል ከለያቸውና ካዳናቸው በኋላ ቁጣውን በኃጢአተኞች ላይ አፍስሷል:: አሁንም ደግሞ በልጁ በክርስቶስ ዘመን የእርሱ የሆኑትን በመነጠቅ ሥርዐት ይወስድና በቀሩት አመጸኞች ላይ ቁጣውን ያፈሳል::

በምድር የቀረ ሰው ሁሉ በተወሰነ ደረጃ በራዕይ ከ6-19 የተጠቀሱት መቅሰፍቶች ደረጃ በደረጃ ይደርሱበታል:: ይህም የሚሆነው በተነገረው ትንቢት መሰረት ነው:: በራዕይ 11:10-12 ላይ

***«...አህዛብ ተቆጡ፤ ቁጣህም መጣ:በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ: ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳንህ ስምህንም ለሚፈሩ ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ ምድርንም የሚያጠፉአትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ»*** ተብሎ ተጽፎአል:: ይህ ዘመን ጌታ የሚበቀልበት ዘመን ይሆናል ማለትነው:: የሰሰው ልጅ ይህ ወቅት እጅግ አሰቃቂ ይሆናል::

7.2.2. በሰማይም በእግዚአብሔር ቅዱሳን መላዕክትና በዲያብሎስ መላዕክት መካከል ጦርነት ይሆናል:: የእግዚአብሔር ወገኖች ሲያሸንፉ ርካሳኑም ወደ ምድር ስለሚወድቁ ለምድር ነዋሪዎች አሰቃቂ በትር ይሆናል::ራዕይ 12:12-17::

7.2.3. በየቤቱ ስልክ ሊደወል ይችላል:: አባትና እናት ልጃቸው፣ እህት ወንድማቸው፣ ልጆች ወላጆቻቸው ወዘተ ስለጠፉ ሁሉም በጥያቄ ይሞላሉ::



ሰብ አማኝ ልጆቻቸውን ሊድሩ ብዙ ወጪ አድርገው ሰርጉ እንደነገ ሆኖ መነጠቅ ቢሆን ምግቡ እንዳለ ሊተውና ሊበላሽ ነው:: የሚበላውም ዘን ይኖናል:: በሁሉም አቅጣጫ የመፈላለጉ ጉዳት ይቀጥላል::

4. የሐሰት ወሬ ከከሃዲ መንግስታት ሊወጣ ይችላል:: በቅዱሳን መሰወር ያምኑ ከሃዲዎች ክርስቲያኖች የተጠሉ ስለሆኑ በተዓምር በአቶሚክ ል አጠፋናቸው በማለት ማስተባበል ይቀጥላል:: በዚህም የብዙ ሰዎች በሐዘን ይመታል:: ስለሆነም የመዳን ቀን የጥንካሬ ቀን ዛሬ ነውና ችንን እንመርምር:: እንጠንቀቅ:: ወደ ፈተና እንዳንገባ ተግተን ፀልይ::

# ክፍል ስምንት

## የመነጠቅ ዓላማዎች

ቀደም ባሉት ዐቢይና ንዑሳን ርዕሶች ስለመነጠቅ በዛ ያሉ ሐሳቦች ተመልክተናል:: ለቀረቡት እውነቶች ከጥቂት ሐሳቦች በስተቀር መሠረቱ ምንጩ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: የመነጠቅ አቃጅና ፈጻሚ ባለቤ እግዚአብሄር ነው:: ጌታ እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩ መነጠቅን ለምን አዘጋጀ? ይህስ ስርዓት እንዲኖር ለምን ፈለገ? የእነዚህ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በሚቀጥሉት ዝርዝር ሃሳቦችና የመጽሐፍ ቅዱ ጥቅሶች እንመለከታለን::

### 8.1. ቅዱሳንን በእግዚአብሔር ፊት ለማቅረብ

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው:: ህልውናው ወይም ማንነቱ ፈጽ ከኃጢአት ጋር በተያያዘ አይነቀፍም:: ማንም ሊቀርበው በማይችል ድን ብርሃን ይኖራል:: አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያየው አይችልም ::1ኛጢሞ 6:16:: ሐዋርያው ጳውሎስም በኤፌሶን 5:27 ውስጥ: «ዕድፈት ወይም የፊ መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆ ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ» በማለ ስለ መነጠቅ ገልጾአል:: በነዚህ ጥቅሶች መሠረት እግዚአብሔር አብ ፊ ለመቅረብ የሚቻለው የክርስቶስ ኢየሱስን አካል የሚመስል በመልበስ ብ ነው:: ይህንንም ደግሞ ማከናወን የሚቻለው ሞትን ድል አድርጐ የተነሳው ጌታ ኢየሱስን በማመን ብቻ ነው:: በተጨማሪም በ1ኛተሰ. 3:13፤ይሁዳ 2 ላይ ስናነብብ በአምላካችንና በአባታችን ፊት እንደምንቀርብ ተገልጿል:: ይህም የሚፈጸመው እግዚአብሔር ባዘጋጀው የመነጠቅ ስርዓት ብቻ ሲታለፍ ነው::



### 8.2. ያንቀላፉትን ቅዱሳን ከኃጢአተኞች ሙታን መካከል ለመለየት

ለረዥም ዘመናት የጌታ ኢየሱስ አዳኝነት ተመስክሮላቸው ጌታን አምነውና እንደ አዳኛቸው ተቀብለው፤ ከሥጋ የተለዩ (የሞቱ) ወይም ያንቀላፉና በመቃብር ያሉ ቅዱሳን ብዙ ናቸው:: እነዚህ ቅዱሳን እንደሌላው ሰው ተቀብረዋል:: ሆኖም የኋለኛው መለከት በሚነፋበት ጊዜ ከኃጢአተኞች ሙታን መካከል ይነሱና ይነጠቃሉ:: በእነዚህ ቅዱሳንና በኃጢአተኞች ትንሳኤ መካከል ቢበዛ የአንድ ሺህ ዓመታት ልዩነት ይኖራል:: እግዚአብሔር ይህንን የመነጠቅ ስርዓት ያዘጋጀው በቅዱሳን ማንቀላፋትና በኃጢአተኞች መካከል ልዩነት መኖሩን ለማሳወቅም ነው:: የመነጠቅ ስርዓት ካልሆነ የሁለቱ ሙታን ሁኔታ ልዩነቱ ጉልቶ አይታይም:: ይህንን ሃሣብ በደንብ ለመረዳት 1ኛተሰ. 4:14፤ ራዕይ 20:4-6፤ 1ኛቆሮ. 15:20-23 ይመልከቱ:: እነዚህ ጥቅሶች የሙታን ትንሳኤ ለህይወትና ለፍርድ ቅደም ተከተል እንዳለው ይገልጻሉ::

### 8.3. ቅዱሳንን ወደ አዘጋጀላቸው ስፍራ ለመውሰድ

በ1ኛተሰ. 4:17 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ..እንነጠቃለን... ብሏል:: መነጠቅ ካለ የግድ ማረፊያ (መድረሻ) ደግሞ ይኖራል:: ይህም መድረሻ ጌታ ኢየሱስ በዮሐ.14:1-3 ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው መንፈስ አዳሽና ታላቅ ተስፋ ነው:: በዚህ ክፍል ጌታ ኢየሱስ ...ስፍራን አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና... ሲል ወደዚያ ወዳዘጋጀው ስፍራ ቅዱሳኑን የሚወስደው ..በመነጠቅ.. ሥርዐት ውስጥ በማሳለፍ ነው:: እውነተኛዎቹ አማኞች ወደ ተዘጋጀላቸው ስፍራ በመነጠቅ ይቀርባሉ፤ ይሄዳሉ ኤፌ. 5:27:: በሰማያዊ ስፍራ እግዚአብሔር በልጁ በጌታ ኢየሱስ በኩል ወዳዘጋጀው ቦታ መድረስ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ መነጠቅ ነው::ከዚህ ውጪ የተሰጠ ተስፋ የለም::

## 8.4. የቅዱሳንን አካል ወደማይሞት አካል ለመለወጥ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በ1ኛቆሮ. 15:35-57 ስንመለከት ስለ ፍጥረታት ልዩ ልዩ አካል ይናገራል:: ስለ በራሪ ወፎች አካል፣ በባህር ስለሚኖሩ አሶች አካል፣ ስለ እንስሳት አካልና፣ ስለምድራዊ ሰው አካል ስለ ሰማያዊ፣ ስለ በሰባሸ፣ ስለ ፍጥረታዊና መንፈሳዊ አካልም በዝርዝር ገልጸ ጽፏል:: ቁጥር 40 ላይ ስለ ሰማያዊና ምድራዊ አካል ክብር ልዩነት ያመለክታል:: ሰማያዊ አካል ሲል አሁን በገነት ..በጻድቃን መንፈሶች ጉባኤ.. ያሉት የሰው መንፈሶች በትንሳኤ ጊዜ ሊለብሱት ስላለው አካል ነው:: ይህ አካል የሚለበሰው በሰማያዊ ስፍራ ሄደን ነው:: ይህንንም የማይሞት፣ የማይፈርስና፣ የማይጠፋ አካል ለመልበስ አሁን ያሉት ቅዱሳን በቅጽበተ ዓይን መለወጥና ያንቀላፉትም አማኞች መነሳት ይኖርባቸዋል:: ይህ ቅዱሳን የሚለብሱት መንፈሳዊ አካል ጌታ ኢየሱስ ከትንሳኤ በኋላ የለበሰውን ይመስላል:: «እርሱም ሁሉን እንኳን ሰራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሰራር ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል» ፊልጵ.3:21:: ልክ መነጠቁ ከመሆኑ በፊት ወይም ልክ በሚሆንበት ጊዜ ሊሆን ይችላል፤ ይህ ሰውነታችን ይለወጣል::

## 8.5. ቅዱሳንን በመንፈስ፣ በነፍስና በሥጋ ፍጹማን ለማድረግ

በዚህ ክፍል የተጠቀሰው የመነጠቅ ምክንያት በተራ ቁጥር 4 ከተጠቀሰው ጋር የሚገናኘው በሥጋ መለወጥ አኳያ ነው:: ከዚህ ለየት ባለ መንገድ ግን እግዚአብሔር የመነጠቅን ሥርዓት እንዲኖር የፈለገበት ሌላኛው ምክንያት ስለ ሰው ነፍስ ወደ ፍጹምነት ደረጃ መድረስም ጭምር ነው:: አስቀድሞ ሲፈጠር የሰው መንፈስ ፍጹም ነበረ:: ለኃጢአትም ሆነ ለሞት እንዲሁም ለዲያብሎስ ተገዝቶ አያውቅም ነበር:: ከውድቀት በኋላ ግን ለክፋት ኃይላት በተለያዩ ሁኔታዎች ተገዢ ሲሆን በዚያም ዲያብሎስን ሲከተል ሰው ልጅነቱ በቀጥታ ለሰይጣን ሆኖአል:: ይህም መንፈሳዊ ሞት ተብሎአል:: በአማኝም ህይወት ይህ የመንፈስ ሞትና የትንሳኤ ህግ



ሊሰለጥንበት ችሎአል:: ለምሳሌ በ2ቆሮ. 7:1 ላይ ...ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ.. ሲል፤ የሰው መንፈስ እንደ ምሳሌ 25:28 ካልተጠበቀ ሊረክስ እንደሚችል ከረከሰም ሞት ሊሰለጥንበት እንደሚችል በግልጥ ያሳየናል::

ቅዱሳን ከተነጠቁ በኋላ በሙሉ ማንነታቸው (በሦስትነታቸው ወይም በሁለትነታቸው) ፍጹም ይቀደሣሉ:: በሰማይ ፍርድ ይኖራል:: ይህ ፍርድ አማኙን ወደ ዘላለም እሳት (ሞት) የሚወስደው ሳይሆን የተወሰነውን ሽልማት እንዲያገኝ የሚያደርገው ነው:: በዚህ ፍርድ ሰዎች ማንነታቸውን የቀድሞ ህይወታቸውን ጉድለትና የእግዚአብሔርን ፀጋ ካዩ በኋላ በመንፈስ በነፍሳቸውና በስጋቸው በዘላለም ቅድስና ይታተማሉ:: ለምሳሌ በ1ኛተሰ. 5:23 ላይ «የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፡ መንፈሳችሁም፡ ነፍሳችሁም፡ ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ:: ፊልጵ. 3:21:: ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ወደ ተለወጠ ደረጃ የምትደርሰው ከመነጠቅ ጊዜ ጀምሮ ነው::

## 8.6. ቅዱሳን በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሽልማትን እንዲቀበሉ

ከመነጠቅ በኋላ ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 14:1-3 እንደተናገረው ቅዱሳንን ወዳዘጋጀው ቦታ በመውሰድ ያኖራቸዋል:: በኢየሩሳሌም (በተዘጋጀው ስፍራ) ደርሰው መኖር ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ በምድር ስለ ሰራው ነገር ፍርድ በጌታ ኢየሱስ ይሰጣል:: ይህ ፍርድ ሽልማት የሚያስገኝ ወይም የማያስገኝ ይሆናል የሕይወትን አክሊል የሚያሳጣ ፈጽሞ አይሆንም:: ዮሐ. 14:1-3፣ 2ኛቆሮ. 5:10፣ ራዕይ 19:1-10፣ ሮሜ 14:10፣1ኛቆሮ. 3:11-15::

## 8.7. ቤተ ክርስቲያንን ከታላቁ መከራ ለማዳን

በመጨረሻው ዘመን ከሚከሰቱ ታላላቅ አስፈሪ ትዕይንቶች ውስጥ አንደኛው በ70ኛው ሱባኤ የሚገለጸው ታናሹና ታላቁ መከራ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቅዱሳን ከዚህ መከራ ሊያመልጡ እንደሚችሉና

የሚያመልጡበትም መንገድ ምን እንደሆነ ተገልጧል:: በራዕይ መጽሐፍ ከምዕራፍ 6-19 ስንመለከት በዚህ መከራ ዘመን በኃጢአተኛው ዓለም ላይ የሚወርደውን የቁጣ (የመቅሰፍት) ዓይነቶች በዝርዝር እናገኛለን:: የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን በዚህ ውስጥ እንዲያልፉ እግዚአብሔር አልፈቀደም:: ሆኖም ግን የመከራው ዘመን እውነተኛ አማኞች(የመከራው ዘመን ቤተ ክርስቲያን) በመስዋዕትነት በዚህ መከራ እንደሚያልፉ ከራዕይ 6:9-11፤ 13:7-10 እና 20:4 መረዳት ይቻላል:: በሉቃስ 21 ጌታ ኢየሱስ ሊመጣ ስላለው ልዩ ልዩ መቅሰፍት ከተናገረ በኋላ ቁጥር 36 ላይ ግን ..ከዚህ ሁሉ.. ለማምለጥ መፍትሔው በፀሎት መትጋት እንደሆነም አስተምሯል:: ..ከዚህ ሁሉ.. ሲል በ በማቴ. 24: ሉቃ. 21ና ራዕይ 6-19 የተጠቀሱትን መቅሰፍቶች ማለቱ ነው:: በተጨማሪም 1ኛተሰ. 5:9 «እግዚአብሔር ድነትን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንድናገኝ ነው እንጂ ለቁጣ ወስኖ አላስቀመጠንም» የሚል ተጽፎ እናነብባለን:: እግዚአብሔር ኖህንና ሎጥን ከቁጣ ሰውሮ እንደ አዳነ በዚህ ዘመን መጨረሻም በመነጠቅ ቤተ ክርስቲያንን ያድናል:: በተጠቀሱት ጥቅሶች መሠረት የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ የሚሆነው ከመከራው በፊት ነው:: እግዚአብሔር ቅዱሳኑን ከመከራው ለማዳን የመነጠቅን ሥርዓት አዘጋጅቷል:: መነጠቅ ከመከራው በፊት እንደሚሆን ሲነገር ግን መከራውን የፈሩ ቅዱሳን ጩኸት እንደሆነ ሲተረጐም ፈጽሞ አይገባም::

## 8.8. ቅዱሳን በበጉ ሠርግ ተካፋይ እንዲሆኑ ለማድረግ

የዘመናት ቅዱሳን ተካፋይ የሚሆኑበት መንፈሳዊና ሰማያዊ ሠርግ ለሺህ ዓመት ሥርዓት ጌታ ኢየሱስና ቅዱሳን ወደ ምድር ከመመለሳቸው በፊት ይሆናል:: ራዕይ 19:7-8:: ይህ ሠርግ የሚሆነው ወደ 70ኛው ሱባኤ (የመከራው ዘመን) ማብቂያ ላይ ነው:: በራዕይ 22:11 ላይ ዓመጸኛው እንዲያምጽ ጻድቁም ጽድቅ እንዲያደርግ ሲፈቀድ ሊከፈለውም ካለው ዋጋ ጋር ተነጻጽሮ ነው:: ዋጋውም ለሁሉ እንደሥራው ይሆናል:: ከዋጋዎቹ አንዱ በ2ኛተሰ. 1:6-7 ተጠቅሷል:: መልካም ላደረጉ ሽልማት ሲሆን ክፉ



ረጉ ደግሞ ቅጣት ይሆናል:: ዮሐ.5: 28-29:: ቅዱሳንን መከራ ያሳዩ ሁሉ ቱ ዓመታት መከራ ሲቀበሉ በሰማይ ደግሞ እግዚአብሔር ለልጆቹ ሠርግ ርጋል:: ይህ ሠርግ በዓይነቱ ልዩ ነው:: ልዩም የሚያደርገው ብዙ ርያት ስላሉት ነው:: ይኸውም 1. እግዚአብሔር የተመሰገነበት 2. ላቆችና ታናናሾች አምላክን እንዲያመሰግኑ ጥሪ የተደረገበት 3. በራዕይ 5 የተጠቀሱት ምናልባትም 24ቱ ሽማግሌዎች: 4ቱ እንስሳት: በቅድመ ከራና መንፈቀ መከራ (ከታላቁ መከራ) በክርስቶስ ደም ተዋጅተው በዙፋኑ ያ የተገኙት ታላቅ ሕዝብና ቅዱሳን መላዕክትም ጭምር ደስ የተሰኙበት ሆነ 4. ተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሱት ሁሉም ሐሴት ያደረጉበትና 5. ታችንና ከአምላካችን መንገስ ጋር የተያያዘ በመሆኑና 6. ክብር ለጌታ ዲቀርብ ጥያቄ የቀረበበት ትዕይንት በመሆኑ ነው:: ረዕይ 19: 7-10:: ህ ሠርግ ግን ተካፋይ ለመሆን የግድ በመነጠቅ ውስጥ ማለፍ ፈልጋል::

## . ሐሰተኛው ክርስቶስ (የአመጽ ሰው) እንዲመጣ በር ለመክፈት

በ2ኛተሰ. 2:7 እና በ1ኛዮሐ. 4:3 የሐሰተኛው ክርስቶስ ወይም ርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ በዓለም እንዳለና በግልጽ እንዳይሰራ አደናቃፊ ደተደረገበት ተገልጿል:: እስካሁን ድረስ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ራውን እያካሄደ ያለው በሚስጢር ነው:: ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ካይ ስላለ ነው:: ከልካዩም ቀደም ብሎ እንደተመለከትነው ቤተ ክርስቲያን ት:: መንፈስ ቅዱስ በመከራው ዘመን በምድር መኖሩን በክፍል ስድስት ራርቷል:: ስለዚህ የዓመጽ ሰው በግልጽ እንዳይሰራ ከብዙ ዓመታት ሮ የሚከለክለው ..የክርስቶስ አካል.. ነው:: በማቴ. 16:18 ላይ ንደተገለጸው ክርስቶስ ኢየሱስ ታላቅ ተጋድሎን ያቆመው በገሃነም ደጆችና ቤተ ክርስቲያን መካከል ነው:: ለዚህም ተጋድሎ በሐሥ. 1:8 እና 2:1-4፣ 3 እንደምናነበው ኃይል ሰጪው መንፈስ ቅዱስ ነው:: በ2ኛተሰ. 2:6-7 ንደተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን (የክርስቶስ አካል) ስትነጠቅ ሐሰተኛው ርስቶስ በር ስለሚከፈትለት ሥራውን በግልጽ ያከናውናል:: እስከአሁን

በተመለከትናቸው የመነጠቅ ዓላማዎች ውስጥ ዘጠኝ ያህል የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ተመልክተናል። እግዚአብሔር ማንኛውንም ሥራውን የሚፈጽመው በዕቅድ ነው። ዕቅዱንም በራሱ አሰራር ይፈጽመዋል። ጌታ ያዘጋጃቸውን የመነጠቅ ዓላማዎች በዝርዝር ስንመረምራቸው በሙሉ በሰው ሀይወት ላይ ያተኩሩ ናቸው። ቅዱሳኑን ከመከራ ለማዳን፣ ሰውን ለማሳረፍ ቦታ ማዘጋጀቱ፣ በበጉ ሠርግ ለማሳተፍ፣ በመንፈስ ነፍስና ሥጋ ሰውን ፍጹም ለማድረግ ማቀዱ ሌሎችንም ማመቻቸቱ እኛኑ ሐጢአተኞች የነበርነውን ሰዎች ከክፉ ለማዳንና ከፍ ለማድረግ ብሎ ነው።

እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ እጅግ ያፈቅራል፤ ይወድዳልም። የእግዚአብሔር ፍቅር ድፍንና አፋዊ ብቻ አይደለም። የተገለጸና በብዛት ደግሞ የሚገለጽ ነው። በምድራችን ላይ የሰው ልጅ በከፍተኛ ደረጃ አስቀምጦ ከሚጠቀምባቸው የከበሩ ዕንቁ ድንጋዮች ውስጥ ወርቅ፡ ብርና አልማዝ ጥቂቶቹ ናቸው። ይህም እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር ይገልጻል። ሆኖም ግን በራዕይ 21:10-21 የተጠቀሱት እንደ በሉር፣ ያክንት፣ ወራውሬ፣ አሜቴስጢኖስ፣ ክርስጵራስስ፣ ሰርዶንክስና ሌሎችም ከመነጠቅና በትንሳኤ በኋላ በሰማይ የተዘጋጁ ክቡር እንቁዎች የተለዩ ናቸው።

ማንኛውም ሰው ለዚህ ለከበረ ህይወት ራሱን እንደ እግዚአብሔር ቃል ሊያዘጋጅ ይገባል። የመነጠቅ ቀን ቀርቧል። ዳግም ልደትን ያላገኘ ቅዱሳንን ጠይቆ በስርዓት ቁጭ ብሎ ሊመሰክርለት ይገባል። ጌታን እንደ ግል አዳኙ የተቀበለ ማንኛውም ክርስቲያን ደግሞ በስርዓት ስለ መነጠቅ ሊያውቅና ለመነጠቅ የሚያበቃውንም ዝግጅት ሊያደርግ ይገባል። ኃይል በመስጠት ወደ እውነት ሁሉ ለመምራት ክብርንም ለማቀዳጀት ሙሉ ስልጣን ያለው የእግዚአብሔር ፀጋ ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን!



**ልዩ ትኩረት**

ልዩ ትኩረት ሲባል መነሳት ያለበትን አንድ መሰረታዊ እውነት ለማሳየት ነው። ይኸውም ለመነጠቅ ሲታሰብ ሌላ አደጋ ውስጥ ላለመግባት ጥንቃቄ ስለሚወሰድበት ጉዳይ ነው። የመነጠቅ ጉዳይ ሲነሳ ልብን በጣም ይሰቅላል። ያስናፍቃል። ቀኑም ቶሎ እንዲደርስና እንድንገባበት ሁኔታው ያስቸኩለናል። ከዚህም የተነሳ እንደ ተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ከአዕምሮአችን ቶሎ ልንናወጥና ወደ ባሰው አደናቃፊ ልምምድ ውስጥ እንዳንገባ ልንጠነቀቅ ይገባናል። መነጠቅ የሚሆነው ሁሉም በተሰማራበት ሳለ ማንም ሳያስበው በድንገትና በቅጽበተ ዐይን ነው። ስለሆነም ማንም የመነጠቅ ቀን በዚህና በዚያ ቀን ነው በማለት ነውጥና አደጋ መፍጠር እንደሌለበት በጥብቅ ይታሰብበት።

# ክፍል ዘጠኝ

## <u>ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች</u>

ከመነጠቅ በኋላ ስለሚፈጸሙ ትዕይንቶች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብዙ ነገሮች እንደሚሆኑ ማየት ይቻላል:: የድህረ-መነጠቅ ክንዋኔዎችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሰይተን እንመለከታለን:: እነርሱም፣

9.1. ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች በሰማይ

9.2. ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች በምድር ናቸው::

### <u>9.1. ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች በሰማይ</u>

በክፍል 6.2.1. ውስጥ ስለ ራዕይ መጽሐፍ አከፋፈል ተመልክተናል:: ከክፍልፋዮቹ ውስጥ ራዕይ 4 እና 5 በሰማይ ስለሚሆኑ ነገሮች የሚገልጽ ነው:: ይህ የራዕይ 4 እስከ 5 ትዕይንት የሚጀምረው በራዕይ 4:1 ላይ መነጠቅ ከሆነ በኋላ በሰማይ የሚፈጸመውን ሥርዓት በማገልጽ መልኩ ነው:: ሌሎችም የራዕይ ምዕራፎች የራዕይ አራትና አምስትን ትዕይንት የሚደግፉ አሉ::

### 9.1.1. <u>በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ</u>

የኋለኛው መለከት ተነፍቶ ያንቀላፉት ቅዱሳን ከተነሱ በኋላ በህይወት ያሉት ቅዱሳን ደግሞ በቅጽበተ ዓይን ተለውጠው ወደ ክርስቶስ ይቀርባሉ:: ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ከአብ የተቀበላቸውን የእግዚአሐር ልጆች በሙሉ ለእግዚአብሔር አብ ያቀርባል:: ዮሐ. 17:6-11፣ 6:37፣44:: እነዚህን ጥቅሶች ስናነብብ ሰዎችን ስለድነታቸው ለጌታ ኢየሱስ የሰጠ አብ ነው:: አብ ለጌታ እንደሰጠው፣ ጌታም በዘመኑ መጨረሻ በደሙ የዋጃቸውን እነዚህን የመንፈስ_በኩራት ያላቸውን ልጆቹን በአብ ፊት ያቀርባቸዋል:: ይህ ስርዓት ደግሞ በእግዚአብሔር ቅዱሳን መላዕክት ሁሉ እጅግ ሊታይ የሚናፈቅ ነው:: 1ኛጴጥ. 1:12፣ ሉቃስ 15:7 እና 10:: እስከ ዛሬ ድረስ ጌታ በደሙ የዋጃቸው ቅዱሳን እንኳን ለመላዕክት ይቅርና በዚህ በምድር ለሚኖሩ እንስሳትም ሆነ



ዎች የተገለጠ አይደለም:: ሮሜ 8:19-24:: በምድር ስለ ሰዎች መዳን መላዕክት ሪፖርት ይቀርብላቸዋል እንጂ የሚድኑትን ነፍሳት የዩአቸውም:: 1ኛጴጥ.1:12:: ሆኖም ከተወሰኑ መላዕክት ጋር ግዚአብሔር ዕቅድ የጥበቃ ግንኙነት ሊደረግ ይቻላል:: ቅዱሳን ግዚአብሔር ፊት እንደሚቀርቡ ከኤፌ. 5:27፣ ቆላ. 3:4 እና 1ኛተሰ.3:13 ይበልጥ መረዳት ይቻላል::

### 1.2. <u>የቅዱሳን በዘላለም ቅድስና መታተም</u>

ጌታ ኢየሱስና ቅዱሳን በአየር ላይ ተገናኝተው በተራ ቁጥር አንድ ንደተጠቀሰው በአብ ፊት ይቀርባሉ:: ከዚያም ወደፊት በኃጢአት ሊከሰሱና ወድቁ ወደማይችሉበት ህይወት ውስጥ ይገባሉ:: ይህንን ህይወት የሚያገኙ ከእግዚአብሔር ነው:: 1ኛተሰ. 3:13:: እዚህ ላይ ሊተኮርበት የሚገባ ውነት አለ:: ይኸውም በዳንኤል 9:24 ላይ ስለ አይሁዶች የተጠቀሰውን ውነት በተመለከተ ነው:: በዚህ ጥቅስ ላይ አይሁዶች ለባኛው ሱባኤ ካለቀ ኋላ ኃጢአታቸው ፈጽሞ ይቅር እንደሚባል በደል እንደማይቆጠርባቸውና ደ ዘላለም ቅድስና እንደሚገቡ ተጠቅሷል:: ይህ የሚሆነው ጌታ ለሺህ መት ለመንገስ ወደ ምድር ሊመጣ ሲል ነው:: የተነጠቁት ቅዱሳን ግን ዘላለም ቅድስና የሚታተሙት በሰማይ ነው:: (1ኛተሰ. 5:23)

### .1.3. <u>የተነጠቁ ቅዱሳን ፍርድ</u>

አንዳንድ አማኞች የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ይህ ፍርድ ሚሆነው በምድር ነው የሚል ሃሣብ ሲኖራቸው ይችላል:: ሆኖም ግን ይህ ምድሩን ፍርድ አያመለክትም:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የታወቁ ስባት ና ዋና የፍርድ ዓይነቶች አሉ:: እነርሱም፣

9.1.3.1. የአማኞች ኃጢአት በመስቀል ላይ መፈረድ ::ዮሐ. 12:31-32

9.1.3.2. የአማኞች ራሳቸውን መፍረድ/መመርመር፤ይህ በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከሚለሩት

9.1.3.3. ነገር አኳያ በእግዚአብሔር ቃል ራስን መበየን ነው::
1ኛቆሮ. 11:31-32:: የእስራኤል ፍርድ እስራኤላውያን ለረጅም ዘመናት በእግዚአብሔር ስቁቋስ ፍርድ አለ:: ሕዝ.20:33-44::

9.1.3.4. የመላዕክት ፍርድ ይህ በእግዚአብሔር ላይ ያመጹትን መላዕክት ይመለከታል:: 2ኛጴጥ.2:4፣ይሁዳ 1:6-7::

9.1.3.5. የተነጠቁ ቅዱሳን አማኞች ሥራ ፍርድ፤ ሮሜ. 14:10፤ 2ኛቆሮ.5:10-11፤1ኛ ቆር.3:11-15::

9.1.3.6. በምድር ያሉ መንግሥታት ፍርድ፤ይህ ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ በሺሁ ዓመት መንግሥት መጀመሪያ የሚሰጠው ፍርድ ነው:: ማቴ.25:31-46::

9.1.3.7. የሙታን ኃጢአተኞች ፍርድ፤ ይህ ከሺሁ ዓመት ፍጻሜ በኋላ ትንላኤ ሆኖ የሚከናወን ፍርድ ነው:: ራዕይ 20:11-15 ሮሜ 2:16፣ ሐሥ.17:31::

በተራ ቁጥር 5 ላይ እንደምንመለከተው የቅዱሳን አማኞች ፍርድ በሰማይ ይሆናል:: ከመነጠቅ በኋላ በሰማይ ከሚፈጸሙት ትዕይንቶች ውስጥ አንዱ ይህ ፍርድ ነው:: ፍርዱ ሽልማት የማያስገኝ ዓይነት እንጂ ከዘላለም ሕይወት የሚለይ አይደለም::

## 9.1.4. ወደተዘጋጀላው ስፍራ መወሰድ

ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 14ኛው ምዕራፍ ውስጥ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ተስፋ አለ:: ይህም ተስፋ ስፍራን ካዘጋጀ በኋላ በዚያ ቅዱሳኑን ማስቀመጡ ነው:: በዕብ. 11:10 ላይ ከተማይቱ መሠረት ያላት፣ እግዚአብሔር የሰራትና የፈጠራት እንደሆነች ተገልጿል:: በተጨማሪም ጌታን አምነው የሚከተሉ እውነተኛ አማኞች ሁሉ በዕብ. 13:14 እንደተጠቀሰው ሰማያዊቱን ከተማ ይናፍቃሉ:: ጌታም በተናገረው ቃልና በሰጠው ተስፋ መሠረት ቅዱሳኑን ወዳዘጋጀልን ስፍራ ይወስደናል:: ራዕይ 3:12፤ 1ኛቆሮ. 2:9::



## 9.1.5. በተዘጋጀላቸው ስፍራ መኖር

ይህ ሃሣብና በተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰው ተቀራራቢነት ያለው ቢመስልም ሁለቱ ልዩነት አላቸው:: መወሰድ ቀዳሚ ነገር ሲሆን ..መኖር.. ደግሞ ሌላ ተከታይ ጉዳይ ነው:: አሁን በዚህ በተረገመ ዓለም ስንኖር ሐዘን፣ ለቅሶ፣ ዋይታ፣ ረሃብ፣ ስቃይ፣ ጉስቁልና፣ ድካም፣ ድህነት፣ በሽታ፣ ደዌ፣ ሁከት፣ ማጭበርበር፣ ሽፍጥና ልዩ ልዩ እስራት ሰፍሮበት ይታያል:: በተዘጋጀልን ስፍራ መኖር ማለት ግን ከበጐ ተቃራኒ ሁሉ ተለይቶ በደስታ፣ በሰላምና በአስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ብልጽግና በመሞላት መቀመጥ ነው::በ1ኛ ቆሮ. 2:9፣ ..ነገር ግን ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ... የተባለው ቃል ተፈጻሚነት ከሚያገኝባቸው ቦታዎች አንዱ በሰማይ ነው:: ይህ ቃል በከፊል ተፈጻሚነት ቢያገኝም በዘላለም ሕይወት የሚፈጸሙ ግን ሌሎች ብዙ ተስፋዎች ገና ይቀራሉ:: ዮሐ.14:1-3::

## 9.1.6. ቋሚ አምልኮ ማካሄድ

የቅዱሳን መነጠቅ ከሆነ በኋላ በሰማይ ከሚፈጸሙ ነገሮች ውስጥ አንደኛውና ትልቁ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ አምልኮ ማድረግ ነው:: የአምልኮው ፕሮግራም ከሚገለጽባቸው መንገዶች ውስጥ መዝሙር መዘመር፣ ለእግዚአብሔር መስገድ፣ ክብር ውዳሴና ምስጋናን ማቅረብና ወዘተ ይገኛሉ::ራዕይ 4:10-11፤ 5:14፤ 7:9-17፤ 19:1-9::

## 9.1.7. የጌታን እራት ስርዓት ማከናወን

ይህ ሥርዓት ጌታ ኢየሱስ እስኪመጣ ቅዱሳኑ በምድር እንጠብቀዋለን::1ኛቆሮ. 11:23-26:: ጌታ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ የሰማያዊ ስርዓት ፈቃድ ደግሞ ለዘላለም ይታሰባል:: ይህንንም ከማቴ. 26:29፤ ማር. 14:25፤ ሉቃስ 22:18 እና 30 መመልከት ይቻላል::

### 9.1.8. የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በሰማይ መከፈት

በራዕይ 11:19 ላይ በሰማይ ቤተ መቅደስ ሲከፈት ይታያል:: የዚህ ቤተ መቅደስ መከፈት በራዕይ 4:1 ካለው የሰማይ ደጅ መከፈት ጋር ተቀራራቢነት አለው:: በዚህ ክፍል በዕብ. 8:5 እና 9:23 የተጠቀሰውም የታቦቱ ሁኔታም ተጠቅሷል:: እግዚአብሔር ብዙ ታላላቅ ነገሮቹን የሚፈጽመው ከቤተ መቅደሱ ሆኖ ነው::

### 9.1.8. የቅዱሳን በበጉ ሠርግ ስርዓት መካፈል

ይህ ሠርግ ታሪኩ በራዕይ 19:1-9 ተጠቅሷል:: በዚህ ሠርግ ተካፋይ የሚሆኑት በቁጥር 7 ላይ ..የበጉ ሚስት.. በሚል መጠሪያ የተጠቀሱት ..ቅዱሳን.. ናቸው:: ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጐናጸፍ ተሰጥቷታልና ይላል:: ይህም ቀጭን የተልባ እግር ልብስ የቅዱሳንን የጽድቅ ሥራ ካመለከተ ቅዱሳን የሚባሉት በ5ቱ የመነጠቅ ዓይነቶች አልፈው በሰማይ የተከማቹ ከትንሳኤ በኋላ በተዘጋጀላቸው ስፍራ የኖሩ እውነተኛ አማኞች ናቸው::

ሌሎች ስለ በጉ ሚስት የሚጠቅሱት ሃሣብ አለ:: የበጉ ሚስት ቤተ ክርስቲያን ናት፣ እስራኤል ናት የሚሉ አሉ:: ሆኖም ግን ይህ አመለካከት ለብቻው እውነት አይሆንም:: ሁለቱም ክፍሎች በበጉ ሚስት ውስጥ ይካተታሉ:: በራዕይ 19:8 ላይ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ የተሰጣቸው በቁጥር 14 ደግሞ እነዚያው ጌታን ተከትለው ወደ ምድር ሲመለሱ ያሳያል:: በትንሳኤና በመነጠቅ ሥርዐት ያለፉ ቅዱሳን ናቸው ማለት ነው::

### 9.1.9. ወደ ምድር ለመመለስና የመጨረሻውን ጦርነት ለመዋጋት መዘጋጀት

በራዕይ 19 የበጉን ሠርግ ከፈጸሙ በኋላ የሚቀጥለው ደረጃ የአርማጌዶንን ጦነት ከመሪያችን ከጌታ ኢየሱስ ጋር ሆነን የምድርን ነገስታት ለመዋጋት መዘጋጀት ነው:: በራዕይ 19:11 ላይ ጌታ ኢየሱስ ተዋጊ



እንደሆነ፣ በራዕይ 17:14 ደግሞ ከእርሱ ጋር ያለን የታመነን፣ የተመረጥን፣ የተጠራን ደግሞ እንደምንዋጋ ይናገራል:: በዘካርያስ 14:5 ላይ ጌታ ከቅዱሳኑ ጋር እንደሚመጣ ይናገራል:: በተጨማሪም ራዕይ 19:11-21 በዝርዝር መመልከት ይቻላል:: በዚህ ጦርነት አሸናፊው ጌታ ኢየሱስና ቅዱሳኑ ይሆናሉ:: በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ጦርነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚሆን ነው:: ይህ ጦርነት በነቢዩ ኢሳይያስና (2:2-4) ሚክያስ (4:1-5) የተነገረው ጦርነት ነው:: ጦርነቱ አህዛብ ሰይፋቸውን ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ የሚቀጠቅጡበት ነው:: በኢዩኤል 3:9-10 ላይ የዓለም መንግስታት ለጦርነት ዝግጅት እያደረጉ ያሉበት ጊዜ ነበር:: ሆኖም ግን ክርስቶስ ኢየሱስ በአርማጌዶን ጦርነት አሸናፊነቱ ከተረጋገጠና ሁሉም መሸነፉን ካወቀ በኋላ ሁሉም ለክርስቶስ ተገዢ ይሆናል ማለት ነው:: ሦስተኛው የዓለም ጦርነት ማለት ይህ ነው:: <u>3ኛው የዓለም ጦርነት እዚህ ላይ ያበቃል::</u> የዓለም መንግሥታት ከ130 ዓመታት በላይ በኢንተርናሲዮናል መዝሙር አማካይነት የፍጻሜው ጦርነት ነው ሁሉም ዘብ ይቁም በቦታው በማለት ሲዘምሩትና ሲናፍቁት የነበረው ጦርነት እዚህ ላይ ይፈጸማል:: የምድር ትዕቢተኞችም ዕድል ፈንታ በራዕይ 14:20 እና 19:17-21 እንደተጠቀሰው ደማቸው እስከ 1600 ምዕራፍ ወይም 320 ኪሎ ሜትር በመፍሰስና ሥጋቸውም ለምድር ዐራዊትና ለሰማይ አዕዋፋት በመሰጠት ይሆናል:: ፍጻሜ የሚያገኙት እነዚህ የአርማጌዶን ጦርነት ተሳታፊዎች ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ እንቅሳቃሽ ክፉ መላዕክቶቻቸውና ሰይጣን ናቸው:: ራዕይ 20:1-4:: ታዲያ ዛሬ በምድራችን ያሉ ልዩ ልዩ ዘማናዊ የጨረር፣ የኑክለርና የኮምፒዩተር የጦር መሳሪያ ያላቸው የጦር ሐይሎች ካላቸው የጦር ሐይልና ከትምክህታቸው የተነሳ ንስሐ የሚገቡ ይመስላል? አሁን በምድሪቱ ላይ ያሉ የጦር ሰራዊቶች ካላቸው የጦር መሳሪያ ጋር የመጨረሻ ዕድላቸው በራዕይ 16:15 ላይ እንደተጠቀሰው ማፈር ብቻ ነው:: አይገርምም?!

የቤተ ክርስቲያንና የመከራው ዘመን ቅዱሳን መነጠቅ ከሆነ በኋላ በሰማይ ከሚፈጸሙት ዐበይት ትዕይንቶች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ተሞክሮአል:: ጌታ ኢየሱስ ጌታ ነው:: እርሱ የፍቅር ጌታ ነው:: ጌታ ኢየሱስ እንደ ሰይጣን ራሱን ሸፍኖ አልኖረም:: ለሰው ልጆች ጥንቃቄና ዝግጅት የሚያስፈልገውን ነገር ራሱ ወደ ምድር በመምጣት በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ ሆኖ አስተምሯል:: ደቀ መዛሙርቱን አሰልጥኖ እውነትን ገልጿል:: በተጨማሪም ከሰማይ እውነተኛ አጽናኝ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ልኳል:: በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ሰውን ፈጽሞ አልበደለውም:: ምንም አልጐዳውም:: ሰው ግን አላወቀም:: ወዴት መጠጋት፣ እንዴት መጠጋትና ተጣብቆ መኖር እንዳለበት ባለመረዳቱ የማያስፈልግ ብዙ ነገሮችን ያዘ::ጉዳቱም እጅግ የከፋ ሆነ::

## 9.2. ድህረ-መነጠቅ ሁነቶች በምድር

ስለ ድህረ- መነጠቅ ክንዋኔዎች በምድር ስናስብ በቀጥታ ከራዕይ ምዕራፍ 6-19 ያለውን የመከራ ዘመንና በውስጡም የሚያልፈውን የእግዚአብሔር ምህረት ለመጠቆም እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል:: የዚህ የመከራ ዘመን ምንነት ወደፊት በዝርዝር ይቀርባል:: ሆኖም አንዳንድ በአቀራረባቸው ለየት ያለ መልክ ያላቸውን ዋና ዋና ነገሮች ማንሳቱ ጠቃሚ ነው:: የራዕይን መጽሐፍ ትንታኔ ስንመለከት የመከራውን ዘመን ልብ እንላለን:: ልክ አውሬው በራዕይ 6:2 ላይ እንደተለቀቀ ሰባቱ ማህተሞች ሲፈቱ የመከራው ዘመን ይቀጥላል:: መከራው የሚፈጸመው በሶስት ዋና ዋና መንገዶች ማለትም በ7ቱ ማህተሞች፤ በ7ቱ መለከቶችና በ7ቱ ጽዋዎች እንዲሁም በሌሎች ልዩ ልዩ መቅሰፍቶች አማካይነት ነው:: ይህ ጊዜ የሰዎች ሁሉ ትምክህት የሚመታበት ጊዜ ነው:: ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን ውሖች፤ ውቅያኖሶች፤ተክሎችና የተፈጥሮ ጥቅማጥቅሞች በሲሶ ደረጃ የሚመቱበት ጊዜ ይሆናል::



ውድ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠርክ ሰው ሆይ! ጠንክር በል! አስተውል! ዛሬ እያብለጨለጨ ያለው ውብ መሳይ ሁሉ አንድ ቀን ወይ ጥለኸው ወይም ደግሞ እንደ ፓኪስታኑና እንደ አሜሪካው የምድር ነውጥና የጎርፍ መጥለቅለቅ ጥሎህ ይሄዳል:: ነገርን መርምር፣ እውነትን ያዝ፣ በዚያም ጽና:: ምንም ቢሆን ምን የእውነተኛው መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ይፈጸማል:: የዓለም ፍጻሜ በፊትህ ቀርቧል:: በራስህ ጥረት ከፍርድ ማምለጥ አትችልም:: መናቅ የትዕቢት ምልክት ነው:: ትክክል የሆነውን የምትሰማውን ዕውነት ያዝ፤ የያዝከውን ደግሞ አትልቀቅ:: በአሁኑ ጊዜ ብዙ መጻሕፍት ዋጋ አጥተዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ብዙ መከራና ስደት ደርሶበት: የብዙ አሉታዊ የሂስ መደሻዎችን ሰባብሮ ለሰው ልጆች ድነት እዚህ አለ:: አልጠፋም፤ አይጠፋምም:: ምክንያቱም የኋላ ደጀኑና ጠባቂው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው:: እውነት ነው:: እውነቱን ያዘው ያከብርሃል:: ሊያዋርድህ ከተዘጋጀውም ምናምንቴ ያላቅቅሃል:: የክርስቶስ መስካሪው መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ ይምራህ:: አሜን!

# ክፍል አሥር

## ለመነጠቅ መሟላት ያለባቸው ልምምዶች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገለጸልን እውነቶች ውስጥ መንፈሴንና ነፍሴን በሐሴት የሚሞላ ቃል (ንግግር) አለ:: ይኸውም፤

በሉቃስ 21:14 ... *በልባችሁ አኑሩት..* በቁጥር 28 ..ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቧልና *አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሱ..*፣ ቁጥር 34 ላይ ደግሞ ..... *ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ..*፣ ቁጥር 36 ላይም ..... በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ *ስትፀልዩ ትጉ..*፣ በማር. 13:23ና በማቴ.24:25 ደግሞ *..እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ አስቀድሜ ሁሉን ነገርኳችሁ..* የተሰኙት የጌታ የፍቅር ማስጠንቀቂያዎች ናቸው:: ጌታ ለሚያምኑበት ሁሉ እውነተኛ የሆነ ያልተለበጠ ፍቅር አለው:: ፍቅሩ ፍጹም ስለሆነ ማንም ሰው ከአእምሯዊና መንፈሳዊ ጽልመት (አለማወቅ) የተነሳ እንዲጐዳ አይፈልግም:: ከዚህም የተነሳ የወደፊቱን ክፉ ነገር መምጣት ገልጾ ከዚያም ሊዳን የሚቻልበትን ዘዴ ሁሉ አዘጋጅቷል:: ደጋግሞም አስጠንቅቆአል::

ጌታ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ይፈልጋል:: ከዚህም በመነሳት ከክፉ ሊድኑ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ሁሉ በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ በኩል አመቻችቷል:: ጌታ ኢየሱስ ስፍራ ሊያዘጋጅልን ሲሄድ ለተዘጋጀልን ቦታ ብቁዎች የምንሆንበትንም መንገዶች ጠቁሞናል (አመልክቶናል):: ጌታ ብቻ ሳይሆን የምጽዐቱና የዓለም ፍጻሜ እውነተኛ ምስክሮችም አጠንክረው አስተምረዋል::

የኋለኛው መለከት በሚነፋት ጊዜ ሙታን ሲነሱና ህያዋንም ሊለወጡ ለመነጠቅና ጌታን በአየር ለመቀበል ወደ እረፍት ስፍራችንም ለመሄድ እያንዳንዱ ቅዱስ አማኝ ሊያሟላቸው ወይም ህይወቱን ሊመረምርባቸው የሚገቡ እውነቶች የሚከተሉት ናቸው::



አንድ አማኝ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነና በመነጠቅ የዘላለሙን ሕይወት ለማግኘት ከፈለገ ለመነጠቅ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በጥንቃቄና በማስተዋል ሊከታተልና ሊኖር ይገባዋል::

### 10.1. የክርስቶስ ኢየሱስ መሆን

ጌታ ኢየሱስም ሆነ ደቀመዛሙርቱ በዚህ ዓለም በምድር ላይ ሲኖር ሁለት ዓይነት ልጆች እንዳሉ ተናግረዋል:: እነርሱም የእግዚአብሔርና የዲያብሎስ ናቸው:: ዮሐ. 8:38፣ 41፣ 44 እና ሐዋርያው ዮሐንስም እንደገለጸው በ1ኛዮሐ. 3:10 ላይ የተጻፉት ናቸው:: የክርስቶስ መሆን ማለት ልክ ጌታ በቃሉ እንዳስተማረው በሐዋርያቱም እንደተጻፈው በትክክለኛው መንገድ፣ ውሸት ባልተደባለቀበት እውነት ገብቶ በዘላለማዊው ህይወት በክርስቶስ ኢየሱስ መኖር ነው:: ህይወት ክርስቶስ ነው:: ህይወት ወይም በክርስቶስ መሆን ማለት በዮሐ. 8 እንደተጠቀሰው የራስን ፍላጐት ለማጽናት ጌታንና የእርሱን እውነት (መንገድ) ተከታዮች ሸንጥን ገትሮ መከራከር አይደለም:: የክርስቶስ ኢየሱስ መሆን ማለት ከአስመሳይነት ህይወት መውጣት ነው::

በ1ኛቆሮ. 15:20-23 እንደተጠቀሰው የመጀመሪያው ትንሳኤ ባለቤት (ተካፋይ) የሚሆኑት ጌታን አምነው ያንቀላፉ (የሞቱ) ብቻ ናቸው:: መነጠቅም የሚሆነው ከትንሳኤ በኋላ ወዲያው ነው:: ለመነጠቅ በመንፈስ ቅዱስና በእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆኑ ማንኛውም አማኝ ነኝ ባይ በቂ (ያረፈ) የልብ ምስክርነት ሊኖረው ይገባል ይህም ደግሞ ስም ብቻ ከመሆን የተለየ ህይወትንና የእግዚአብሔር ልጅነትን ይጠቀልላል::ገላ. 5:24፣ ዮሐ. 1:12-13::

### 10.2. በክርስቶስ ኢየሱስ ብርሃን መጓዝ

ጌታ ኢየሱስ የዓለም ብርሃን ነው:: በዮሐ. 1:4-5፣ 8:12፣ 9:5 እና 12:35-46 ስንመለከት ጌታ ..እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ.. ሊል ህይወቱ፣ ንግግሩ፣

ትምህርቱ፣ ፍቅሩ፣ ጥበቡ፣ ርህራሄው፣ ባጠቃላይ ተግባሩ ሁሉ ትክክለኛና እውነተኛ ምንም ዓይነት ነውር የሌለበት መሆኑን ሊያመለክት ነው:: ብርሃን የጽድቅና የእውነት ምሳሌ ሲሆን ጭለማ ደግሞ የኃጢአትና የርኩሰት ምሳሌ (መግለጫ) ነው:: በብርሃን መመላለስ (መኀዝ) ማለት ከክርስቶስ ጋር በኅብረት መኀዝ ማለት ነው:: ይህ ኅብረት ደግሞ ፈጽሞ ጌታን መምሰል ይኖርበታል:: 1ኛዮሐ. 1:5-7 ስንመለከት .....ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን፣ እውነትንም አናደርግም::.. ማለቱ እውነተኛ አማኝ ኃጢአትን አይሰራም ማለቱ ነው:: በተጨማሪም በ1ኛዮሐ. 2:8-11 በአጠገብ ያለውን ጐረቤት፣ የሥጋ ዘመድንም ሆነ ባዕድ የሆነውን በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ሰው መጥላት ነፍስ ገዳይነትና፣ በጨለማ መመላለስም እንደሆነ ይገልጻል:: ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 5:14 ላይ ..እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ::.. ሲል ከእኔ የተቀበላችሁትን በመንፈስ ቅዱስ የሆነውን የጽድቅ ሥራ በኃጢአት ለሚኖሩ (ዓለማውያን) ትገልጻላችሁ ማለቱ ነው:: ይህ ንግግሩ ግን እኔ የእግዚአብሔር ልጅ እናንተም የእግዚአብሔር ልጆች፤ እኔ አምላክ እናንተም አምላክ ናችሁ ማለቱ አይደለም:: በብርሃን መመላለስ ማለት ጌታ ባስተማረው የህይወት ኑሮ፣ (ዮሐ. 14:6) እርሱን መስሎ መኀዝ ማለት ነው:: ቆላ. 2:6::

ታዲያ እነዚህ ራሳቸውን በቤተ ክርስቲያን ክልል በክርስቶስ ወዳጅነትና በብርሃን መስመር እንደሚኀዙ አጥብቀው የሚያስተምሩ፣ ነገር ግን በስውር የክርስቶስን ደቀ መዛሙርት የሚያሳድዱ የሚገድሉና የሚያስገድሉ ምን ይባላሉ? ለመሆኑ ጌታ ኢየሱስ ሰው ጥሉ፣ አስወግሩ፣ በቀል የእናንተ ነው፣ ብድራቱን ክፈሉ፣ ክፉን በክፉ አሸንፉ ብሏል? ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች አሁን እንነጠቃለን ብለው ያስባሉ ወይስ ያምናሉ? ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልወጣ/ያልተገኘ እምነት ከየት ይሆን? እንግዲህ ራሳችሁን መርምሩ:: ራሳችሁን አታስቱ:: በብርሃን የማይመላለስ፣ በ1ኛቆሮ. 11:1 እንደተጠቀሰው ልክ የጌታን ህይወት መስሎ የማይኖር ፈጽሞ አይነጠቅም:: መነጠቅ በኃይለ-ቃልና ኮስተር ባለ ፊት በነጐድጓድ ድምጽ ..እነጠቃለሁ! በሚል ኀይለኛ



ንግግርና ምኞት አይገኝም:: መነጠቅ በመፈክር አይደረስበትም:: የቆምህ መስሎህ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ::

## 10.3. <u>በመንፈስ መኖርና መመላለስ</u>

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሁለት ሃሣቦች አሉ:: እነርሱም፣ በመንፈስ መኖርና በመንፈስ መመላሰስ (መኀዝ) ናቸው::

በመንፈስ መኖር ማለት ከኃጢአት በክርስቶስ ደም የሚያነጻውን፣ የህይወት መንፈስ የሆነውን ከጌታ መቀበልና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለት ነው:: አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቅ በመንፈስ ይኖራል ማለት ነው:: ለዚህም አማኙ ሊኖርባቸው የሚገቡ ብዙ የህይወት ልምምዶች አሉ::

በመንፈስ መመላለስ ማለት በሮሜ 8:14 እንደተጠቀሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት በማግኘት መኀዝ ማለት ነው:: አንድ ሰው ጌታን እንደግል መድኃኒቱ ሲቀበል የእግዚአብሔር ልጅ የሚያደርገውን መንፈስ ቅዱስ ያገኛል:: ለዘላለም በውስጡ በሚኖረውም መንፈስ አማካይነት በገላ. 5:22-23 የተጠቀሱትንና ሌሎችንም የመንፈስ ፍሬዎች ያፈራል:: ከእነዚህም ፍሬዎች ውስጥ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም (ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ወዳጅነት እንዲኖረው የሚረዱት)፤ ትዕግስት፣ ቸርነትና በጐነት ደግሞ (ከሰውና ከፍጥረታት ጋር የጠበቀ ጤናማ ግንኙነት እንዲኖረው የሚረዱት)፣ እምነት የዋህነትና ራስን መግዛት ደግሞ (ከራሱ ጋር ትክክለኛ ሕብረት እንዲኖረው የሚረዱት) የመሳሰሉትም ይገኛሉ::

በመንፈስ መመላለስ ማለት ከመንፈስ ቅዱስ በሚገኙ ከእግዚአብሔር ጋር በማይጋጩ ባህርያት መኀዝ ማለት ነው:: ሰው ሦስትነት አለው:: ይህም በ1ኛተሰ. 5:23፣ በዕብ. 4:12 እና በዘፍ.2:7 ላይ ተገልጿል:: ሰው መንፈስ ነፍስና ሥጋ አለው:: እግዚአብሔር ሰውን ለምን እንዲህ ፈጠረው? በሦስትነት የተፈጠረበት ምክንያት ሰው በመንፈሱ ከመንፈሳዊው ዓለም በተለይ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝ፤ በነፍሱ የአእምሮን፣

የማውጠንጠንን፣ የስሜትና የፊቃድ ሥራዎችን እንዲለራና ሥጋው ደግሞ ከውጫዊው ዓለም ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ ነው:: ለመሆኑ እግዚአብሔር በመንፈስህ በኩል በቅዱስ መንፈሱ ተራክቦ (ህብረት) ሲያደርግ ትረዳለህ (ጃለሽ)? ለክንቱ ጉዳይ መንፈስ አልተለጠንምና ተጠንቅቀን መንፈስ ቅዱስ ሲናገረን አዳምጠን ልንታዘዝ ይጠበቅብናል::

## 10.4. ብጹዕና ቅዱስ መሆን ያሻል

ብጹዕ ማለት የተባረከ፣ የተመረቀ፣ እጅግ ደስተኛ የሆነ የሐሴት ሰው ማለት ነው:: ቅዱ ማለት ደግሞ ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚያምን የሚኖር፣ ከኃጢአት የራቀ፣ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ እንደተባለ የሚኖር ማለት ነው:: ማንኛውም ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኙ አድርጐ የተቀበለ ሁሉ በቅድስናና በንጽሕና ሲኖር ይገባዋል::

ብዙ አማኞች በቅድስና መኖር አይቻልም ይላሉ:: ሆኖም ግን ይህ የኃጢአተኞች ወይም የክርስቲያን መሳይ ሰዎች ጩኸት፣ የስጋውያን ልፋፌ ነው:: ከእግዚአብሔር ቃል አኳያ ቅዱስ መሆን ይቻላል:: ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 17:17 ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው፣ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ ሲል፤ ጴጥሮስም በ1ኛ ጴጥ. 1:16 ስለ ቅድስና ሲናገሩ ለማስመሰል አልገለጹትም:: ስለሆነም ከትንሳኤ በኋላ የመነጠቅን ህይወት ለማየት ብጹዕና ቅዱስ መሆን ያሻል:: ለሚያምን ደግሞ ሁሉ ይቻላልና:: ራዕይ 20:4-6፣ ማር. 9:23::

## 10.5. በክርስቶስ ኢየሱስ መሆን

ይህ ሃሣብ በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ..የክርስቶስ መሆን.. ትንሽ ይለያል:: የመጀመሪያው ከሰይጣን ልጅነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት መለወጥ ሲሆን ይህ ግን ወደ እግዚአብሔር ከመጡ በኋላ ወደ ዓለም ላይመለሱ ጌታንም ሳይክዱ በጌታ ኢየሱስ እቅፍ እስከ መጨረሻ ጸንቶ መቆምን የሚያመለክት ነው:: ይህም እውነት በ2ኛቆሮ.5:17-18 ተጠቅሷል::



ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ይላልና:: አንዳንድ ክርስቲያኖች ጌታን ከተቀበሉ በኋላ እስከ መጨረሻ ጌታን በመታዘዝ የመትጋታቸውን ጉዳይ ቸል ይሉታል:: ውጤቱም ህይወታቸው ወደ ቀድሞው መመለስ ነው:: አንዳንዶች ደግሞ ..እኔን ጌታ ኢየሱስ በህይወት መጽሐፍ ስሜን ከጻፈ በኋላ ብዕር አንስቶ ስሜን የሚሰርዝ ሕጻን አይደለም:: ጌታ የዚህን ያህል ፈጽሞ ጨካኝ አይደለም በሚል ከንቱ ምኞት አንጻ ተጽፌአለሁ በማለት የኃጢአት ወዳጆችና እስረኞች ከሆኑ ዋል አደር ብለዋል:: ቃሉ ግን የሚለው እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል ነው::

## 10.6. ያለ ማቋረጥ መትጋት ያስፈልጋል

በምሳሌ 12:27 ላይ ..ታካች ሰው አደን ምንም አያድንም ለሰው የከበረ ህብት ትጋት ነው.. ይላል:: ሰው በመንፈሳዊውም ሆነ በቁሳዊው መስክ ተሰማርቶ በደንብ ቢተጋ የልቡን መሻት ከእግዚአብሔር ያገኛል:: የትጋት ዋነኛ አስፈላጊነቱ የያዙትንና ያልጨበጡትን መልካም ነገር አጥብቆ ለመያዝ፣ የማያስፈልገውንም ለማራቅ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ስለ ትጋት ስናስብ ትኩረት ልንሰጥበት የሚገባው አቅጣጫ፣

- 10.6.1. መመረጥንና መጠራትን ከማጽናት አኳያ
- 10.6.2. ሲመጣ ካለው ክፉ ከማምለጥ አኳያ
- 10.6.3. መንፈስ ቅዱስን ካለማሳዘን አንጻር
- 10.6.4. በፀሎት ከመጠንከር አኳያ
- 10.6.5. የጌታን ምጽዐት ከመጠበቅና ፊቱ ከመቆም አንጻር
- 10.6.6. ሙሉ ደመወዝን ከማግኘት አኳያ
- 10.6.7. የእግዚአብሔርን እውነት (በተቀበሉት መክሊት ከመነገድ-ካለመቀበር) ከማካፈል አንጻር
- 10.6.8. ሥራ ፈትና ፍሬቢስ ካለመሆንና ከሌሎችም እውነቶች አኳያ ናቸው:: ሉቃ. 21:34-36፤ 1ኛጴጥ. 5:8::

## 10.7. መልካም መሆንና ማድረግ

በሮሜ 12:9፣ 14-21፣ 1ኛጴጥ. 3:10-12ትን በተጨማሪም ዮ
5:28-29ን ስናነብ ጌታ ምን ያህል ክፉ ነገርን እንደሚጠላ ያሳየናል:: ክ
የሆነውን እንደ ልዩ ርኩስ ነገር ተጸይፈን ከመልካሙ ነገር ጋር መጣ
ይኖርብናል:: ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ...መልካም ያደረ
ለህይወት ትንሳኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሳኤ ይወጣሉና... ሲል ክ
መስራት ሰውን ምን ያህል ለዘላለም ጥፋት የማዘጋጀት ኃይል እንዳለ
በግልጽ መረዳት ይቻላል::

በአሁኑ ወቅት በዓለማችን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ረሃብተኞች
የተራቆቱ፣ ህመምተኞች ... እያሉ እግዚአብሔር ፀሐይና ዝናብ ሰጥቶ ምድ
ያበቀለችውን እህል ወደ ባህር ማፍሰስና በየማከማቻው አበስብሶ ማቃጠ
እንዴት ያለ ታላቅ ክፋት ይሆን? ሆኖም በፍርድ ቀን ምላሽ ይሰጡበታል
ለሌላው ማካፈል መልካም ከመሆን የሚገኝ (የሚመነጭ) መልካም (በ
ተግባር ነው:: ህይወታችንን ስናየው ምን ያህል ስውርና ግልጽ የሆነ ክፋ
አለበት? መልካምነት ከችግር የተነሳ ርቆን ይሆን?

## 10.8. ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ መሆን ያሻል

ጌታ ኢየሱስ የሚመጣው በኤፌ. 5:27፣ 1ኛዮሐ. 3:2
እንደተጠቀሰው ያለ ነውርና ነቀፋ ያሉትን እድፈትና የፊት መጨማደ
የሌለባቸውን ልጆቹን ሊወስድ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ንጹህ ነው:: ንጹህ (ቅዱ
የሆነውን) ለማየት ዘወትር ንስሃ መግባት ያስፈልጋል:: ከድካም የተ
ዘወትር ኃጢአት ውስጥ ከመዘፈቅና ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ በፍርሃት
በመንቀጥቀጥ በንስሃና በቃሉ በፀሎት ወደ በሰጠው ፈተና ሳለመግባ
መታጠብ እጅግ ይጠቅማል::



## 10.9 በቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ መግባት ያሻል፤

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ሁለት ዓይነት ቤተ ክርስቲያናት ተጠቅሰዋል:: እነርሱም፣ እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያንና ጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን ናቸው::

### 10.9.1. እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን

ይህች ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው እንደ ህይወታቸው መሪና አዳኝ አድርገው ጌታ ኢየሱስን የተቀበሉ ዘወትር በንጽህናና በቅድስና እንደ ቃሉ የሚኖሩ ቅዱሳን የተከማቹበት ናት:: የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባላት በሁለት ስፍራ ማለትም በምድርና በሰማይ (በጻድቃን መንፈሶች ጉባኤ) ይገኛሉ:: ይህች ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም የህይወቷ እንቅስቃሴ ጌታን የሚመስሉ አባላትን ትይዛለች:: በክርስቶስ ደም የተዋጁ ናቸው፤ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁም ናቸው:: የሰማይ ርስት መያዣም አላቸው:: ይህም መንፈስ ቅዱስ ነው:: ማንኛውም የክርስቶስ ነኝ የሚል ሁሉ ሆኖም በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቀ የእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ክፍል ወይም የክርስቶስ አካል መሆን አይችልም:: ቆላ. 1:18፣ 1ኛቆሮ. 12:13፣ ኤፌ. 1:13-14 ስንመለከት የሰማዩ ርስታችን መያዣ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ መታተም ነው:: ይህም መታተም ሰው ጌታን ሲቀበልና በላዩ ያለው ኃጢአት በጌታ ኢየሱስ ደም በመንፈስ ቅዱስ አሰራር ነጽቶ ስሙ በህይወት መጽሐፍ ሲጻፍ ነው:: ኤፌ. 1:20-23:: ስለመነጠቅ በመንፈስ ቅዱስና በእውነተኛው ቃሉ አማካይነት የክርስቶስ አካል በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ መግባት ያስፈልጋል::

### 10.9.2.. ጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን

ጋለሞታ ማለት ባሏን ቤት አስቀምጣ ከሌላ ወንድ ጋር የምታመነዝር ሴት ማለት ነው:: እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ግን ከአንዱ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ..ባልሽ ፈጣሪሽ ነው.. እንደተባለ የምትጣበቅ ናት:: ከኢየሱስ ሌላ ማንም

በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ፈጽሞ አይስለጥንባትም:: የጋለሞታ[illegible] ቤተ ክርስቲያን መሪና አንቀሳቃሽ የጥፋት ልጅ የሆነው ሐሰተኛው ክርስ[illegible] ነው:: ይህች ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካውም በሐይማኖቱም ቁልፍ የሆነ[illegible] ስፍራ ትይዛለች:: ህይወቷ በሙሉ ከዓለማዊ ኑሮ አይለይም:: የሃይማኖ[illegible] ስርዓቷ ገንዘብ ለማግኘትና የራሷን የገነነ ስም ለማስጠራት ነው:: ከአለ[illegible] መንግሥት ስደትና መከራ እንዲደርስባት ፈጽሞ አትሻም:: ባለማወቅ ይ[illegible] በማወቅ ከገዢዎች፣ ከአለቆችና ከባለሥልጣናት ጋር ወዳጅነቷ የጠነ[illegible] ነው:: በማንኛውም ሁኔታ መገፋትን አትፈልግም:: ክብሯ: ማዕረጓና ጤን[illegible] እንዲጠበቅ ትናፍቃለች:: የነፍሳት መዳን፣ የዘላለምን ህይወት መው[illegible] ተቀዳሚ ተግባሯ አይደለም:: በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የቆሙት[illegible] የሚጓዙትን ከዓለማዊ መንግስት ጋር በመተባበር ያለ በቂ ምክንያትና ማስ[illegible] ታሳድዳለች፣ ትይዛለች፣ ትወግርና ትገድላለች::ዘርዘር ባለ መል[illegible] የጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ባህርይ በራዕይ 17 ውስጥ በግል[illegible] ተቀምጧል::

10.9.2.1. በመጨረሻ ዘመን አብዛኛው ህዝብ በዚች ቤተ ክርስቲያን አባ[illegible] ናቸው:: ቁጥር 1፣ 15::

10.9.2.2. የምድር ነገስታትና ነዋሪዎቹም ወዳጆቿ ናቸው፤ ቁጥር 2::

10.9.2.3. በራዕይ 13:5-7 እንደተጠቀሰው እግዚአብሔርንና መላዕክትን ወዘ[illegible] የሚሳደበው አውሬ ወይም ሐሰተኛው ክርስቶስ መሪ ና[illegible] (በሐይማኖት ጉዳይ) ቁጥር 3::

10.9.2.4. በብዙ አቅጣጫ የራሷን ክብርና መቀማጠል ፈላጊ ናት፤ቁጥር 3-4::

10.9.2.5. ስሟ ነው እንጂ ..የእግዚአብሔር ተከታይ.. ኑሮዋ በሙሉ በርኩሰትና አጸያፊ ነገር የተሞላ ነው:: ቁጥር 5-7::

10.9.2.6. ሰዎች (አባሎቿ) የሚያውቁት እውነት የሚመስል ውጪአዊ መጠሪያ (መታወቂያ) አላት፤ ውስጣዊ (ሚስጢር የሆነ ስምም አላት):: ቁጥር 5::

10.9.2.7. ስለ ጌታ ኢየሱስ በእውነት የሚቆሙትንና የሚመሰክሩትን ቅዱሳን አማኞች ደም ታፈሳለች:: ቁጥር 6::



ዛሬ ታዲያ እንዲህ የሚያደርጉ እግዚአብሔርን እንከተላለን የሚሉ የሉም? ሐሰተኞች ናቸው በሚል ስም ቅዱሳንን እንደ ጳውሎስ (ሳውል ሳይለወጥ እንደነበር) የሚያስቃዩ በአብያተ ክርስቲያናት ስም የቆሙ የሉም? ጌታ ኢየሱስ ንቀኋቸው፣ አጥፏቸው፣ ግደኋቸው ፈጽሞ አላለም:: እስከ መከር ተዉአቸው ነው ያለው:: ታዲያ ከመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ውጪ የሆነ ህይወት የማን ነው? መሪውስ ማን ነው? የጋለሞታይቱ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ይህ ነው:: የከፋት ሥራዋ በእርግጥ እጅግ ያስደንቃል:ቁ.7:: የአውሬውና (ሐሰተኛው ክርስቶስ) የምድር ነገስታት በራዕይ 19:11-20 እንደተጠቀሰው ጌታ ኢየሱስና ቅዱሳኑ ከሰማይ ሲመጡ ለመውጋት የሚዘጋጁ ከሆነ በአውሬው ራስ ላይ የተቀመጠችውም ጋለሞታ ቤተክርስቲያን እንዲሁ ታስተባብራለች:: ራዕይ 17:12-14፣ 19:19::

ማንኛውም እግዚአብሔርን ጌታ ኢየሱስንና መንፈስ ቅዱስን እወዳለሁ፣ አከብራለሁ፣ እታዘዛለሁ የሚል ሁሉ ከዚች በስም ከምትኖር ጋለሞታ ቤተ ክርስቲያን ራሱን ሊያነጻ ይገባል:: ይህ ዘመን የእውቀትና የምርመር ዘመን ነው:: ሐዋ. 17:10-11፣ ዳን. 12:4:: በሌላው ሰው ግፊትና ልመና ልምጥምጫም የሚኖርበት ጊዜም አይደለም:: እውነትን ለሚፈልጉ ቅኖች እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በኩል እጅግ ቅርብ ነው:: ወደ እውነትም ሁሉ ይመራል:: ዮሐ. 16:13:: ለመኖር ብላችሁ ሁሉን የፈጠረውን በእውነተኝነት የሚያፈቅራችሁን ጌታ ኢየሱስን በኑሯችሁ የምትበድሉት በፊልጵ. 3:18-19 እንደተጠቀሰው ከማያምኑ ጋር በመመሳጠር የጌታን ቁስል የምትወጉ የአብያተ ክርስቲያናት ክፍል አማኞች ነን የምትሉ ወዮላችሁ! እውነተኛ ክብር የሚገኘው ከጌታ ጋር በመጣበቅ እንጂ የአውሬውን መንፈስ በማገልገልና የዓለም ወዳጅ በመሆን ፈጽሞ አይደለም:: እኔ ይህንን ጽሑፍ ስጽፍ ማንንም ልፈርድ አይደለም:: ለመንቃት፣ ለመዳንና ለመንፈሳዊ ትግል ስመነሳት ሁኔታዎችን ላመቻች እንጂ:: ለ30 እና ለ80 ዓመት ምድራዊ ደስታ ተብሎ ዘላለማዊውን ባርኮት ማጣት ምንኛ የሚዘገንን

ነው:: ስለዚህ የምድራዊ ኑሮ እየተበከለ ሁሉ እየጨለመ ሲሄድ የወፍ ድም
እንኳን ሰውን በሚያስበረግግበት በዚህ ዘመን በፍጹም ልብ ..ፍራ እን
የትዕቢትን ነገር አታስቡ. እንደተባለ በመፍራት ወደ ጌታ ኢየሱ
በተከታታይ ንስሃና ከሐጢአት በመራቅ መመለስ ያስፈልጋል:: ይህ
ጋለሞታ ቤተ ክርስቲያን ምንም ያህል ለክብሯ ብትሮጥና ከከሃ
መንግሥታት ጋር ብትሰበጣጠርም በራዕይ 17:16-17 እንደተጠቀሰው
ባከበሯት መንግሥታት እጅ መልሶ እግዚአብሔር ያደቅቃታል:: ሰው
በምንም ዓይነት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ካልጀመረ በቀር ለኑሮው ትክክለኛ
በረከትን (ጥቅምን) ለማግኘት ወሳኝ አይደለም:: ደግሞም ፈጽሞ
አያውቅበትም:: ስለሆነም እምነቷ ያልተበረዘውን፣ መሳይ ህይወት የሌለባትን
እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ፈልገን እንጠጋ:: ተጠንቀቁ::

## 10.10. የሦስቱን ሰባኪዎች ምስክርነት አጥብቆ መከታተል

ለሰው ልጅ የውስጥ ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ ሰጪ እንደ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ምንም የለም:: የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በማቴ. 18:16 ላይ ...በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና... ይላል:: የአንድ የክርስቶስ ተከታይ ነኝ የሚል ሰው ህይወት ያለ ውጪአዊና ውስጣዊ ማስረገጫ (ምስክር ሰጪ) ዝም ብሎ አርቲ ቡርቲ (ከንቱ) በሆነ ነገር ሊመራ ፈጽሞ አይገባም:: የህይወቱን አቋም እንዲመዝን ትክክለኛ ምስክር ሰጪ ኃይላት ያስፈልጉታል:: እነዚህም ቢያንስ ሁለት ቢበዛ ሦስት መሆን አለባቸው:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ሰዎች፣ መላዕት፣ እግዚአብሔር ተፈጥሮ፣ ጽሑፎችና እንስሳት ስለ ሰው ህይወት ምስክርነት ሲሰጡ ተመልክተናል:: እኔ ግን ከእነዚህ ውስጥ በ2ኛ ተሰ. 2:1-2 ወደ ተጠቀሱት መስካሪዎች እድንመለከት እፈልጋለሁ::

በዚህ ክፍል ስለ ጌታ ኢየሱስ መምጣትና ስለ ቅዱሳንም ወደ ጌታ መሰብሰብ የሚመሰክሩ ሦስት ክፍሎች ተጠቅሰዋል:: እነርሱም፣



10.10.1. መንፈስ ቅዱስ (ትንቢት)
10.10.2. ቃል (ተናጋሪዎች፣ ሰባኪዎች)
10.10.3. መልዕክት (የሚጻፉ ደብዳቤዎች) ናቸው::

### 10.10.1. መንፈስ ቅዱስ

በሮሜ 8:14-16 እንደተጠቀሰው አንድን አማኝ (ቅዱስ) የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሚመጣው ነገር ሊነግረው ይችላል:: ዮሐ. 16:13 በዚህ ክፍል የሚመጣውንም ይነግራችኋል ይላል:: ሰው መንፈሱ ከኃጢአት ነጽቶ ትንሳኤን ካላገኘ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ግንኙነት አይኖረውም:: የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ለመስማት ከኃጢአት ተጽዕኖ መላቀቅ ያሻል:: ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በትንቢት ወይም በማይነገር መቃተት ተናግሮ ይመራዋል::

### 10.10.2. የተናጋሪዎች (ሰባኪዎች) ቃል

በአሁኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞሉ አገልጋዮች እግዚአብሔር አሉት:: ወደፊትም ይመጣሉ:: በምድረበዳ እንደጮኸው መጥምቁ ዮሐንስ የጌታን ምጽዓት የሚናገሩ በሐጢአት የሚጓዙትንም የሚገስጹ ባሪያዎች አሉ:: የእነርሱንም ምስክርነት ጠጋ ብሎ በማማከር መቀበል ያሻል::

### 10.10.3. መልዕክት

በአሁኑ ዘመን በጋዜጦች፣ መጽሔቶችና መጻሕፍት በኩል ብዙ መንፈሳዊ ጽሑፎች ይወጣሉ:: የእነርሱንም ምስክርነት ማዳመጥ እጅግ ይጠቅማል::

እዚህ ላይ በማላሰቢያነት ልጠቅሰው የምወደው ነገር አለ:: ይኸውም የሰይጣን አገልጋዮችም በእነዚህ በሦስቱና በሌሎችም ሊጠቀሙና ሊያምታቱ እንደሚችሉ ነው:: እውነትን ለሚፈልግ ሰው ከላይ በጠቀስኳቸውም ሆነ

በሌሎች እግዚአብሔር ሲመሰክርለት ቢያንስ የሦስቱ ልክ ከሆነ የሚቀጥለው የቀደመውን ያጸናል:: ግን እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላውም ሲናገር ማስተዋል ያሻል :: ኢዮብ 33:14:: በህይወትህ ስትጓዝ በውስጥህ መንፈስ ቅዱስ በማይነገር መቃተት ሊናገርህ ይችላል:: ያንን ድምጽ ወደ ልብህ ልታመጣው ትችላለህ:: እየተጓዝ(ሽ)ክበት ያለው የህይወት መንገድ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ በውስጥ መንፈስህ ሰላምን፣ ደስታንና ኃይልን በመስጠት እንድትጓዝበት ያጸድቅ(ሻ)ሃል:: ያበረታታሀል:: ነገር ግን በተበላሸ ጐዳና እየሄድክ ከሆነ ሁልጊዜ ያለማቋረጥ የሚሰማህን ስሜት ይልካል:: ይህም ..የበደለኝነት ስሜት.. ይባላል:: ልብ እናድርግ! የበደለኝነት ስሜት ማለት እየተጓዝንበት ያለው መንገድ ልክ አለመሆኑን የሚያመለክት ማለት ነው:: እውነትን ፈልገህ ስታገኘው ስትጓዝበትም ሰላምና ጸጥታ ይሰማሃል:: ያኔ የበደለኝነት ስሜት ካንተ ይለያል::

የመነጠቅ ቀን እጅግ ቀርቧል:: ጌታ ኢየሱስ ወንዶችና ሴቶች ቅዱሳኑን ሊወስድ ቶሎ ይመጣል:: ለመነጠቅ ከፈለግን ከላይ ከቁጥር 1-10 ያሉትንና ሌሎችንም እግዚአብሔርን መስለህ እንድትጓዝ የሚረዱህን መንፈሳዊ መመሪያዎች ልትከተል ይገባል:: እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመኖር የመጽሐፍ ቅዱስ ወዳጅ መሆን ያሻል:: ያኔ ብርሃን ይበራልሃል::ከምታፍርበትም ምናምንቴ ሁሉ ታመልጣለህ:: ፀጋ ይብዛልን:: አሜን!!!



# ክፍል አሥራ አንድ

## መነጠቅን የምንናፍቅበት ምክንያቶች

እግዚአብሔር በዕውቀቱና በሁሉንቻይነቱ ፍፁም ነው:: ሁሉን በሚያውቅ ማንነቱ ስለማይጠራጠር ተስፋ ይሰጣል:: የሰጠውንም ተስፋ ይፈጽማል:: እርሱ የሚሰጠውም ተስፋ ፍፁም በረከት ያለበት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጻፉት 6208 ትንቢቶች ውስጥ ዋነኛው ጌታ ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያቱ ስለመነጠቅ የተናገሩት ነው:: ዩሐ14:1-3፤1ተሰ.4:17:: መነጠቅ አማኞች በሙሉ ሊናፍቁት የሚገባ የሕይወት ልምምድ ነው:: ስለሆነም ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አኳያ አማኞች ልባቸውን በመነጠቅ ላይ ሊያኖሩ ይገባል::

እውነተኛ ዳግም ልደትን ያገኙ ክርስቲያኖች በሙሉ መነጠቅን ሊናፍቁ ይገባል ምክንያቱም:-

### 11.1. ክርስቶስ ኢየሱስ የሰጠው ህያው ተስፋ ስለሆነ ነው::

ጌታ እየሱስ በምድር ቆይታው ለደቀ መዛሙርት እጅግ የተከበሩ ትምህርቶችን አስተምሮአቸዋል:: ካስተማራቸውም ውስጥ አንዱ የእርሱን መሄድ አስበው ሲያዝኑ በጊዜው ተመልሶ መጥቶ ሊወስዳቸው እንደሚችልም በማጽናኛ ቃል መናገሩ ነው:: ስፍራን ካዘጋጀ በኋላ «ወደ እናንተ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» (ዮሐ.14:1-3) ማለቱ ታላቅና ክቡር ተስፋን መስጠቱ ነው:: ይህ ቃል ለዘመኑ አማኞችም የሚያስተላልፈው ዕውነት አለ:: ክርስቲያኖች የጌታን መሄድ ሲያስቡ መመለሱንም ይናፍቃሉ:: ይህ ተስፋ በእርግጠኝነት ተሰጥቷቸዋል:: ተስፋውም እነዚህ ቃሎች የታመኑና ዕውነተኞች ናቸው ተብሎ እንደተጻፈ የታመነና ዕውነተኛ ተስፋ ነው:: ስለሆነም ዳግም ልደትን ያገኙ ክርስቲያኖች በሙሉ ተስፋው እስኪፈፀም ድረስ ዘወትር በጉጉት የመነጠቁን ቀን ሊጠባበቁ ይገባል:: ክርስቶስ ኢየሱስ የሰጠውን የተስፋ ቃል ቸል ማለት ወደ ሙሉው መርገም መግቢያ መንገድ

ነው:: ጌታ በዚህ ቸልታ ምንም አይደሰትበትም:: ክርስቶስ የሰጠውን ተስ[ፋ] መጠበቅ ጌታን የማክበሪያው አንደኛውና ትልቁ መንገድ ነው:: አሜን!!

## 11.2. ዘላለማዊ ፅድቅ ውስጥ ለመግባት

ነብዩ ዳንኤል ከመልዓኩ ገብርኤል ስለ 70ኛው ሱባኤ መልዕክት ተቀብሏል:: 70ኛው ሱባኤ ሲያልቅ ለእስራኤላውያን የሚፈፀሙላቸው ስድስት ልምምዶች ተጠቅሰዋል /ዳን9:24/ እነዚህም ልምምዶች የአመፃ ማብቃት፣ የኃጢአት መፈፀም /ማለቅ/፣ የበደል መስረይ፣ ዘላለማዊ ፅድቅ ውስጥ መግባት፡ የራዕይና ትንቢቶች መታተምና የቅድስተ-ቅዱሳኑ መቀባት ናቸው:: ይህም ማለት ሰባኛው ሱባኤ ሲያልቅ ስለ እስራኤላውያን የተነገሩት ትንቢቶችና የታዩት ራዕዮች በሙሉ ተፈጻሚነት ያገኛሉ:: ከኃጢያትም ጋር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይለያያሉ፣ ኃጢያት መስራት ስለማይኖር የአይሁዶችም በደል አይቆጠርም፣ መተላለፋቸው በሙሉ ይደመሰሳል:: ምክንያቱም የሰቀሉትን ኢየሱስን ሙሉ በሙሉ አውቀውትና ተረድተውት ስለሚቀበሉት ከሰቀሉት ጌታ ም ጋር የሚኖራቸው እርቅ ሙሉ ስለሚሆን ዓይኖቻቸውም ስለሚበሩ ነው:: በተጨማሪም ሱባኤው ሲያልቅ የቤተመቅደሱ መረገጥና የቅድስተ-ቅዱሳንም መርከስ ይወገዳል፣በዚህም ዘላለማዊው ፅድቅ ውስጥ ይገባሉ:: ይህም ማለት ሁልጊዜ ልክ የሆነ ሥራ መስራት ሕይወት ውስጥ መግባት ማለት ነው::

ከላይ የተዘረዘሩት ስድስት መሠረታዊ ሐሳቦች በሰፋት ቢተነተኑ ብዙ ማለት ይቻላል:: ሆኖም ግን አንድ ሊተኮርበት የሚገባ ነገር አለ:: ይኼውም አይሁዶች /እስራኤላውያን/ ከጌታቸው ጋር ታርቀው ዘላለም ፅድቅ ውስጥ ሲገቡ አይሁድ ያልሆኑ ሌሎች ክርስቲያናዊ አማኞችም ወደ ዘላለም ፅድቅ ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ ይመቻቻል:: ይህም የሚሆነው መነጠቅ በሚፈፀምበት ጊዜ ነው:: በመነጠቅ ጊዜ ያንቀላፉት /የሞቱት/ አማኞች በማይሞት በማይበሰብስ ፣ በማያረጅ፣ ኃጢያት በማይሰራና በማይወድቅ አዲስ አካል ስለሚነሱ፣ ያልሞቱት ደግሞ በተመሳሳይ ሰውነት ስለሚለወጡ



ሁለቱም ወደ ዘላለማዊ ፅድቅ ውስጥ ይገባሉ ማለት ነው:: ጊዜው ይርዘም እንጂ አህዛብም ካመኑ ክርስቶስ በምድር በሚነግስበት ጊዜ ይህ ዕድል ለእነርሱም ይደርሳቸዋል::

## 11.3. ከሰማይ /ከገነት/ ቅዱሳን ጋር ለመገናኘት

ከመጀመሪያው ፃድቅ ከአቤል ጀምሮ እስከ መጨረሻው ጋለሞታይቱ ደሙን የምታፈስው ቅዱስ/ቅድስት/ ያለበትን ስፍራና ማንነታቸውን ማየት የሚቻለው በመነጠቅ ነው:: መነጠቅ ወደ ፃድቃን መንፈሶች መድረሻው ብቸኛው መንገድ አይደለም:: አማኞች በማንቀላፋት ወይም በመሞት እዚያ ይገባሉ:: ዕብር. 12፥22-24:: በገነት፣ በደስታ የተሰበሰቡ አእላፋት መላዕክት፣ በብሉይ ኪዳን ከታችኛው ገነት /የአብርሃም እቅፍ/ የተነጠቁና ወደ ሰማይ የተዘዋወሩ ቅዱሳን፣ የሁሉ ዳኛ የሆነው እግዚአብሔርና ፍፁማን የሆኑ የፃድቃን መንፈሶች ወዘተ ይገኛሉ::ፍፁማን የሆኑ ፃድቃን መንፈሶች ስንል ከዚህ ከደካማው ሰውነት የተለዩና ኃጢአት መስራት የማይችሉ በዘላለም ቅድስና የተሞሉ ማለት ነው:: እነርሱ ያሉበት ቦታ ለመድረስ እያንዳንዱ አማኝ ማንቀላፋት ወይም መነጠቅ ይኖርበታል::

## 11.4. የክርስቶስን የሚመስለውን አዲሱን አካል ለመልበስ

አካል ሁሉ የተለያየ ነው:: ምድራዊ፣ ሰማያዊ፣ የሚሞት፣ የማይሞት፣ ተፈጥሯዊና ልዕለ ተፈጥሯዊ፣ ሰዋዊና እንስሳዊ፣ ወዘተ አካል ይገኛል:: ጌታ ኢየሱስም ሆኑ ሐዋርያቱ በተለይ የክርስቶስን ስለሚመስለው አካል ግልጽ አድርገው ተናግረዋል፤ ፅፈውማል:: ሐዋርያው ጳውሎስ «ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን፣ የሚሞተውም የማይሞተውን ሊለብስ ይገባልና፣ ይላል:: 1ኛቆሮ15፥53::የምንለብሰው አዲሱ አካል ከክርስቶስ አካል ጋር ተመሳሳይነት አለው:: በተጨማሪም በራሱ እንደሚሆን አሰራር ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሰውነታችንን ይለውጣል ይላል ::ፊሊጵ3፥21:: ይህ የለበስነው አካል ደካማ ስለሆነ ኃጢአት ሊሠራ ሊሞትና ለአዳጋ ሊጋለጥ የሚችል ሲሆን፡ ከመነጠቅ /ከትንሳኤ/ በኋላ የምንለብሰው

አካል ግን የመሬት ስበት ሳይዘው በቀጥታ ወደ ላይ መውጣት የሚች
ነው:: ሐሥ.1:9-11:: በሥጋ ዓይንም ይታያል:: የተዘጋ በር፣ጥቅጥ
ሐይል፣ የሰው ተግዳሮት ሊቋቋመው አይችልም:: በአብ ፊት መቆ
/መቀመጥ/ይችላል:: የፀሐይ ኃይልም ሆነ የኒውክለር የጨረር ሐይ
ሊያቃጥለውና ሊያጠቃው አይችልም:: ከተፈጥሮም ሆነ ከሰው ሰራሽ ኃይ
ውጪ መሆን የሚችል ነው:: ስለሆነም መነጠቅን የምንናፍቀው ያ አስደና
የክርስቶስ አካል ምን እንደሚመስል ለማየት ነው::

## 11.5. በሞት ላይ ለዘላለም ለመንገስ

በዘመናት መካከል የሰዎችን ልጆች ሲያንቀጠቅጥ የኖረው ሞ
ከቅዱሳን ጋር ያለው ግንኙነት ለዘላለም የሚቋረጥበት ዘመን ይመጣል::
ሞት የቁም፣ የአካልና የዘላለም/የነፍስ/ ተብሎ በሦስት ይከፈላል:: መነጠ
ከሦስቱም የሞት ዓይነቶች ይታደጋል:: አንድ አማኝ አንዴ ከተነጠቀ ማንነ
ከእግዚአብሔር ጋር በሕይወትና በዕርቅ ስለሚኖር የዘላለም ሞት አያገ
ውም:: ከዚህም የተነሳ ነው ጳውሎስ ክርስቶስ ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋ
ቅዱሳን ሲያንቀላፉ ወይም በቅጽበተ-ዓይን ሲለወጡ *ሞት ለዘላለም ተዋጠ*
ያለው:: መነጠቅ አማኝን የሞት ወዳጆችና አጃቢዎች ከሆኑት ከሲኦልና
ከኃጢአት ለዘላም ይለያል:: ስለሆነም የተነጠቀ አማኝ በክርስቶስ አማካኝነት
በሞት ላይ ነግሦአል ማለት ነው::1ኛቆሮ15:54:: አንድ ቅዱስ ሲነጠቅ
በክርስቶስ የሆነውን ድል ተቀዳጅቷል ማለት ነው:: /ቁ. 57/ አማኝ ሲነጠቅ
የሚቀበለው ታላቅና ክቡር ስጦታ «ድል *መንሳት*» ይባላል:: አማኝ ሲነጠቅ
ሰይጣን ከአማኙ የግል ሕይወት ይናፍቅ የነበረውን ድል ነሺነትሙሉ በሙሉ
ያስረክባል:: እንደ የአስቆሮቱ ይሁዳና ዴማስ ይጠባበቀው የነበረውን የአማኝ
-ን ውድቀት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያጣል:: ሰይጣን ድል መንሳቱ ይቀርና
ድል ይደረጋል/ባለድል መሆንን ሙሉ በሙሉ ይከለከላል/:: ስለሆነም ይህን
ክቡር ህይወት ለመቀዳጀት ዘወትር መነጠቅን መናፈቅ ይኖርብናል::



## 11.6. በመፅናናት ለመኖር

በቅድመ መነጠቅ ያለው ሁኔታ በቀላሉ የሚኖርበት አይደለም:: አስጨናቂና የምጥ ጣር መጀመሪያ ጊዜ ነው:: ማቴ24፥6-7፤2ኛጢሞ3፥1:: ሁሉ ነገር ወደ ፍፃሜ የሚቸኩልበት ጊዜ ስለሆነ ትርምስ፣ ስቃይ፣ ዕልቂት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ መተላለቅ፣ ሥጋዊነት ወዘተ የሚበዛበት ዘመን ነው:: ያለው የፖለቲካ ይዘት፤የኤኮኖም ሁኔታ፡ የተፈጥሮ አደጋ ክስተት፡ ችነፈሩ፤ጭንቀቱ፡ ረሀቡ፡ የምድር ነውጡ፡ የአውሎንፋሉ አደጋ፡ የህዝብ በህዝብና የመንግስት በመንግስት ላይ መነሳት፡ የፍቅር መቀዝቀዙ፡ ወዘተ በጣም የሚያስጨንቅ ነው:: ስለሆነም በወቅቱ ያለውን ሁኔታ ተቃቁሞ በመጽናናትና በመኖር በዩሐ.14:1 እንደተጠቀሰው ወደ ተዘጋጀልንም ሥፍራ ለመድረስ የምንናፍቀው መነጠቅን በመጠበቅ መሆን አለበት:: መጽ/ቅዱስ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተፅናኑ ያለው፡ በደመና እንነጠቃለን የሚለውን ቃል በማለብ ነው:: /1ተሰ4፥17-18/:: ብዙ የሚያውክ ተስፋ አስቆራጭ ነገር ሲመጣ መፍትሄው የመነጠቅን ቀን መናፈቅ ነው::

## 11.7. ራስን በቅድስና ለመጠበቅ

ጌታ እግዚአብሔር እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ብሎአል:: ይህ የቅድስና ሕይወት እግዚአብሔርን ከምንመስልባቸው መንገዶች/መልኮች ውስጥ ዋነኛውና አንዱ ነው:: ቅዱስ በመሆን በጌታ ቤት መኖር በዘላለም ቅድስና የኖረውን ፈጣሪአችንን ለማየት እንድንናፍቅ ያደርገናል:: ቅድስና በአማኞች ህይወት ከሚያነሳሳባቸው ዋና ነገሮች ውስጥ ዋነኛው እግዚአብሔርን እንድናይ ማስናፈቁ ነው:: ዕብ12፥14:: አማኞች በሙሉ በቅድስና ሲኖሩ «እኛ አገራችን ከሰማይ ነው» /ፊሊጵ.3፥20/ ማለትን ሁልጊዜ ይለማመዳሉ:: ለመነጠቅ የሚናፍቀው ሰው ሁልጊዜ ራሱን በቅድስና ይጠብቃል:: ምክንያቱም የማይነጠቁ ፈሪዎች፣ ውሾች (የእግዚአብሔርን የሚመስሉ የሰይጣን አገልጋዮች)፣ አስማተኞች፣ ነፍሰ ገዳዮች ወደ ከተማይቱ የመግባት ዕድል ስለማይኖራቸው ነው:: ራዕይ 21:8::

## 11.8. ጌታ ያዘጋጀልንን ቦታ ለማየት

መነጠቅን እንድንናፍቀው የሚያደርገን ጌታ ያዘጋጀልንን ሥፍ ሲያሳየን የሚችል መንገድ በመሆኑ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ «በአባቴ ቤት ብ መኖሪያ አለ ሥፍራን አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ» ብሏል፡፡ዮ.ሐ14፥1-3 ይህ የተዘጋጀልን ስፍራ ቅዱስ ስፍራ ነው፡፡ ኃጢያት፣ ሞት፣ ሐዘን፣ ችግር የተፈጥሮ ቀውስ፣ ህመም፣ ማጣት፣ አደጋ (የአካል ጉዳተኝነት) ጦርነ ወይም ማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር የለበትም፡፡ ዛሬ በምድራች የምናያቸውና የምንሰማቸው የቀውስ ዓይነቶች፤የፖለቲካ ተፅዕኖ፣ ዘረኝነት የፆታ ግጭት፣ የሰው ስጋ መብላት፣ ድህነት ወዘተ በሙሉ በሰማይ አይገ ም፡፡ በዚያ ስንኖር፡ በዚህ ምድር ጣታችን ወይም አንገታችን ላይ ለጋብ በቀለበትነት ወይም በሐብል መልክ ለመጠቀም ጣርና ውድ የሆነብን ወር በተዘጋጀልን በሰማይ የእግራችን መቆሚያ ይሆናል፡፡ራዕይ 21:18-19፡፡ ጌ ባዘጋጀልን በሰማያዊ ስፍራ ከወርቅ ይልቅ እጅግ የከበሩት እንደ ወራውሬ ያክንት፣ክርስጵራስስ፣ በሉር፤አሜቴስጢኖስና የመሳሰሉት ክቡ ድንጋዮች/እንቁዎች ይገኛሉ፡፡ ራዕይ 21፥19-20፡፡ መነጠቅን መናፈቅ ያለብ ይህንን የከበረ ስፍራ ለማየት ነው፡፡

## 11:9. ጌታ ኢየሱስን ለማየት

ለብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ የተተረከለት ያ ልዩ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ምን ይመስል ይሆን? እስከ ዛሬ በቢሲየን የሚቆጠሩ ታሪክ የተተረከላቸው ብዙ ኀያላን ነበሩ፤ ነገስታትን፡ መሪዎችን፡ አየን ታሪካቸውንም ሰማን፤ ገድላቸውንም አነበብን፡ ሞተው ግን መነሳታቸውንና ሰይጣንንም ሆነ ተከታዮቹን ሲያንበረክኩ ፈጽሞ አላየንም፤ አልሰማንምም፡፡ ታሪካዊው ጌታ ኢየሱስ ግን ይህንን ማድረግ ችሏል፡፡ ያንን የዓለም ፕሮፌሰሮችና ዶክተሮች ሲያነፁት ያልቻሉትን ኃጢአቱን በከበረው ደሙ ያጠበውን ከቃሉ መረዳትና በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ዳግም ልደትን ያስገኘ ልንን፣ አባ አባት ብለን እንድንጮህ የልጅነት መንፈስ የሰጠንን ፣ ከሠይጣን ልጅነት ወደ እግዚብሔር ልጅነት የለወጠኝን፣ ከጠላቶቻችን ከአጋንንት ኃይል



ያላቀቀንን፣ ከአውሬው ዕጣ ፈንታ ነፃ ያወጣንን፣ ያዳነንን፣ ከውርደት ወደ ክብር ያሸጋገረንን፣ ያንን ክፉ ሳይሰራ ሲሰቃይ የሚያደረጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው በማለት ማንም ሲገልጽ ያልቻለውን ፍቅር በመስቀል ላይ የገለጠውን አፍቃሪና ለራሱ ያልሣሣውን ቸሩን መሲህችንን ጌታ እናየዋለን፡፡ አዳኝነቱን ርህራሄውን ወሰን የሌለውን ጥልቅ የሆነ ፍቅሩን ብቻ ሣይሆን ሁለንተናውን ከዘላለም ክብሩ ጋር ሆኖ እናየዋለን፡፡ ካልተነጠቅን ጌታን በሙሉ ክብሩ አናየውም፡፡ በመነጠቅ ጌታን ለማየት ስንናፍቅ አብሮ የተያያዙ ልምምዶችንም እንፈፅማለን፡፡ ለምሣሌ የጌታን መምጣት እናስቸኩላለን፡፡ 2ኛ ጴጥ3፥12፡፡ ጌታን ለማየት ከመናፈቃችን የተነሣ ስለመነጠቅ ባሰብን ጊዜ ለእኛ መገለጡን እናስቸኩላለን ማለት ነው፡፡ በአጸደ-ሥጋ ስንኖር የመነጠቅ መለኮታዊ ስርዓት በህይወታችን ካላለፈ ጌታን አናየውም፡፡ ስለሆነም ጌታን ለማየት መነጠቅን ልንናፍቅ ይገባል፡፡1ተሰ4፥17፡፡

## 11:10. የትንሣኤውን ኃይልና ምንነት ለማወቅ

ከሞት የተነሱ ቅዱሣንና ያንቀላፉ ቅዱሳን ሲለወጡ የሚለብሱት መንፈሳዊ አካል ተመሳሳይ ነው፡፡ አንድ አማኝ ሲነጠቅ ወዲያው የክርስቶስን የሚመስለውን አካል ስለሚለብስ በትንሳዔ ያለውን ኃይል ይረዳል፡፡ ትንሣዔ የመለኮት መንገድና አሰራር ነው፡፡ ትንሳዔ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከአስፈሪው ጠላት የመሰያያ አድማስ ነው፡፡ መነጠቅ ሲሆን መለወጥ፣ መለወጥም ሲሆን የትንሳዔው ኃይል በዚያ ይታያል፡፡ ለዚህ ነው በራዕይ 20:4-6 በፊተኛው ትንሳኤ ዕድል ፈንታ ያለው ብጹዕ ነው የተባለው፡፡ ክርስቶስንና አዲሲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን እንድናይ ሥልጣን በሚያስጨብጠን ትንሳኤ ተሳታፊ ከመሆን የበለጠ ምን ደስታ አለ?

## 11:11 ተስፋ መቁረጥን ለመቋቋም

አበውም ሆኑ የዘመኑ ምሁራን ሲናገሩ «ከስህተት ሁሉ የከፋ ስህተት ተስፋ መቁረጥ ነው» ይላሉ፡፡ ይህ አባባል ከታሪክም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አንጻር ሲታይ እውነትነት አለው፡፡ እውነተኛ ተስፋ የተገኘ ህይወትን

እንደሚያስመልም ምግብ ነው:: በእንፃሩ ደግሞ ተይዞ የነበረው ተስፋ ሲጠፋ ወይም ሲቆረጥ ያንኑ ያህል አጥንትን ያነቅዛል:: የሰው ተስፋው ሲሞት ሕይወቱም አብሮ ሊሞት ይችላል:: ስለሆነም ክርስቲያን በሕይወቱ ያለው የዘላለም ህይወት ተስፋ ተሚጥጦ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳይወድቅ ሁልጊዜ የመነጠቅን ቀን መጠበቅ ይኖርበታል:: ተስፋ ሲባል ደግሞ ዓይነቱ ብዙ ነው:: ተስፋ ሲበዛ እውነተኛ ተስፋ ላይሆን ይችላል:: ኦሌ ኤሪክሰን _«የአንድ አራሽ ንግግር»_ በተባለው ፅሁፋቸው ስለብዙ ተስፋ አደጋ « ተስፋ መቼም ተስፋ ነው፣ ብዙ ተስፋ ግን ምናምን ባዶ ከንቱና የሚሸነግል አለኝታ ነው» በማለት ፅፈው ነበር:: ይህ እውነት ነው:: የጠቢቡ ሰለሞን ተስፋ ብዙ በመሆኑ ነው አክባሪ ፈጣሪውን ለማንገሥና ለመታዘዝ ጊዜ ያጣው፤ በምድራዊ ቋንቋ መልካም ቢሆንም ብዙ ተስፋ አዕምሮን ይይዛል፡ ልብን ያከብዳል፣ የፀሎትንና የቃሉን የጥናት ጊዜ ይወስዳል:: ብዙ ተስፋ እንደተስፋው ዓይነት ኀዘን ያበዛል:: ልብንም ያከብዳል:: ስለሆነም ተስፋ የተደረገበት ሁሉ የባለተስፋውን ህይወት ይቆጣጠራል፤በዚህ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች /አማኞች ከመባከናቸው የተነሳ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይወድቃሉ:: ስለሆነም ወደ ራስ ማንነት የሚመጡትን ብዙ የተስፋ ዓይነቶች በመቆጣጠር ሁሉንም ተራ በማስያዝ ባመቺው ጊዜ ልንጠቀምባቸው ወይም ደግሞ ልንቃወማቸው ይገባል:: ሆኖም ግን የጌታን በአየር መመለስና የመነጠቅን ቀን አጥብቆ የሚከታተል ክርስቲያን ራሱን ይቆጣጠራል:ይገዛል፡ በመጠንም ይኖራል::

### 11:12. ክፉን ፀንቶ ለመቃወም

እውነተኛ ክርስቲያን መንፈሳዊ መታወቂያ አለው፤ይህም መታወቂያው የመስቀሉ ሕይወት ነው:: መስቀሉን ተሸክም ዕለት ዕለት ጌታን የሚከተል አማኝ ዘወትር መልካሙን የዕምነት ገድል የሚጋደል ነው:: ይህ ክርስቲያን ክፉ ኃይላትን በመቃወም ይመላሰላል:: የተሰያዩ ክፉ ቀናትና ልዩ ልዩ ፈተናዎች ሲገጥሙት ተቃውሞው ፅኑ ነው፤ የክፉን አሠራር በመቃወሙ ክርስቶስ ኢየሱስን ይመስላል:: ንፅረተ-ዓለሙ (አመለካከቱ) ወጥና ስርዓት ያለው ነው:: አይወላውልም:: በክፉው ቀን ለመቃወም የሚያስችለው የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ የለበሰና ሊለብስም የተዘጋጀ ነው:: ኤፌ 6፥14-18:: ክርስቶስ እንደሚመጣና እንደሚነጠቅ አምኖ የሚጠባበቅ አማኝ ኃይል ይኖረዋል:: ከዚህም የሚወጣ ተስፋው ኃያልና ፅኑ ነው:: የመስቀሉን ሕይወት አይጋፋም::



# ክፍል አስራ ሁለት

## ማስጠንቀቂያ

_ማስጠንቀቂያ_ ከቶውንም ያለ ምክንያት አይሰጥም፤ ማስጠንቀቂያ ከሚመጣው ጐጂ ነገር ለማምለጥ፣ ራስን ለማዘጋጀት፣ ራስን ለማንቃት እጅግ ይጠቅማል:: ማስጠንቀቂያ ነገሮችን በቅድሚያ ቀምሞ ለመደቆስ ያነሳሳል:: ካስፈላጊውም የረብ ቦታ ያደርሳል:: ማስጠንቀቂያ በማቴ. 24:39 ያላወቁ አለቁ ከተባለባቸው የኖህ ዘመን ሰዎች የከፋ ህይወት ያወጣል:: ጌታ የሰጣቸውን የማትጊያ ንግግሮች (መልዕክቶች) እጅግ ልንጣበቅባቸው ይገባል::

### 12.1 በአንድ ወፍጮና እርሻ ለምንሠራ

ጌታ ኢየሱስ ከተናገራቸው አስደናቂ ትንቢቶች ውስጥ አንዱ በማቴ24:40-41 ያለው ነው:: ቃሉም በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ላይ ይውላሉ፣ አንዱ ይወሰዳል ሌላውም ይቀራል ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ አንዷ ትወሰዳለች ሌላይቱም ትቀራለች የሚለው ነው:: በዚህ ቃል ውስጥ በቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ሀረግ «በዚያን ጊዜ» የሚለው ነው:: ይህ ጊዜ የቱ ነው? ጊዜው የሎጥንና የኖህን ዘመን የሚመስለው የሰው ልጅ ዘመን ነው:: ሉቃ 17:26-30:: ወፍጮ እርሻና ህንጻ ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው:: በክርስትና እርሻ/ህንጻና ወፍጮ ላይ ሁለት ዓይነት ሰዎች እንደሚኖሩ ያመለክተናል:: 1ኛቆሮ3:9:: በክርስትና እርሻ ላይ በመጨረሻው ዘመን አንዱ ወደ ጌታ ሊወሰድ ሌላውም ላይወሰድ የሚችል ሰው እንደሚኖሩ ያመለክተናል::

በአሁኑ ጊዜ በስመ ክርስትና ቤተ ዕምነት ብቻ ከ300 የሚበልጡ ንዑሳን ቤተ ዕምነቶች ተመሥርተዋል:: ቤተ ዕምነቶቹ ሁለቱንም ዓይነት ፆታ ይዘዋል:: ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነገር ሁለቱም ዓይነት ሰዎች በአንድ ዓይነት ዕምነት ላይ ሆነው አንዱ ሲወሰድ ሌላው መቅረቱ ነው::

በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት የሰዎች ወደ ፀሎት ቤት አመጣጥ አነሳሹ ኃይል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወንጌልና እምነት አለመሆኑ ነው፡፡ በፀሎት ቤት ውስጥ በአፋቸው አማኝ ነን እያሉ በድርጊት የድፍረት ኃጢያት የሚሠሩ፣ ለጥቅም ብለው የሚያመልኩ፣ ወላጆቻቸው አማኞች ስለሆኑ እነርሱን ለማስደሰት የሚፀልዩና የሚዘምሩ፣ የፀሎት ቤቱ አቀማመጥ ደስ ስላላቸውና ዕድሉ ስለተገኘ ለረጂም ጊዜ የሚመላለሱ፣ እጮኛ ፍለጋ የሚመጡ፣ ከቤተ ክርስቲያን የስጋ ጥቅም ለመግኘት የሚመላለሱ፣ በአጃቢነት የሚኖሩ፣ ጥሩ ጓደኛ ስላላቸው የሚያገለግሉ ወዘተ ይታያሉ፡፡

ሰዎች ራሳቸውን እንክርዳድ ነኝን? እባብ ወይስ ጊንጥ ነኝን? ብለው መፍረድ ወይም በቃሉ ሥልጣን ማንነታቸውን ሊመረምሩ ይቸግራቸው ይሆናል፡፡ ስለሆነም ከምክንያቶች የተነሳ ተመሳስለው ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በተፈጥሮ ቀልጣፋነታቸው ፕሮግራም መሪ፣ ባለዕውቀት በመሆናቸው ሰባኪ የሆኑ፤ የሙዚቃ መሣሪያ የመጫወት ችሎታ መያዛቸው የአምልኮ ወይም የመዘምራን ቡድን መሪ መሆናቸው አገልጋይ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ትክክለኛውን የድነት ህይወት አላገኙት ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ጌታ መጥቶ የራሱ የሆኑትን ሲወስድ ሌሎች ባሉበት የሚቀሩት፡፡ ይህ ምንኛ አሳዛኝና ምስኪንነት የበዛበት ህይወት ነው?

ስለሆነም በስመ ክርስትና በየቤተ-ዕምነቱ ያለን ክርስቲያን የተባልንና ነን! ነኝ! ብለን የምናምን አጥብቀን ልንጠይቀውና ሳንንሳፈፍ በመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ስለማንነታችን ለምንጠየቀው ጥያቂ ምላሽ ልናገኝለት የሚገባ ነገር እንዳለ ሊተኮርበት ይገባል፡፡ ይኸውም የኂለኛው መለከት ቢነፋ በቅጽበተ-ዓይን ከሚለወጡት ወይም በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ፈንታ ከሚኖራቸው ክፍል ነኝ ወይስ አይደለሁም? ለሚለው ጥያቄ በእርግጠኝነት መልስ ማግኘቱ ላይ ነው፡፡ የመነጠቅ ጉዳይ ዕውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያንን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ ብሎ መነጠቅ አለመነጠቁን የሚያውቀው ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ



ው ማለት ከተጠራጣሪነት ተለይቶ ሊታይ አይችልም፡፡ አንድ ሰው ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አካል ውስጥ እንዴት መግባት ይችላል? ሰው መዳኑ እርግጠኛ መሆን ይችላል? ለመነጠቁስ? ለእነዚህ ጥያቄዎች መጽ/ቅዱስ ግልፅ መልስ ይሰጣል፡፡ ስለሆነም ረጋ ብሎ እንደ ቤሪያ ክርስቲያኖች ልብንም ሰፋ አድርጎ ቃሉን በቀንና በሌሊት በመመርመር እርግጠኛ የሆነውን ነገር መረዳት ተገቢ ነው፡፡

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የክርስቶስ ተከታዮች ወይም የክርስትና እምነት ተከታዮች በቤተ ዕምነት ደረጃ ዋነኞቹ ከ300 በላይ ደርሰዋል፣ አነስተኞቹ ወደ ሺህ የሚደርሱም አሉ፡፡ ለምሳሌ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት፣ ሜተዲስት፣ ካቶሊክ፣ አርቶዶክስ፣ ተሃድሶ ኦርቶዶክስ፣ተሃድሶ ካቶሊክ፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ አድቬንቲስት፣ ክርስቲያን ሳይንስ፣ የጂሆቫ ምስክሮች፣ ሐዋርያት ወዘተ በሙሉ በክርስትና ዕምነት ሥር ይመደባሉ፡፡ ጥቂቶች ባይቀበሉም ሁሉም በክርስትና ወፍጮ ላይ ወይም ህንጻና እርሻ ላይ ይሠራሉ፡፡ መለከት ሲነፋ ከውስጣቸው የሚነጠቁ ሲኖሩ የማይነጠቁ አሉ ማለት ነው፡ በቤተ ዕምነቱ ሥር ሆነው እንዴት ሳይነጠቁ ይቀራሉ? ለዚህ መልሱ ለመነጠቅ መሟላት ያለባቸውን ልምምዶች መመልከቱ ይጠቅማል፡፡ ባጭሩ ግን ለመመለስ የክርስትና ዕምነት ተከታይ አባላት ሦስት ዓይነት ክርስቲያኖች መኖራቸውን ልብ ማለት ነው፡፡

አንድ ክርስቲያን 1. ፍጥረታዊ 2. ስጋዊ/ነፍሳዊ/ 3. መንፈሳዊ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል፡፡ *ፍጥረታዊ ክርስቲያን* ስንል ከመጽሐፍ ቅዱስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተዋሃደ /በተቀናጀ/ አሠራር ህይወቱ ያልተመሠረተ ነገር ግን እንደተወለደ በስም ክርስቲያን የተባለ ሆኖም ለሰው በማይታይ ለእግዚአብሔር ግን በሚታይ ሁኔታ ክፉ የሚሰራ እርሱ ፍጥረታዊ ክርስቲያን ይባላል፡፡ ይህ ሰው ሐጢአትን እንደውኃ ይጠጣል እንደ እንጀራ ይበላል፡፡ አስገዳጅ ሁኔታ በተፈጠረበትና ባመቸው ጊዜ ክፉ ስራን መስራት ትክክል እንዳይደለ እያወቀና እየተረዳ ያልፈለገውን ክፉ ስራ ይሠራል፡፡

አስመስራትን አይችልም:: ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስላሌለው ነው :: ሐሥ. 2:1-4፣1:8፣ሉቃ. 24:49:: ያምናል ዕምነቱ ግን ፊር የሰቀቀ ነው:: በዚህ ዓይነቱ ሰው የፈሪሃ እግዚአብሔር ማንነት ዘወትር ባጠገቡ እንዳለ አይሰማውም:: ስለሆነም እንደተፈጠረ ያለ ነው በሐሳቡ ግን ክርስቲያን ነኝ አማኝ ነኝ ጌታን አፈቅራለሁ፣ እወደዋለሁ ሲል ይችላል ይሁን እንጂ የዚህ ዓይነቱ ክርስቲያን ገና ንስሀ ያልገባ ፍጥረታዊ ሰው ነው:: ስለሆነም አልዳነም::

በመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ቋንቋ ንስሀ ሦስት ክፍሎች በቅደም ተከተል ይያዛል:: ይኼውም 1. *ኃጢያተኛ መሆንን ማወቅ ነው:* ይህም የኃጢአት ሰንኮፍ ገና በማህፀን ሳለ በተፈጥሮ አብሮት የተወለደና የኖረ መሆኑን እስካለው የህይወት ደረጃ በሠራው ኃጢአት እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔር የሆኑትን እንዳሳዘነ ገብቶት መልሶ ጌታውን በማስቀጣቱ የተፀፀተ ማለት ነው2. በኃጢአቱ ካዘነና ከተፀፀተ በኋላ ወደ እግዚአብሄር በሠራው ክፉ ሥራ *የተናዘዘ ወይም ኃጢያቱን ለጌታው የተናገረ* 3. በኃጢአቱ ተፀፅቶ ከተናዘዘ በኋላ ከኃጢአት ለመራቅ ወስኖ ወደፊት *ከሐጢአት ለመራቅና በቅድስና ለመኖር ውሳኔ ያደረገ* ሰው ንሥሀ ገብቷል ይባላል::

ይህ ሰው /ወንድም ሆነ ሴት/ ከእግዚአብሄር ጋር እርቅ ያደረገና ከጥንተ-አብሶ /ውርስ ኃጢአት/ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የታጠበ ከመሆኑም በላይ ሰይጣናዊ ኃይላት /ሰይጣንና አጋንንቱ በማንነቱ ላይ ሥልጣን የሌላቸው ነው:: በመስከታዊ አሠራር የእግዚአብሔር ልጅ ነው:: በየትኛውም የክርስትና ዕምነት ሥር ባሉ ቤተ ዕምነታት ስር ቢኖርም ይህ ሰው መለከት በሚነፋበት ጊዜ ይነጠቃል:: በአንጻሩ ግን በሐጢአት የሚኖርና በርኩሰት የሚመላለስ ከሆነ በተመሳሳይ ቤተ ዕምነቶች ውስጥ ቢሆንም የስም ክርስቲያን ስለሚሆን የመነጠቅ እድል አይገጥመውም::



*ማንኛውንም የዚህ ዓይነት ክርስቲያን እንዳይነጠቅ የሚያደርገው ፍጥረታዊ ክርስቲያን መሆኑ ነው::* ሁለተኛው የክርስቲያን ዓይነት *ስጋዊ ወይም ነፍሳዊ* የምንለው ክርስቲያን ነው:: ሥጋዊ ክርስቲያን ክርስቶስን አምኖ፣ ንስሀ ገብቶ ወደ ቅድስናው ሙላት ለመድረስ ትግል የሚያደርግ ሲሆን ከመንፈሳዊ ልጅነት፤ ካለማወቅና ከድካም የተነሳ ኃጢአትን የሚለማመድ ነው:: ይህም ቢሆን ንሰሀ ይገባል:: በሠራው ሥራ ነፃነትና ሰላም አይሰማውም:: ይፀፀታል:: የነዚህን የሁለቱንም ዓይነት ክርስቲኖች ታሪክና ልምምድ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንና ከኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ህይወት መረዳት ይቻላል::1ኛቆሮ3:1-4:: የዚህ ዓይነቱ ሰው ኃጢአቱ ስለተሰረየለትና አባ አባት ብሎ የሚጠራበት የልጅነት መንፈስ ስለተሰጠው መለከት ሲነፋ ይነጠቃል::

ሦስተኛው *መንፈሳዊ ክርስቲያን* የምንለው ነው:: ይህ ሰው በመንፈሳዊ ህይወቱ ያደገ፣ የጠነከረ፣ የፅድቅን ቃል ለይቶ የሚያውቅ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሚታይበት፣ በመንፈሳዊ ጉዳይ የሚተጋ፣ ፈጣሪውን የሚያገለግልና ዕውነተኛ የሆነ ነው:: 1ኛ ቆሮ2:6-16:: ይህ ሰው የኋለኛው መለከት ቢነፋ ይነጠቃል:: አንድ ክርስቲያን ከሦስቱ የክርስቲያን ዓይነቶች ውስጥ የትኛውን እንደሚመስል ማረጋገጥ ይኖርበታል፤ ይህም ይቻላል:: እንግዲህ ክርስቲያን ነኝ ባይ ሁሉ ልብ ሊለው የሚገባው ምስጢር ያለው እዚህ ላይ ነው:: የአንዲቱ መወሰድ የሌላዪቱም መቅረት ወይም የአንዱ መነጠቅና የሌላውም መቅረት ምሥጢር ጉዳዩ ያለው እዚህ ላይ ነው::

## 12.2 የልብ መክበድ

ጌታ ኢየሱስ በምድር ሲኖር ለደቀመዛሙርቱ ካስጠነቀቃቸው ዕውነቶች ውስጥ አንዱ በምድራዊ ነገር ልባቸው እንዳይከብድ ማስተማሩ ነበር ሉቃ. 21:34:: ጌታ ስለትዳርም በማለብ ልባችሁ እንዳይከብድ ሲል የሚያውቀው ምሥጢር መኖሩን ያመለክተናል:: አንድ የመኪና ባትሪ ሲሰራና አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ ባትሪው ኃይሉን ቢቀንስ እንዲሰራ ቻርጅ

ይደረጋል/ኃይል ይሞላል/ በተመሳሳይ መልኩ አንድ ወንድም በምድራዊ ነገር ልቡ ከበደ ሲባል በምደራዊ ነገር ቻርጅ ተደረገ ወይም የሕይወቱን አብላጫ ክፍል ለምድራዊው ነገር አዋለ ማለት ነው:: አንዲት እህት ወይም ወንድም ልቧ ከበደ ሲባል አማኙ በግልም ሆነ በቡድን 1. ለመፀለይ 2. ቃሉን ለማንበብና ለማጥናት 3. ወደ ፀሎት ቤት ሄዶ ለማምለክ ማለትም ለመፀለይ፣ ለመዘመር ርዳታ ለማድረግ፣ ለሌለው ለማሰብና ለመለገስ፣ ለማያዊውን በረከትና ህይወት ለማሰብ ጊዜ አጣች ማለት ነው:: ስለ ትዳር በማሰብ ሲል ትዳር የሚያመለክተው ትንሽ ልጅም ይሁን ትልቅ ለው ለምድራዊ ኑሮ የሚከፍለው ማናቸውም ዓይነት ዋጋ ተግባርና እንቅስቃሴ ነው:: በቀድሞ ዘመን ትዳር ሲባል ሁለት ተቃራኒ ፃታዎች ተጋብተው አብረው መኖር ሲጀምሩ ነበር:: ሆኖም ግን ትዳር ማለት ያላገቡም ሆኑ ያገቡ ሰዎች የዕለት ዘላቂ ኑሮአቸውን ለማከናወን የሚወሰዱት እንቅስቃሴዎችና ተግባራት ናቸው::

ከበደ ማለት ወደ ታች ተሳበ ወይም ሚዛን ደፋ ማለት ነው፤ የሰው ልቡ ማለትም ዝንባሌውም ሆነ ስሜቱ መረዳቱም ሲከብድ ከምድራዊ ነገር ጋር ሲተሳሰር መንፈሳዊነቱ ይወድቃል፣ ዕውነተኛነትን ይጥላል፣ በመቀጠልም አንድ ጊዜ ወደ ዓለም ሌላ ጊዜ ደህሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ያያል፤ በነገርም ገቢ ይሆናል:: ግድየለሽና ትህትና የተለየው ይሆናል፤ አንድ ቀን እንቅፋት የሚጥለው መሆኑን ይዘነጋል:: ንፁህ ወይም ቅዱስ አድርጎ ራሱን ሲቆጥር በውስጡ ግድፈት መኖሩን ይዘነጋል:: ተመስገን ጌታዬ ሞላ ጎተራዬ ከማለት ይልቅ ተመስገን ሆዴ ሞላህ ብሎ ፈጣሪውን አናንቆ ሆዱን ያሞካሻል:: እውነተኛ አምላኩን ሲከፋው አይገድደውም፤ሆዴን ብቻ አይክፋው! ይላል:: የዚህ ዓይነት ሰው በምድር ስለመረፈቅ ዘውታሪ ስለሆነ ስለመነጠቅ ማሰብ ጉዳዩ አይደለም:: ለዚህ ሳይሆን ይቀራል መንገድ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ልባችሁ እንዳይከብድ ያለው! *በከበደ ልብ ብዙ መሰኮቶችና በሮች ለለሚኖሩ የሚመላለሱበት ይበዛል*:: መመላለሻ ከሆነ ደግሞ ይረገጣል፤ ነፃነት የሚጠፋው እዚህ ላይ ነው ስለሆነም ልባችን አይክበድ!!



## 12.3 የመራቅና መቅረብ ክስተት

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና በከፍተኛ ደረጃ ከሚሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች አንዱ «ከእነዚህ ደግሞ ራቅ» የሚለው ነው:: በአንድ በኩል መራቅ ካለ በሌላ በኩል ደግሞ መቅረብ ይኖራል:: ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ መልዕክቱን ሲያስተላልፍ ከምን መራቅ እንዳለባቸው አጠንክሮ ገልጾአል:: ለምሳሌ በ2ኛጢሞ 3:1-9 ጳውሎስ ከ25 የማያንሱ የመጨረሻው ዘመን ሰዎችን የኃጢአት ልምምዶች ይዘረዝርና ቁ.5 ላይ ከነዚህ ደግሞ ራቅ ይለዋል:: ይህ ራቅ የሚያመለክተው ከሰዎቹ ተለይቶ ገዳም መግባትን ሳይሆን እዚያው አጠገባቸው ሆኖ እንደሎጥ በኃጢአት ሥራቸው ፃድቅ ነፍስን እያስጨነቁ በኃጢአት ሥራቸው ሳይተባበሩ መኖርን ነው:: 2ኛጴጥ2:7-8፤ቲቶ.3:9-11:: ክፉና መልካም፣ ኃጢአትና ፅድቅ፣ ሰይጣንና እግዚአብሔር ፍፁም ተቃራኒና የማይታረቁ ማንነቶችና ክስተቶች ናቸው:: እንደዚሁም የእግዚአብሔር ልጆችና የሰይጣን ልጆች ቅርፃዊ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ይዘታዊ ልዩነታቸው ከፍተኛ ነው:: ያላቸው የይዘትና የዓላማ ልዩነት በመሐላቸው ያለውን የግንኙነት ርቀትና ቅርበት ይወስነዋል:: ወደ ሰው ለመቅረብ ተብሎ ከእግዚአብሔር አይራቅምና:: ምክንያቱም አደጋ ስላለው ነው::

መዝሙረኛው ዳዊት «እነሆ ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉና፣ ከአንተ ርቀው የሚያመነዝሩትንም ሁሉ አጠፋሃቸው» ሲል ከእግዚአብሔር መራቅ በቀጥታ የጊዚአዊውንም ሆነ የዘላለማዊውን ጥፋት እንደሚያመጣ ተረድቶአል:: ስለሆነም የወሰነው «ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል» በማለት ነበር:: መዝ. /73/:27-28:: ስለመቅረብና ስለመራቅ ስናስብ አንድ አስቸጋሪ ነገር አለ:: ይኸውም በመጽሐፍ ቅዱስና በድህረ-ቤተ ክርስቲያ ምስረታ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሰዎች ወድደው ነው ከእግዚአብሄር ርቀው የጠፉት? አውቀው ይሆን ፈጣሪያቸውን የካዱት? ወይስ ደግሞ ሃሌ ሉያ እያሉ እየዘመሩ ሆኖም የተበረበሩ፣ የሰበኩ ሆኖም በጌታ ያልረኩ፣ ቃሉን ያስተማሩ ሆኖም በክፋት የመረሩ ብዙ አይደሉምን?

ሰው በቀን ከ3 እስከ 5 ጊዜ ለስጋው እንደሚበላ ሁሉ ከፈጣሪውም ሳለመራቅ ለመንፈሳዊ ህይወቱም በተከታታይ መመገብ አለበት:: ሲበላም እንጀራውን በመራራ ቅጠል የመብላትን ያህል ወይም በአፉ ቃሉ እየጣፈጠው በሆዱ መምረሩን እየተገነዘበ መመገብን ሳይረሳ መሆን አለበት:: ራዕይ10:8-11:: በዘመኑ ክርስትና ሴቱ ሆያሆዬ ወንዱ አበባየሆይ የሚል ይመስላል! ሰው እንዴት ከፈጣሪው ይርቃል? ለዚህ በቂ መልስ ለማግኘት የራቁ ሰዎችን ህይወት መለስ ብሎ ማጤን ነው:: ሰውን ከእግዚአብሔር የሚያርቀው 1. ሰው ነው:: ይሄ ሰው ጎደሎ ወይም ግማሽ ሰው ነው:: ጎደሎ ሰው በአፉ ፈጣሪውን እያሞካሸ /ያከበረ እየመሰለ/ በድርጊት የሚክደው ነው:: ይሄ ሰው አሰናካይ ነው:: 2. ዓለም /Cosmos/ ዓለም ሲባል ማንኛ ውም ሰው ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀርብ ግለሰቡን ማርኮ /አንቆ የሚይዘው ኃጢአት አሳቃፊ ልምምድ፣ ምኞት፣ ሲስተም ወይም ምድራዊ ቅንባሮ፣ የተቃራኒ ፆታ ፍቅር፣ ክብር፣ ስግብግብነት፣ በሙሉ በ2ኛጢሞ3:1-9 የተጠቀሱት ሁሉ ሰውን ከእግዚአብሔር ያርቁታል:: 3. አጋንንት: አጋንንት ሰውን ከእግዚአብሔር ያርቁታል:: እነርሱ በዕድሜ፣ በዕውቀት፣ በችሎታ፣ በልምድ፣ በሸፍጠኝነት፣ በአፈጣጠር ወዘተ ሰውን ይበልጡታል:: ሰው በልዩም ሆነ በጋራ ፀጋ ስለተጠበቀ /Special & Common Grace/ በፈጣሪው እርዳት መኖር ቻለ እንጂ መናፍስት ሰውን መጫወቻ ሊያደርጉት ይችሉ ነበር:: ለምሳሌ፤ እኛ ከተነጠቅን በኋላ እነዚህ በጌታ ሐይል የተያዙና የተከለከሉ አጋንንት ሰውን እንዲያሰቃዩ መለቀቃቸው አይቀርም :ራዕይ9:1-10:: ያኔ ለአውሬው ተከታዮች ወዮ! ከእግዚአብሔር ርቀው ለሚሳደቡ ሰዎች፣ ስቃያቸውን ባንወድድም ከትንቢቱ ቃል አንፃር ስለነዚህ ከእግዚአብሔር ስለራቁ ሰዎች ወዮ እንላለን:: ራዕይ 9 በሙሉ ይነበብ:: ራዕይ16:12-15::

ክርስቲያን ጥንቁቅ ነው የሚባለው እውነተኛ አምልኮን ሲያመልክ ነው: ከእውነተኛ አምልኮዎችም ዋነኛው በያዕቆብ 1:27 «እንደተገለጸው በዓለም ከሚገኘው ዕድፍ ሰውነትን መጠበቅ ነው» ታዲያ ዛሬ ያለ ጋብቻ



በልቅ ወሲብ በመርካት እንኑር፣ እንደፈለገን እናስወርድ፣ የሰው ስጋ እንመገብ፣ ሰውን ገድለን ወደ ሌላ ዓለም እናሸጋግረው፣ ወዘተ በግል ብልሹ ፍልስፍናና ሃይማኖት አዕምሮአችን ሲመረዝና ህይወታችን መኖር ሲጀምር ዝም ከተባለ፣ ኃጢአቱ እንደ ፅድቅ ከተቆጠረ እንዴት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይቻላል? ፍፁም ዘበትና የማይታሰብ ነው:: ስለሆነም ለመነጠቅ የሚፈልጉ ሁሉ መንፈሳዊ ርቀት /Spiritual Distanciation From God/ የት በታና ሁኔታ ላይ እንደሚጠነሰስ አስተውሎ አውቆ ስለመራቅ መጠንቀቅ ያሻል:: በ1980ዎቹ አጋማሽ ላይ ኢ.ቲ.ቪ. እማር በነበረበት ጊዜ ቪክ እንደርስን በመባል የሚታወቁ መምህር በማለዳ የአምልኮ ፕሮግራማችን ላይ ቃል ሲያካፍሉ አንድ የማይረሳ ንግግርን አስተላልፈው ነበር:: ይኸውም ምንም እንኳን እኛ ሙሉ ጊዜአችንን ሰጥተን መጽሐፍ ቅዱስን የምንማር ብንሆንም ካልተጠነቀቅን በስተቀር ከእግዚአብሄር ልንርቅ እንደምንችል የሚያሳስብ ነበር:: ቀላል ማስጠንቀቂያ አይደለም::

## 12.4 <u>የግል የፀጋ ስጦታ ልምምዶች ለመነጠቅ ዋስትና ስላለማስገኘታቸው</u>

ይሄ ዘመን የእነ ዘመነ እንኮዬ/የእነ እንደልቡ ዘመን ነው:: ካመቸና ካስኬደ ቀጥል የሚባልበት፣ አስተዋይነትና ጭምትነት ከሰው ህይወት የኮበለለበት ዘመን ነው:: ግለአማክሎአዊነት /ግላዊነት/ ኃይል ያገኘበትና የምዕራቡ ዓለም ፍልስፍናና ስነ ልቦናዊ አመለካከት እንዲሁም አንፃራዊ ዕውነትና አንፃራዊ ሥነምግባር /Relative Truth and Relative Ethics/ ሥር እየሰደዱ ያሉበት ዘመን ነው::

አትንኩኝ! ተዉኝ! ሁኔታው ባወጣው ያውጣኝ! በጉዳዩ ጣልቃ አትግቡብኝ፣ ጅቡ ቢበላኝም ይብላኝ፣ ብሞት ለራሴ ብኖር ለራሴ የሚባልበት ዘመን ነው:: ዕውነት የሚባል ፅዩፍ ሆኖ የታየበት ጊዜም ነው:: አሞፅ 5:10 ፣ 2ኛጢሞ4:3-4/:: ላንተ ዕውነት የሆነልህ ለእኔ ውሸት ሊሆን ስለሚችል፣ ላንቺ ክፉ የሆነው ለእኔ መልካም፣ ላንተ መልካም የሆነው ለእኔ ክፉ፣ ለአንዱም ኃጢአት የሆነው ለሌላው ፅድቅ ሆኖ የሚታይበት አመለካከትና

የአንፃራዊነት አካሄድ እየተበራከተ የመጣበት ጊዜ ነው:: ለምሳሌ አንድ ሰው የራሱን መንፈስ: መንፈስ ቅዱስ ነው ብሎ ቢል እሺ. ለእርሱ ዕውነት ሊሆን ይችላል ተብሎ ግለሰቡ እንደልቡ እንዲፈረጥጥና እንደፈለገ እንዲያቧትር ወይም አንድ ወፍ ገድሎ ሳለ ሺህ ወፎች ገደልኩ ሲል የሚሳቅለትና የሚጨበጨብለት ጊዜና ልምምድ ውስጥ ገብተናል::

ከዚህም የተነሳ ቀድሞ በአንዱ በመንፈስ ቅዱስ የሚሠራው እውነተኛ መንፈሳዊ ልምምድ /በፀጋ ስጦታዎች መጠቀም/ ዛሬ በአንዳንድ ቦታ መንፈስ ቅዱስ ከማዳኑ የተነሳ ለስሜት ወለድና አጋንንት ወለድ መንፈሳዊ መሰል እንቅስቃሴና ልምምድ ሥፍራ ሲይዝ ይታያል::

ሰው መንፈስ ነፍስና ስጋ አለው:: ወይም ሰው ውስጣዊ ሰውነትና ውጪአዊ ሰውነት አለው:: ሰው በውስጣዊ ሰውነቱ ከመንፈሳዊ ዓለም ጋር ተራክቦ/ኅብረት/ ሲያደርግ በስጋዊ አካሉ አማካይነት ደግሞ ቁሳዊ ከሆነው ዓለም ጋር ኅብረት ወይም ግንኙነት ያደርጋል:: ሰው በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ተጠቅሞ ከማንነቱ ጋር ተራክቦ እያደረገ ያለው መንፈሳዊ ኃይል ምንጩ ከየት እንደሆነ ካልለየ በስተቀር አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል:: በክርስቶስ አማኝ የሆነ ክርስቲያን ጥንቃቄ እስካላደረገ ድረስ አጋንንት ሊነግሩት፣ ሊያስተምሩትና ሊናገሩት ይችላሉ? ይህንን ሐሳብ በአጽንኦት ሊገልጽልን የሚችለው ጥቅስ በ1ኛጢሞ 4:1-2 ያለው ነው:: በዚህ ጥቅስ ውስጥ:-

«መንፈስ ግን በግልጥ: በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል» የሚለው ዕውነት ቢሆን በዚህ መንገድ አማኝ የነበሩ ሰዎች ከክፉ ኃይላት ጋር ተራክቦ ካደረጉ በኋላ ሀይማኖታቸውን እንደሚክዱ ያመለክተናል:: የሚካደው ሃይማኖት ትክክለኛው እስከሆነና ክህደትን አስተላላፊዎቹም በውሸተኞች ሰዎች የሚጠቀሙ አጋንንት/መናፍስት ከሆኑ ሰዎቹን ለማግኘት ልዩ ልዩ መሣሪያዎች፣ ዘዴዎችና መቅረቢያዎች እንዳላቸው ማሰብ አያዳግትም:: ታሪኳ በሐሥ.



16:16-18 ተጠቀሰው የሟርተኝነት መንፈስ የነበረባትን ሴት መንፈስ የሰብከትን የሙገሣ ዘዴ ተጠቅሞ ሐዋርያው ጳውሎስን ሊያስተው ሞክሮ ነበር:: መንፈሱ ተባባሪ፣ የወንጌል አገልጋይ መስሎ በልጅቷ ሲናገር ሐዋርያቱ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ባይነቁበት ኖሮ ልጅቷን ተከታይ ሆነው ሊስቱ የሚችሉበት ክስተት ሊገጥማቸው ይችል ነበር:: ዛሬ አንዳንድ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ነን ባይ ቤተ ዕምነቶች ምን ያህሉ ከዚህ የስህተት አሰራር የፀዱ ይሆን?

የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረችው ኤልዛቤል የጌታን ባሪያዎች በማሴሰን ታስት ነበር፤ ጎላ ባለ መልኩ መሳት ባለበት ቦታ ከክፉ ኃይላት ጋር ግንኙነት ወይም የእነርሱ ተፅዕኖ የለም ማለት አይቻልም:: የአስቆሮቱ ይሁዳን ታሪክ ስንመለከት ሰይጣን ሊቆጣጠረው ሲል በሀሳቡ ክፉ ሀሳብ አስገባ ከዚያም ራሱ ገባበት:: ለመሆኑ አስቆሮቱ ይሁዳ ከ12ቱ ጋር በተመረጠና ሥልጣን ተሰጥቶት ለአገልግሎት በወጣ ጊዜ ሽባ ተርትሮ፣ የሞተ አስነስቶ ድውያንን ፈውሶ፣ በፀጋ ስጦታዎች ተጠቅሞ ተዐምራት አድርጎ ነበር? ወይስ ዝም ብሎ ለ3 ተኩል ዓመታት አጃቢ ነበር? መልካም፤ ይህንን ለአንባቢያንና ለመንፈስ ቅዱስ መተው ይሻላል::

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ሰዎች አሉ? አንድ ሰው አለ እንበል ይህ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መመላለስንና መስራትን እንደ አገልግሎት አያይም፤ ሆኖም ግን ችሎታው ስላለው ይሠራል:: ስራውም መሰበክና መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር ነው:: ይህ ሰው ለመስራትና ለዕለት ኑሮው ገንዘብ /ገቢ ለማግኘት እንጂ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚመላለሰው ስለዳነ ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ አይደለም:: የዚህ ዓይነቱን ሰው ሰይጣን እንደምን ይመለከተዋል? እውነተኛ አማኞችን ለማግደያ ይጠቀምበት ይሆን? በዩሐ. 16:1 እንደተጠቀሰው ትንቢት መፈፀሚያ ሊሆን ይችል ይሆን? አዎን እንግዲህ የመነጠቅን ቀን በናፍቆት የሚጠብቅ ክርስቲያን ወደዚህ ዓይነት መጠለፍ ውስጥ እንዳይገባ በብርቱ ሊጠነቀቅ ይገባዋል:: እንግዲህ ራስን መመርመር ጠቃሚ የሚሆነው እዚህ ላይ ነው:: 1ኛቆሮ.11:32-35::

በርዕሱ ላይ እንደተጻፈው የፀጋ ስጦታዎች ልምምድ መንግስተ ሰማይ ለመግባት ዋስትና እንደማይሰጡ ተገልጦአል:: እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲጠቀሙባቸው በእርግጥ ትልቅ መፅናናትን ወደ ጌታ መጠጋትን ሊያስገኙ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ዕምነትን ሊያሳድጉ ይችላሉ:: ሆኖም ግን የፀጋ ስጦታዎቹ በግል ህይወታችን ስለተገለጡ በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ እንደምንገባ እርግጠኞች ነን ማለት አይቻልም ለማለት ነው:: ይህ እውነት የሚሆነው ሰይጣን ራሱ ልክ የፀጋ ስጦታዎችን የሚመስሉ አጋንንታዊ የማታለያ፣ የመጥቀሚያ እንቅስቃሴ ሊያደርግ ስለሚችል ነው:: ይህንን ሐሳብ በበለጠ ለመረዳት ማቴ7:22፣ 2ኛቆሮ11:13-15፤ 2ኛተሰ2:9-11፣ ራዕይ13:12-14 ማንበቡ ይጠቅመናል::

ሐዋርያው ጳውሎስ እኔ ለሰዎች ከሰበክሁ በኋላ የተጣልሁ እንዳልሆን ራሴን እየጎሰምሁ አስገዛለሁ ሲል በእርሱ ደረጃ እንኳን ካገለገለ በኋላ መጣል /ከንቱ መሆን ሊኖር እንደሚችል ቃሉ ያስረዳናል:: በተለይ በማቴ7:22 ላይ የተጠቀሱት ዓይነት ሰዎች ጌታ ከቶ አላውቃችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ሲላቸው ለመለኪያነት ማስረጃ ያቀረቡት በፀጋ ስጦታዎች መጠቀም መቻላቸውን ነበር፤ እግዚአብሄር ፀጋውን ሊያፈስስ ይችላል፡ ያንን ሲያደርግ ግን ሰዎች እንዲያምኑትና ንስሀ ገብተው ህይወታቸውን እንዲያስተካክሉ ለመርዳት ነው:: ሆኖም ግን ራሳቸውን እንደ ንፁህ ሰው የሚያዩበት ከሆነ ትዕቢትን ያመጣል:: ስለሆነም ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነስቶ ይጀምራል የሚለውም ቃል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው እዚህ ላይ ነው:: ራስን በቅድስናና በንፅህና እየጠበቁ እግዚአብሔርን በመፍራት መመላለስ እንጂ የፀጋ ስጦታዎች በሕይወቴ ስለሰሩ ወደ እግዚአብሔር መንግስት በሙላት እገባለሁ ማለት እንደማያስችል ሊተኮርበት ይገባል:: በተጨማሪም በምድረ በዳ በጣም አስደናቂ በሆነ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ /በድንቅ፣ በተዐምራትና በምልክቶች/ ታጅበው ኖረው በመጨረሻ ግን ከሁለት ሰዎች በስተቀር በምድረ በዳ የቀሩትን እስራኤላውያን ልብ ልንልና ለተግሳጽ የሚሆን



ትምህርት ልንወስድ ይገባናል፤ ድንቅ ማየት መንፈሳዊ ላያደርግ ይችላል:: 1ኛቆሮ. 10:1-12::

## 12.5 የእግዚአብሔርን ኃይል የጣለ እምልኮ

ሐዋርያው ጳውሎስ የመጨረሻውን ዘመን ሰዎች ከገለጠባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የአምልኮት መልክ ኖሮአቸው ኃይሉን የካዱ መሆናቸው ነው::1ጢሞ3:5:: የአምልኮት መልክ ማለት ማንኛውም ውጪአዊ በሆነ መልኩ ሰው የሚረዳው፣ የሚያየውና የሚሰማው ግርግር ማለት ነው:: ሰባኪነት፣ የመጽ/ቅዱስ አስተማሪነት፣ ዝማሬ፣ ፀሎት፣ ፕሮግራም መምራት፣ ማስመለክ ወዘተ በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይቻላል:: አምልኮ ውጫዊና ውስጣዊ የሆነ መልክ አለው::

### 12.5.1. ውጫዊና ውስጣዊ እምልኮ

ስለሁለቱም ምንነት በዝርዝር ለመተረክ ሁኔታ ባይፈቅድም መረጃ ለማግኘት የግድ ስለ ሰው ሰብዕና መመልከት ይኖርብናል:: የሰው ሰብዕና በሁለት ይከፈላል:: ይኸውም ልብስ ሰብዕናና ዕውን ስብዕና ናቸው:: ልብሰ ሰብዕና ስንል ማናቸውም ሰው በአይኑ ተመልክቶ በጆሮው ሰምቶ ብያኔ ወይም አስተያየት ሊሰጥበት የሚችለው እንቅስቃሴ ነው:: ሰው አስመስሎ ለማሳመን የሚገልጣቸው የሚያደርጋቸው ለገሃዱ አለም የተጋለጡት ልምምዶች በልብሰ ስብዕና ደረጃ ይፈረጃሉ::

እውን ሰብዕና የምንለው ደግሞ የግለሰቡን የውስጥ ማንነት አመልካች የሆነ፡ ግለሰቡ ለብቻው የሚያውቀው ወይም እግዚአብሔር የሚያውቀው የሕይወት አቋም ሐሳብና ዝንባሌ እውን ሰብዕና ይባላል:: የማማከር አገልግሎት ምሁራን እንዳመለከቱት እነዚህ የሰብዕና ዓይነቶች 1. በተጣጣመ መልኩ 2. በተቃረና መልኩና 3. በተዘበራረቀ መልኩ በሰው ህይወት ሊገለጡ እንደሚችሉ ይናገራሉ:: ስዚህ እውነት ማስረጃ ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎችን መመልከት ይጠቅማል::

አምኖንና አቤሴሎም ሁለቱም ዓይነት የሰብዕና ልምምዶች ታይተውባቸዋል፤ አምኖን አሞኛል ብሎ ለትዕማርና ለዳዊት መልዕክት ሲልክ የውስጥ ሰብዕናው ግን በወሲብ ስሜት ተይዞ ነበር /2ኛሳሙ13/:: አቤሴሎም ወደ አባቱ ወደ ዳዊት በችኮላ ቀርቦ ሲስመውና በማለዳም ወጥቶ ሕዝቡን ሰላም እያለ ልቡን ሲሰርቅ በልብሰ ሰብዕና ደረጃ የአባቱ ረዳት ተባባሪና አክባሪ ይመስል ነበር:: በዕውን ሰብዕናው ግን መፈንቅለ መንግስት አድርጎ በዙፋኑ ላይ ለመቀመጥ ነበር:: እስቲ አቤሴሎምን በአንድ ሁኔታ እንመልከተው:: ለምሳሌ የእስራኤላውያን መንፈሳዊ የክብር በዐላት በሆኑ ጊዜ በነዚያ ቀናት ህዝቡ ዳዊትም ፈጣሪያቸውን ሲያመልኩ ሲወጡ ዳዊት በንፁህ ልብ ጌታውን ሲያመልክ አቤሴሎምም በህዝቡ መሃል አብሮ ያመልክ ነበር:: አሁን የዳዊት ልብና የኤሴሎም ልብ በእግዚአብሔር ፊት ምን እንደሚመስል መገመት አያዳግትም:: የዳዊት አምልኮ በልብሰ ሰብዕና በዕውን ሰብዕና አንፃር ጤናማ /ለእኛ ያልታወቁ እንዳሉ ሆነው/ ሲሆን፤ የአቤሴሎም ግን የሚጋጭ ነበር:: ወይም የአቤሴሎም አምልኮ በልብሰ ስብዕና ደረጃ ነው ማለት ይቻላል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በቀባው በዳዊት ላይ የመነሳት ድብቅ ሰብዕና ስለነበረው ነው::

ዛሬም ቢሆን በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዚህ ዓይነት ብዙ ሰዎች አሉ:: ልባቸው እንደ ዴማስ ፊፅሞ ዓለምን የወደደች ገና ዓለምን ወደ መውደድ ያዘነበለ ወይም የተነሳሳ፣ ተጠራጣሪነት ያለባቸው፣ የእግዚአብሔርን ሚችነትና አለመኖር በመቀበል ዳርቻ ላይ ያሉ ይኖራሉ:: የእነዚሁ ሰዎች ሰብዕና የተደበላለቀ ነው:: ውሳኔ አላደረጉም እንጂ ለብዕናቸው እርስ በርሱ ይጋጫል:: ለምሳሌ ታሪኩን በ3ኛ ዩሐንስ 9-10 የምናነብበው ዲዮጥራጢስ በአንድ በኩል አገልጋዮች የሆኑትን እንደ ሐዋርያው ዮሐንስ ያሉትን ሰዎች ይቃወማል፤ ይለያያል፣ ያለ አግባብ ከቤተክርስቲያን ሰዎችን ያወግዛል፤ የዚህ ሰው ዋነኛ ዓላማ በምዕመኑ መሐል አለቃ ወይም ባለስልጣን የመሆን እውን ስብዕናው ስላለው ነው:: ይህ ሰው በሐዋርያት ደረጃ ያሉትን የጌታ አገልጋዮች ማክበር ካቃተው ልብሰ



ስብዕናውንና እውን ስብዕናውን አስታርቆ ለመኖር የተቸገረና ማንነቱ የተደበላለቀበት ሰው ነው:: ይሄ ሰው የአምልኮት መልክ አለው፤ሆኖም ግን የጌታን መንፈስ ቅዱስና ከእርሱ የሚስርፀውን የጌታ ኃይል (ሐሥ. 10:38፣1:8) በደንብ ያውቀው ይሆን ? የዚህ አገልጋይና የሚመራቸው ምዕመናንስ ሕይወት ፍፃሜ ምን ይሆን? ከአምኖናዊው አቤሴሎማዊ ስብዕና ራሳችንን ልንጠብቅ ይገባል::

የመነጠቅን ቀን ተስፋ የሚያደርግ ክርስቲያን ከሚያካሂዳቸው ታላላቅ ተጋድሎዎች ውስጥ ዋነኛው እውንና ልብሰ ሰብዕናውን አስታርቆ መኖር መቻሉ ነው:: ዕውነተኛና ትክክለኛ አምልኮ የሚባለው ሰው በውስጡ እንዳለ በውጫዊው ማንነቱም ሲሰራ ነው:: አስመሣይነት ፣ ቅጥፈት ፣ ግብዝነትና ታይታ በሌለበት ልባዊ አካሄድ ማምለክ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል:: ለዚህም ዓይነት አምልኮ ሰውን ብቁ የሚያደርገው ሰው የውስጥ ሰውነቱ (መንፈስና ነፍሱ) 2ኛቆሮ4:16-18 በሚቀድሰው የዕውነትና የህይወት ቃል ተቀድሶ ሲነፃ ነው:: ዮሐ6:63 ፣17:17:: እግዚአብሔርንም ሆነ ሰውን ከልብ ለመውደድ ቀጥሎም ዕውነተኛ አምልኮን ለማካሄድ መሠረቱ ነፍስን ማንፃት ነው::1ኛ ጴጥ1:2::

ዳግመኛ የተወለደ ሁሉ በውስጡ ተዘርቶና አድጎ ፍሬ በሚያፈራው ቃል ሲሞላ ለስጋዊነትና ለዓለማዊነት ስፍራ አይኖረውም:: ገላ 5:21-22፤1ኛ ጴጥ1:23:: በህይወቱ የመንፈስ ፍሬ የበዛለት ክርስቲያን አማኝ እውንና ልብሰ ስብዕናው ሣይጋጭበት በንፁህ ህሊና ፈጣሪውን ያመልካል:: ስለሆነም ከመጨረሻው ዘመን የአስመሣይ አማኞች የተዘቡ የአምልኮ ልምምዶች ያመልጣል:: ይህ ሰው (እህት ሆነች ወንድም) ለመነጠቅ ራሱን አዘጋጅቷል ማለት ነው::

የአምልኮት መልክ ኣላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል የሚለው ትንቢት እንዳይፈፀምብን ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል:: ዓለማችንን ቃኘት ስናደርግ የግልሙትና ባህሪ ሊኖራቸው የሚችሉ የአውሬው መንፈስ ያገኘ

ቸው ቤተ ክርስቲያናት ሊኖሩ እንደሚችሉ በራዕይ 17 እና 18 ተጠቅሷል። በተለይም በዮሐ. 16:1 « እንዳትሰናከሉ ይህን ተናግሬአችኋለሁ» ከምኩራባችሁ ያስወጧችኋል፤ ከዘህም በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል» የሚለው ለአምልኮት መልክ ዓይነተኛ ምሣሌ ነው። ልብ ሊባል የሚገባው ዕውነት እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን አምላኪ ነን ማለታቸው ነው፤ ሆኖም ግን የእውነተኛ አምላኪዎች ገዳዮች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ በጣም ሃብታሞች ሆነው ድሆች በመሐከላቸው ገብተው እንዳያመልኩ የሚያደርጉ ወይም ደግሞ በሙያ (ሣይንቲስቶች፣ ዶክተሮች፣ በዘርያ የሚገናኙና ወዘተ) ብቻ በአንድነት ሆነው ለማምለክ የተሰባሰቡ እንዳሉ ይሰማል፣ ይነበባል። አካሄዳቸውን እስካልመረመሩ ድረስ በስጋ እየዘሩ መሆናቸውንና ውጤቱም መበስበስን ማጨድ እንደሆነ ልብ ሲባል ይገባል። የኋለኛው መለከት ሲነፋ ለመቅረት የሚጋለጡ ፈጪዎችና አራሾች/ገንቢዎች እነዚህ ሲሆኑ ይችላሉ።

### 12.6. ራስን ለመታለል አደጋ ስለማጋለጥ

ህይወት፣ መንፈስ፤ ዕውነት፣ መንገድ፣ ብርሃን፣ መብራት፣ ሕግ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ብዙ የከበሩ ዕውነቶችን ይዞአል። ጳውሎስ ለገላትያውያንና ለቆሮንቶሳውያን አማኞች ሲፅፍ «አንዱ ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላልና» ገላ. 6:3። ስለዚህ እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ፤(1ኛቆሮ10:12) ሲል የመታለል ሕይወት ሲደርስባቸው እንደሚችል ያመለክታል። የገላትያ ክርስቲያኖች ጳውሎስ ያስተላለፈላቸውን ወንጌል፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ ሆኖ የተረከላቸውን እውነት በልዩና በተሳሳተ ወንጌል ለወጡት ።ገላ1:6-8፣3:1-2። ይህንን ሲያደርጉ አስፍስፈው የሚፈልጓቸው ሐሰተኞች በአካባቢአቸው መኖራቸውን ዘንግተው ነበር። ገላ4:17። ራሳቸውን በእርስ በርስ መነካከስ፣ ነፃነት በመሰል ባርነት፣ ለሥጋዊነት፣ አጋልጠው ነበር። በተጨማሪም በምዕ. 6 ላይ የሳቱ ሰዎችን በየዋህነት ማቅናት ተዘንግቶ ነበር፤ ለዚህም መንፈሳዊነት የተዘነጋበት ህይወት ልምምድ ውስጥ እንደተገባ



ይታያል። ጠቅለል ባለ መልኩ የገላትያ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ወደ ማታለል አዘማሚያ ውስጥ ገብተው ነበር ማለት ይቻላል።

በተመሳሳይ መልኩ ዛሬም በእግዚአብሔር ቤት ሲኖሩ ሰዎች ራሳቸውን ሲያታልሉ እንደሚችሉ ሊዘነጋ አይገባም። ለምሳሌ ሁለት በአንድ ወፍጮ ሲፈጩ አንዲቱ ስትነጠቅ ሌላይቱ አልተነጠቀችም በክርስትና ህይወት መኖሩ በቸልታ ስለተመለከተች ነው። በእርሻ የሚያርሰውም ቢሆን ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም ዓይነት አማኞች በክርስትና ሲኖሩ እንደቀላል ነገር ቆጥረው ኖረው አንዱ ወደ ክብር ሲሄድ እነርሱ መቅረታቸውና መዋረዳቸው ራሳቸውን ማታለላቸው አይደለም? ያለ ጥርጥር ነው። መንፈሳውያን የሆኑ ይመስላቸዋል ግን አይደሉም። 1ኛቆ. 19:37። 6 ዘጠኝን/9/ ስለመሰለች ዘጠኝ ናት ማለት አይቻልም፤ ስድስት ናት እንጂ።

ታሪካቸውን በ1ኛቆሮቶስ የምናነበው ቆሮንቶሳውያን ጳውሎስ እስራኤላውያን እንዴት በምድረበዳ ወድቀው እንደቀሩ የተረከላቸው ያለ ምክንያት አልነበረም። ሳይቆሙ የቆሙ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሳይበረቱ የበረቱ፣ መንፈሳውያን ሳይሆኑ የሆኑ መስሎ ታይቷቸዋል። ለምሳሌ ሲጣሉ ሲጨቃጨቁ፣ እኔ የጳውሎስ ነኝ የአጵሎስ ነኝ ወዘተ እያሉ ሲለያዩ ራሳቸውን እንደመንፈሳዊ ሰው መቁጠራቸው መታለላቸው ነበር። ከዚህ አቋማቸው /ከስጋዊ ክርስቲያንነት/ ቶሎ ተመልሰው ክርስቶስን ካልመሰሉ በስተቀር ውድቀት በፊታቸው እንዳለ /1ኛቆሮ10:12/ ያመለክታቸዋል። እንዲህ ሳይሆኑ ሆኖ መገኘት ራስን ማታለል ነው።

በአሁኑ ዘመን አንዳንድ በቤተ ክርስቲያን ያሉ አማኞች ስለ መፀለይ ግድ የሌላቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሳያነብቡ ሲውሉና ሲያድሩ ምንም የማይሰማቸው፣ ሲጠሉ፣ ሲጣሉ፣ ሲያጣሉ፣ ሲሰርቁ፣ ሲዋሹ፣ ሲያሟርቱ፣ ሲያለያዩ፣ በስሙ-ክርስትና ሲነግዱ፣ ሲያጭበረብሩ፣ ሲሰብኩ፣ ሲዘምሩ፣ ከቤታቸው ጣሪያ ሥር ያሉ ቤተሰባቸውን ሳያገለግሉ፣ መንፈሳዊውን ነገር በስጋ ሲተኩ፣ አስመሳይነት ነግሦ እውነተኝነት ሲከሳና ሲከስምን

የማይሰማቸው፣ የጌታ ቤት ፈርሶ የራሳቸውን ሲሰሩ ምንም የማይሰማቸው፣ የጌታን ምፅዓት በመድረካቸው እንዳይሰበክ ረቂቅና ግልጽ ገደብ ሲያበጁ ወዘተ ምንም የማይመስላቸው ሕሊናቸው በጋለ ብረት ተጠብሶ /1ኛጢሞ4:2-3/ ደንዝዘው የሚኖሩ አሉ:: ታዲያ እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን እንዳላታለሉ በምን ያረጋግጣሉ? *መታለል ገደል መንከባለል* ማለት ይሄ አይደል? መሰከት ቢነፋ እንነጠቃለን ይሉ ይሆን? የዚህን ዓይነት ህይወት በ1ኛ ቆሮ. 6:10 እና በገላ. 5:21 የሚለማመዱ ክርስቲያን ነን ባይ ሰዎች «የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርስም» የሚል ቃል እንደተፃፈባቸው ግልፅ ነው:: 1ኛ ቆሮ.6:10፤ ገላ. 5:21:: ስለሆነም ራሳችንን እንዳናታልል:: አሜን በተባለለት ቃል እንኑር:: አሜን!!

## 12.7. <u>ተግቶ በርን የመጠበቁ ጉዳይ/ልምምድ</u>

ጌታ ኢየሱስ ግልጽ ወዳጅ ነው:: የክርስቶስ ወዳጅነቱ ከሚገለጥባቸው ዋነኛ መንገዶች ውስጥ አንዱ ዕውነትን ማስታወቁና ማስተማሩ ነው::ይህንንም የዚህ ዓለም ወኪል ገዢ ከሆኑት ለአንዱ ለጲላጦስ እውነት ልናገር /ልመስክር ተወልጃለሁ ብሎ ከተናገረው መረዳት ይቻላል:: ዮሐ18:36-37:: ጌታ ለደቀ መዛሙርቱና ለተከታዮቹ እውነትን በመናገር ፍቅሩን ከገለጠባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ሊጠቁ የሚችሉባቸውን አቅጣጫዎች በማመልከቱ ነበር:: ይህንንም ጌታ በማርቆስ 14 ላይ እንዴት እንደተናገረ ማግኘት እንችላለን::

«ስለዚያች ቀን ወይም ሰዓት የሰማይ መላዕክቱም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም፣ ጊዜው መቼ እንዲሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፣ ትጉ፣ ፀልዩም፣ ቤቱን ትቶ ወደ ሌላ አገር እንደሄደ ሰው ነው:: ለባሮቹ *ሥልጣን* ለእያንዳንዱም *ሥራውን* ሰጥቶ *በረኛውን እንዲተጋ አዘዘ*፣ እንግዲህ በማታ ይሁን በእኩለ ሌሊት ወይም ዶሮ ሲጮህ ወይም በማለዳ ቢሆን ባለቤቱ መቼ እንደሚመጣ አታውቁምና ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ



እንዳያገኛችሁ ስለዚህ <u>ትጉ</u>:: ለእናንተም የምነግራችሁን ለሁሉ እላለሁ <u>ትጉ</u>::» ቁ32-37::

ከላይ ከተጠቀሱት ሐሳቦች ውስጥ ስለ መነጠቅ ስናስብ ልዩና ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጣቸው የሚገባ ዕውነት አዘል ቃላት ውስጥ በረኛ፣ ትጉ፣ ተጠንቀቁ፣ ፀልዩ፤ አዘዘ፣ ድንገት፣ ተኝታችሁ፣ ለሁሉ እላለሁ ይገኛሉ:: «ትጉ» /መትጋት/ የሚለው ቃል ብቻ 4 ጊዜ ተጠቅሷል:: የቃሉ መደጋገም ምን ያህል ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው ያመለክታል:: «ትጉ» የሚለው ቃልና፣ ተጠንቀቁ፣ ፀልዩ፣ ንቁ፣ የተሰኙት ቃላት ተቃራራቢ ናቸው:: የመትጋት አስፈላጊነትና የመተኛት አላስፈላጊነት ተደጋጋፊነታቸው የማያጠያይቅ ነው:; አለመትጋት ባለበት መተኛት አለ፣ የመተኛትም ውጤት በአጠገብ ላለ ክፉ መጋለጥ ነው:: የተኛ ሰው ስለ አካባቢው ምንም አያውቅም:: የተኛ ሰው ትኩረት ቢያደርግም በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ /ህልም/ በሚደረጉ ተዕይንቶች ላይ ነው:: የተኛ በሩቅ ሊከሰት ስላሰው አደጋና ጉዳት አያውቅም ቢያውቅም ተመልሶ ይተኛል:: በመንፈሳዊ አነጋገር ብንወስደው ቁ.34 ላይ «<u>በረኛውን እንዲተጋ አዘዘ</u>» የሚለው ዐረፍተ ነገር ብዙ ነገርን ያመለክታል:: አንድ ክርስቲያን በሕይወቱ ያስቀመጠው የከበሩ እውነቶች አሉት:: ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ፣ የፀጋ ስጦታዎች፣ የመንፈስ ፍሬዎች፣ አገልግሎት፣ መንፈሳዊ ገድል፣ ስለ ክርስቶስ መመስከር፣ ድሆችን መርዳት በዓለም ከሚገኝ ርኩሰት ራስን መጠበቅ ወዘተ ይገኛሉ:: ባጭር ቃል ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ያልተቀበለው ምንም ዓይነት መልካም ስጦታ የለም:: ሆኖም ግን በሕይወቱ የታዩና ሊታዩ ያሉ መንፈስዊ ስጦታዎች ተወግደው የስጋ ሥራዎች እንዲገቡበት ውጊያ ያካሂዱበታል:: እንግዲህ የክርስቲያን በረኛነቱ የሚለካው እዚህ ላይ ነው::

በአገር አቀፍም ሆነ በዐለም አቀፍ ደረጃ ከልዩ ልዩ አገሮች የእግር ኳስ ተጫዎች ስፖርተኞችን ስንመለከት የበረኛው ብርቱነት ከሌሎች አጋር ተጫዋቾች ጋር ተደምሮ ለቡድኑ አሸናፊነት ወሳኝ ነው:: በሠለጠነው መሠረት በረኛው ካልተጋ ቡድኑ ይጠቃል:: በረኛ መሃል ሜዳ ገብቶ ወይም

የ3ና የ5ን ቁጥር ቦታ ተከቶ ሊጫወት አይፈቀድለትም እንዲህ ካደረገ ይቀጣል:: ከጨዋታ ውጪም ሊገለል ይችላል:: በተመሳሳይ መልኩ አንድ አማኝም ወደ ህይወቱ ገብቶ መንፈሳዊነቱን ከሚያስለቅቁ ወይም ወደ መንፈሳዊነት ደረጃ እንዳይደርስ ከሚገዳደሩ ረቂቃን መንፈሳዊ ቀበሮዎች (ገላ: 5:16-21፣ ሮሜ.1:28-32፣1ኛቆሮ 5 እና 6፣ 2ኛጢሞ3:1-9፣ ራዕይ 21:8፣22:15) ወዘተ ሕይወቱን ማጠር ይኖርበታል:: በተለይ በ2ኛጢሞ3:1-9 የተጠቀሱት አሉታዊ ክስተቶች በህይወቱ ከታዩ ላለመነጠቅ ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ሊተኮርበት ይገባል::

ዕብራውያን 12:17 ስናነብ የበረከት ሕይወቱን ስላስቀማው ኤሳው እንመለከታለን:: ኤሳው ብኩርናውን ካስነጠቀ በኋላ መልሶ ለማግኘት ቢፈልገውም ሊያገኘው አልቻለም:: ኤሳው ያንን ሂደት እንዴት ተግቶ ለመቋቋም እንደ ብርቱና ጠንቃቃ በረኛ አልተጋም? በቅድመ መከራ የሚደረግ ትጋት ብዙ ሲጠቅም በድህረ መከራ የሚደረግ ትጋት በእሳት የማለፍ ያህል በመጠኑ ይጠቅማል:: ምክንያቱም ወዲያው የሺሁ ዓመት ሥርዐት ስለሚቀጥል ተግቶ ድነትን የፈለገ ሊደርስበት ይችላል:: በዚህ ምድር ትጋት፣ አስፈላጊ ነው፣ ከመነጠቅ በኋላ ደግሞ በዘላለም ቅድስናና ፅድቅ ውስጥ ስለሚገባ እዚያ ትጋት አያስፈልግም:: ለትጋት ጊዜ አሁንና በቅድመ መነጠቅ ነው:: ክርስቲያኖች በማየትና በመስማት ወደ ሕይወታችን ከሚዘምቱ ረቂቃን የህይወት አሉታዊ ትዕይንቶች ልንጠነቀቅ ይገባል::

## 12.8. ለመከራ ያለው መነኩሴ መጽሐፉን ሽጠ

ስደት መልኩ ብዙ ነው:: ስደት የማይመስል ስደት አለ፣ ድብቅ እንዲሁም ግልጽ ስደት አለ:: እግዚአብሔር ወይም ሰይጣን የሚያመጣውና የውጭ ሰው የሚያመጣው፣ ሰው ራሱ በብስለት ጉድለት የሚያመጣውም ስደት አለ:: አንዳንድ የስደት ዓይነት ክርስቲያኑን ሲያበረታው ሌላው ዓይነት ደግሞ ይጥለዋል:: ማቴ.13:21::



ከሁሉ ግን የከፋው የስደት ዓይነት ስውር ስደት ነው:: ስውር ለአሳዳጁም ሆነ ለተሳዳጁ እምብዛም አይታወቅም:: ስውር ስደት የሚመጣው ጠቃሚ፣ አስደሳችና በጎ መስሎ ነው:: ስውር ስደት በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠቃው ወደ አሉታዊ ልምምድ የሚያደሉ ስጋውያን ክርስቲያኖችን ነው:: የስውር ስደት ዋነኛ አቀንቃኝ ዲያብሎስ ነው:: የተወሰኑ ክርስቲያኖች ህይወታቸው የትኛው ዓይነት አሉታዊ ልምምድ ላይ (አለመፀለይ፣አለማንበብና ከቅዱሳን ጋር ንፁህ ህብረት አለማድረግ) ሊጠቁ እንደሚችሉ ስለማያውቁ ሁኔታዎች ካላመቹ በስተቀር የገሃነም ደጆች ፊት ለፊት ስደትን አያመጡባቸውም::

ከንባባት እንደምንረዳው ክርስቲያን አማኝ በግልና በህብረት ፀሎት፣ በግልና በህብረት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ትምህርት፣ ከቅዱሳን ጋር ባላቸው ህብረት የሚተጉ ከሆኑ ከወቅቱ ስደት ድነዋል ማለት ይቻል ይሆናል:: ይህም ከሌሎች መንፈሳዊ ልምምዶች ጋር ተደምሮ ነው:: ከ400 ዓመታት በፊት አሜሪካ በተቆረቆረችበት እስከ 1950ዎቹ ዓመታት ድረስ ሕዝቡ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና አስተምህሮ፣ ለፀሎትም የነበረው አክብሮት በጣም ከፍተኛ እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል:: ባለፉት 40 ዓመታት መጀመሪያ ላይ ግን አስቀድሞ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ይሰጥ የነበረው የመጽሀፍ ቅዱስ አስተምህሮና ፀሎት ከክፍሎች ወጥቶ በየፀሎት ቤቶች ይግባና ይሰጥ ተብሎ ሲወሰን ውድቀት በአገሪቱ ላይ ማንዣበብ እንደጀመረ ንባባትና የሰዎች ንግግሮች ያረጋግጣሉ::

በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ከሚተላለፉ ስብከቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመለሱ» የሚል ነው:: ለምን ይህ ስብከት አስፈለገ? ይህ ጥሪ፣ ትምህርትና ስብከት ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት አብዛኛው ወይም ከፊሉ ሕዝብ ከመጽ/ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚጋጭ ልምምድ ውስጥ ስለገባ ነው: በዲቪና በልዩ ልዩ መንገድ ከተለያዩ አገሮች ወደ አሜሪካ የገቡ ሕዝቦች የየአገራቸውን፣ ባህል፣ ሐይማኖት፣ ቋንቋና ልምምዶች ይዘው

ገብተዋል:: የተወሰኑት የምዕራቡ ዓለም ህዝቦች ደግሞ ወደ ሉላቀፋዊነት /Globalization/ የሚያተኩር የመቀባበል አዝማሚያ ስለ ሚታይባቸው አምልኮአቸውንም ሆነ መንፈሳዊ አስተምህሮአቸውን በአዳዲስ አመለካከቶች ዕምነቶችና ልምምዶች እየተኳቸው ስለሆነ ለቅዱሳን ሰዎች የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ዕምብዛም ዋጋ አልተሰጠውም:: አልፎ አልፎ መጽ/ቅዱስ አይሁዳውያን የፃፉት ቃል ነው የሚልም የሐሳብ ስንዘራና ትንታኔም ስለሚያቀርቡ በየምክንያቱ ለእግዚአብሔር ቃል ዋጋ መስጠቱ ቀንሷል::

በቀደሙት ዘመናት የአንድ እውነት እርግጠኝነት መለኪያው ምንድነው ሲባል በማዕከላዊነትና በዋንኝነት ይጠቀስ የነበረው *የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ* የሚል ምላሽ በመጥቀስ ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ግን ከአንዳንድ ሥነ መለኮታውያንና ፈላስፎች አስተምህሮ በመነሳት ለአንድ እውነት አስረጋጭ ምስክር ሊሆን የሚችለው ተሞክሮ /Experience/፣ አመክንዮ /Rationalization/፣ አንፃራዊ-ሥነምግባር /Relativized Ethics/፣ ባህል /Culture/፣ ሳይንስ /Science ወዘተ ናቸው የሚል ምላሽ በመሰጠት ላይ ይገኛል:: ከላይ የተጠቀሱት የእውነት ማዕኛዎች እንደየሁኔታው አስፈላጊና ጠቃሚ ቢሆኑም እንደ ዋነኛ የእግዚአብሔር እውነት ማጽኛና መስካሪዎች ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም::

ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በመጥቀስና በመቀበል ዋነኛ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ከእጃቸው ያስመለጡ ብዙ ሰዎች ዛሬ በአለማችን ይገኛሉ:: ከዚህም የተነሳ የህይወት መመሪያ የሆነው ዕውነት ስለተቀማ፣ ክፉና ደጉንም የመለየት አቅም ስለጠፋ ጨለማውን ብርሃን፣ መልካሙን ክፉ፣ ፅድቁን ኃጢአት፣ ልኩን ስህተት፣ ፈጣሪውን የሞተ፣ ሰውን አምላክ፣ ሲኦልን የሌለ፣ ገነትን ሌላ ዓለም፣ የሰዎችን መናፍስት የአጋንንት፣ ቅዱሳን መላዕክትን አጋንንት፣ በሲኦል ያሉትን ሞተው የተነሱ፣ መግደልን ፅድቅ፣ እንስሳትን ሰዎች፣ ሰዎችን እንስሳት ወዘተ ወደ ማለት



ደረጃ ተደረሰ:: ዳሩ መመሪያ የሌለው፣ መንገድንም የማያውቅ ፍጡር እንዴት ወደ ትክክለኛው ሕይወት ይደርሳል? በአሁኑ ጊዜም የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባላት መጽሐፍ ቅዱስን *ታላቁ ውሸት* ብለው ስለሚያጣጥሉትና ስለሚዋጉት አንዳንድ ክርስቲያኖችም ይህ ክፉ ሐሳብ ተፅዕኖ እያደረሰባቸው ይገኛል:: መጽሐፉን ጣሉ፣ ራሳቸውንም ጣሉ፣ ስለሆነም ለእግዚአብሔር ፍርድ የተጋለጡና የሚጋለጡ ሆኑ *ለመከራ ያለው መነኩሴ መጽሐፉን ሸጠ* የተባለው ይህ አይደል? ስለዚህ ቅዱሳን ሁላችን መጽሐፍ ቅዱሳችንን አጥብቀን ልንይዘው ይገባል:: ባለሙያዎቹ ***የተሸጠ ዕቃ አይመለስም*** ይላሉ:: የተሸጠ ዕቃና ከእጅ ያመለጠ ንብረት አንድ ናቸው:: አንድ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ በእጁ እያለ በትክክል ሊጠቀምበት ካልቻለ ከእጅ ካመለጠው እቃ በምን ይለያል? መልሶስ እጅ ለማስገባት ትልቅ ዋጋ ያስከፍል የለም::

### 12.9. ከተሳሳቱ አመለካከቶች አደጋ ስለመጠበቅ

ከእነዚህም ውስጥ ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው::

#### 12.9.1. ስለ ጌታ ዳግም ምፅዐት

12.9.1.1. በጌታ ዳግም ምፅዐትና በመነጠቅ መሃከል ልዩነት የለም

12.9.1.2. ክርስቶስ ሲመጣ አይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል ተብሎ ተፅፎአል /ራዕይ1:7/:: የወጉት እስራኤላውያን/ሌሎችም/ በምድር ገጽ ላይ ተበታትነዋል:: ታዲያ ኢየሱስ ሲመጣ አንዱ ንፍቀ ክበብ ጨለማ ሌላው ብርሃን ከሆነ የወጉት ሁሉ እንዴት ያዩታል? ይህ የምፅዐት አመለካከት ስህተት ነው ይላሉ::

12.9.1.3. የጌታ ኢየሱስ መመለስ መንፈሳዊ መመለስ ነው ይላሉ:: ይህም ማለት ክርስቲያኖች በሙላት በምድሪቱ ከኖሩና መንፈሳዊነት ካየለ ይህ ጌታ መመለሱን ያሳያል::

12.9.1.4. የክርስቶስ በሰዎች ልብ መኖር ነው::

12.9.1.5. ሰው በምድር ኑሮው አብቅቶ ሲሞትና ወደ ጌታ ሲመለስ ያ ምፅዐት ነው::

## 12.9.2. ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ

12.9.2.1. መነጠቅ ማለት ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላና ኃይል ተቀብሎ በዚህ ዓለም ጣጣ ላይ የበላይነት ተቀዳጅቶ በሥጋ ሥራ ላይ አሸናፊ ሲሆን ነው ይላሉ::

12.9.2.2. በተመስጦ መሆን ነው::

12.9.2.3. በአዕምሮ ወደ ልዩ ዓይነት ራዕይ ወይም ሕልም ውስጥ መግባት ነው::

ስለ ጌታ ምፅዐትና ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከላይ የተጠቀሱት አመለካከቶች ትክክለኛነት የላቸውም:: አንዳንዶቹ ከመነጠቅ ጋር ባልተያያዘ ትንሽ ተቀራራቢ ትርጉም ይኖራቸዋል::

ስለ ጌታ ኢየሱስ ምፅዐት በመንፈሳዊ ወይም በራዕይ ደረጃ የማይፈፀም ለመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ማስረጃዎች አሉ:: ከነዚህም ማስረጃዎች ውስጥ ዋነኞቹ የክርስቶስ በቃሉ መናገሩ፣ የነቢያቱ፣ የመላዕክቱና ሌሎችም አገልጋዮች ምስክርነት መስጠታቸው ነው:: የሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን ድምጽ በግልጽ ከለማይ መስማቱና ከእርሱም ጋር ንግግር ማድረጉ ጌታ ኢየሱስ በሰማይ በአብ ቀኝ መሆኑን እስጢፋኖስ እየተወገረ በነበረበት ጊዜ ወደ ሰማይ ሲመለከት ክርስቶስን ማየቱ /ሐዋ 7 እና 9/፣ ጌታ ኢየሱስ ወደ ላይ ሲወጣ መታየቱ ወደፊትም እንደሚወጣ በቂ ማስረጃዎች ናቸው:: በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስን ምዕራፎች ስንመረምር ስለ ጌታ ምፅዐት በብሉይ ኪዳን ብቻ 1527፣ በአዲስ ኪዳን ደግሞ 318 ጊዜ ባጠቃለይ ከ1845 ጊዜ ወይም በ17 ቁጥሮች ውስጥ አንድ ጊዜ መጠቀሱ ተረጋግጧል:: ይህ እውነት ነው:: ከዚህም በላይ በክፍል አንድ ከምልክቶቹ አንጻር በዝርዝር ይገለጸል::



## 12.9.3. ስለ ቀናትና ዘመናት

በተጨማሪም ስለ ጌታ ዳግም ምፅዐትም ሆነ ስለ ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጊዜአትና ዘመናትን ጠቅሶ በዚህ ቀን በዚህ ወር እንዲህ ይላል ማለትም ፈፅሞ ስህተት ነው:: ለምሳሌ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እንመልከት::

12.9.3.1.1. ዊሊያም ሚለርና አድቬንቲስቶች በክርስቶስ በ1943/4/ ላይ ይመጣል:

12.9.3.1.2. የጂሆቫ ምስሮች ቤተ-ዕምነት መሥራች ቻርለስ ራስል ክርስቶስ ኢየሱስ በ1914 መንግስቱን በምድር ሲመስረት ይመጣል:

12.9.3.1.3. የዓለም አቀፉ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆኑት ኸርቨርት ደብልዩ አርምስትሮንግ ክርስቶስ በ1972 ይመጣል:

12.9.3.2. ኤድጋር ዊሲነንት መነጠቅ በ1988 እንደሚሆን 58 ምክንያቶችን አቅርበው ነበር::

12.9.3.3. የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አባልና የአለማቀፋዊት አሸናፊ ቤተ ክርስቲያን ነቢይት የአርማጌዶን ጦርነት በ1990 ዓ.ም ይሆናል ብላ ነበር:

12.9.3.4. የአዲስ ኪዳን ነቢይት ነኝ ባይዋ ሜሪ ስቲዋርት ረልፍ ክርስቶስ ከ1990 ዓ.ም በፊት ይመለሳል ብላ ነበር:

12.9.3.5. የዳሚ ሚሽነሪ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነው የደቡብ ኮሪያው ሊ.ጃንግሪም መነጠቅ ጥቅምት 1992 ዓ.ም ይሆናል ብሎ በብዙ አሳማኝ ማስረጃዎች ስለተናገረ ወደ 30,000 ያህል አባለት ያላቸውን ንብረታቸውን ሸጠውና አውርሰው ሴቶች ለመነጠቅ እንዲቀልላቸው ፅንሳቸውን አስወርደውና ነጫጭ ልብሶች ለብሰው የመነጠቁን ቀን ሲጠብቁ ሳይሳካ ቀርቷል::

12.9.3.6. ሃሮልድ ካምፒንግ የተባለውና በአሜሪካ በሬድዮ ፕሮግራም የሚያገለግለው ፓስተር መነጠቅ በ1994 ይሆናል ብሎ ነበር:

12.9.3.7. ደብሰን ኢድ የተባሉትም አገልጋይ ክርስቶስ በ2000 ዓ.ም ሊመጣ እንደሚችል 50 ማስረጃዎችን አቅርበው ነበር /የዘመን አቆጣጠር እ.ኤ.አ. ነው/::

ከላይ የተጠቀሱትን ትክክል ያልሆኑና ትንቢትነታቸው በታሪክ ተፈትነው ያልተፈፀሙ ንግርቶች በወቅቱ በተቀባዮቻቸው ዘንድ ችግር ሳይፈጥሩ አልፈዋል ማለት አይቻልም::

ማንኛውም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነ ትንቢት ሁሉ ስህተት መሆኑ በጊዜ፣ በታሪክና በመንፈስ ቅዱስ መስካሪነት ይረጋገጣል:: ስለሆነም የጌታን በአየር መመለስና እርሱን ስመቀበል ስለመጓዝ ስናስብ ከተጻፈው ሳናልፍ መሆኑን መዘንጋት የለብንም::

መቼም ጊዜው የአዲስ ኪዳንና የሥልጣኔ ዘመን ስለሆነ ታለፈ እንጂ እንደ ቃሉ ቢሆን እነዚህ ትንቢቶቻቸው ያልተፈጸሙ ተንባዮች በድንጋይ ተወግረው መሞት ነበረባቸው:: ምክንያቱም ብዙ አደጋ ስለ ፈጠሩ ነው::

ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር... እርሱ ይገደል:: ... ነቢዩ የተናገረው ቃል ባይፈጸም ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው:: ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው:: ዘዳ. 18:20-21:: እነዚህ ሰዎች በምዕመኑ ዘንድ ችግር ፈጥረዋል:: ችግርም የፈጠሩት የውዥንብርን መንፈስ ስላመጡ ነው:: መለኮታዊ ነገር በጣም የተከበረ ነው:: የእምነት ጉዳይ ስለሆነ ትንቢት በጉጉት ይጠበቃል፣ ሳይፈፀም ሲቀር ግን ያሰናክላል:: የሚያሰናክለውም፣ በቤተ ክርስቲያን ያሉትን በእግዚአብሔር ዕውነት ላይ እንዲጠራጠሩ፣ አገልጋዮችን እንዲርቁ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችና ነቢያቱ ላይም ጥያቄ እንዲያድርባቸው፣ በማድረግ የጌታ ምፅዐትም ሆነ የቅዱሳን መነጠቅ ስህተት ነው ወደሚል ድምዳሜ እንዲመጡና እምነታቸው እንዲላላ በማድረግና ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያሉትም ወደ ጌታ ቤት እንዳይመጡ በር በመዝጋት ነው::



ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን በስሙ የሚነሱ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትና ክርስቶሶች ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ በማወቅ እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ ማቴ24:25፤ እነሆ በዚህ ነው ቢሉአችሁ አትውጡ፤ አትመኑ በማለት ጠንከር አድርጎ ተናግሮአል:: በዓለም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከጌታ ምፅዐት ጋር በተያያዘ የሀሰት ትንቢት ተናግረው ከፍተኛ ዕልቂት ከፈፀሙት ውስጥ ዋነኞቹ ጂም ጆንስ፣ ዴቪድ ኮሬሽና ጆሴፍ ኪብዌትሪ የማይረሳ ጠባሳ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያስቀመጡ ናቸው:: ጂም ጆንስ የዛሬ 30 ዓመት አካባቢ የምፅዐት ቀን ቀርቧል ብሎ በስብከቱ በማስፈራራት በአሜሪካ 914 ሰዎችን ገድሎአል፤ መሲህ ነን ባዩ ዴቪድ ኮሬሽ እ.ኤ.አ. በ1990ዎቹ አጋማሽ አካባቢ ዋኮ በተባለች የአሜሪካ ከተማ ለ100 ያህል ሰዎች ዕልቂት ምክንያት ሆኖአል::

የጆሴፍ ኪብዌትሪ የፈፀመው የእልቂት ዓይነት በዓለም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያውና አስቃቂው ነው:: ኪብዌትሪ በዩጋንዳ ራሱን በተሳሳተ ሃይማኖት ውስጥ ያስማራና የዓለም ፍጻሜና የአርማጌዶን ጦርነት በዲሴምበር 31,2000 ይሆናል በማለትና ሰዎች ንብረታቸውን እንዲሸጡ ወይም እንዲያወርሱ በማነሳሳት ከ925 በላይ ክርስቲያኖች እንዲያልቁ ያደረገ ነው:: ሚያዝያ 10,2000 የታተመው የታይምስ መጽሔት ከሞቱት ሰዎች ውስጥ 155 ሰዎች በሩጋዚ፣ 153 በድኖች በቡሁንጋ፣ 81 ሰዎች በሩሾጁዋ ተቀብረው እንደተገኙና፣ 530 ሰዎች በካኑንጋ በዚሁ የኑፋቄ ዕምነት ተከታይ በሆኑት ግቢ ውስጥ እንደሞቱና በእሳት ተቃጥለው እንደተገኙ ተዘግቧል::

እነዚህ ሰዎች የፕሮቴስታንት አማኞች ናቸው:: በስመ የፍጻሜ ዘመን አስተምህሮ ግን ሕይወታቸው ያለ አግባብ ጠፍቷል:: ታዲያ የዚህ ዓይነት ዕልቂት እንዲፈፅም አነሳሽ ኃይሉ ማንነው? ተጠያቂው ማንነትስ የት ይገኛል? ይሄ በዮሐ.8:44 እንደተጠቀሰው የሐሰት አባትና ነፍስ ገዳይ የሆነው የዲያብሎስ ሥራ ነው:: ታዲያ ከዚህ ሁሉ አማኝ ውስጥ አንድ እንኳን የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ የሚሰማና ለእውነት የሚታዘዝ ወይም ደግሞ ሃይ

የሚል ጠፍቶ ያ ሁሉ ሕዝብ በጎረቤት አገር በዩጋንዳ ያለቀው? የዚህ ዓይነት ታሪክ ነገ ኢትዮጵያ ውስጥ ይደገም ይሆን? ወይስ እኛ የተለየን ስለሆንን ሲያልፍም አይነካን! እንል ይሆን? እንግዲህ « ዛሬ አጥሬን የነቀነቀ ነገ ቤቴን ያፈርሳል » በሚል የአበው ምሳሌ ወገባችን በመታጠቅ መብራታችንን ልናበራ ይገባናል:: የጥንቃቄ ትልቁ ሥራ አማኙን መጠበቁ ላይ ነው:: የጥንቃቄም መሠረት ዕውቀትና ማስተዋል ናቸው::ምሳ2:11:: ማስተዋልንም ያላስከተለ ዕውቀት ከመገልበጥ/ከጥፋት አይታደግም:: ፊልጵ. 1:11፣ ሆሴዕ 4:14::

የጌታ ዳግም ምፅዐትም ሆነ የመነጠቅ ትምህርት እጅግ የሚስብና የሚያነቃቃ ነው:: ቅዱሳን እንፅናናበታለን፣ እንበረታታበታለን: ምክንያቱም የተባረከ ተስፋችን ስለሆነ ነው:: ቲቶ2:11-13:: አንድ ጊዜ መነጠቅ ሕይወት ውስጥ ከተገባ ኃጢአትን፣ መሳትን፣ ሥጋዊነትን፣ መከራን፣ የምድሪቱን መርገም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለይቶ መሄድ ነው:: መነጠቅ ወደ ዘላለም ሕይወት መግቢያ ከፍተኛው በር ነው: መነጠቅ ይህንን ያህል የሚባርክና ሕያው ተስፋን የያዘ ከሆነ በማስተዋል ካልተለማመዱት አሉታዊ /Negative/ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል:: 2ተሰ2:2:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች «በቃል፣ በመልዕክት ቢሆን ወይም በመንፈስ የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ ከአዕምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን» ያለው ችግር ስለገጠመው ነበር:: የመነጠቅ ነገር በጥንቃቄ ካላዩት አዕምሮን ያናውጣል::

ቀደም ብሎ ታሪካቸውን በአሉታዊ መልኩ ያነበብነው የመነጠቅ ቀን ናፋቂ አማኞች እዚያ ቀላልና ከባድ አደጋ ውስጥ ሊወድቁ የቻሉት ከዕውቀትና ከማስተዋል ማጣት/ማነስ የተነሳ ነው:: ይህ አሉታዊ ታሪክ እኛ ንም እንዳይደግመን ልናተኩርበት ያሻል:: በተለይም ምልክቶች እየፈጠኑና እየበዙ ሲሄዱ ማስረጃነታቸው ግልጽ ሆኖ እየታየ ሲመጣ ነቃና ረጋ ማለት ያስፈልጋል:: ተማሪ በትምህርቱ፣ ነጋዴ በንግዱ፣ አስተማሪ በማስተማሩ፣



ሁሉም በየስራውና አገልግሎት ዘርፉ በደረሰበት ሊመላለስ እንጂ ሊናወጥ አይገባውም:: /አይገባትም/:: ይህ ትምህርት በተሰጠባቸው በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍሎችም ክፉ ሊያናውጣቸው የሞከራቸው ወገኖች ነበሩ:: ከማውቃቸው ውስጥ ዋነኞቹ አንድ ወንድም የመነጠቅ ቀን ቀርቧል ብሎ ተው እያልኩት ቤቱን መሸጡ፣ አንድ ሌላ ወንድም ደግሞ እጮኛውን እንደዮሴፍ በስውር ሊተዋት ሲል ጌታ በመገሰጥ መከልከሉ፣ አንድ አካባቢ ደግሞ ክርስቶስ እ.ኤ.አ በ1992 ስለሚመጣ ትምህርት መማር ምን ያደርግላችኋል ተብለው ተማሪዎች መናወጣቸውና የመሳሰሉት ናቸው::

<u>እነዚህ ስህተቶች ሊፈጸሙ የቻሉት አሁን እየተፃፈ ያለውን የማስጠንቀቂያ ትምህርት</u>

<u>በጥንቃቄ አስተውሎ ካለመስማትና በተሳሳተ መንገድ ከመተርጎም የተነሳ ነው::</u>

የትንቢቶችን መፈፀም እያየን የጌታን መቅረብና የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ እንረዳለን እንጂ ቀንንና ሰዓትን ወራትንም በማስላት የአዕምሮን ሚዛን ልናዛባና ልናስለቅቅ አይገባም:: መነጠቅ የሚፈፀመው: ሁለቱ በአንድ ወፍጮ ይፈጫሉ፣ ወይም በአንድ እርሻ ያርሳሉ እንደተባለ ሁሉም በየመስኩ ተሠማርቶ ሳለ በድንገት ነው፤በመስካችን ላይ ሆነን ዕምነታችንን ሳንጥል ተግባራችንንም ሳንፈታ፣ ልባችንንም ጌታን እስክንረሳ ክብደት ውስጥ እንዲገባ ሳንፈቅድ ስንኖር የመጨረሻው መለከት ሲነፋ ከተዘጋጀን እንነጠቃለን:: መንፈሱን ማዳመጥ ከቻልን ሮሜ8:14፣16፣ እርሱ ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል፣ ሊመጣ ያለውንም ያሳስበናል፣ ሐ16:12-13: በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለን ጌታ በድንገት መጥቶ ይወስደናል:: ቤቱም ያስገባናል:: ባጭሩ ሕይወታችንን ልንመራ የሚገባን እንዲህ ነው::

ክርስቶስ ሲመጣ፣ የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ሲነሱ እኛም በቅጽበተ ዓይን ከተነሱት ጋር ጌታን በአየር ለመቀበል ከሚነጠቁት ክፍል እንጂ ከሚቀሩት ክፍል እንዳንሆን ጌታ ፀጋውን

*ያብዛልን:: እውነት የሆነውና ዕውነትን የሰጠን፣ በዕውነቱ እየቀደሰና ወ[illegible] እውነት እየመራ በእውነት የሚያኖረን እውነተኛም የሆነው ጌታ ኢየሱ[illegible] ቶሎ ይምጣልን::አሜን!!*

## 12.10. <u>*ሥራ-ፈት ስለመሆን*</u>

*ሥራ-ፈት* ማለት እግዚአብሔር ለሰው እንዲያከናውነ የሰጠው[illegible] ተግባር መልቀቅ ወይም መተው ማለት ነው:: ሰዎች ዓላመዎቻቸው[illegible] ተግተው እንዳይፈጽሙ የሚያደረጉዋቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋነኞቹ ተስፋን በተሳሳተ መንገድ መረዳት አንዱ ነው፡፡

ለክርስቲያኖች ከተሰጡን የተባረኩ ተስፋዎች ውስጥ ዋነኛው የጌታችን የክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እኛ መምጣትና የእኛም ወደ እርሱ መሰብሰብ ነው:: ጌታን ከምናይባቸው መንገዶች ውስጥም ትልቁ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ነው:: ሆኖም ግን ቀደም ብሰን እንደተመለከትነው ተስፋን በተሳሳተ መንገድ ተረድተው ችግር የፈጠሩና የተጎዱም እንደነበሩ ታሪክ ይመሰክራል:: ለምሳሌ ሰሰ መነጠቅ ሰናስብ አንዱ የምነጠቅና ያም የተሻለ ሕይወት ከሆነ ለምን በዚህ ምድር ላይ መከራ እቀበላለሁ፤ ለምንስ ትምህርቴን አጠናለሁ? ምን ያደርግልኛል? ለምንስ ቤት እሰራለሁ? ለምንስ እነግዳለሁ? ጋብቻስ ምን ያደርግልኛል? ቢልና እጁን አጣጥፎ ቢቀመጥና የመነጠቅን ቀን ቢጠብቅ የተባረከውን ታላቅ ተስፋ ለከፋ ጉዳት ሊያደረገው ይችላል:: ስለሆነም የዚህ መልዕክት አንባቢና አድማጭ ሁሉ ስለመነጠቅ ሲያስብ በመጠን መኖርንም ሳይዘነጋ ዓላማንና ተግባርን፤ በምድርም ሊጨብጥ ያሰውን ከመድረስ ወደ ኋላ ሳይል በደረሰበት መመላለስን እንዲቀጥል ደራሲው በጥብቅ ያሳስባል::



## 12.11. <u>ጌታ ይመጣል ወይም አይመጣም፤ መነጠቅ አለ፤ ወይም የለም፤ ብቻ!!</u>

የዚህ የማጠቃለያ ርዕስ ዓላማ ኢየሱስን ተቀብለው መዳናቸውን ላረጋገጡና ወደ ክርስቶስ አካል ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት ለወሰኑ ብቻ ነው::

መሀል ሰፋሪነት በጣም አደገኛ ልምምድ ነው:: ይህ ልምምድ እንኳን ከጌታ ይቅርና ከራስም ያርቃል:: ወደ ሰይጣን ማህበርም ይቀላቅላል:: ምክንያቱም መሀል ሰፋሪነት ተጠራጣሪነት ነውና ምንም ዓይነት በረከት ከጌታ አያስገኝም:: በቃሉም የሚጠራጠር ሰው ከጌታ አንዳች ያገኝ ዘንድ አይምሰለው ተብሎ ተጽፎአልና:: ያዕ.1:8:: ወላዋይ ክርስቲያን እንደ ሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን ራሱን ለመተፋት ያዘጋጀ ነው:: ራዕይ 3:15-17:: ወላዋይ ሆኖም ክርስቲያን ነኝ ባይ አማኝ በፈጣሪው የእውነት ቃል ላይ ተጠራጣሪ ተሳዳቢ ነው:: ሰቃሉ ፍርሀትና አክብሮት የለውም፤ ቢኖረውማ ገና ዱሮ በመታዘዝ ይገልጠው ነበር:: ወላዋይ ክርስቲያን ፍሬ ማፍራት አይችልም:: ምክንያቱም ክቡር የሆነው ቃል በዕምነት ስላለተዘራ ለበቅል ስለማይችል ፍሬ ከማፍራት ይልቅ የሚቀርበው ለመቆረጥና ማገዶ ለመሆን ነው::

ወላዋይ ወይም ተጠራጣሪ ክርስቲያን ለእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን የጎን ወጊ እጥንት፤ የመቀመጫ ሚስማር፤ የእግር እሾህ፤ናቸው:: እውነተኞች አማኞችንና ጌታን ክርስቶስ ኢየሲስን ሲያሳዝኑ፤ መንፈስ ቅዱስንም ሲያስከፉ ይኖራሉ::

ስለሆነም ክርስቲያን ነን ካላችሁ ሁለት ዓይነት ህይወት አትኑሩ:: ወይ በራድ (ከሀዲና የሰይጣን ልጅ) ካልሆነም ትኩስ (አማኝና የእግዚአብሄር ልጅ) ሁኑ:: እንዲህ ከሆነ አቋማችሁ ክርስቶሰ ይመጣል! ወይም አይመጣም! ይሆናል:: ይህ ነው ትክክለኛ ክርስትና፤ ይህ ነው ትክክለኛ ዓለማዊነት!

## ማጠቃለያ

ባለፉት አስራ ሁለት ክፍሎች ስለ መነጠቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊነትና ከመነጠቅም የተለየ ስለመሆኑ፣ስለ መነጠቅ ዓይነቶችና ትዕይንቶች፣ለመነጠቅም መሟላት ስላለባቸው ልምምዶች፣ከታሪክና ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በማገናዘብ ለማየት ችለናል:: መነጠቅ እውነት ነው:: እውነትም የሚያደርገው ከ6208 የመ/ቅ ትንቢቶች ውስጥ አንዱ ስለሆነና ትንቢትም የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ ነው:: መነጠቅን በይበልጥ እውነት የሚያደርገው በታሪክ ያለፉ የሁለት ነቢያት የህይወት ልምምድ ነው:: እነዚህም ነቢያት ሔኖክና ኤልያስ ናቸው:: የነቢያቱን የሕይወት ልምምድ ልዩ የሚያደርገው ሞትን ሳያዩ በእምነት መወሰዳቸው ነው:: ይህም ሊሆን የቻለው አካሔዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረጉ ነው:: ዘፍ. 5:24፣ 2ኛ ነገ.2:15:: ዕብር. 11:5-6:: የሁለቱም ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር የተጣበቀና ጻድቅ በእምነት እንደሚኖር ያለ ኑሮ ነበር::

ማቴ. 17:1-4 ስናነብ በመገለጥ ተራራ ላይ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ከታዩት ሁለት ነቢያት ውስጥ አንዱ ኤልያስ ነው:: ሌላውም ሙሴ ነበር:: የሁለቱም በዚያ መገኘት ያለ ዓላማ አይደለም:: ሙሴ የሙታንን የወደፊት ትንሳኤ የሚመለክርና የሚወክል ሲሆን ኤልያስ ደግሞ ሞትን ሳያዩ በሕይወት ሳሉ በቅጽበተ-ዐይን ተለውጠው በእግዚአብሔር መንግስት የሚገኙ -ትን የሚወክል ሆኖ ነው:: በሰማይ የዘላለሙ መንግስት የሚገኙት እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች ናቸው:: ስለሆነም በዚህ ዘመን መጨረሻ ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ አሁን ያለነው ክርስቲያኖች ተለውጠን እንደ ኤልያስና እንደ ሔኖክ ጌታን በአየር ለመቀበል እንነጠቃለን:: በቅርብ ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ቅዱሳን ከዚህ ዓለም በመነጠቅ ይሰወራሉ:: ይህም የሚሆነው በመነጠቅ ስርዐት ምክንያት ነው::



<u>ኤልያስና ሔኖክ አካሔዳቸውን ከጌታ ጋር አድርገው ወደ ሰማይ እንደተወሰዱ እኛም ለመነጠቅ የሚያስችል የጌታ የዘወትር ፀጋ ከመንፈስ፣ከነፍስና ከስጋችን ጋር ይሁን:: አሜን!!</u>

አሜን! አሜን የሆነከው ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎ ና!!

## ልዩ ማስታወሻ

1. የቀን አቆጣጠርን በተመለከተ እ.ኢ.አ (እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ካልተባለ በስተቀር በሙሉ እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር ነው::
2. የልጆችን መነጠቅ በተመለከተ የግል አመለካከታችንን መያዝ እንችላለን:: በዚህ ጉዳይ የተለያዩ አመለካከቶች ስላሉ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ተጽዕኖ ፈጥሮ መለያትን ማምጣት ዓላማው እንዳይደለ አንባቢ እንዲያተውለው ያሳስባል::
3. ስለ መነጠቅ ጊዜ ሦስት ዓይነት አመለካከቶች መኖራቸውን ስናነብብ የትንቢቱ አፈጻጸም በታሪክ ስለሚገለጥ ብዙ መቸገር አስፈላጊ አይደለም::
4. ጽሑፉ ውስጥ አንዳንድ ቦታ ተባዕት ጾታ ላይ ያተኮረ ቢመስል ለውን ባጠቃላይ ለመጥቀስ ስለተፈለገ እንጂ ልዩነትን ለመፍጠር እንዳልታሰበ ልብ ይባል::

<u>ሙዳየ-ቃላት</u>

| | |
|---|---|
| ሀሰተኛው ክርስቶስ | እኔ እግዚአብሔር ነኝ እያለ (2ኛ ተሰ.2:4) የሚሳደበውና ትንሹ ቀንድ<br>እንቆቅልሽ ፈቺ: የአመፅ ሰው: የጥፋት ልጅና አውሬው: ተቃዋሚና ባለ<br>666ቱ በመባል የሚታወቀው የእውነተኛይቱ ቤተ/ክ ራስና ጌታ የሆነው<br>የክርስቶስ ተቃዋሚ፤ በስጋ የተገለጠው ሠይጣን ነው:: |
| ሁነት | የነገሮች ትዕይንት፤አፈጻጸምና አደራረግ |
| ህያው አማኝ | ወንጌል ተሰብኮለት ጌታን በመቀበል ሐጢአቱ በክርስቶሰ ኢየሱስ ተሰርዮለት በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቆ የእግዚአብሔርን ልጅነት ሥልጣን አግኝቶ አባ አባ በማለት ዘወትር የሚጸልይ፤ቃሉንም ሁልጊዜ የሚያጠናና ጠንካራ የሕይወት ትጋት ኖሮት ሌሎችንም እያተጋ የዘላለምን ሕይወት ያለማቋም የሚናፍቅ ክርስቲያን:: |
| ልብሰ-ሰብዕና | በውጪአዊ መልክ የሚታይ የሰው የህይወት ልምምድ፤ ምናልባትም ይህ ሰብዕና ከውስጣዊውና ዕውን ከሆነው ሰብዕና ጋር ተቃራኒ ወይም ተመመሳሳይ ሊሆን ይችላል፤ ትክክለኛውን ሕይወት የሚሸፍን ውጪአዊ የሕይወት እንቅስቃሴ ነው:: |
| ልዕሰ-ተፈጥሯዊ | ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ማናቸውም ዓይነት ሥራ፤ ለምሳሌ በአማኞች ሕይወት የሚታይ እንደ ተአምራት: ድንቆችና በሰው የማይደረጉ ምልክቶች:: |



| | |
|---|---|
| ሎጥ ዘመን (የ) | የሰዶምና የገሞራ ምድር ሰዎች አካሄድ የተበላሸበትና እንደ ግብረ-ሰዶም ዓይነት የሐጢአት ልምምዶች የተካሔዱበት ጊዜ ሆኖ እግዚአብሔር ሰውን በእሳትም ዲን ዝናም ያጠፋበት ጊዜ:: |
| መሰወጥ | በግሪክ አላሣ ሲሆን ትርጉሙ ወደ ሌላ ዓይነት መልክ መቀየር፤ሌላ መልክ መያዝ ማለት ነው:: |
| መረግድ | አረንጓዴ ቀለም ያነውና አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተገነባችባቸው የከበሩ የመሰረት ድንጋዮች ውስጥ አንዱ፤ |
| መረፈቅ | መቀመጥ፤ ማረፍ፤ መወዘፍ፤ መረፈቅ ይህ እንደ ባህሉ አሉታዊ ትርጉምም አለው:: |
| መቶ አርባ (144000) | አይሁዶች: ወንድ ልጅ በመባል የሚጠሩና በመከራው አጋማሽ ላይ አራት ሺ አውሬውን ለመቃወም ሲነሱና አውሬውም ሲቃወማቸው ሲል በመከራው አጋማሽ ላይ ወደ ሰማይ የሚነጠቁ አይሁዶች:: |
| መንፈሳዊ ርቀት | አንድ አማኝ ሳያውቀው የቆመ መስሎት የውስጥ ሕይወቱ እየተሸረሸረ የሚሄድበትና ፈጣሪውን ከማምለክና ከትክክለኛው መንፈሳዊነት የሚለይበት አሉታዊ ልምምድ ነው:: ለምሳሌ በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? ተአምራትስ አላደረግንምን? ትንቢትስ አልተናገርንምን? ሲሉ ከቶም አላወቅኋችሁም እንደተባሉ:: |
| መንፈስ-በኩራት(የ) | ሰው በሐጢአት ምክንያት ሞቶ የነበረው መንፈሱ ጌታን ሲቀበል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ዳግም ልደትን ሲያገኝና መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ የእግዚአብሔርን ልጅነት ሥልጣን ሲቀበል የሰው መንፈስ የሚያገኘው ትንሣኤ፤ |

**መከራው ዘመን (የ)** የ 9.2 ን አጭር ማብራሪያ ይመልከቱ::

**መንፈቀ-መከራ** የመከራው ግማሽ (5.2 ይመ.)::

**ሚስት (የበጉ)** የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን፤ 144000 አይሁዶች፤የመከራውን ዘመን ቤተ ክርስቲያንና ሁለቱንም ነቢያት ጨምሮ ከትንሣኤና ከመነጠቅ ቀጥሎ በሰማይ በበጉ በክርስቶስ ሠርግ ላይ የሚገኙ ቅዱሳን የሚጠሩበት መጠሪያ ስም:: ይህ እስራኤልን ወይም ቤተ ክርስቲያንን ብቻ የሚያመለክት አይደለም::

**ማሴሰን (ሴሰኛ)** አንድ አማኝ ንፁህ መንፈሳዊ ህይወትን እንዳይለማመድ ዓለማዊ ኑሮን ደባልቆ እንዲይዝና በመዳራት እንዲመላለስ የሚደረግ ዘዴ:: ለምሳሌ የራዕይ 2 የትያጥሮኗ ኤልዛቤል የጌታን ባሪያዎች ታሴስን እንደነበር ማለት ነው::

**ሞት ለዘላለም ተዋጠ** ሞት በቅድሚያ በክርስቶስ ቀጥሎም በቅዱሳን ትንሣኤ ሰዎችን ይዞ የማስቀረት ሐይሉ ተወስዶ ባዶውን የቀረበት ወይም የሞትና የሲኦል መክፈቻ የተወሰደበትና የተሸነፈበት ጊዜና ሁኔታ::

**ሠርግ** በ70ኛው ሱባኤ ማብቂያ ላይ የበጉ ሚስት አባላት (5ቱ የተነጠቁ ክፍሎች) በሰማይ ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው ከሰማይ ስራዊት ጋር ሐሴት የሚያደርጉበትና የክርስቶስንም መንገስ አዋጅ የሚሰሙበት፤ ወደ ምድርም ለመመለስ የሚዘጋጁበት ሁኔታ (ራዕይ 19:4-10):

**ስመ የፍጻሜ ዘመን** የትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊና መን/ቅዱሳዊ ወይም ቤተ ክርስቲያናዊ



**...ተምህሮ** ሳይሆን የዚህ ዓለም ፍጻሜ ደርሷል በሚል ሰበብ ሰዎችን የሚያጠፉበት እንቅስቃሴ ነው:: ለምሳሌ ጂም ጆንስ 914 ሰዎችን የጨረሰው፤ ዴቪድ ኮሬሽ 112 ሰዎችን የፈጀው፤ ጆሴፍ ኪብዌትሪና ሚስቱ ከ925 በላይ ሰዎችን ያስገደሉት በስመ ዘመነ ፍጻሜ መቅረብ አዕምሮን በማናወጥ ነው::

**...ባው ሱባዔ** ሱባዔ ማለት ሻቡዓ ከሚል የዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ሰባት ወይም ሳምንት ማለት ነው:: ስለ ሱባዔ በትንቢት መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈው በዳን. 9:24-29 ባለው ክፍል ነው:: ሰባው ሱባዔ ማለት ሰባ ሰባቶች ወይም 70x7=490 ዓመታት ማለት ነው:: እነዚህም 490 ዓመታት እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ የሚያደርጉት በደል፤ሐጢአትና መተላለፍ ሁሉ ተወግዶ፤ ስለ እነርሱም የተነገረው ትንቢትና የታየውም ራዕይ የሚፈጸምበትን እንዲሁም እነርሱ ወደ ዘላለም ቅድስናና ፅድቅ የሚገቡበትን ጊዜና ሁኔታ የሚያመለክት ነው::

**ሰባኛው ሱባዔ** ይህ ከተነገሩት ሰባ ሱባዔዎች ውስጥ የመጨረሻውን ሰባት ዓመታት የሚይዝ ነው::በተነገው ትንቢት መስረት እስራዔላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ዕርቅ ማድረግ የነበረባቸው መሲሁ በተገደለ ጊዜ ከ34 እስከ 40 ዓመተ ምህረት ነበር:: የቤተ መቅደሱ ንጽህናና የአምልኮአቸው ትክክለኛነት እስከተጠበቀ ድረስ የሱባዔው አቆጣጠር ይሰራ ነበር፤ ሆኖም ግን በ34 ዓመተ ምህረት ማለትም በ69ነኛው ሱባዔ መሲሁን ሲገድሉ የሱባዔው አቆጣጠር ለጊዜው አቆመ:: ምክንያቱም ከእግዚአብሄር ጋር ስለተጣሉና የቤተ መቅደሱም አምልኮ ስላቆመ ነው::

ስለሆነም ሰባኛው ሱባዔ እስካሁን አልተፈጸመም:: ሆኖም ሰባኛው ሱበዔ የሚጀምረው በነቢዩ ዳንዔል እንደተነገረው እስራዔል አውሬው ክርስቶስ እውነተኛ ው መሲህ መስሏት ልትቀበለው ለአንድ ሱባዔ ውል በምታደርግበት ጊዜ ይሆናል:: ዳን. 9:27:: ይህ ጊዜ በራዕይ 12 እንደተተነበየው እስራኤል እንደገና በአውሬው የምትቸገርበትና ወደ በረሃ የምትሸሽበት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያልሆነ ታላቅ የመከራ ጊዜ ነው:: ማቴ. 24:21-22፤ ሉቃስ 21:36:: ይህም የያዕቆብ የመከራ ዘመን የሚባለው ነው:: ይህ የመከራ ጊዜ በክርስቶስ ኢየሱስ በመላዕክቱና በሚስቱ ከሰማይ መውረድ ምክንያት አውሬውና ጭፍራዎቹ የሰማይን ሰራዊቶች ሲወጉ በሚከፍቱት በአርማጌዶን በሚጀመረው የፍጻሜ ጦርነት በክርስቶስ ኢየሱስ አሸናፊነት የሚጠቃልል ይሆናል::

**ሰርድዮን** እንደ ደም በጣም ቀይ የሆነ ቀለም ያለውና አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተገነባችባቸው ክቡረ ዕንቁዎች ውስጥ አንዱ ነው::

**ሰርዶንክስ** ውኀ ሰማያዊና እንደ ደም በጣም ቀይ ሆነ ቅልቅል ቀለም ያለው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተገነባችባቸው ክቡር ድንጋዮች ውስጥ አንዱ ነው::

**ሰንፔር** ከአልማዝ ቀጥሎ በጣም ጠንካራ የሆነና ሰማያዊ መልክ ያለው ሰማያዊቱ አየሩሳሌም ከተሰራችባቸው የከበሩ ዕንቁዎች ውስጥ አንዱ::

**(የ)ሰው ልጅ ዘመን** ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ሦስት የእግዚአብሔር ቁጣዎች የሚገለጡባቸው ዘመናት ተጠቅሰዋል:: እነርሱም የኖህ፡ የሎጥና የሰው ልጅ ዘመናት ናቸው:: ሉቃስ 17:26-30:: የሰው ልጅ ዘመን



የጀመረው ክርስቶስ ኢየሱስ ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ ነው:: ሉቃስ በትንቢቱ ልክ ኖህና በሎጥ ዘመን እንደነበረ በሰው ልጅ ዘመንም እንዲሁ ይሆናል ብሎአል:: ስለሆነም ከጌታ ልደት ጀምሮ እስካሁንና እስከ ሺሁ ዓመት ፍፃሜ ያለው ጊዜ የሰው ልጅ ዘመን ይሆናል ማለት ነው:: የሰው ልጅ ዘመን ከሚታወቅባቸው ባህርያት ውስጥ ትልቁ የሰዎች ሐጢአት እጅግ ማየሉ ነው:: ትልቁ የሐጢአት መግለጫ ማለትም ሰው አምላክ ነው የሚባልበትና ሰዎች ወደማይስረይ የሐጢአት ልምምድ ውስጥ የሚገቡበት ወቅት ነው:: ማቴ.24:36-39፤2ኛ ተሰ.2:4::

**ሲኦል** ከመጀመሪያው ሐጢአተኛ ከሞተ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ሐጢአተኛትንሳዔ የሚኖሩ ሐጢአተኞች እስከ ታላቁ ፍርድ ድረስ መንፈሳቸው የሚጠበቅበት ስፍራ::

**ሳይንሳዊ ፊክሽን** በወቅቱ ሲታይና ሲሰማ ልብ ወለድ ሆኖ ከተወሰኑ ጊዜአት በኋላ ግን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በእርግጠኛነት መልኩ በታሪክ ሲገለጥ የሚችል በሐሳብ ደረጃ ያለ ጽሑፍ ወይም ንግግር:: በተመሳሳይ መልኩ ክርስቲያን ፊክሽንም አለ::

**ሺህ ሁለት መቶ** አውሬው ከእስራኤል ጋር የሰባት ዓመት መከራ ውል አድረገ

**ስድሳ(1260) ቀናት** በመከራው አጋማሽ እስራኤልን ሲያሳድድ ከፊሉ ሕዝብ ወደ ሌላ ስፍራ የሚሰደድበትና የሚቆይበት ቀናት ቁጥር ነው:: እነዚህ ቀናት ከ42 ወራት (30 ቀናትx42=1260); ከዘመን ዘመናትና የዘመን እኩሌታ

| | |
|---|---|
| | ወይም ከ 3 ተኩል ዓመታት ጋር እኩል የሆነ ጊዜ ነው:: |
| የሺህ ዓመት | ከሰባኛው ሱባዔና ከአርማጌዶን ጦርነት ቀጥሎ በምድር ላይ በግልጽ |
| መንግስት | ለዓለም መንግስታት እየታወቀ የሚፈጸም ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ጋር የሚገዛበትና የሚያስተዳድርበት ዘመን:: |
| ሽማግሌዎች (24ቱ) | በቅድመ መከራ መነጠቅ በዘመናት ያለፉ ቅዱሳንን ወክለው በሰማይ በእግዚአብሔርና በዙፋኑ ዙሪያ ባሉት 24 ዙፋኖች ላይ የሚቀመጡ የዳኑ ቅዱሳን፤ ምናልባትም ከብሉይና ከኪዳን የሚወከሉ የካህናት አገልጋዮች ቁጥርም ሊሆን ይችላል:: |
| ቅጽበተ-ዐይን | እጅግ በጣም ፈጣንና በአዕምሮ ለማስላት የሚያስቸግር ፍጥነትና መለኮታዊነት ያለው ትዕይንታዊ እንቅስቃሴ:: |
| ቅድመ-መከራ | ከታላቁ መከራ በፊት ማለት ነው:: |
| በቁም መንፈሱ የሞተ፤ | ሐጢአቱ ያልነጻና ጌታን ያልተቀበለ ሆኖም ግን አማኝ ነኝ የሚል:: |
| ቢረሌ | አንጸባራቂና ውኀ-አረንጓዴ ቀለም ያለው የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መሰረቶች ከተሰሩባቸው አስራ ሁለት ዓይነት ድንጋዮችአንዱ:: |
| ትንሣዔ | የሰው አካል ከሞተና ከተቀበረ በኋላ በመለኮታዊ አሰራር የማይጠፋውን: የማያረጀውን: የማይበሰብሰውንና ያልተዋረደውን አካል ለብሶ ሞትን ድል አድርጎ የሚነሳበት ሁኔታ:: |
| ነጋዊ-ድህረ-መከራ መነጠቅ | ማብራሪያ 5.3.3 ይመልከቱ:: |



| | |
|---|---|
| (የ)ኖህ ዘመን | በዘፍጥረት 6 እንደምናነብበው የሰው ልጅ ሐጢአት እጅግ ከመብዛቱ የተነሳ ሰዎች ሁሉ መንገዳቸውን ያነሳሹበትና ከኖህና ከቤተሰቡ በስተቀር ሁሉም ሰዎች በጥፋት ውኃ የጠፉበት ጊዜ ነው:: |
| አቡቀለምሲስ | በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትዕምርቶችን (መልክቶችንና ምስሎችን) በማቅረብ በራዕይ፤ በህልምና በሌላም መልክ የሚገለፅ መልዕክት ማስተላለፊያ መንገድ:: |
| አምቡዋታሪ | ወሬ አናፋሽ: ተናጋሪ ስራ ፈት: አዘጥዛጭ:: |
| አቤሴሎማዊ ወ | ***አፉ ቅቤ ልቡ ጩቤ*** እንደሚባለው ልክ አምኖን እህቱን ትዕማርን |
| አምኖናዊ ሰብዕና | አሞኛል ብሎ እንዳመነዘራት፤ አቤሴሎምም አባቱን ዳዊትንና ወንድሙን አምኖንን የከበረ በሚመስል ሰላምታና ግብዣ አታልሎ የመፈንቅለ መንግስትና የሞት አደጋ እንዳደረሱ ልክ በተመሳሳይ መልኩ በመልካም አስመስለው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጉዳት የሚያመጡ የግለሰቦችና የቡድኖች አካሔድ የሚጠራበት መለያ ነው:: |
| አመክንዮ | የማውጠንጠን ችሎታ: ምክንያት የመፍጠርና የማቅረብ ችሎታ:: |
| (የ)አመፅ ምስጢር | ፊት ለፊት ወይም በስውር ነገር ገሐድ ሳይወጣና ሳይታወቅ የሚደረግ የተቀውሞ አካሔድ፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙ በአመዛኙ የአውሬውን ጥልቅ አሰራር ያመለክታል:: ከቤተ ክርስቲያን መመስረት ጀምሮ እስከ መነጠቅ ድረስ በስውር ይሰራ የነበረውን ተቃውሞ ከመነጠቅ ቀጥሎ የሚቀወመው ስለማይኖር በግልጽ መስራት ይጀምራል:: |

| | |
|---|---|
| አንጻራዊ ሥነምግባር | ፍጹም የሆነ ሥነ ምግባር የለም:: ሥነምግባር እንደየባህሉና እንደየአገሩ ሊለያይ ይችላል:: በአንዱ ሕብረተሰብ ተቀባይነት ያለው በሌላው ተቀባይነት ላይኖረው ስለሚችል ሥነምግባር ፍጹማዊነት ሊኖረው አይችልም የሚል አመለካከት ነው:: |
| አንጻራዊ ዕውነት | እውነት ፈጹማዊነት የለውም:: እውነት እንደየባህሉና አገሩ ይለያያል:: |
| አሜቴስጢኖስ | ደማቅ ሰማያዊና ደማቅ ቀይ ቀለም ያለው ከ12ቱ የሰማይቱ ኢየሩሳሌም ደጆች ውስጥ አንደኛው መሰረት የተሰራበት የከበረ ድንጋይ:: |
| አምናዊ-ድህረ መከራ መነጠቅ | ማብራሪያ 5.3.1. ይመልከቱ:: |
| የአርማጌዶን ጦርነት | ክርስቶስ ኢየሱስ በሰማይ የበጉን ሠርግ ሥርዐት ከፈጸመ በኋላ ከተነጠቁ ቅዱሳን ጋር አውሬውንና ጭፍራዎቹን በጽድቅ ተዋግቶ ድል የሚያደርግበት ሁኔታ ራዕይ 19:14-21:: |
| አውሬው | በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ 15 ስሞች ያሉትና የቀንድ ስሙ ትንሹ ቀንድ: የችግር አስወጋጅ ስሙ ዕንቆቅልሽ ፈቺ: የማሳሳት ስሙ ሐሰተኛው ክርስቶስ: የንጉስ ስሙ ፊተ ጨካኝ ንጉስ: የቁጥር ስሙ 666: የሰው ስሙ አመጸኛ: የእንስሳ ስሙ አውሬው በመባል የሚታወቀው የፅድቅ ጠላት:: |
| አዲሱ አካል | ጌታን አምነው ከሞት የሚነሱ ቅዱሳን የሚለብሱት የማይጠፋ: የማያረጅ: የማያበሰብስና የማይጠፋ እንዲሁም ሐጢአት መስራትና መውደቅ የማይችለው ዘላለማዊ የሰው መንፈሳዊ አካል ነው:: |
| አጥንት-አንቃኸር | መንፈሳዊ ወኔን በመስለብ ማንነትን ለሐዘን የሚገልጥና የሚጎዳ ሁኔታ:: |



| | |
|---|---|
| አጸደ-ሥጋ | አሁን በመንፈስ በነፍስና በስጋ ሁኔታ ያለው ያልሞተው ማንነታችን:: |
| ቤተክርስቲያን | ወንጌል ተሰብከላቸውና የክርስቶስን አዳኝነት አምነውና ተቀብለው በክርስቶስ ደም አማካኝነት የሐጢአትን ስርየት አግኝተው ስማቸውም በህይወት መዝገብ ተጽፎ በመንፈስ ቅዱስ መታተም አማካኝነት የእግዚአብሔርን ልጅነት ሥልጣን ያገኙ ምዕመናን:: |
| እግዚአብሔር-ሞቷል አስተምህሮ: | በእነርሱ ጊዜና ሁኔታ የፈለጉት እግዚአብሔር ስላልተገለጠ በፈጣሪ ትዕግስትና ታጋሽነት ላይ በማሾፍ እግዚአብሔር ሞቷል በማለት ተናገሩትን የፍሬድሪክ ኒቼንና የተከታዮቹን ተሳዳቢ ሥነ መስኮት የሚያመለክት ነው:: |
| ከፊል አምናዊ-ድህረ መነጠቅ መከራ | ማብራሪያ 5.3.2. ይመልከቱ |
| ኬልቄዶን | ውሀ ሰማያዊ:ደብዘዝ ያለ ነጭ:ጥቁር ቡናማና በጣም ቀይና ቢጫ የሆኑ አራት ዓይነት ሕብረ-ቀለማትን የያዘ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተሰራችባቸው አንጸባራቂ የከበረ ድንጋዮች ውስጥ አንዱ:: |
| ክሪስቲሎቤ | አረንጓዴ:ቢጫና ወርቅማ ዓይነት ኅብረቀለም ያለው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ደጆች ከተሰራችባቸው በጣም የከበሩ ድንጋዮች ውስጥ አንዱ: |
| ክርስጵራስስ | ቢጫ: አረንጓዴና ሰማያዊ ዓይነት ቀለም ያለው የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም |

ደጆች ከተሰሩባት የከበሩ ድንጋዮች ውስጥ አንዱ::

**ወራውሬ** ፈዘዝ ያለና አረንጓዴና ቢጫ ዓይነት ቀለም ያለው የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መሰረቶች ከተሰራችባቸው የከበሩ ድንጋዮች ውስጥ አንዱ::

**ወንድ ልጅ** (ማብራሪያ 4.3.4. ይመልከቱ):: ባጭሩ ኢሳ. 66:7-8 እና ራዕይ 12:4-5 በማነጻጸር ሲፈታ ወንድ ልጅ የተባለው በቀጥታ የሚያመለክተው በመከራው ዘመን አውሬውን ለመፋለም ግምባራቸውን ታትመው የሚነሱ አይሁዳዊ የሆኑ 144000 የእግዚአብሔር ባሪያዎች ናቸው እንጂ ወንዱ ልጅ ኢየሱስን የሚያመለክት አይደለም::

**ወንዶችና ሴቶች** ሁለቱንም ጾታ የያዙ በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔርን ልጅነት

**ባሪያዎች:** ሥልጣን ተቀብለውና መንፈስ ቅዱስን ተሞልተው ጌታን የሚያገለግሉ ቅዱሳን::

**(የ)ውሸተኞች** ከአጋንንት ረቂቅና ግልጽ የትምህርት ተጽዕኖ የተነሳ አዕምሮአቸው ደንዝዞ

**ግብዝነት** ዕውነተኛውን ህይወት ትተው በማስመሰል የሚኖሩ አማኝ ነኝ ባዮች::

**ዕውን-ሰብዕና** የልበስ ሰብዕና ተቃራኒ ወይም ተመሳሳይ ሊሆን የሚችል ሆኖም የሰውን ትክክለኛ የውስጥ ማንነት የሚወክል የሰው የህይወት አቋም::

**ዘላለማዊ ዕድቅ** በክርስቶስ ያመኑ የሰው ዘሮች ሁሉ ወደፊት የሚገቡበትና የሚኖሩበት ሐጢአት የማይሰራበት ሁልጊዜ ልክ ሆነተ ሕይወት::



**ዘመን መጣ** በራዕይ 9:15 እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ምድርን የሚያጠፉትን ለመቅጣትና ፈቃዱንና ዓላማውን ለመፈጸም የሚነሳበትን ሰዓት: ቀን:ወርና ዓመት የሚያመለክት::

ሁሌ አሳቢና አድራጊ::

**ዘውታሪ**

**ያክንት** ቀይና ቢጫ ዓይነት መልክ ያለው የሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ደጆች ከተገነቡባቸው የከበሩ ደንጊያዎች ውስጥ አንዱ::

**ድህረ-መከራ መነጠቅ** መነጠቅ ከመከራው ቀጥሎ እንደሚሆን የሚደግፍ ሐሳብ 5.3 ይመ.

**ድነት** ሐጢአትን በማወቅ በመናዘዝና በመራቅ ክርስቶስንም በማመን የሚገኝ የዘላለም ሕይወት::

**ገነት** ጻድቃን ሰዎች ከሞቱ በኋላ መንፈሳቸው እስከ ትንሳኤ ድረስ የሚቆይበት ከምድር በታችና በላይ ያለ ስፍራ:: ገነት አራት ዓይነት ሊሆን ይችላል: ይኸውም የንጋት ኮከብ የነበረው ሰይጣን ይኖርበትና ይገዛበት የነበረው ሕዝ. 28፤ቀጥሎ አዳምና ሔዋን ይኖሩበት የነበረው ዘፍ.3፤የአብርሓም ዕቅፍ በመባል የሚጠራው ሉቃስ 22፤ (አሁን ወና የሆነው ገነትና) በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ሲሞቱ መንፈሳቸው እስከ ትንሳዔ የሚቆይበት ሰማያዊ ስፍራ ዕብር. 12:23-26::

**ጋለሞታይቱ ቤተ** መለያቸው ገንዘብ ወዳድነት የሆነ: የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን የሚሉና

**ክርስቲያን:** (ዮሐ.16:1)፤ የአምልኮት መልክ ኖሮአቸው የፈጣሪን ሐይል የካዱ 2ኛጢሞ.3:5፤ በአንጻሩ ደግሞ እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ በግልፅ የሚናገሩ (ቲቶ 1:16) ከልዩ ልዩ ቤተ ዕምነቶች የተውጣጡና

| | |
|---|---|
| | በመጨረሻው ዘመን አውሬውን ተከተለው የሚነሱና የነቢያትን ደም በማፍሰስ የሚጠጡ አስመሳዮች:: ራዕይ 17:5-6፤18:24:: |
| ጥንተ-አብሶ | ከጥንት ከመሰረቱ ክሰው ዘር ሲወራረስ የመጣ የሐጢአት እርሾ:: |
| (የ)ጻድቃን-መንፈሶች ጉባዔ | እስከ ትንሳዔ በገነት የሚቆዩ ቅዱሳን አማኞች:: |
| ፊቱ መቆም | ክርስቶስ ኢየሱስ በታላቅ ክብርና ግርማ ሲገለጥና ሲመጣ የዓለም መንግሥታትና ጭፍራዎቻቸው በጌታ ቁጣ ፊት መቆም ተስኗቸው_የሚያሳዩትን መንቀጥቀጥና መሸሽ የሚያመለክት እንዲሁም በእርሱ ያመኑት በክብርና በነፃነት ሲቀበሉት የሚያሳይ ትዕይንት ነው:: |



## ምህጻረ-ቃላት

1. ሐ(ዋ)ሥ.= ሐዋርያት ሥራ ቲዎሎጂካል ኮሌጅ
2. መ.ቅ.= መጽሐፍ ቅዱስ
3. መን.ቅ.= መንፈስ ቅዱስ አውሮፓውያን አቆጣጠር
4. ሙ.ቃ.ይ.= ሙዳየ ቃላት
5. ኢ.ቲ.ሲ.=ኢቫንጀሊካል
6. ይመ.= ይመልከቱ
7. እ.ኤ.አ.= እንደ
8. እ.ኢ.አ.= እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ይመልከቱ:

## መዘክረ መጻህፍት


1. Demy, Timothy & Ice, Thomas. Fast Facts on Bible Prophecy. Eugere, Oregon: Harvest House Publishers.
2. Dobson, Ed.(1997). Remarkable Events Pointing To The End. Grand Rapids, Michigon: Zondervan Pub. House.
3. Erickson, Millard J. (1977). Contemporary Options in Eschatology. Grand Rapids, Michigan: Baker Book House.
4. Jennings Dake. (1963). Dake's Annotated Reference Bible. Lawrenceville, Georgia: Dake Bible Sales Inc.
5 Froese, Arno. (1997). How Democracy Will Elect The Anti-Christ. Colombia, Sc: Olive Press Publishers.
6. Hindson, Ed. (2001). Understanding the End Times. Lyncburg: Jerry Fallwell Ministries.
7. Hunt,Dave & Mcmahon. (1985). The Seduction of Christianity. *Spiritua Discernment in the Last Days*. Eagene, Oregon: Harvest House Publishers.

8. Lahaye, Tim. (1972). The Beginning of the End. Wheaton, Illinois: Tyndale House Publishers.

9. Lugt, Herbert Vander. (1983). There is a New Day Coming. Grand Rapids, Michigan: Radio Bible Class.

10. Malgo, Wim. 50 Questions Most Frequently Asked About the Second Coming. Columbia, South Carolina: Midnight Call Inc.

11. Staton, Lewis Dr. (1988). The Final 42 Months. N. Carolina.

12. Walvoord, John F./1990/ Armageddon Oil and Middle East Crisis. Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House.

13. Zeller, John/Dr/. (1968) . The Second Coming of Ages. Michigan: New Era.

14. ኦሌ ኤሪክሰን. (1965) የአንድ አራሽ ንግግር. አዲስ አበባ ኢትዮጵያ: ሴንትራል ማተሚያ ቤት::

## መጽሔቶች

15. Midnight Call. Sept.1992. pp.9-10.

16. Midnight Call. June. 1995. pp. 8-13.

17. Midnight Call. Sept. 1995. pp. 7-8.

18. Midnight Call. Feb. 1995. p. 18.

19. Midnight Call. July. 1995. p.28

20. Time Magazine, April 10,2000 pp.28-29.

————————————//////////////————————————



ፍካሬ 666ትን አዘጋጅተው በማስነበብ *ዘመኑን እንቃኝ ያሉን መጋቢ* ...ኩ ከበደ አሁን ደግሞ ለመነጠቅ ተዘጋጁ ሰዓቱ አልቋል ይሉናል:: የዘመን ...ተላ ላይ የደረስነው እኛ ከዘመኑ ጋር አብረን እንዳናልቅ ወደ ተዘጋጀልን ...ፍራ ለመሄድ የግድ በተጠንቀቅ መኖር አሰብን:: ስዚህ ደግሞ ይህች ...መጽሐፍ ትረዳናለችና እናንብባት::

*መጋቢ አበበ ሥዩም: የምሥራቅ አዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ::*

ይህ መጽሐፍ ብዙ የሚያጽናና የሚያበረታታና ወደ ሰማይ መነጠቅን እጅግ የሚያስናፍቅ ነው:: መቼም በመነጠቅ እውነት ውስጥ መኖርና መመላለስ ታላቅ በረከትና ተስፋ ያለው ሕይወት ነው::ይህ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ሰው ሁሉ ስለ ተመኘ በቻ ተነጥቆ ወደዚህ ሰማያዊ ተስፋ አይገባም:: በእግዚአብሔርም አይወሰድም:: ጽሑፉ የእያንዳንዳችንን ሕይወት የሚነካና በሚያነብበው ሰው ላይ ወደደም ጠላ በህይወቱና በአመለካከቱ ላይ ታላቅ በጎ ተጽዕኖን የሚያሳድር ነው:: በከፍተኛ ሁኔታ የየግልና የጋራ ሕይወታችንን ቻሌንጅ የሚያደርግ ነው:: ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሔኖክም ሞትን እንዳያይ በዕምነት ተወሰደ፤ እግዚአብሔርም ስለ ወሰደው አልተገኘም፤(ዕብር.11:5) እንዲሁም በ1ኛ ዮሐ. 3:3 በእርሱም ይህንን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንፁህ እንደሆነ ራሱን ያነጻል እንደሚል፤ አንባቢ ሆይ! ወደ እግዚአብሔር የሚወሰድ በጌታ ኢየሱስ አምኖ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነና ዕለት ዕለት በጌታ ኢየሱስ ደም ከሐጢአት እየነጻ በቅድስናና በሕይወት ንጽህና የሚኖር ብቻ ነው:: እያንዳንዳችን በዚህ እውነት ራሳችንን እንፈትን ዘንድ ይህንን ጽሑፍ ያቀረበልንን ወንድማችንን መጋቢ ተኩ ከበደን ጌታ አምላካችን አብዝቶ ይባርከው! አሜን::

ዶክተር ፍሬው ተገኔ:
ደቡብ አ.አ መሠረተ ክ/ቤት ክርስቲያን

የቅዱሳን በአየር መነጠቅ በአጠቃላይ የነገረ ፍጻሜ ትምህርት የቤተ ክርስቲያን መድረክ እየተነፈጋቸው ካሉ ትምህርቶች መካከል የሚገኙ በመሆናቸው ይህ መጽሐፍ የረሳነውንና የተውነውን ትምህርት እንድናስታውስ የሚያነቃ ደወል ነው:: በነገረ-ፍጻሜ ዙሪያ ያሉትን የተለያዩ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች በመጽሐፉ ውስጥ በመጠቀሳቸው አንባቢያን የራሳቸውን አመለካከት እንዲያዳብሩ በር ከመክፈቱም በላይ ለተጨማሪ መረጃ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን እንዲያጠኑ ስሜትን ይኮረኩራል:: የቅዱሳን መነጠቅ የዕምነታችን አንኳር ክፍል እንደመሆኑ በዚህ አንጻር መጽሐፉ ቁም ነገሮችን ያስጨብጣል:: በዚህ በመጨረሻ ዘመን የመነጠቁ ባርኮት ተካፋዮች እንድንሆን ከተሳሳተ ልምምድና አስተሳሰብም እንድንርቅ ጸሀፊው የሚያስተምሩትንና የሚመክሩትን ልብ ብለን ልናጤነው ይገባል::

ኢንጂነር ደሳለኝ አበበ

በኢትዮጵያ ገነት ቤተ ክርስቲያን የካራቆሬ ገነት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ: